# የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሀዲይኛ የሆነ የአሥራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከትና የፈተና ውጤታቸው ዝምድና

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት

በ

ወንድወሰን በየነ

ግንቦት 15/1989 ዓ.ም

# የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሀዲይኛ የሆነ የአስራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከትና የፈተና ውጤታቸው ዝምድና

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

በቋንቋዎች ጥናት ተቋም
አማርኛን በማስተማር ዘዴ
ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ፅሑፍ

በ
ወንድ ወሰን በየነ

ግንቦት 15/1989 ዓ.ም.

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

# የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሀድይኛ የሆነ የአስራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርትያላቸው አመለካከትና የፈተና ውጤታቸው ዝምድና

በ

ወንድ ወሰን በየነ
የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

## የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

| | |
|---|---|
| [illegible] | |
| አማካሪ | ፊርማ |
| RICHTER, Renate | |
| ፈታኝ | ፊርማ |
| Teshome Demisse | |
| ፈታኝ | ፊርማ |
| ፈታኝ | ፊርማ |

# ምስጋና

ይህ ጥናታዊ ፅሑፍ ተጀምሮ እስኪጨረስ ድረስ በመከታተልና የተዛቡ ሐሳቦች ተስተካክለው የአንድምታ ዐድታቸውን ጠብቀው እንዲጓዙ ያልተረፈ ጊዜያቸውን ሰውተው በቅንነት የረዱኝ አማካሪዬ ዶክተር ደጀኔ ለታ ቀዳሚ ተመስጋኝ ናቸው።

የኢኮኖሚና የሞራል ድቀት ሳያሸንፋት የቤተሰብ ሐላፊነትን ብቻዋን ተሸክማ በሐሳብም ሆነ በገንዘብ ከጐኔ ቆማ ያስተማረችን የባለቤቴ የወ/ሮ አጥናፍ ቦጋለ ሊመለስ የማይችል ውለታዋ አለብኝ። የልጅነት ስሜትና ፍላጐታቸውን ተቋቁመው ጠንክሬ እንድሠራ እያበረታቱ በትዕግሥት ለጠበቁኝ ልጆቼ ለሰብለ ወንድወሰንና ለክንፈ ወንድወሰን ምስጋና አቀርባለሁ።

ከኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነፅሑፍ ትምህርት ክፍል አባላት በተጨማሪ ያለምንም ቅሬታ በሥራዎቼ ላይ ምሁራዊ አስተያየትና ማቴሪያል እየሰጡ ያበረታቱኝ ዶክተር ሀብታሙ ወንድሙ፣ ዶክተር ታደለ አዳሙና አቶ ደረጀ ገብሬ እንዲሁም በሂሳብ ሥራ የረዱኝ ጓደኞቼ አቶ ተስፋሁን ዓለሙና አቶ ምስግና ተስፋይ ከልብ የማይጠፋ ባለውለታዎቼ ናቸው።

መጠይቆችን በማባዛትና ተፈላጊ ሰነዶችና መረጃዎችን እንዳገኝ ለተባበሩኝ የሀዲያ ዞን ትምህርት መምሪያ ጽ/ቤት፣ የአራቱም ትምህርት ቤቶች ርዕሳነ መምህራንና የአማርኛ መምህራን፣ እንዲሁም የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ያደረጉልኝ እገዛ ለዚህ ውጤት ያበቃኝ በመሆኑ ከልብ አመሰግናቸዋለሁ። በተለይም በማቴሪያልና በሐሳብ የደገፉኝ የጓደኞቼ የአቶ ጥላሁን ፀጋዬ፣ የአቶ ገመዳ ደዕሲቾና የአቶ አዳነ ቆጢሶ ውለታ የሚረሳ አይደለም።

# አኅፅሮተ ጥናት / Abstract/


የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋና ትምህርት ያላቸው አመለካከት ከፈተና ውጤታቸው ጋር ያለውን ዝምድና መመርመር ነው። ተጠኝዎች በሀዲያ ዞን በሚገኙ አራት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች /ዋቸሞ፤ የካቲት፤ ሞርሲጦ፤ ጊምቢቹ/ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሀዲይኛ የሆነ የአሥራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው።

በነዚህ ትምህርት ቤቶች ከሚገኙ የአፍ መፍቻቸው ሀዲይኛ ከሆኑ ተማሪዎች ውስጥ በብድግ ብድግ ናሙና /randum sampling/ ዘዴ የተመረጡ አንድ መቶ ሀያ ተማሪዎች በጥናቱ ታቅፈዋል። ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋና ለትምህርቱ፤ ለመማሪያ መፅሐፉ፤ ለመምህራኑና ለቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ ያላቸውን አመለካከት የሚለኩ በአራት ተላውጦዎች /variables/ የተከፈሉ አርባ ስምንት በሊከርት አፃፃፍ ስልት የተዘጋጁ የፅሑፍ መጠይቆች ሞልተዋል። ተማሪዎች ለቋንቋውና ለትምህርቱ ለሚኖራቸው የአመለካከት መሥረታ የድጋፍ መረጃ ለማግኘት በዚሁ አፃፃፍ ስልት የተዘጋጁ መጠይቆች በመምህራን ተሞልተዋል። የተማሪውን የክፍል ውስጥ እንቅስቃሴና የመምህሩን የትምህርትና የክፍል አያያዝ ለማገናዘብ የክፍል ምልከታም ተደርጓል። ተማሪዎች በአንደኛ መንፈቀ ዓመትና በመሠናዶ /model/ ፈተናዎች በክፍል መምህራን የተሰጧቸው የፈተና ውጤቶች ከየትምህርት ቤቱ የውጤት ዝርዝር /mark list/ እንዲለቀሙ ተደርጎ ለጥናቱ አስፈላጊ መረጃዎች ተሰብስበዋል። ከጥናቱ ጭብጥ ጋር የተዛመዱ ድርሳናትም ተከልሰዋል።

ተማሪዎች በቀረበላቸው መጠይቅ መሠረት፤ ለመምህሩ፤ ለቋንቋውና ለትምህርቱ አዎንታዊ አመለካከት እንዳላቸው የተጠናቀረው መረጃ ሲያመለክት በመማሪያ መፅሐፉ ላይ ግን አሉታዊ አመለካከት አስመዝግበዋል። ከመምህራን መጠይቅ የተገኘው የምላሽ ውጤት ደግሞ ለተማሪዎቻቸው፤ ለመፅሐፉና ለሙያቸው ጠንካራ አሉታዊ አመለካከት አሳይተዋል።

የተማሪዎች አመለካከት በፆታ ልዩነት ላይ ከግምት የሚገባ መራራቅ አላሳየም። በገጠርና በከተማ ነዋሪዎች መካከል ግን የከተማ ነዋሪዎች ከገጠር ነዋሪ ተማሪዎች የተሻለ አመለካከት ሲያስመዘግቡ፤ በትምህርት ቤቶች መካከል ደግሞ የየካቲት ትምህርት ቤት ተማሪዎች ዝቅተኛ የጊምቢቹ ከፍተኛ አዎንታዊ የአመለካከት ውጤት አሳይተዋል።

የመጠይቆች አስተማማኝነት /reliability/ ከተረጋገጠ በኋላ /0·84/ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋና ትምህርት ያላቸው የአመለካከት ውጤትና መምህራን በሁለቱ ፈተናዎች ከሰጡት የፈተና ውጤት አማካይ ጋር በተዛምዶ ስታቲስቲካዊ ቀመር ሲሰላ በተማሪዎች አመለካከትና በፈተና ውጤታቸው መካከል ፋይዳ ያለው ጥምረት አልታየም። ነገር ግን የሁለተን ፈተናዎች አማካይ ነጥብ ወደ አስታራቂ “ቲ” ስኮር /standardized T-score/ ተለውጦ ሲሰላ በመምህራን መካከል የፈተና ውጤት አሰጣጥ ስልት ልዩነት መኖሩን አሳይቷል። ከሁሉም ትምህርት ቤቶች የጐላ የውጤት አሰጣጥ ልዩነት የታየበት የየካቲት 25/67 ትምህርት ቤት ተለይቶ የሦስቱ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች አመለካከትና የ‘ቲ’ ስኮሩ ውጤት ሲሰላ ከግምት የሚገባ ተዛምዶ አስገኝቷል። የየካቲት ትምህርት ቤትም ለብቻው ሲሰላ ፋይዳ ያለው ተጣምሮ አሳቷል። ስለዚህም በአመለካከትና በፈተና ውጤት መካከል ዝምድና መኖሩን ውጤቱ አመል ክቷል።

ከዚህ በመነሳት ተማሪዎች በሚማሩት የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸው አመለካከት በፈተና ውጤታቸው ላይ ሊንፀባረቅ የቻለ በመሆኑ መምህራንም ሆኑ የቋንቋ ማስተማሪያ መፅሐፍት አዘጋጆች ይህንኑ ግንኙነት ከግምት በማስገባት ከተማሪዎች ፍላጐት፤ ማንነትና የአካባቢ ሁኔታ ጋር ስምሙ የሆነ የማስተማሪያ ዘዴ መጠቀምና በትምህርት ይዘት አመራረጥ ላይም በጥናት የተደገፈ መረጃ ላይ ተመርኩዘው ማቅረብ እንደሚያስፈልጋቸው ለመጠቆም ተሞክሯል።

# ማውጫ

ርዕስ ገፅ

ምስጋና ........................................................................ i

አጠቃሎ ........................................................................ ii

ምዕራፍ አንድ፡ መግቢያ ........................................................ 1

1·1 የጥናቱ ዳራ ........................................................ 1

1·2 የጥናቱ ዓላማ ........................................................ 4

1·3 የጥናቱ ፋይዳ ........................................................ 4

1·4 የጥናቱ ወሰን ........................................................ 5

1·5 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች ........................................ 6

1·6 የቃላት ትርጓሜና የምኅፃር አጠቃቀም ................................ 7

ምዕራፍ ሁለት፡ ክለሳ ድርሳናት ................................................ 9

2·1 የሀዲያ ማንነትና የትነት ................................................ 9

2·2 በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት የአመለካከትና ውጤት ዝምድና .... 13

2·2·1 የአመለካከት ግላዊና ባህርያት ........................................ 13

2·2·2 የአመለካከት መሠረታዊ ምንጮች ........................................ 16

2·2·2·1 ወላጆች፣ ባልንጀሮችና ማህበረሰብ ................................ 20

2·2·2·2 መምህሩና የማስተማሪያው ሥነዘዴ ................................ 24

2·2·2·3 የመማሪያ መፃሕፍት ................................................ 29

2·3 የአመለካከትና ውጤት ዝምድና ................................................ 35

ምዕራፍ ሦስት፡ የአጠናን ስልት ................................................ 39

3·1 የተማሪዎች፣ የመምህራንና የትምህርት ቤቶች አመራረጥ ............ 39

3·1·1 የትምህርት ቤቶች አመራረጥ ............................................ 39

3·1·2 የተማሪዎች ናሙና አወሳሰድ ............................................ 39

3·1·3 የመምህራን ናሙና አወሳሰድ ............................................ 40

3·2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ............................................ 40

3·2·1 መጠይቆች ........................................................ 40

3·2·1·1 የተማሪዎች መጠይቅ ................................................ 40

ርዕስ ገፅ

3·2·1·2 የመምህራን መጠይቅ ........ 41
3·2·2 የክፍል ምልከታ ........ 42
ምዕራፍ አራት፡ የመረጃዎች ውጤትና ትንተና ........ 44
4·1 ከተማሪዎች ምላሽ የተገኘ የአመለካከት ውጤት ........ 44
4·1·1 በእያንዳንዱ ተላውጦ ላይ የተገኘ አመለካከት ........ 45
ሀ · ለቋንቋውና ለትምህርቱ ........ 46
ለ · ለመፅሐፉ ........ 52
ሐ · ለመምህሩ ........ 57
መ · ወላጆች ፣ ባልንጀሮችና ማህበረሰቡ ........ 62
4·1·2 አመለካከት በፆታ ........ 66
4·1·3 አመለካከት በመኖሪያ ቦታ ........ 68
4·1·4 አመለካከት በየትምህርት ቤቶች ........ 69
4·1·5 አጠቃላይ የተማሪዎች አመለካከት ውጤት ........ 70
4·2 ከመምህራን የተገኘ የአመለካከት ውጤት ትንተና ........ 76
4·2·1 ለተማሪዎች ........ 77
4·2·2 ለመጽሐፉ ........ 83
4·2·3 ለሙያቸው ........ 85
4·3 የክፍል ምልከታ ማስታወሻ ዘገባ ........ 91
4·4 የተማሪዎች አመለካከትና የፈተና ውጤት ዝምድና ........ 96
ምዕራፍ አምስት፡ ማጠቃለያ፣ የጥናት ግኝቶችና አስተያየት ........ 103
5·1 ማጠቃለያ ........ 103
5·2 የጥናት ግኝቶች ........ 106
5·3 አስተያየት ........ 108
ዋቢ መፃሕፍት ........ 112
አባሪዎች ........ 116

# የሠንጠረዦችና አባሪዎች ዝርዝር

ሠንጠረዥ


| | | ገፅ |
|---|---|---|
| 1· | የሀዲያ ሕዝብ ብዛት በኢትዮጵያ ........................ | 13 |
| 2· | ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋና ለትምህርቱ ያላቸው አመለካከት .......... | 46 |
| 3· | ተማሪዎች ለመፅሐፉ ያላቸው አመለካከት ........................ | 53 |
| 4· | ተማሪዎች ለመምህሩ ያላቸው አመለካከት ........................ | 58 |
| 5· | ወላጆች ባልንጀሮችና ማህበረሰቡ የሚያሳድሩት ተፅዕኖ ................ | 62 |
| 6· | የተማሪዎች አመለካከት በፆታ ........................ | 67 |
| 7· | የተማሪዎች የአመለካከት ልዩነት በመኖሪያ ቦታ ........................ | 68 |
| 8· | የተማሪዎች አመለካከት በየትምርት ቤቱ ........................ | 70 |
| 9· | አጠቃላይ የተማሪዎች አመለካከት ........................ | 71 |
| 10· | መምህራን ለተማሪዎቻቸው ያላቸው አመለካከት ........................ | 73 |
| 11· | በመማሪያ መፅሐፉ ላይ የመምህራን አመለካከት ........................ | 78 |
| 12· | መምህራን ለሙያቸው ያላቸው አመለካከት ........................ | 83 |
| 13· | የተላውጦዎች እርስ በርስ ተዛምዶ ሜትሪክስ ........................ | 86 |
| 14· | የመምህራን አጠቃላይ አመለካከት ........................ | 90 |


አባሪዎች


| | | |
|---|---|---|
| 1· | ተማሪዎች በየተላውጦዎች ያስመዘገቡት አመለካከት፣ የፈተና ውጤትና የአስታራቂ 'ቲ' ስኮር ውጤት ........................ | 117 |
| 2· | ለተማሪዎች የቀረበ መጠይቅ ........................ | 120 |
| 3· | ለመምህራን የቀረበ መጠይቅ ........................ | 126 |
| 4· | ከየትምህርት ቤቱ የተወሰዱ የተማሪዎች የፈተና ውጤቶች .......... | 130 |
| | 4·1 የቀቸሞ ትምህርት ቤት የፈተና ውጤት ........................ | 130 |
| | 4·2 የየካቲት ትምህርት ቤት የፈተና ውጤት ........................ | 132 |
| | 4·3 የሞርሲጦ ትምህርት ቤት የፈተና ውጤት ........................ | 133 |
| | 4·4 የጊምቢቼ ትምህርት ቤት የፈተና ውጤት ........................ | 134 |
| 5· | በየትምህርት ቤቱ የተደረጉ ዝርዝር የክፍል ምልከታ ውጤቶችን የማጠቃለያ ዐብይ ነጥቦች ........................ | 136 |

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1·1 የጥናቱ ዳራ /Background of the Study/

በቋንቋ ትምህርት ሂደት በተለይም በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ክንውን ወቅት ተማሪውን የተለያዩ ማህበራዊ፣ ሥነልቡናዊ፣ ሥነትምህርታዊና ሥነልሳናዊ ችግሮች ይገጥሙታል። በትምህርቱ ሂደት ላይ ተፅዕኖ ከሚያደርሱ በርካታ ተላውጦዎች ውስጥ አንዱ ተማሪው ለቋንቋውና ለትምህርቱ የሚኖረው አመለካከት ነው። በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ ተማሪውን የሚገጥሙት ነገሮች ከአመለካከት ምሥረታው ጋር በቀጥታም ይሁን በስላች ግንኙነት አላቸው። ለትምህርት የቀረበው ቋንቋና የትምህርት ሥርዓቱ፣ የማስተማሪያ መሣሪያዎች፣ መምህሩና የሚጠቀምበት የማስተማሪያ ዘዴ፣ የተማሪው ባልንጀሮች፣ ወላጆችና ማህበረሰቡ፣ ተማሪው ለትምህርቱ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ አመለካከት እንዲያዳብር ተፅዕኖ ከሚያደርሱ ጉዳዮች ውስጥ በዋንኛነት የሚጠቀሱ ናቸው። /ሙለር 1971፡ 290፤ ስሚዝ 1982፡ 82፤ ሀርመር 1990፡4፤ 251፤ ሪቨርስ 1989፡ 132/

ተማሪው በነዚህ ጉዳዮች ላይ አዎንታዊ አመለካከትና ጥሩ ፍላጐት ካለው የትምህርቱ ሂደት የተቃና ውጤቱም አበረታች ይሆናል። በተማሪዎች አመለካከትና በውጤታቸው መካከል የጠበቀ ግንኙነት እንዳለም በብዙ ምሁራን ጥናቶች ተረጋግጧል። /አንደርሰን 1967፡ 6፡8፤ ታደለ 1990፡ 139/ በምሁራኑ የጥናት ውጤት መሠረት፣ አዎንታዊ አመለካከት ከጥሩ ውጤትና ከንቁ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ጋር ሲጣመር አሉታዊ አመለካከት ያላቸው ደግሞ በትምህርታቸው አዝጋሚ በቋንቋ ክሂል ዕድገት ደካሞች በውጤታቸውም ዝቅተኛ እንደሆኑ ይጠቁማሉ። /አኖዳ 1976፡ 156፤ ጋርደነር 1985፡ 41፤ ስፖለስኪ 1969፡ 271-72፤ እንዱቢን 1986፡ 14፤ ሊትልውድ 1984፡ 56፤ ሙለር 1971፡ 290፤ አንደርሰን 1967፡ 235፤ ታደለ 1990፡ 141/

ለተማሪዎች ውጤት ዝቅተኝነት መንስዔ ከሚሆኑ ጉዳዮች ውስጥ አንዱ ሊያዳብሩት የሚችሉት አሉታዊ አመለካከት ከሆነ ጥሩ ውጤት እንዲያመጡ ለማስቻል

ተማሪዎች የግድ ወደ ቋንቋው ትምህርት እንዲገቡ ከመግፋት ይልቅ በቅድሚያ አመለካከታቸውን ወደ አዎንታዊነት መለወጥ የሚቻልበትን ስልት መሻት ይገባል። የትምህርት ሥርዓቱንና የማስተማሪያ መሣሪያዎችን ከተማሪው ፍላጐት ጋር እንዲጣጣሙ ማድረግና የማስተማሪያው ሥነዘዴ ተማሪዎችን አነቃቅቶ በማሳተፍ አመለካከታቸውን አዎንታዊ ማድረግ በሚችል ስልት በማቅረብ መለወጥ ይቻላል። /ሉድዊንግ 1983፡216፣ እነዱቢን 1986፡15፣ ጋርድነር 1985፡ 89/

የተማሪዎችን አመለካከት አዎንታዊ ለማድረግ ከሚረዱ ጉዳዮች ውስጥ ለቋንቋ መማሪያ/ማስተማሪያ ተብለው የሚዘጋጁ መፅሀፍት ናቸው። መጻሀፍቱ ሲዘጋጁ፣ ተማሪው ቋንቋውን ለምን ዓላማ ሲል እንደሚማረው፣ ፍላጐቱ ምን እንደሆነ፣ ለትምህርት ለቀረበው ቋንቋ ያለውን አመለካከት፣ የወጣበትን ማህበረሰብ ማንነትና ፍላጐት፣ ያለበትን የዕውቀት ደረጃ፣ ለቋንቋው ትምህርት የቀረበበትን ሁኔታ … ወዘተ በአግባቡ ማወቅ በሚያስችሉ የጥናት መረጃዎች ላይ ተመሥርተው መሆን ይገባቸዋል። /ሪቻርድስ 1987፣ እነዱቢን 1986፡13፣ ሪቨርስ 1989፣ 133/

አሁን በሥራ ላይ ያለው የ12ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ሲለበስ /1984 ዓ.ም/ ግን "የሲለበሱ አዘገጃጀት በጥናት ላይ ያልተመሠረተ መሆኑ ግልፅ ነው። … ሲለበሱ አጠቃላይ መመሪያ መሥጠት እንጂ የየአካባቢውን የቋንቋ ችግር መፍታት አለመቻሉ መጨን ይኖርበታል።" የሚለውን ሐሳብ በመግቢያው ላይ አስፍሯል። በዚህ ሁኔታ የቀረበ ማስተማሪያ መሣሪያ የተማሪዎችን ፍላጐት አሟልቶ አመለካከታቸውን አዎንታዊ ያደርጋል ብሎ መጠበቅ ያስቸግራል። ከዚህም ሌላ መፅሐፉ የትኛውን አካባቢና ተማሪ ኢላማ እንዳደረገ ግልፅ ካለመሆኑም በላይ አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎችን ከግምት ያስገባ አይመስልም። ስለዚህም ለአማርኛ ቋንቋና ለትምህርቱ እንዲሁም ለማስተማሪያ መፅሐፉ የተማሪዎች አመለካከት ምን እንደሆነ ታውቆ ለወደፊት ዝግጅት በመረጃ መጋቢነት ጥናት ሊቀርብ ይገባል።

ከፍ ብሎ እንደተጠቆመው በተማሪዎች አመለካከትና በውጤታቸው መካከል ያለውን ጥብቅ ግንኙነት በተመለከተ በርካታ የውጭ ሰዎች በተለያዩ ተማሪዎችና የቋንቋ ትምህርቶች ላይ ጥናት አካሂደው ዝምድናውን አረጋግጠዋል። አዎንታዊ አመለካከት ከከፍተኛ ውጤት፤ አሉታዊ ደግሞ ከዝቅተኛ ውጤት ጋር እንደተጣመረ አሳይተዋል። /ሙለር 1971፡ 290፤ እነጆርጅ 1985፡ 472፤ አኖዳ 1976፡ 152/

በአገር ውስጥም ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ስላላቸው አመለካከት ጥናት ካቀረቡ ምሁራን ውስጥ ፀሐዬ ተፈራ /1977/፤ ብርሃኑ ገ/ማርያም /1976/፤ ታሪኩ ፋንታዬ /1988/፤ ወርቁ በሻዳ /1982/ ለተለያዩ የትምህርት ደረጃዎች ማሟያ ያቀረቧቸው ፅሑፎች ተጠቃሽ ናቸው። በጥናቶቻቸው የታቀፉት ተማሪዎች ከፊሎቹ ለቋንቋውና ለትምህርቱ አዎንታዊ አመለካከት እንዳላቸው ሲያረጋግጡ /ታሪኩ 1988፡74/ የቀሩት ደግሞ /ፀሐዬ 1977፡ 244፤ ብርሃኑ 1976፡115፤ ወርቁ 1982፡ 44/ አሉታዊ አመለካከት እንዳስመዘገቡ ያሳያሉ።

ይህ ጥናት ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸውን አመለካከት ስለሚያጠና ከላይ ከተጠቀሱት የአገር ውስጥ ሥራዎች ጋር ይቀራረባል። ይሁን እንጂ አመለካከት ከውጤት ጋር ያለውን ተዛምዶ ሰለሚያነፃፅር የተለየ ነው። እንዲያውም እንደአብዛኞች ሥራዎች አማርኛን ከእንግሊዝኛ ቋንቋ ጋር የማያወዳድርና በቀጥታ ስለአማርኛ ብቻ የሚመለከት ከመሆኑ በተጨማሪ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው በሆነ ተማሪዎች ላይ የተመሠረተ መሆኑ ሌላው የመለያ ነጥቡ ነው።

አጥኚው የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሀዲይኛ የሆነ ተማሪዎችን ለስምንት ዓመታት ሲያስተምር የአብዛኞቹ ተማሪዎች የፈተና ውጤት ዘቅተኛ መሆኑን ተገንዝቧል። ከዚህ ሁኔታ በመነሳት "ምናልባት ለውጤታቸው ዝቅተኛ መሆን መንስዔው አመለካከታቸው ይሆን? ከሆነስ መፍትሔ አይገኝለትምን?" የሚሉ ጥያቄዎችን እንዲያነሳ ተገድዷል። ስለዚህም ጥናቱ የሚከተሉትን ለአመለካከት ምሥረታ ምንጭ ሊሆኑ የሚችሉ ጥያቄዎችን ለመመለስ ይሞክራል።

- ተማሪዎች ለቋንቋውና ለትምህርቱ ምን ግምት አላቸው?
- ተማሪዎች ለመምህሩና ለስልቱ ያላቸው አተያይ ምንድነው?

- ተማሪዎች ለመማሪያው መፅሐፍ ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል?
- በተማሪዎች አመለካከትና በውጤታቸው መካከል ምን ዓይነት ዝምድና ይታያል?

ለዚህ ጥናት ከላይ የተጠቀሱት የጥናት ጭብጦችና ጥያቄዎች የመነሻ ነጥቦች ናቸው።

## 1·2 **የጥናቱ ዓላማ** /Objective of the Study/

የዚህ ጥናት አጠቃላይ ዓላማ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሀድይኛ የሆነ የአሥራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ከፈተና ውጤታቸው ጋር ያለውን ዝምድና መመርመር ነው።

ይህንን አጠቃላይ ዓላማ ከግብ የሚያደርሱ ሌሎች ዝርዝር ዓላማዎችም አሉት። እነርሱም፡-

1· ተጠኝ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋና ለትምህርቱ ያላቸውን አመለካከት መመርመር፤

2· ተማሪዎች ለመምህራቸውና ለሚያስተምርበት ስልት የሚሰጡትን ግምት ማወቅ፤

3· ተማሪዎች በመማሪያው መፅሐፍ ላይ ያላቸውን አተያይ አጥንቶ መረጃ ማግኘት፤

4· ተማሪዎች በቋንቋው ትምህርት ላይ ለሚኖራቸው አመለካከት ወላጆች፤ ባል ንጀሮችና ማህበረሰቡ የሚያደርሱትን ተፅዕኖ ከተማሪው ማረጋገጥ፤

5· የተማሪዎች አመለካከት በፈተና ውጤታቸው ላይ ምን ያህል እንደሚንፀባረቅ ማረጋገጥ።

## 1·3 **የጥናቱ ፋይዳ**/Significance of the Study/

የቋንቋውን ትምህርት ቀልጥፎ ለማቅረብና ተማሪውን ሊደርስበት ከሚፈለገው ግብ ላይ አድርሶ የታለመውን የባህርይ ለውጥ ማምጣት ይቻል ዘንድ የተማሪው አመለካከት አዎንታዊ መሆን አጋዥነት አለው። ስለዚህም የማስተማሪያ መሣሪያዎችን ከተማሪው ማንነት፤ ፍላጐትና ከትምህርቱ ማግኘት ከሚሻው ሁኔታ አኳያ አጥንቶ ማዘጋጀት ያስፈልጋል። መምህራንም የተማሪው የመማር ፍላጐት ተነቃቅቶ፤ ለትምህርቱ አዎንታዊ

አመለካከትን አዳብሮ እንዲማርና ለጥሩ ውጤት እንዲበቃ በጥሩ የማስተማር ስልትና ብቃት ትምህርቱን ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል። የተማሪው ቤተዘመዶችና ማህበረሰቡም ጭምር ለቋንቋውና ለትምህርቱ ያላቸው ግምት ቀና ሆኖ ለተማሪው የመማር እንቅስቃሴ ደጋፊ እንዲሆኑ የሚያስችሉ ዘዴዎችን መሻትም ሌላው አስፈላጊ ጉዳይ ነው። ስለዚህም የዚህ ጥናት ውጤት ለተለያዩ ክፍሎች ጠቀሜታ ይሰጣል የሚል እምነት አለ። ከነዚህም ውስጥ:-

1· የሥርዓተ ትምህርት ነዳፊዎች፣ የመርሀ ትምህርትና የመማሪያ መፃህፍት አዘጋጆች ከአሁኑ የተሻለ በፍላጐት አሰሳ ላይ የተመሠረተና የተማሪዎችን አመለካከት ሊያበረታታ የሚችል የትምህርት መሣሪያዎች ለማዘጋጀት በመረጃ ጠቋሚነት ያገለግላል።

2· መምህራን የተማሪዎችን አመለካከት አዎንታዊ አድርጐ ውጤታቸውን ለማሻሻል የሚያስችል የማስተማር ስልት ለመጠቀም ስለአመለካከት ምንጮችና አመሠራረት በማሳወቅ ጠቃሚ መረጃ ያስገኛል።

3· ጥናቱ ባተኮረበት አካባቢ የሚገኙ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸውን አመለካከት በማሳወቅ ለወደፊቱ በአካባቢው በአማርኛ መምህርነት ለሚመደቡ መምህራን በመረጃ ጠቋሚ ሰነድነት ያገለግላል።

4· ወደፊት በዚህ ርዕስ ላይና ዙሪያ ጥናት ለሚያደርጉ ሰዎች መነሻ ይሆናል ተብሎ ይታመናል።

## 1·4 የጥናቱ ወሰን /Delimitation of the Study/

ይህ ጥናት መሠረቱን የጣለው በሀዲያ ዞን በሚገኙ አራት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች /ዋቾሞ፣ የካቲት፣ ሞርሲጦ፣ ጊምቢቹ/ በሚማሩ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሀድይኛ በሆኑ የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ነው።

ጥናቱን በሁሉም የክፍል ደረጃ ተማሪዎች ላይ መሥርቶ ማጥናት የተጠቃለለ ውጤት ላይ ለመድረስ የተሻለ ቢሆንም ሰፊ ጊዜና ከፍተኛ ወጪን ይጠይቃል። ስለዚህም ካሉት የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ውስጥ በአስተሳሰብም ሆነ በትምህርት በሳል ይሆናሉ፣

የተሻለ መረጃንም ይሰጣሉ በሚል እምነት በአሥራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ተካሂዷል።

ጥናቱ የተማሪዎቹ አመለካከት ከፈተና ውጤታቸው ጋር ያለውን ተዛምዶ ብቻ የሚመረምር ነው። አንድ የማስተማሪያ ዘዴ መርጦ በማስተማር በቅድመ ሙከራና ድኅረ ሙከራ ወይም በመለያ /control/ና በሙከራ /expermental/ ቡድን ክፍሎ የተማሪዎችን አመለካከትና ውጤት መሻሻል አለመሻሻሉን በፈተና የሚለካ ሳይሆን ባሉበት ሁኔታ ውስጥ ያላቸውን አመለካከት በመምህራን ከሚዘጋጀው የአንደኛ መንፈቀ ዓመትና የመሰናዶ /model/ ፈተና ውጤት ጋር የሚያነፃፅር ነው። በተለይ የሞዴል ፈተናው፣ በአዘገጃጀቱ ከየትኛውም የክፍል ፈተና ይልቅ የተገቢነት ደረጃውን በአማካይ ሊጠብቅ ይችላል ተብሎ ስለታመነበት፣ የሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ይዘቶችን ሁሉ አጠቃልሎ እንዲይዝ ጥረት ስለሚደረግበት፣ ተማሪዎችም የሞዴል ፈተናን በጥሩ ውጤት ማለፍ ማለት የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተናውን ለመሥራት በጥሩ ሁኔታ እንደመዘጋጀት ስለሚቆጥሩትና ከፍተኛ ጥረትና ዝግጅት የሚያደርጉበት በመሆኑ እንዲሁም በክፍል ትምህርቱ መምህራን ወይም በቡድን የሚዘጋጅ በመሆኑ ለማናፃፀሪያነት ተወስዷል። ይህም ሆኖ ተማሪውን በአንድ የፈተና ውጤት ብቻ ከመፈረጅ ያድን ዘንድ የአንደኛ መንፈቀ አመት/first semester/ ፈተና ውጤት በተደራቢነት ተወስዶ የሁለቱ ውጤት እንዲያዝ ተደርጓል።

## 1·5 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች /Limitations/

ጥናቱ የተመሠረተባቸውን ሀዲይኛ ተናጋሪ ተማሪዎችን ከየትምህርት ቤቱ ከሌሎች ቋንቋ ተናጋሪዎች ለይቶ ለማውጣትና ቅድመ ጥናት ለማካሄድ በየትምህርት ቤቱ ተደጋጋሚ ምልልስ ማድረግ የግድ ነበር። ነገር ግን የቦታው ርቀት በዩኒቨርሲቲው በአንደኛ ተርም ይሰጡ ከነበሩ ኮርሶች ጋር አቀናጅቶ ለመሥራት ለአጥኚው ከፍተኛ ችግር ነበር።

ከሁሉም በላይ ግን ጥናቱን ቀደም ብሎ በታሰበው ስፋትና ወቅት ለማጠናቀቅ የተሰጠው ጠባብ የጊዜ ገደብ ውጥረት በተመላበት ሁኔታ እንዲሠራ ጫና ፈጥሯል።

በተለይ ደግሞ ሊፈቀድ የሚገባው የጥናት ፈንድ እጅግ ዘግይቶ መለቀቅና ያስፈልጋል ተብሎ ከተጠየቀውም መጠን ተቀንሶ 15% ብቻ መፈቀዱ አጥኚውን ካልተዘጋጀበትና ሊወጣው ከማይችል ችግር ውስጥ አስገብቶታል። ይሁን እንጂ የተጠቀሱት ችግሮች በተመሪማሪው ላይ ውጥረት ከመፍጠራቸው በስተቀር በጥናቱ ጥልቀትና ጥራት ላይ ተፅዕኖ አልነበራቸውም።

## 1·6 የቃላት ትርጓሜና የምኅፃር አጠቃቀም

### 1·6·1 የቃላት ትርጓሜ*

**አመለካከት:-** አንድ ሰው ከሚገናኘው ነገር /ሁኔታ/ ጋር ከሚፈጥረው መስተጋብር የሚመነጭ ለጉዳዩ ያለው ቀረቤታ፣ ውዴታ፣ጥላቻ፣ ግምት፣ አተያይ … ወዘተ ነው።

በዚህ ሥራ ተማሪውን የሚገጥሙት ሁኔታዎች የአማርኛ ቋንቋና ትምህርቱ፣ የመማሪ መፃህፍቱ፣ መምህሩና የቋንቋው ተናጋሪ ማኅበረሰብ ናቸው።

**አሉታዊ አመለካከት:-** ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት፣ ለመፅሐፉ፣ ለመምህሩና ለማህበረሰቡ የሚሰጡት አጉል ግምትና ጥላቻ፣ መጥፎ አተያይ ነው።

**አዎንታዊ አመለካከት:-** ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋና ለትምህርቱ የሚኖራቸው ውዴታ ጥሩ ግምት፣ መልካም አተያይ ለማለት ነው።

---

*በዚህ ሥራ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ ተወስደው ወደ አማርኛ የተተረጐሙ ቃላት በጥናቱ አካል ውስጥ በገቡበት ቦታ የተሰጣቸው ስያሜ በቅንፍ ውስጥ የተቀመጠላቸው በመሆኑ የሙዳየ ቃላትን አስፈላጊነት ለመቀነስ አስችሏል።

1·6·2 ምኅፃረ ቃላት

- ሀዞፕኢልመ - ሀዲያ ዞን ፕላንና ኢኮኖሚ ልማት መምሪያ
- ደብብሀፕኢልቢ- ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ፕላንና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ
- ዓ·ም - ዓመተ ምህረት

  በዚህ ጥናት ውስጥ 'ዓ·ም' የሚል ምኅፃረ ቃል የሌላቸው የዘመን ቁጥሮች ሁሉ እንደአውሮፓውያን አቆጣጠር የተመዘገቡ ሲሆኑ 'ዓ·ም' ያለባቸው ግን በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ተፅፈው የተጠቀሱ ናቸው።
- ጠ·ድ - ጠቅላላ ድምር
- መጠ· - መጠይቅ
- መ/ራን - መምህራን

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

## 2·1 የሀዲያ ማንነትና የትነት

የሀዲያ ብሔረሰብ በአዲሱ የፌድራላዊ መንግሥት አወቃቀር መሠረት የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ውስጥ ከሚገኙ በውል ከሚታወቁት አርባ አምስት /ሀምሳ አምስት ይሆናሉ/ ብሔረሰቦች ውስጥ አንዱ ነው።

ስለሀዲያ ብሔረሰብ ማንነትና ጥንታዊ ታሪክ የሚያወሱ ድርሳናትን ያስቀመጡ የታሪክ ምሁራን ሀዲያ ከነገደ ኩሽ ወገን እንደሆነ ይጠቁማሉ። ብራውካምፐር /1973፡ 34-35/ እንደሚሉት ጥንታዊ ሀዲዮች በመጀመሪያ ከኢሲያ ትልቁ ባህር ዳርቻ የተነሱና የአረቢያን ባህረ-ገብ መሬት /peninsula/ አልፈው ቀይ ባህርን በማቋረጥ ወደ ሀበሻ መሬት የመጡ ናቸው። ሀበሻ ምድር ከገቡ በኋላ የአሁኑ ትግራይና ወሎ በሚያካልሉት ቦታ ራያ ላይ ሠፍረው “እንጄቦ” የሚል ስያሜ ያለው መንግሥትም አቋቁመው እንደነበር ይጠቁማሉ። የሀዲያ መንግሥት በዘመኑ ግዛቱን ከሸዋ እስከ በሽሎ ወንዝ ድረስ አስፋፍቶ ነበር። ነገር ግን በዘመናቸው ኃይልና ሥልጣኔ የነበራቸው ሴማዊ ቋንቋ ተናጋሪ የነበሩ ክርስቲያኖች ወደ ደቡብ በሚያደርጉት መስፋፋት ሀዲዮች በቅድሚያ ሰፍረውበት የነበውን ራያን እንዲለቅቁ በመገፋታቸው ወደ ደቡብ እያፈገፈጉ ሄደው በመጨረሻም አሁን በሚገኙበት ቦታ ተሰባስበዋል። ይህንን ታሪካዊ ሁኔታ ሳ.ጺ.ሶ /1982፡ 103/፣ ሀይሌ /1971፡ 2/ ሰፋ አድርገው ያትቱታል።

ብሔረሰቡ ‘ሀዲያ’ የሚለውን ስያሜ ያገኘው ለብሔረሰቡ የዘር ሀረግ አባት ነው ከሚባል ሰው መጠሪያ እንደሆነ ይነገራል። ‘ሀዲያ’ የሚለው ቃል የሁለት ሀዲይኛ ቃላት ጥምር ነው። ይህም ‘ሀዳ’ እና ‘እያ’ ሲሆኑ ‘ሀዳ’ ማለት ‘ብዙ’ ማለት ሲሆን ‘እያ’ ደግሞ ተሸካሚ፣ ቻይ ማለት ነው። ሁለቱ በአንድ ላይ ተጣምረው ‘ሀዲያ’ የሚል ጥምር ሲፈጥሩ ትርጉሙ ብዙ የሚሸከም፣ ትዕግሥተኛ፣ ለብዙ ሀላፊነት የሚበቃ፣ ብዙ ቤተሰብን ማስተዳደር የሚችል ማለት ይሆናል። /ቆጠሮ 1975፡1፣ አየለ 1986፡2/

ሀዲዩች ጦረኛ መሆናቸው የሚነገርላቸው ቢሆንም ከሰሜንም/ሴማውያን/ ሆነ ከደቡብ/ኦሮሞ/ በገጠማቸው የሀይል ግፊት ምክንያት ወደ የትኛውም አቅጣጫ መግፋት ባለመቻላቸው አሁን የሚገኙበትን አካባቢ እንደያዙ ቆይተዋል። ይሁን እንጂ ጦርነት ባደረጉባቸው አካባቢዎች ውስጥ ከተዋጊው ተስማምተው የሚኖሩና ከበርካታው የሀዲያ ጎሣ የተለዩ ሀዲዮች በተለያዩ ብሔረሰቦች ውስጥ እንደሉ ታሪኩ ይጠቁማል።

የሀዲያ ብሔረሰብ የዘር ሀገር አንድ ቢሆንም በብሔረሰቡ ውስጥ የጎሣ ልዩነቶች አሉ። ከነዚህ የጎሣ ክፍፍሎች ውስጥ በዋንኛነት የሚታወቁት ሶሮ ባደጉ ሌሞ ሻሽጉና በደዋቾ የሚባሉት አምስት ጉሣዎች ናቸው። ከነዚህ የጎሣ ግንዶች የዘር ሀረጋቸውን የሚመዙ አሁን የሀዲያ ህዝብ በሚኖርበት ክልል ውስጥም ሆነ በጦርነቱ ወቅት ይሁነኝ ብለው አዲሱን ጦረኛ ተቀብለው በሌሎች ክልሎች ውስጥ የሚገ ኙ ንዑሳን ክፍሎች ይገኛሉ። ከነዚህም ውስጥ ኡሩሶ፣ ሀባሎ፣ ሻመና፣ ሳዳመና፣ ወረመና፣ ደከማ/ሊቢዶ፣ ቀቤና፣ ጃወሮ፣ ለራሶ፣ ባርጋጌ፣ ባሊ ተብለው የሚታወቁ ይገኙበታል። /ሀይሌ 1973፡ 131- 132፤ ደሳለኝ 1983፡1፤ ኃለየሱስ 1984፡3/

ሀዲያ በዞን መስተዳድር ሥር የተዋቀረ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዘጠኝ ዞኖች አንዱ ነው። የዞኑ ርዕሰ ከተማ ሆሳዕና ሲሆን ከአዲስ አበባ 230 ኪሎሜትር ርቀት ላይ ይገኛል። የሀዲያ ዞን መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ በ7°13'44 - 7°55'24 ሰሜን ኬንትሮስ እና በ 7°23'15 -38°07'50 ምሥራቅ ኬክሮስ መካከል ይገኛል።

የዞኑ አጉራባች ድንበረተኞች፤ በምዕራብ የጊቤ ወንዝ፤ ደቡብና ደቡብ ምሥራቅ ሰሜን አሞና ከምባታአላባ ጠንባሮዞኖች፤ በሰሜንና ምሥራቅጉራጌ ዞን፤ በምሥራቅ ከብላቴ ወንዝ ይካለላል።ዞኑ በክልሉ ከሚገኙ ዞኖች በህዝብ ጥግጋት ብዛት በሦስተኛ

ደረጃ ላይ የሚገኝ ሲሆን በካሬ ኪሎሜትር 273·7 ነው። የዞኑ የቆዳ ስፋት 3404·4$km^2$ መሆኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ። /ሀዞፕኢልመ 1987፡ 1-2/

ሀዲያ ዞን በሦስት ኩታ ገጠምና በአንድ ነጥል ወረዳዎች የተከፈለ ሲሆን እነዚህም ሌሞ፣ ሶሮ፣ ከንተብና ሲቂ ናቸው። ከነዚህ ውስጥ የሲቂ ወረዳ በከምባታ አላባ ጠንባሮ ዞን ከሌሎቹ ተቆርጦ ለብቻው ይገኛል። የዞኑ አየር ንብረት በቆላ፣ ወይናደጋና ደጋ የሚከፈል ሲሆን ዓመታዊ አማካይ የሙቀት መጠን ከ14°ሴ - 23°ሴ ይደርሳል። የደጋውና ወይናደጋው አማካይ የዝናብ መጠን 1400 - 1500 ሚሊ. ሲሆን በቆላማ ሥፍራዎች ከ600-1100 ሚሊ. ይሆናል። በዞኑ ከፍተኛና ዝቅተኛ ቦታዎች፣ የኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ ተቀፅላዎችና መካከለኛ አምባዎች ሲገኙ ከፍታቸው ከባህር ጠለል በላይ ከ800-3200ሜ ይሆናል። /ሀዞፕኢልመ 1987፡3/

በ1987 ዓ·ም በተደረገው የቤቶችና ህዝብ ቆጠራ ውጤት መሠረት ዞኑ በጠቅላላው 1050151 ነዋሪዎችን ያቀፈ ሲሆን ከዚህ ውስጥ የሀዲያ ብሔረሰብ ብዛት በዞኑ 820775፣ በክልሉ 874498፣ የሱማሌን ክልል ሳይጨምር በዘጠኙ የኢትዮጵያ ክልሎች 53478 በጠቅላላው 927976 ይደርሳል።* /ለዝርዝሩ ሠንጠረዥ '1'ን ይመልከቱ።/

ብሔረሰቡ እንደማንኛውም ህዝብ የራሱ የሆነ ማህበራዊ ህይወት የሚመራ፣ የራሱ ባህልና ቋንቋ ያለው ነው። ክልሉና ህዝቡ እንደማንኛውም የኢትዮጵያ ህዝብ ሁሉ በኢኮኖሚ ልማትም ሆነ በትምህርት ወደ ኋላ ከቀሩት ብሔረሰቦች አንዱ ነው። /ደብብሕፕኢልቢ 1976፡ 72/

የሀዲያ ህዝብ ኑሮ በአመዛኙ የተመሠረተው በግብርናና በጥቃቅን የንግድ ሥራ ላይ ነው። በዞኑ የህዝብ ብዛት የተነሳ ለእርሻም ሆነ ለከብት ግጦሽ የሚውል የመሬት ጥበት ስላለበት ችግሩን ለመቅረፍና ኑሮን በብልሃት ለመምራት በጠባቡ መሬት በሰፊው የሚያለማው የእንሰትን ተክል ነው። እንሰት እንደ አካባቢው ብሔረሰቦች /ጉራጌ፣ ከምባታ፣ ሲዳማ፣ ወላይታ .../ ከፍተኛውን የምግብ ፍጆታ ይሸፍናል።

*ውጤቱ ከአስሩ ክልሎች የህዝብ ቆሠራ ውጤት የተወሰደ ነው።

ህዝቡ በግብርና ሥራም ሆነ በሌላው የችግርና የደስታ ማህበራዊ ግንኙነት የመደጋገፍና የመተጋገዝ ባህል አለው። ጌጃና ቀዳ የሚባሉት አዋቂ ልጅ፣ ሴት ወንድ ሳይል ሁሉም በየፊናው የሚረዳዳበት የህብረት ሥራ መረዳጃዎች ናቸው። በብሔረሰቡ የመስቀል በዓል በጥብቅ የሚከበር ዓመታዊ በዓል ሲሆን በህብረተሰቡ የሚጠበቁ የሠርግ፣ የለቅሶና የግርዘት ሥርዓት አለው። /ቆጠራ 1975፡4፣ አየለ 1986፡4/

የዞኑ ኢኮኖሚ በእርሻ ላይ የተመሠረተና በልማትም ሆነ በትምህርት ወደኋላ ከቀሩት ዞኖች ውስጥ የሚመደብ ቢሆንም ከአፀደ ሕፃናት እስከ አጠቃላይ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አሉት። ከነዚህ ውስጥ አፀደ ህፃናት 7፣ አንደኛ ደረጃ 138፣ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ 43፣ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ 5፣ በጥቅሉ 193 ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ። በታችኞቹ የክፍል ደረጃዎች የብሔረሰቡ ልጆች በአማካይ የተሻለ የትምህርት ዕድል ያገኙ ቢሆንም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መማር ከሚገባቸው ወጣቶች ውስጥ በትምህርት ገበታ ላይ የሚገኙት 7·5% ብቻ ናቸው። በጥቅሉ የዞኑ የትምህርት ሥርጭት ሽፋን 20% ብቻ ነው። /ሀዞትመ 1988፡3፣ ጣሰው 1988፡1/

የሀዲያ ህዝብ የሚናገረው ኩሻዊ ግንድ ያለውን ሀዲይኛ ቋንቋ ሲሆን በወስጡ /ኡ፣ኢ፣አ፣ኤ፣ኦ/ የሚሉት አናባቢዎች አሉት። እነዚህ አናባቢዎች አጥረውና ፈዝመው ሲነበቡ በቃል ላይም ሆነ በአገባብ የትርጉም ለውጥ ያመጣሉ። በቋንቋው የጉሮሮ ዕግድ /ዕ/ (glottal stop) በተናባቢነት ይገኛል። /ፕ፣ገ፣ነ፣ሸ፣T/ የሚሉት ተናባቢዎች አይገኙም። ነገር ግን አሁን በላቲን ፊደል በቋንቋው በተቀረፀው የፊደል ገበታ ላይ እነዚህንና የኦሮምኛ ተናባቢ ድምፅ ልሳን የሆነውን /DH/ በማስገባት ለተውሶ ቃላት እየተጠቀመባቸው ነው። የቋንቋውን የነጣላ ዐረፍተ ነገር አወቃቀር፣ ባለቤት —ተሳቢ—ግሥ ሂደትን ነው /ሎይድ 1876፡ 149፣ ሀይለየሱስ 1984፡ 2/።

የሀዲያ ብሔረሰብ በአሁኑ ሰዓት በአዲሱ የፖለቲካ ሥርዓት መንፈስ ተደራጅቶ፣ የራሱን ዞናዊ መንግሥት መሥርቶ፣ በራሱ ቋንቋ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ሥርዓት ዘርግቶ፣ በላቲን ፊደል የዕሑፍ ሥርዓቱን ቀርፆ፣ ልጆቹን በማስተማር ላይ ይገኛል።

በዞኑ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች አማርኛ ከአንደኛ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ባሉት ትምህርት ቤቶች እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት ይሰጣል። ተማሪዎች ቋንቋውን ሲማሩት /ሀድይኛ ተናጋሪዎች/ በሁለተኛ ቋንቋነት ነው። ይህ ጥናት የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሀድይኛ የሆኑ ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋነት አማርኛን ሲማሩ ለቋንቋው ትምህርት ያላቸውን አመለካከት ከሚያስመዘግቡት የፈተና ውጤታቸው ጋር ያለውን ተዛምዶ ለመመርመር መሠረት አድርጎ ተነስቷል።

ሠንጠረዥ 1

የሀዲያ ህዝብ ብዛት በአሥሩ የኢትዮጵያ ክልሎች*

| ክልል | ከተማና ገጠር | | | ከተማ | | | ገጠር | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር |
| አዲስ አበባ | 4533 | 3439 | 7972 | 4528 | 3431 | 7959 | 5 | 8 | 13 |
| ትግራይ | 6 | - | 6 | 6 | - | 6 | - | - | - |
| አማራ | 85 | 34 | 119 | 65 | 26 | 91 | 20 | 8 | 28 |
| ደቡብ ሕ· | 436779 | 437719 | 874498 | 22727 | 22540 | 45267 | 414052 | 415179 | 829231 |
| ኦሮሚያ | 19169 | 19665 | 38834 | 2376 | 2263 | 4639 | 16793 | 17402 | 34195 |
| ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | 1227 | 958 | 2185 | 76 | 33 | 958 | 1151 | 920 | 2071 |
| ጋምቤላ | 527 | 456 | 983 | 56 | 47 | 103 | 471 | 409 | 880 |
| አፋር | 1267 | 808 | 2075 | 435 | 300 | 735 | 832 | 508 | 1340 |
| ድሬዳዋ | 468 | 815 | 1283 | 815 | 468 | 1283 | - | - | -- |
| ሐረሪ | 9 | 12 | 21 | 9 | 12 | 21 | - | - | - |
| ድምር | 464417 | 463559 | 927976 | 31093 | 29125 | 60218 | 923324 | 434434 | 867758 |

*ሠንጠረዡ የሱማሌ ክልልን አይጨምርም።

*ውጤቱ በአሥሩ የኢትዮጵያ ክልሎች የህዝብ ቆጠራ ተጠናቅሮ የተወሰደ ነው።

## 2·2 በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት የአመለካከትና የውጤት ዝምድና

### 2·2·1 የአመለካከት ግለፄና ባህርያት

አመለካከት ሥነልቡናዊና ባህርያዊ ይዘት ያለው ከሰዎች ውስጣዊ ስሜት፣ እምነት፣ ግምት፣ … ወዘተ ጋር የታያያዘ ስለሆነ በባህርይው ውስብስብ፣ ተለዋዋጭ፣ ረቂቅና ድብቅም ነው። አመለካከት ለብዙ ጊዜ ከዳበረ ልምድና ባህርይ ጋር ተወሳስቦ የሚገኝና

ሽሽግም በመሆኑ ስለአንድ ጉዳይ የሚኖር የሰዎች አመለካከት አንዳንድ ጊዜ በቀላሉ ሊገለፅ ሲችል በሌላ ጊዜ ደግሞ ይደበቃል። ይሁን እንጂ በቀጥታ ከጉዳዩ ጋር ሊገናኝ ከሚችል ሁኔታ ጋር አገናኝቶ ሲመረመር ወይም እንዲወጣ የሚገፋፋውና የሚያነሳሳው አጋጣሚ ሲገኝ በቃል፣ በአካላዊ እንቅስቃሴ፣ ወይም በገሀድ ሊታይ በሚችል ድርጊትና የባህርይ ግልጠት ሊታወቅ ይችላል። /አፐንሔይም 1986፡106፣ ጋርድነር 1985፡8/

ዱቢንና አልሽቴይን /1986፡15/ እንደሚሉት በርግጥ የአመለካከት መለኪያዎች በጣም አስቸጋሪና ጥንቃቄን የሚጠይቁ ናቸው። አመለካከት ከሰዎች ባህርይ ጋር የተወሳሰበና ከሱም የሚመነጭ በመሆኑ መለኪያው ፍፁም ሊሆን ይችላል ማለት ያስቸግራል። እስካሁን አመለካከትን ለመለካት በጥቅም ላይ ከዋሉ መሳሪያዎች ውስጥ መጠይቅና ቃለ መጠይቆች ናቸው። እነዚህም ቢሆኑ የተጠያቂውን ውስጣዊ ስሜትና እምነት ፈልቅቀው የማውጣት ፍፁም ኃይል አላቸው ለማለት አያስደፍርም። ምክንያቱም ተጠያቂዎች /መላሾች/ አንዳንድ ጊዜ ግልፅ ሆነው የሚያምኑበትንና የሆኑትን ሳይሆን ጠያቂው ይፈልገዋል ብለው የገመቱትን ወይም የራሳቸውን ውጫዊ አስተያየት ብቻ የሚገልፁበት ሁኔታ ስለሚያጋጥም ነው። ስለዚህም ነው አመለካከትን ማጥናት ከባድም ውስብስብም የሚሆነው። ይሁን እንጂ የሚቀርቡት መጠይቆች በጥንቃቄ ተዘጋጅተው ለማወቅ በሚፈለገው ጉዳይ ላይ ያነጣጠሩ ሆነው በአዘገጃጀታቸውም ቀጥተኛ፣ ኢ-ቀጥተኛ፣ ዝግና ክፍት ተደርገው በማሰባጠር በምጣኔ የተዘጋጁ ከሆኑ የታለመውን ጉዳይ ለማውጣት ይችላሉ። በዚህ ሐሳብ ስፖለስኪ /1989፡ 49/ እና አፖንሔይም /1986፡106/ ሙሉ በሙሉ ይስማሙበታል። ጋርድነርም /1982፡192/ የመጠይቆቹ መለኪያነት ሦስቱን የተገቢነት መመዘኛዎች ማለትም ተንባይ ተገቢነት፣ ቅንብራዊ ተገቢነት እና ይዘታዊ ተገቢነት ጠብቀው የተቀረፁ ከሆነ ጥሩ መለኪያ ሊሆኑ እንደሚችሉ ለአለር በሰጠው የተቃውሞ ምላሽ መጣጥፍ ላይ ይጠቁማሉ። በዚሁ ስልት ክሮካልና ሌሎች ተጠቅመውበት ጥሩ ውጤት እንዳገኙበትም ጨምረው ይጠቁማሉ።

አመለካከት እያንዳንዱ ሰው በውስጡ ከሚያልፍበት ሁነት /ከሚገናኘው ነገር/ ጋር ሊኖረው የሚችለውን ቀረቤታና ርቀት ወይም ከተስተጋብሮቱ የሚመነጭን አስተሳሰብ፣ የሚሰጠውን ግምት፣ ሊኖረው የሚችለውን ፍላጎትና ስለጉዳዩ ያለውን አተያይ

ሊያጠቃልል ይችላል። ስለዚህ ስለቀረበው ጉዳይ ግለሰቡ /ቡድኑ/ የሚኖረው አመለካከት ከጉዳዩ /object, referent/ ጋር እንዲዋሀድ ወይም እንዲቃረን ሊያደርግ የሚችል ሥነል ቡናዊ ውዴታና ጥላቻ ልሽቀትና መነቃቃትን ሊያስከትል ይችላል።

ከአመለካከት ውስብስብነትና ድብቅነት ባህሪይ አኳያ የተለያዩ ሰዎች የተለያየ ብያኔ እንደሰጡት ታደለ /1990/ ይጠቃቅሷቸዋል።

‘አመለካከት እያንዳንዱ ሰው ካለበት ሁኔታ ጋር የሚያዛምደው አእምሮአዊ ዝግጅት፣ በልምድ የተዋቀረና በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ተፅዕኖ የሚያርፍበት የጠቅላላ ሁኔታዎች የምላሽ /response/ መግለጫ ነው።’ /አለሮርት 1956/ “የእያንዳንዱ ሰው የእምነትና የአስተሳሰብ መዋቅር፣ ስሜታዊ ተራክቦ፣ ለአንድ ነገር /ሁኔታ/ ሊኖር የሚችል ባህርያዊ ቀረቤታ ወይም ርቀት ነው።” /እነ ሀርዲንግ 1954/ “እያንዳንዱ ሰው በአንድ ነገር ላይ ያለው ውስብስብ ግን ሊመዘን የሚችል አጠቃላይ ተስተጋብሮት ወይም በእያንዳንዱ ግለሰብ አስተሳሰብ መሠረት የሚፈረጅ ለነገሮች የሚኖር አተያይና ግምት ነው።” /ጋርድነር 1985፡9 እኘንሔም 1986፡106/ ይሉታል።

ስሚዝ /1971፡82/ እንደሚሉት አመለካከትን ይማሩታል። ከተማሩት ደግሞ ያስተምሩታልም። እንደ ቋንቋ ሁሉ አመለካከትን የሚማሩትና በልምድ የሚያዳብሩት እምነት፣ አተያይም ነው። ይህ ከሆነ ደግሞ አመለካከት ከደም ጋር የተዋሀደና አብሮ በቀል /innate/ ሳይሆን በትምህርትና በልምድ የሚገኝ ነው። አንድ ሰው አንድን ነገር የመውደድ ወይም የመጥላት ባህርይን ይዞ አይወለድም። የመውደድና የመጥላት ባህርያት የሚዳብሩት ተማሪውን በሚገጥሙት የተለያዩ ሁኔታዎች መነሾነት ነው። በቋንቋ ትምህርት ሂደትም ምንም እንኳን ተማሪው በመጀመሪያ ጥሩ አመለካከት ወይም ከሁሉም ገለልተኛ /neutral/ የሆነ ግምት ይዞ ቢገባም በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ በሚገጥሙት ነገሮች ነው ለትምህርቱም ሆነ ለቋንቋው ያለው አመለካከት የሚለወጠው። ስለዚህ አመለካከት በሚገጥሙን ነገሮች ሁሉ ሊለወጥ፣ ሊዳብር፣ ሊበላሽም ሆነ ሊቃና የሚችል ይሆናል። ይህ ከሆነ ዘንድ የአመለካከት ባህርይው ሁኔታዊ /situational/ እና ተለዋጭ /changeable/ ነው ወደሚለው ውሳኔ ያደርሳል።

ሉድዊንግ ይህንኑ የአመለካከት ተለዋጭነት ከግምት በማስገባት የተማሪዎች አመለካከት አሉታዊ ቢሆን እንኳን አዎንታዊ አድርጎ ትምህርቱ የታለመለትን ግብ እንዲመታ ተማሪዎቹም ከትምህርት ፕሮግራሙ ፍፃሜ ማግኘት የሚፈልጉትን ጥቅም እንዲያገኙ ለማድረግ ይቻላል ይላሉ። የአመለካከትን መለወጫ ዘዴም ሲጠቁሙ:-

> የቋንቋ ትምህርት ፕሮግራም ውጤታማ ሊሆን የሚችለው የትምህርት ሥርዓቱንና የማስተማሪያ ዘዴውን ከተማሪዎች ፍላጐት እንፃር መቅረፅ ስንችል ነው። በዚሁ ላይ ራሳችንን /መምህራን/ ተማሪዎች ለሚማሩት ቋንቋ ካላቸው አመለካከት ጋር አጣጥመን መቅረብ ከቻልን በትምህርቱ ሂደት ጐጂ የሆኑትን እንቅፋቶች ማስወገድ ከመቻላችንም በላይ ተማሪዎች የቋንቋውን ትምህርት በቀና አመለካከትና በነቃ ፍላጐት እንዲቀበሉት ማድረግ እንችላለን። /ሉድዊንግ 1983፡216/

አመለካከት በተለያዩ ግለሰቦች ላይ የተለያዩ ገፅታዎች አሉት። ምንጮቹም እንዲሁ በርካታ ናቸው። ተማሪው የወጣበት ቤተሰብ ማህበራዊ ተባልጦ /social status/፣ ሁለተኛ ቋንቋውን እንዲማር የቀረበበት ሁኔታ፣ ያለፈ የህይወት ገጠመኙ፣ ጭንቀትና ፍራቻን ለሚፈጥሩ ሁኔታዎች የመጋለጡ ደረጃ፣ መሰናክሎችን የመቋቋም ችሎታው፣ ያካበተው ዕውቀት፣ የኢኮኖሚ አቋም፣ ራሱም ሆነ ቤተሰቡ የተሰማራበት የሥራ መስክ፣ ያለፈ የፈተና ውጤት፣ የመኖሪያ አካባቢና ሌሎችም ግለሰባዊ ጉዳዮች / personal factorss / እንደ ፆታ፣ ዕድሜ፣ ዝንባሌ፣ ፍላጐትና ... ወዘተ ያሉት ሁኔታዎች ለአመለካከት ምሥረታ ምንጭም ተፅዕኖ አድራሽ ተላውጦዎችም እንደሆኑ ስሚዝ ብሪርና ሎክን/1971/ ጠቅሰው ያመለክታሉ /1971፡82/ እነዚህኑ ጉዳዮች ሙለየርም /1971/ ትኩረት ሰጥተዋቸዋል።

ስለዚህ ተማሪዎች ለሚማሩት ቋንቋና ለትምህርቱ ያላቸውን አመለካከት ለመረዳት እነዚህን የአመለካከትን ባህርያትና ተላውጦዎች ትኩረት ሰጥቶ መመልከት ይገባል።

### 2·2·2 የአመለካከት መሠረታዊ ምንጮች

ለአመለካከት ምሥረታ በርካታ ሥነትምህርታዊና ማህበራዊ ይዘት ያላቸው ሁኔታዎች ምንጮች ሊሆኑ እንደሚችሉ የተለያዩ ድርሳናት ያስገነዝባሉ። /ታደለ 1990፡139/

ስለአመለካከትና መነቃቃት ምንነትና ከቋንቋ ትምህርት ሂደት ጋር ስላላቸው ተዛምዶ በርካታና ተደጋጋሚ ጥናቶችን ካደረጉ ምሁራን ውስጥ ጋርድነርና ተባባሪዎቹ ተጠቃሽ ናቸው። ጋርድነር /1985፡41/ የተማሪዎችን የአመለካከት ምንጮች በሁለት ክፍሎች መድበው ይመለከቷቸዋል። እነዚህም አንድ፤ አጠቃላይና ዝርዝር፤ ሁለት፤ ማህበራዊና ትምህርታዊ የሚሏቸው ናቸው።

በመጀመሪያው ክፍል ዝርዝር ብለው የሚመለከቷቸው፣ ተማሪው ስለሚማረው ቋንቋና ስለትምህርቱ ያለውን አመለካከት ሲሆን አጠቃላይ ብለው የሚከፍሏቸው ደግሞ በአጠቃላይ ስለቋንቋ ትምህርትና ስለቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ ያለውን አመለካከት ይይዛል ይላሉ። በመቀጠልም በትምህርቱ ሂደት ተማሪው በሁለቱም ዘርፎች ላይ ጥሩ አተያይ ካለው ለውጤቱ አጋዥ እንደሚሆን ጠቁመው በተለይ ግን ከውጤት ጋር ቀጥተኛና ወሳኝ ተዛምዶ እንደሚያሳዩ የሚጠበቁት ዝርዝር አመለካከቶች /ለቋንቋውና ለትምህርቱ/ ናቸው።

ጋርድነር በመቀጠል እነዚህንና /አጠቃላይና ዝርዝር/ ሌሎችንም ያጠቃለሉበት ምደባቸው ትምህርታዊና ማህበራዊ ብለው የከፈሉት ነው። ትምህርታዊ በሚሏቸው ውስጥ ተማሪው ለመምህሩ፣ የቋንቋውን ትምህርት ለሚማርበት ስልትና ሁኔታ፣ ለማስተማሪያ መሣሪያዎችና በጠቅላላው ከመማር ማስተማር ሂደት ጋር በሚገናኙ ጉዳዮች ላይ ያለውን አመለካከት ያጠቃልሏቸዋል። በማህበራዊ ሥር ደግሞ ተማሪው ስለሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰብ፤ ስለባህላቸው፣ ስለቋንቋቸውና ስለሌሎች ከትምህርቱ ውጭ የሆኑ ነገሮችን ያካትቷቸዋል።

ጋርድነር እንደሚሉትና ሌሎችም እንደሚስማሙበት /ስፓለስኪ 1969፤ እና ዱቢን 1986፡14/ ከነዚህ የአመለካከት ምንጮች ውስጥ ተማሪው ስለትምህርቱና ስለቋንቋው የሚኖረው አመለካከት ከውጤቱ ጋር ያላቸው ዝምድና ሲታይ ሁለቱም በዕኩል ደረጃ ዝምድናቸው የጠበቀ ላይሆን ይችላል። ለምሳሌ አጠላቃይና ማህበራዊ ባህርይ ያላቸው ምንጮች በውስጣቸው ጥቅልና የተለያዩ በርካታ ጉዳዮችን የሚይዙና በቀጥታ ከትምህርቱና ከክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደት ጋር ያላቸው ግንኙነት በበርካታ

ሁኔታዎች ውስጥ አልፎ የሚመጣ ነው። ነገር ግን ዝርዝርና ትምህርታዊ የሆኑ አመለካከቶች ቋንቋውን፣ ትምህርቱን፣ መምህሩንና የክፍል ውስጥ ተራክቦውን በቀጥታ የሚያቅፉ በመሆናቸው በመለኪያው ወቅት ተፅዕኖአቸው/አስተዋፅዖአቸው/ ከተማሪዎች የፈተና ውጤት ላይ ፈጥኖ የሚንፀባረቅ ይሆናል። ይሁን እንጂ የምንጭነት ሀይላቸውን በደረጃ ለማየት እንጂ ሁለቱም ክፍሎች በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት ላይ ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱ ተላውጦዎች መሆናቸውን ግን አያስቀረውም ይላሉ። /ጋርድነር 1985፡ 41-43/። ጋርድነር በአመለካከትና በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት መካከል ስላለው ተዛምዶ ያቀረቧቸውን ጥናቶች አስመልክቶ ሔስ ያቀረቡትና በተቃዋሚ ጐራ የተሰለፉት አለር /1982፡183/ የተጠቀሙባቸውን የአመለካከት መለኪያዎች ተገቢነት ከመጠራጠር በቀር እነዚህን ተላውጦዎች እንዳሉ ተቀብለዋቸዋል።

ከነዚህ በተጨማሪ ሌሎች ጉዳዮችም አብረው የሚታዩ እንደሆኑ ስሚዝ፣ ሙለርና ሬይነርት ይጠቃቅሷቸዋል። የተማሪው ቀደምት የትምህርት ውጤት ዝቅተኛ መሆን፣ በራሱ ብቁ አለመሆን፣ ግምትን፣ የደካማነት አስተሳሰብን፣ ትምህርቱን አስቸጋሪና ከባድ አድርጐ የመቁጠር ግምቱን ስለሚያጐለብተው ለትምህርቱ አሉታዊ አመለካከትን ያዳብራል።

በሌላ በኩል ደግሞ ተማሪው በሁለተኛ ቋንቋነት የቀረበለትን ቋንቋ የሚማረው በምርጫ ማጣት ወይም በትህምርት ተቋሙና በሥርዓተ ትምህርቱ የሚሰጥና መማር ስለሚገባው ወይም ለምዝገባ ስለሚያበቃው በመሆኑ ብቻ ከሆነና ተማሪው እያደር በትምህርቱ እየገፋ ሲሄድ ከቋንቋው ትምህርት የሚያገኘው ጥቅም ሥርዓተ ትምህርቱ የነደፈውን የትምህርት ፕሮግራም መስፈርቶች ከመሟላት አልፎ ለወደፊት ህይወቱ ብዙም ፋይዳ እንደማይሰጠው አድርጐ ሲገምት አመለካከቱ ዝቅ እያለ ይሄዳል። ስለዚህም አመለካከቱ አዎንታዊው ጥቂት፣ ያለየለት /neutral/ በርከት ያለ ሲሆን አሉታዊው አብላጫውን እጅ ይይዛል።

ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋ ለብዙ ጊዜ ተምረው የራሳቸውን ብሔረሰብ ቋንቋ እስከመርሳት የሚደርሱበት ወይም በእፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሲጠቀሙ የሁለተኛ ቋንቋው

ተፅዕኖ የሚያደርስበት ሁኔታ ይኖራል። ነገር ግን ቀስ በቀስ የራሳቸውን ማንነትና የራስ ቋንቋና ባህል ባለቤትነት ጥያቄ እንስተው ራስን መናፈቅ ሲጀምሩ ሁኔታው የተከሰተው የሁለተኛው ቋንቋ ባደረሰባቸው ተፅዕኖ ምክንያት መሆኑን ሲረዱ የቋንቋውን ትምህርት ሊጠሉት ይገፋፋሉ። ለቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብም የሚኖራቸው ግምት እየላላ ይሄዳል።

በትምህርቱ ሂደት ወቅት ተማሪውን ወደጭንቀትና ፍራቻ ሊገፉት በሚችሉ ሁኔታዎች ውስጥ እንዲገባ የሚያደርጉት ሁኔታዎች ሲገጥሙት አጠቃላዩን የትምህርቱን ሂደት ጠልቶ ትምህርቱን እስከማቋረጥ ይደርሳል። ጥቂት ቆይታ አድርጐ ቢማርም ውጤቱ እያሽቆለቆለ ይሄዳል። እነዚህና የመሳሰሉት ጉዳዮች ከአመለካከት ምሥረታ ምንጮች ውስጥ የሚጠቀሱ እንደሆኑ ክፍ ሲል የተጠቀሱት ምሁራን ይጠቁማሉ። /ስሚዝ 197፡18-28፤ ሙለር 1972፡290-291፤ ሬይነርት 1970፡107/

ዱቢንና አልሽቴይን /1986፡1415/ ደግሞ ለአሉታዊ አመለካከት ምሥረታ ምንጭ የሚሆኑ ጉዳዮችን ዘርዘር አድርገው ይገልፃሉ። በአንድ ቋንቋ ላይ አሉታዊ አመለካከት መዳበር ከተለያዩ ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ብሔራዊና ማህበራዊ ግጭቶች ጋር የተዛመደ ነው። ለምሳሌ አንድ አገር በሌላ አገር /ማህበረሰብ/ በቅኝ ግዛት የተያዘች ከሆነች አብዛኛው ህዝብ ለቅኝ ገዥው ማህበረሰብና ቋንቋ ጥላቻ ይኖረዋል። የገዥው ማህበረሰብ ቋንቋ ለጋራ መግባቢያ ወይም ለትምህርት መስጫነት የዋለ ከሆነ ተማሪዎች የግድ እንዲማሩት ስለሚደረግ ከወጡበት ማህበረሰብ ጭምር ለቋንቋው ትምህርት አሉታዊ አመለካከት ያሳድራሉ። ከዚህ ሌላ ደግሞ የፍላጐት ግጭቶች ለአሉታዊ አመለካከት መነሻ ይሆናሉ። የትምህርት ተቋሙ ትምህርቱን የሚያቀርብበት ዓላማ ተማሪው ቋንቋውን ሊማር ከ፡ፈለገበት ዓላማ /ለወቅታዊ ወይም ለዘለቄታ ጠቀሜታ/ ጋር የማይገናኝ ከሆነ አሁንም ለቋንቋውና ለትምህርቱ አሉታዊ አመለካከት ይኖረዋል። በውጤቱም ዝቅተኛ ይሆናል።

እነዚህ ተላውጠዎች እንደተጠበቁ ሆነው ከሁለተኛ ቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ጋር የጠበቀ ግንኙነት አላቸው በማለት ጋርድነር /1985፡41/ የተመለከቷቸውን

ትምህርታዊና ማህበራዊ የሆኑ በተማሪው አመለካከት ላይ ተፅዕኖ የሚያደርሱ ዋና ዋና ጉዳዮችን በተናጠል እንመልከታቸው።

2·2·2·1 ወላጆች፣ ባልንጀሮችና ማህበረሰብ

ተማሪው በመደበኛ የትምህርት ሥርዓት ለሚሰጥ የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት የተጋለጠበት የተለያዩ ምክንያቶች ሊኖሩት ይችላሉ። ከነዚህ ምክንያቶች ውስጥ ከላይ እንደተጠቀሰው ቋንቋው በሥርዓተ ትምህርቱ ውስጥ እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት ወይም በአገሪቱ ከሚገኙ የተለያዩ ቋንቋዎች በአጋጣሚ ወይም በአዋጅ አንዱ ተመርጦ በትምህርት መስጫ ቋንቋነት በመቅረቡ ብቻ በምርጫ ማጣት ወይም በሁኔታዎች አስገዳጅነት ሊሆን ይችላል። ይህ ከሆነ ተማሪው ትምህርት ቀስሞ ወደፊት በሚገጥመው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ህይወት ውስጥ ተሳታፊ ለመሆን ወይም የራሱን የዕውቀት ደረጃ አደላድሎ ለመቅረብ የሚችለው ሲማር በመሆኑ በቀረበው የትምህርት ሥርዓት ውስጥ ገብቶ ቋንቋውን ሊማር ግዴታ ይሆንበታል። ከዚህ ውጭ ደግሞ በራሱ አነሳሽነትና ፍላጐት የተለያዩ ዓላማዎችን ለመምታት ሲል በውዴታ ሊማረውም ይችላል። ሁኔታው የትኛውም ይሁን /ውዴታ ወይም ግዴታ/ የተማሪው ቤተሰብና የወጣበት ማህበረሰብ ለተማሪው የመማር ፍላጐትና አመለካከት አፈጣጠር አስተዋፅዖ ይኖራቸዋል።

ፒኩናስ /1976፣ 61-70/ ወላጆች ለልጆቻቸው የሚያስተላልፏቸውን ባህርያት አስመልክተው እንደሚሉት፣ ቤተሰብ በልጆቻቸው ላይ የዘር ደምን ማስተላለፍ ብቻ ሳይሆን ስለአካባቢያቸው ሁኔታ የግንዛቤ አቅጣጫን ማስያዝ ተቀዳሚ ተግባራቸው ነው። ቤተሰብ ለልጆቻቸው ክብካቤን ከማድረግ በተጨማሪ ሃይማኖታቸውን ማስተማር፣ ባህልና ሥነምግባርን ማስተላለፍ፣ የስብዕና መሠረታቸውንም የማስጨበጥ ድርሻ አላቸው። ወላጆች በልጆቻቸው የወደፊት ባህርይና ስብዕና ምሥረታ ላይ የሚኖራቸው አሻራ ጥቂት የሚባል አይደለም። የቤተሰብ የስብዕና ባህርያትና ለተለያዩ ነገሮች የሚኖራቸው አመለካከት የልጆችን የባህርይ መሠረት የሚያርቅ ይሆናል። የህፃናት የግንዛቤ አቅጣጫ በዘመዶቻቸው ሞዴልነት ይወጣል። ቤተሰብ ቊልቁና ከፍተኛ ኃይል ያለው የትምህርት ተቋም ነው። ከዚሁ ባላነሰ ደረጃ ተማሪው ያደገበት አካባቢ፣ ጐረቤቶች፣ ባልንጀሮችና

አጠቃላይ ማህበረሰቡ በህፃናት የስብዕና፣ የባህል፣ የአመለካከትና የግንዛቤ ቀረፃ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ አላቸው ይላሉ። በዚህ ሐሳብ ሊትልውድ 1984፣ 55/ ይስማማሉ።

ህፃናት በቅድሚያ የሚቀርፁትና የሚያንፀባርቁት አስተሳሰብ ከቤተሰባቸው የቀዱትን እንደሆነ ላምበርት/1974፣ 95-96/ ደግሞ ያረጋግጣሉ።

> ወላጆች የህፃናት የመጀመሪያና መሠረታዊ አስተማሪዎች ናቸው። ህፃኑ ስለቤተሰቡ ማንነት፣ በማህበራዊ ተባልጦ ውስጥ የሚገኝበትን ቦታና ደረጃ፣ አንዱ ማህበረሰብ ከሌላው ተለይቶ እንዲታይ የተደረገበትን ምክንያት፣ የባህልና የቋንቋ ልዩነቶችን እንዲሁም አጠቃላይ የስብዕናውን ቀረፃ ከቤተሰቡ ይቀስማል። ስለራሱ የየትኑትና የማንነት ደረጃና ስለሌሎችም በአእምሮው ከቀረፀ በኋላ በመጀመሪያዎቹ የትምህርት ቤት ቆይታዎች የሚገጥሙት ሁኔታዎች ቀደም ብሎ ካዳበረው አስተሳሰቡ ጋር እየተለዩበት ከሄዱ እነዚህ እምነቶች እየተጠናከሩ ይሄዱና ራሱን ከሌላው ማህበረሰብና ቋንቋ እየለየ ብሔረሰባዊ ተቃርኖ ውስጥ እየገባ ይሄዳል። የሚማረውንም ቋንቋ ከወጣበት ብሔረሰብ አንፃር መመልከት ይጀምራል ይላሉ።

ተማሪው ስለቋንቋና ስለተለያዩ ብሔረሰቦች ከቤተሰቡ የቀዳው አመለካከትና በትምህርት ቤት በቀረበው ቋንቋና የትምህርት ሥርዓት መካከል የሰፋ ልዩነት እየተፈጠረ ሲሄድ ወደራሱ ውስጥ ብቻ የሚመለከት ይሆንና በትምህርቱ ሂደት ላይ ያለው ተሳትፎ ይቀንሳል። የሁለተኛ ቋንቋውንና ተናጋሪዎቹንም እየጠላ ይሄዳል። በተለይም ደግሞ መምህሩና የክፍል ጓደኞቹ ተማሪው ለወጣበት ማህበረሰብና ለቋንቋቸው አነስተኛ ግምት የሚሰጡ ከሆነ ጥላቻው እየተባባሰ አመለካከቱም አሉታዊ እየሆነ ይሄዳል። በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለ የቋንቋው ትምህርት በትምህርት ሥርዓቱ ውስጥ በመገኘቱ ብቻ የግድ እንዲማር ሲደረግ ደግሞ የመማር ፍላጎቱ እየሟሸሸ የቋንቋውን ትምህርት ከወጣበት ማህበረሰብ አኳያ እንዲመለከተው ይገፋፋል በማለት ሙለር /1971፡290/ ያጠናክሩታል።

ስሚዝ /1971፡84/ ተማሪውን ካደገበት አካባቢ ጋር በማያያዝ ሲያብራሩ፣ ተማሪው ባደገበት አካባቢ በሁለት ጉሣዎች መካከል ግጭት እተፈጠረ በየወገኑ ተከፍለው በጥላቻ ሲተያዩ መኖራቸውን ሲመለከት ካደገ አንዱ በአንዱ ላይ ያለውን የቅራኔና የጥላቻ ባህርይ በአእምሮው በመቅረፅ የጐሠኝነት ስሜት እየተጠናወተው ይሄዳል። ይኸው የጐሠኝነት

ባህርይው በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማረው ቋንቋና በቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ ላይም ሊንፀባረቅ ይችላል።

ሙለር ተማሪዎች ከቤተሰባቸውና ከአካባቢያቸው የቀረፁት የጐሠኝነት ስሜት በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት ላይ መንፀባረቁን በመረጃ ሲያስረግጡ፡

> ሙለርና ሚለር በኪንታኪ ተማሪዎች ላይ ባደረጉት ጥናት ተማሪዎች ለፈረንሳይኛ ቋንቋ ያላቸው አመለካከት አሉታዊ ሆኗል። ለዚህም ምክንያቱ በጥቅም ላይ የዋሉት የማስተማሪያ ዘዴና የትምህርት መማሪያዎች ሲሆኑ ሌላው ዋንኛ ጉዳይ ከተማሪዎቹ የብሔረሰባዊ ስሜት የመነጨ አመለካከት ነው። ተማሪዎቹ የፈረንሳይኛ ቋንቋን ያለፍላጐት እንዲማሩ በመደረጋቸውና ለፈረንሳዮች ባላቸው መጥፎ አመለካከት አነስተኛ ውጤት አሳይተዋል። ይህንን ስሜት ከወጡበት የኪንታኪ ማህበረሰብ ይዘውት የመጡት ነው። /1971 ፡ 294/ ይላሉ።

ላምበርትና ተከርም /1972 ፡ 175/ በሞንትሪያል በሚገኙ ተማሪዎች ላይ ባደረጉት ጥናት በእንግሊዞችና በፈረንሳይ ካናዳውያን ማህበረሰቦች መካከል ለዓመታት የቆየው ውጥረትና ጥላቻ በቀጥታ ከአዋቂዎች ወደ ልጆች ተላልፎ በትምህርቱ ሂደት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ እንዳደረሰ አረጋግጠዋል። ወላጆችና ያካባቢው ማህበረሰብ እንዱ ለአንዱ ባለው አነስተኛ ግምትና ጥላቻ ምክንያት በተማሪዎች አመለካከትና በውጤታቸው ላይ እንደተንፀባረቀ የጥናት ውጤታቸው ማሳየቱን ይጠቁማሉ። ጋርድነር /1985 ፡ 109/ በዚህ ሐሳብ ይስማሙበታል።

ስሚዝ /1971 ፡ 83/ እንዲሚሉት ለትምህርት ለቀረበው ቋንቋ አሉታዊ አመለካከት ያለው ወላጅ ልጁ ለትምህርቱ እንዲነቃቃ ለማድረግ አይሻም። በአንፃሩ ደግሞ ለሁለተኛው ቋንቋና ለተናጋሪዎቹ መልካም ግምት ያለውና ይልቁንም ወላጆች በዚሁ ቋንቋ ዕውቀት ጥሩ ልምድ ያላቸውና ልሳነ ክልኤ ከሆኑ ልጁ ይህንኑ መልካም ግምት ይዞ ትምህርቱን በንቃት እንዲከታተል ግፊት ያደርጋል። ይህንኑ ሐሳብ ጋርድነር /1985 :44/ ይደግፉታል።

ስፓለስኪ /1969 ፡ 272/ ካሮልን ጠቅሰው፡በተማሪዎች የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት ላይ የወላጆች አመለካከት ከፍተኛ ተፅዕኖም አስተዋፅዖም እንዳለው ይጠቁማሉ።

ቤተሰብ ተማሪው የሚማረውን ሁለተኛ ቋንቋ በቤት ውስጥ በብዛት የሚጠቀምበት ከሆነና ለቋንቋውም ጥሩ ግምት ካለው ልጁ ለትምህርቱ ያለው ፍለጐት ከፍተኛ ከመሆኑም በላይ ጥሩ ውጤት ማስመዝገብ እንዲችል ሁኔታዎች የተመቻቹለት ይሆናል። ምክንያቱም ተማሪው ቋንቋውን ከትምህርት ቤት ውጭ በቤት ውስጥ የመማር ዕድሉ የሰፋ ከመሆኑ ባሻገር የሁለተኛው ቋንቋ የሚነገርበትን አካባቢ እንዳገኘ ያህል ይጠቀምበታል። ለቋንቋውም እንደቤተሰቡ ሁሉ ጥሩ አመለካከት ያዳብራል።

ማክላጉሊን /1991 ፡ 126/ በውጤታቸው ስኬታማ የሚሆኑ ተማሪዎች ለታላሚው ቋንቋና /target language / ለተናጋሪው ማህበረሰብ ባህል ቀና አተያይ ያላቸውና በቋንቋው ለተለያዩ ጉዳዮችና በተለያዩ ዐውዶች ላይ ለብዙ ጊዜ በውዴታ ልምምድ የሚያደርጉት ናቸው። ከቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ ጋርም ቅልቅል የመፍጠር ፍላጐታቸውም ጠንካራ ይሆናል በማለት ይስረግጣሉ። በዚህ ሐሳብ ሊትልውድ /1989 ፡ 55/ ይስማሙበታል።

ጋርድነርም/1985፡ 7/ እነዚህ አመለካከቶች የሚዳብሩትና የሚመሠረቱት ያለጥርጥር ከቤተሰብና ከአካባቢ ነው። በማህበረሰቡ ይጐለምሳሉ። በተማሪው ባል ንጀሮች ደግሞ የበለጠ ይጠናከራሉ። በመጀመሪያ ጊዜ እነዚህ የአመለካከት መሠረቶችና ደረጃዎች በግልፅ ተለይተው ላይጤኑ ይችላሉ። ነገር ግን ተማሪው በትምህርቱ ሂደት ውስጥ ከገባ በኋላ እያደር እየወጡ፤ በተለያዩ አጋጣሚዎች እየተንፀባረቁ በመጨረሻ ለትምህርቱ ሂደትና ለጥሩ ውጤት እንቅፋት በመሆን በግልፅ መታየት ይጀምራሉ። ይላሉ እነ ሬይሞንድም /1990/ በዚሁ ላይ አበክረው አስያየታቸውን ይሰጣሉ።

እንደ ሀርመር /1990 :4/ አስተሳሰብ ደግሞ፤የተማሪው አመለካከት ባካባቢው በሚገኙ ነገሮች ሁሉ ይሳባል። ለምሳሌ የተማሪው ቤተዘመዶች ለታላሚው ቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰብ ባህልና ቋንቋ ጥላቻ ያላቸው ከሆነ የልጆቻቸው አመለካከት አሉታዊ እንዲሆን የማድረግ ሀይል አላቸው። የተማሪው ባልንጀሮች ለሚማሩት ቋንቋ ያላቸው አመለካከት አሉታዊ ወይም አዎንታዊ መሆንም ተመሳሳይ ውጤት ያመጣል። ባል ንጀሮቹ፤ የሚማሩት ቋንቋ ጠቃሚና አስፈላጊ፤ ቋንቋውን ማወቅ ለወደፊት ማህበራዊ ህይወት ብሩህ ተስፋ የሚጭር አድርገው በትጋት የሚሳተፉበት ከሆነ ተማሪው ተመሳሳይ

ጥረት እንዲያደርግ ይገፋፋል። የወጣበት ማህበረሰብና ያደገበት አካባቢም ተመሳሳይ ውጤት አለው።

የሁለተኛ ቋንቋን መማር የቋንቋውን ሥነልሳናዊ ባህርያት ብቻ ማጥናት ሳይሆን የሌላ አዲስ ማህበረሰብን ባህልና ልምድም ጭምር መማር ነው። ውጤቱም ልሳነ ክልኤ ብቻ ሳይሆን ባህለ ክልኤ መሆንም ነው /እነ ላምበርት 1972 ፥ 154/ — ስለዚህ ተማሪው ለቋንቋው ብቻ ሳይሆን ለቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ ባህልና ልምድ እንዲሁም የአኗኗር ዘይቤ መልካም ግምት ሊኖረው እንዲችል ከቤተሰቡ ጀምሮ ባልንጀሮቹና የወጣበትም ማህበረሰብ የሚሰጡት የአመለካከት መሠረት በአዎንታዊ መንገድ የተገነባ ከሆነ የተማሪውን አመለካከት አዎንታዊ ከማድረግ አልፎ በውጤቱ ጥሩ እስመዝ፡ገቢ እንዲሆን አጋዥነት አለው።

2·2·2·2 <u>መምህሩና የማስተማሪያው ሥነዘዴ</u>

ለሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት የቀረበው ተማሪ ትምህርቱን በሙሉ ፍላጐትና በንቃ ተስትፎ መማር ይችል ዘንድ ሁኔታዎችን ለማስተካከል ጥረት ከሚያደርጉ ክፍሎች ውስጥ ትልቁን ድርሻ እንዲወስድ የሚጠበቀው ከተማሪው ጋር የቅርብ ግንኙነት ያለው መምህሩ በመሆኑ የመማር ማስተማሩን ድባብ ለማመቻቸት ያላሰለሰ ጥረት እንዲያደርግ ይጠበቅበታል። /ሀርመር 1990፤ ስፓለስኪ 1969/

መምህሩ፤ ተማሪዎች ቋንቋውን ሲማሩ ምን እንደሚሰማቸው፤ በትምህርቱ ሂደት በፍላጐትና በንቃት መሳተፍ አለመሳተፋቸውን፤ ለቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብና ለትምህርቱ ያላቸውን መልካምና መጥፎ አመለካከት፤ ስለራሱ ስለመምህሩና ስለሚጠቀምበት የማስተማሪያ ስልት ያላቸው አተያይ ምን እንደሆነ፤ ቋንቋውን ለምን ዓላማ ሊማሩት እንደሚፈልጉ ... ወዘተ በውል አጢኖ ከተማሪዎች ሁኔታ ጋር የተሰማማ የማስተማር ቅያስ መፍጠርና ለተማሪዎች ቀና አመለካከት ኖሮት የትምህርቱን ሂደት መምራት ይገባዋል። ነገር ግን መምህሩ ራሱ ለሚያስተምረው ቋንቋና ለማህበረሰቡ እንዲሁም ለተማሪዎቹ አጉል አመለካከት ካለው የትምህርቱ ሂደት አደጋ ላይ ይወድቃል። ስለዚህ ተማሪው ድክመት በሚያሳይበት የትምህርት ክፍል እገዛ በማድረግ፤ የመማር

ፍላጐቱን በማነቃቃት ለትምህርቱ ያለውን አመለካከት ቀና እንዲሆን በማነሳሳት ሙያዊ ግዴታውን የመወጣት ሀላፊነት አለበት። /ሀርመር 1990፡ 4፤ 225፤ ሪቨርስ 1989 ፡ 132፤ ቻስቴይን 1983፡126/

ራይት /1987 ፡ 43/ የክፍል ውስጥ ትምህርት የቡድን ሥራ ነው። በመማር ማስተማር ክንውን ተማሪው ሙሉ ተሳታፊ እንዲሆንና የተማሪ-ተማሪ፤ የተማሪ-መምህር ግንኙነት እንዲጠናከር፤ ተማሪው ራሱ ከሚሠራው እንዲማር ··· ወዘተ የማድረግ ሀላፊነት የመምህሩ ነው።

ጥሩ መምህር የሚባለው ለተማሪዎች ፍላጐት ስሉ /sensitive/፤ በማስተማር ዘዴው ስልታዊ፤ በመምህር ተማሪ ግንኙነት የመማማር ዘዴ አምኖ የሚተገብር፤ በሚያስተምረው የትምህርት ዓይነት /ቋንቋ/ በቂ ችሎታ፤ ፍላጐትና የተደላደለ ዕውቀት ያለው ነው። እንዲህ ያለ መምህር የተማሪዎችን አመለካከትና የመማር ፍለጐት አዎንታዊ ማድረግ አይሳነውም/ዝኒ ከማሁ 1987 ፡ 225/ ለቋንቋው ትምህርት አዎንታዊ አመለካከት ያለው ተማሪ የክፍል ውስጥ ጠንካራ ተሳታፊ ሊሆን እንደሚችል መምህሩ ሊገነዘብ ይገባዋል /ሹይና ፋሶልድ 1973 ፡ 36/።

መምህሩ ቋንቋውን የሚያስተምርበት ስልት የተማሪዎችን አመለካከት ለመለወጥና ለማቃናት ከፍተኛ አስተዋፅዖ አለው። /ጋርድነር 1985 ፡ 8/ የተማሪው አመለካከት አሉታዊ ቢሆን እንኳ የቋንቋው ትምህርት በክፍል ውስጥ የሚሰጥበት ሁኔታ ሳቢነት ያለውና አስደሳች ከሆነ፤ መምህሩም ለተማሪው ደግ አመለካከት ኖሮት እገዛ በማድረግ ካፀረታታው የመማር ፍላጐቱ እየጨመረ ይሄዳል። ይህ ሊሆን የሚችለው ደግሞ መምህሩ በቋንቋው ላይ በቂ ችሎታና ዕውቀት ሲኖረው፤ የተማሪዎችን ፍላጐት ለመጠበቅ የሚጨነቅ ሲሆን ነው። ነገር ግን መምህሩ በቂ ዕውቀት የሌለው፤ ለተማሪዎች ፍላጐትና ስሜት ደንታ ቢስ ከሆነ፤ አሰልቺና መንቻካ የማስተማር ስልት ከተጠቀመ፤ ከተማሪዎቹ ጋር መቀራረብ ከሌለው ተማሪው ቀድም ብሎ ጥሩ አመለካከት ይዞ ቢቀርብ እንኳን ፍላጐቱ እየሚሸሽ አመለካከቱ ዝቅ እያለ ይሄዳል። /ታሮንና ዩሊ 1989 ፡35፤ ሊትልውድ 1984 ፡ 55፤ ሮቢንሰን 1991 ፡ 80/

ጋርድነር /1985፡ 41/ ይህንኑ ጉዳይ አስመልክቶ፣ አንዳንድ ጊዜ ተማሪዎች ለቋንቋው ጥሩ አመለካከት እያላቸው ጥሩ ውጤት የማያመጡበት ጊዜ ያጋጥማል። ይህ የሚከሰተው ለመምህሩና ለስልቱ እንዲሁም ለማስተማሪያ መሣሪያዎች ባላቸው ጥላቻ የተነሳ ትምህርቱን ሊያጠኑትና በወጉ ሊከታተሉት ስለማይፈቅዱ የፈተና ውጤታቸው ዝቅተኛ ይሆናል። ስለዚህ መምህሩ ለተማሪዎችና ለሚያስተምረው ቋንቋ እንዲሁም ለሙያው ያለው አመለካከት በተማሪዎች አመለካከትና ውጤታቸው ላይ ተፅዕኖ ይኖረዋል። ይህንኑ ሐሳብ መድህኔ /1986 ፡ 11/ አበክሯ ይመለከቱታል።

ስሚዝ /1971 ፡ 87/ እንደሚጠቁሙት ተማሪው ስለትምህርትና መማር ማሰብ ከመጀመሩ በፊት ማህበራዊ ቅቡልነትና የሠላም ዋስትና ሊያገኝ ይሻል። በትምህርቱ ሂደት የጭንቀት፣ የውጥረትና የፍራቻ ስሜቶች እንዲጫኑት ከተደረገ በቋንቋው ላይ ል ምምድ ከማድረግ ይልቅ በክፍል ውስጥ በሚፈጠሩ ክስተቶች ሁሉ የሚበረግግና አፈ-ል ጉም ይሆናል። ህፃናት እንደ እንስሳት የተሰጣቸውን ሁሉ የሚቀበሉ፣ እየተገረፉ የሚገሩ ወይም እንደ ሮቦት ፕሮግራም በመምህሩ ስሌት የሚገጣጠሙ አይደሉም። ተማሪዎችን አስተምሮ ለጥሩ ውጤት ለማብቃት መምህሩ ከተማሪዎቹ ጋር ግብቡ፣ ተገቢ አክብሮት የሚሰጥ፣ የማስተማር ስልቶችን እንደተማሪዎቹ ማንነት ለማመቻቸት ጥረት የሚያደርግ መሆን ይገባዋል። ማስተማር በሳይንስ ላይ የተመሠረተ ጥበብ ነው። ምርጥ መምህር በርካታ የግለሰብና የማህበረሰብ ጉዳዮችን በክፍል ውስጥ በማምጣት የተለያዩ የተማሪ ልዩነቶችን አጢኖ በመመልከት ከሁኔታው ጋር አጣጥሞ የሚከወን የማስተማር ስልት ቀይሶ ተፈላጊ የመማር ክንውኖችን ማቅረብ የሚችል ነው በማለት አስረግጠው ያስገነዝባሉ። በዚህ ሐሳብ ማክአተር /1983 ፡ 88/ ይስማሙበታል።

ሙለር /1971 ፡ 296/ ይህንኑ የመምህር ተግባር በማጠናከር፣ ተማሪዎች በጥሩ ፍላጎት እንዲማሩና ጥሩ ውጤት እንዲያስገኙ የትምህርት ክንውን አቅርቦት ጥራት መጠበቅ ይገባዋል ይላሉ። የትምህርት ክንውኑ ከተማሪዎች ችሎታ፣ ዕውቀትና ዝንባሌ ጋር ስምሙ መሆን እንደሚገባውና ተማሪዎች ለትምህርቱ የቀረቡበትን ዓላማ ተገንዝበው ወደ ግቡ እንዲጓዙ ማስቻል እንደሚጠበቅበትም ያሳስባሉ። እስካሁን አንዱ ከአንዱ ለአንድ ሁኔታ ይሻላል ከሚባል በስተቀር ፍፁምና እንከን የለሽ የሚባል የማስተማሪያ ዘዴ

ስለሌለ እንደሁኔታው ሊለዋወጡ የሚችሉ አመቺ የማስተማር ቴክኒኮችን እያለዋወጠ መጠቀም አንዱ ብልሀት እንደሆነ ያመለክታሉ።

ናፕ /1972 ፡ 27/ ደግሞ መምህራን እርግጥ ስለአካባቢያቸውም ሆነ ስለተለያዩ ነገሮች የራሳቸው ግንዛቤ፣ ፍላጐትና አመለካከት አላቸው። ይህም ቢሆን ግን መምህሩ ራሱ የሚያምንበትንና የሚፈልገውን አስተሳሰቡን እንዳለ ተማሪዎች እንዲቀበሉት ከማድረግ ይልቅ ተማሪዎች የሚፈልጉትን መሆን፣ የሚመርጡትን እንዲይዙ ዕድል መስጠት፣ ግን የታለመውን ዓላማ እንዳይስቱ መስመር ማስያዝ እንጂ የእኔን መስመር ብቻ ተከተሉ በማለት የራሳቸውን የፍላጐት አቅጣጫ እንዲያጥፉ እንቅፋት መሆን የለበትም በማለት ያስቀምጣሉ።

መምህሩ የቋንቋውና የትምህርቱ ብቸኛ ምንጭ ተደርጐ መቆጠር የለበትም። እሱ ከሌለ ሁሉም ነገር እንደሚቆም ወይም የክፍሉ የመማር ክንውን ባለቤት መምህሩ ብቸኛው አስኳል ሰው ተደርጐ ሳይወሰድ ተማሪዎች እርስ በርሳቸው በሚያደርጉት መስተጋብር መማማር መቻላቸው ከግምት ገብቶ ዕድሉ ሊሰጣቸው ያስፈልጋል። መምህሩ የትምህርቱን ሂደት የሚመራ፣ እንቅስቃሴውን የሚያፋጥን፣ የሚያስተምርና የሚማርም ሆኖ የተማሪዎችን የቋንቋ ተግባቦት ደረጃ ለማዳበር ሰፊ የልምምድ ዕድል የሚሰጥ መሆን ይገባዋል። ተማሪ የሚማረው መምህሩ በሚነግረው ብቻ ሳይሆን ራሱም ከሚያደርገው መሆኑ በውል ሊታወቅ ያሻል። /ሪቻርድስ 1987 ፡ 24፣ ግሪን 1979 ፡ 185/

በሌላ በኩል በጥንታዊና በባህላዊ የትምህርት ተቋማትና በኋላ ቀር የትምህርት መሣሪያዎች እንዲሁም በማይለወጥ የማስተማሪያ ስልት የሰለጠኑ መምህራን ከዘመናዊ አስተሳሰቦችና የትምህርት መሣሪያዎች ጋር ራሳቸውን ማጣጣም ይቸግራቸዋል። /እንዱቤን 1986፡ 31/። በነዚህ መምህራን የሚማሩ ተማሪዎች እንግራዊ በሆነ መንገድ ሲታይ የመማር ፍላጐታቸው ተጠብቆ የክፍል ውስጥ የተማሪ-መምህር ግንኙነት ተጠናክሮ በዘመናዊ የማስተማሪያ ሥነዘዴዎች የመማር ዕድል ያገኛሉ ማለት አያስደፍርም። የዚህ ዓይነቱ ሁኔታ ሲያጋጥም ተማሪዎች ለመምህሩም ሆነ ለቋንቋው ትምህርት ያላቸው አመለካከት እያደር እያሽቆለቆለ በመሄድ በውጤታቸውም በአመዛኙ ዝቅተኛ ይሆናሉ።

የመማሪያ ክፍሎች የተለያዩ እንቅስቃሴዎች የሚታዩባቸው ገፀ-ብዙ ቦታዎች መሆናቸውን መምህራን በውል ያውቃሉ። የመማሪያ ክፍል በተለያዩ ርዕስ ጉዳዮች ላይ በበርካታ ተሳታፊዎች ብዙ ክንውኖች የሚፈፀሙበት፣ ከተለያዩ አቅጣጫዎች የተለያዩ ፍላጐቶች የሚንፀባረቁበት፣ በርካታ የሀሳብ ግጭቶች የሚፋጩበት፣ የተለያዩ ባህርያት በአንድ ላይ የታጨቁበት፣ በጥቅሉ የገሀዱ ዓለም የተለያዩ የህይወት መልኮች የሚታዩበት አስቸጋሪ ቦታ ነው። ስለዚህ መምህርነትና ማስተማርን ከውጭ ሆነው ከሚገምቱ ሰዎች ይልቅ በወስጡ የሚገኙ መምህራን የበለጠ ስለሚያውቁት የተቀናጀ የክፍል አመራር ለማድረግ ሰፊ ዝግጅት፣ ጥረት፣ ብቃትና ፍላጐትም ሊኖራቸው ይገባል። /ኑናን 1990 ፡ 20/

በመቀጠልም፣ መምህራን የተቃና የትምህርት ሂደትን ለመምራት፣ ምንና እንዴት ማስተማር እንሚገባቸው ከዚህ በታች የቀረቡ ነጥቦችን በማንሳት ራሳቸውንና ሥራቸውን መገምገም ከቻሉ ተማሪዎቻቸውን በንቃት አሳትፈው ከተፈለገው ዓላማ ላይ ለማድረስ ይችላሉ። የመምህርነት ሥራ ድርሻቸውንም ተማሪውን ማዕከል በማድረግ ለመወጣት ብቁ ይሆናሉ በማለት ዋንኛ ነጥቦችን ያስቀምጣሉ።

- ክፍል ውስጥ ይገሮቸው የቀረብኩት የትምህርት ዓላማዎች መሠረታቸው ምንድነው?
- የትምህርቱን ይዘት ለመምረጥ በዋንኛነት ትኩረት የሰጠሁባቸው ጉዳዮች ምንድናቸው?
- ይገፀው በገባሁት የትምህርት ዕቅድና ክፍል ከገባሁ በኋላ በተደረገው ክንውን መካከል ያለው ዝምድና ምን ያህል ነው?
- የነደፍኳቸው ዓላማዎች፣ የመረጥኳቸው የትምህርት ይዘቶችና ያወጣሁት የትምህርት ዕቅድ በማስተማር ስልቴ ምን ያህል ተጣጥመው ቀርበዋል?
- በክፍል ውስጥ የተፈጠሩ ክስተቶች ምን ያህል ከዕቅዴ እንድወጣ አድርገውኛል?
- ተማሪዎች በትምህርቱ ሂደት ወቅት በእኔ ባህርይና ድርጊት ታውከው ነበር? ከሆነስ ምን አስከተለ?

- በክፍል ውስጥ እኔ ብቻ አብዛኛውን ጊዜ በገለፃ ወስጃለሁ ወይስ ተማሪዎች እንዲሳተፉበት አድርጌያለሁ?
- ለተማሪዎች ያደረግሁላቸው ገለፃና ማብራሪያ ምን ያህል ግልፅነትና ጠቀሜታ ነበራቸው?
- ከተማሪዎቼ ጋር ያለኝ ግንኙነት ምን ይመስላል? ከተወሰኑ ተማሪዎች ጋር ብቻ ነው ወይስ ከሁሉም መልካም ቅርርብ አደርጋለሁ?
- ተማሪዎች ለትምህርቱ እንዲነቃቁ ምን ያህል ጥረት አድርጊያለሁ?

እነዚህ ነጥቦች /ጥያቄዎች/ የትምህርቱን ሂደት ለማቃናትና የተማሪዎችን የመማር ፍላጐት ለማነሳሳት የትኛውም መምህር ራሱን እየጠየቀ በመገምገም ሊጠቀምባቸው የሚገቡ ስልቶች ናቸው። /ዝኒ ከማሁ 20/

በጥቅሉ ተማሪዎች ለቋንቋ መምህራቸውና ለሚያስተምርበት ስልት የሚኖራቸው አመለካከት በቋንቋው ትምህርት ላይ ተፅዕኖ የማድረስ ሀይል አለው። ስለዚህም መምህራን የተማሪዎችን የመማር ፍላጐት፤ የዕውቀት ደረጃ፤ የክፍል ውስጥ ምቹ ድባብ፤ በመጠበቅ ለማስተማር ጥረት ሊያደርጉ ያስፈልጋል። ለሚያስተምሩት ቋንቋ፤ ለትምህርቱና ለተማሪዎቻቸው እንዲሁም ለሙያቸው ፍቅር፤ በሚያስተምሩበት ቋንቋ በቂ ዕውቀትና ችሎታ ኖሯቸው ትምህርቱን በማያሰለች ስልት እያቀነባበሩ፤ የተለያዩ ስልቶችን እያፈራረቁ ካቀረቡ የተማሪዎቻቸውን አመለካከት ወደ አዎንታዊነት ለውጦ ውጤታቸውን ማሻሻል ይቻላቸዋል። ለተማሪዎቻቸውም ጥሩ የቋንቋ ሞዴል ሊሆኑ ይችላሉ።

2·2·2·3 <u>የመማሪያ መጻሕፍት</u>

የተማሪው የቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ አገሪቱ በምትከተለው የቋንቋ ፖሊሲና የሥርዓተ ትምህርት ዓላማ ላይ ተመሥርቶ ለተወሰነ የክፍል ደረጃ ይመጥናል ተብሎ በሚዘጋጅ ሲለበስ ውስጥ የቀረቡ የትምህርት ዓላማዎች፤ ይዘቶች፤ ክንውኖችና ግምገማዎች በተግባር የሚንፀባረቁበት ከተማሪው ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው የመጨረሻ ግብ መምቻ መሣሪያ ነው። የሁለቱ ውህደት፤ አንድነትና ተደጋጋፊነት ይል ቁንም ተተግባሪነት ለክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደት መቃናትና መከሸፍ መመዘኛ

ነው። ለአዘገጃጀቱ ማጠንጠኛ የሆነው የተማሪው ሁኔታና ማንነት ከግምት ውስጥ መግባት ደግሞ ዋንኛውና ወሳኝ ጉዳይ ነው።

መርሀ ትምህርትን ለመቅረም ሆነ የመማሪያ መፅሀፍትን ለማዘጋጀትና ለመምረጥ /የመምህሩና የማህበረሰቡ ሁኔታም ሳይዘነጋ/ የመረጃው ምንጭ በቅድሚያ ከተቀባዩ ከተማሪው መነሳት ይገባዋል። ተማሪው ለትምህርት የቀረበውን ቋንቋ ለምን ዓላማ ብሎ ይማረዋል? በቋንቋው ለወቅታዊ ጉዳይ ወይስ ለዘለቄታው ሊጠቀም ይሻል? ለትምህርቱ የቀረበበት ሁኔታ ምንድነው? ለቋንቋውና ለትምህርቱ ያለው ፍላጐትና አመለካከት ምን ይመስላል? ተማሪው የወጣበት ቤተሰብ፣ ኅብረተሰብ፣ የላከው መሥሪያ ቤት፣ የትምህርት ተቋሙና መንግሥት ከትምህርቱ መጨረሻ ምን እንዲሆንለት ይጠብቃል? ተማሪው ምን ዓይነት የባህርይና የቋንቋ ክኂል ዕድገት እንዲያመጣ ይሻል? … ወዘተ የሚሉ ጥያቄዎች ለመረጃ አሰሳ ምንጮችና በትምርቱ ሂደት ላይ ተፅዕኖ ሊያመጡ የሚችሉ ጉዳዮች በመሆናቸው በመጀመሪያ አሰሳ ሊደረግባቸው ይገባል። /ሮቢንሰን 1991 : 3፣ ታሮን እና ዩሊ 1989: 3-5፣ ሐርመር 1983 : 2 ፣ ዋይት 1988 : 89፣ ሪቻርድስ 1987 : 13፣ ሪቨርስ 1983 : 1፣ ሪቨርስ 1981 : 12-13/

ከነዚህ ጭብጠ መረጃዎች በመነሳት የተዘጋጁ የመማሪያ/ማስተማሪያ መሣሪያዎች ከታለመው ዓላማ ላይ ማድረስ ስለመቻላቸው ከዝግጅቱም በኋላ ቢሆን የሚነሱ ሌሎች ጥያቄዎች በርካታ ናቸው። የቀረቡትን የትምህርት ልምዶች ተማሪው በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ ተግባራዊ ሊያደርጋቸው ይችላልን? የታላሚውን ቋንቋ ክኂላት ለማዳበር ብቃት ያላቸው የትምህርት ይዘቶችና ልምምዶችን አካትተዋል? ለመምህሩም ሆነ ለተማሪው የመማርና የምርጫ ነፃነት የሚሰጡ ናቸው? የተማሪውን የመማር ፍላጐት አነቃቅተው ጥሩ ሊያስትፉ ይችላሉ? የተማሪውን የዕውቀት ደረጃና ችሎታ የሚጠብቁ ናቸው? በአዘገጃጀትና አቀራረባቸው ተማሪው ላለበት ሁኔታ፣ ለወጣበት ማህበረሰብና ለአካባቢው ትኩረት ሰጥተው በአማካይ ለሁሉም ተቀራራቢነት ባለው ደረጃ ሊጠቅሙ ይችላሉ? … ወዘተ የሚሉ ጥያቄዎች አሁንም የመመዘኛ መስፍርቶች ናቸው። እነዚህንና የመሳሰሉትን ሸልደን /1987/ የመማሪያ መጻህፍት ማሟላት የሚገባቸውን ነጥቦች ሲጠቃቅሷቸው ካኒንግስዎርዝም /1989 ፡ 6/ ትኩረት አርድርጐባቸዋል።

ከዚሀ አንፃር የ12ኛ ክፍል አማርኛ ሲለበስ /1984 ዓ.ም/ የተማሪው ፍላጐት፣ የወጣበት አካባቢና ለቋንቋው ትምሀርት የቀረበበት ሁኔታ ሳይጠናና ትኩረት ሳያገኝ የተዘጋጀ በመሆኑ በመጨረሻው ውጤት ላይ በተለይም በተማሪው የመማር ፍላጐትና አመለካከት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያደርስ እንደሚችል መገመት ይቻላል። ምክንያቱም ለመማሪያው መፅሐፍ መሠረቱ ሲለበሱ ነውና።

ዱቢንና አልሽቴይን /1986 ፡ 13-15/ ይህንኑ የፍላጐት አሰሳ መሠረታዊነት በማጠናከር፣ የግለሰቦችና የማህበረሰቦች ፍላጐት አሰሳ ሳይደረግ የሁለተኛ ቋንቋ ትምሀርት ፕሮግራምን መዘርጋት የማይታሰብ ነው ይላሉ። በዚሁ ጭብጠ ነገር ላይ ታሮንና ዮሊ/1989 ፡ 5/ ይስማሙበታል። በመቀጠልም የፕሮግራሙ አዘጋጆች ተማሪዎች ለትምሀርቱ ያላቸውን አመለካከት አዎንታዊ ለማድረግ የሚያግዙ ሳቢና አነቃቂ የመማሪያ መፃህፍትን ለማዘጋጀት ከፍተኛ ጥረት ማድረግ አለባቸው።

ሪቻርድስ /1983 :6/ የቋንቋ ትምሀርት ፕሮግራም ውጤታማ ለመሆን ከሚከተሉት ሁኔታዎች ላይ መነሳት ይገባዋል ይላሉ።

- ተማሪዎች ለቀረበው የቋንቋ ትምሀርት ያላቸው ፍላጐት ምን እንደሆነ በቅድሚያ ማወቅ
- እነዚህን ፍላጐቶች ሊያሟሉ የሚችሉ የትምሀርት ዓላማዎችን መንደፍ
- የሚመረጡት የትምሀርት ይዘቶችና ልምምዶች የተማሪውን ፍላጐት ሊያስተናግዱ የሚችሉ እንዲሆኑ ማድረግ

እነዚህን የመነሻ መሠረቶች ይዘው የተነሱ የማስተማሪያ መሣሪያዎች የተማሪውን ተግባቦታዊ ችሎታ የሚያፋጥኑ፣ ፍላጐቱን አነቃቅተው የመፍጠር ሀይሉን የሚያጐለብቱ፣ በርካታ ጠቃሚ ልምድና ይዘቶችን በውስጣቸው ያካተቱ፣ ተማሪው የራሱን የቋንቋ ክኂል የማሻሻል ዕድገቱን ራሱ ሊገመግም የሚያስችሉ … ወዘተ እንዲሆኑ ይጠበቃል። /ዝኒ ከማሁ 1983፡ 26/

የትምህርት ፕሮግራምን ለመንደፍ በፍላጐት እሰሳ ላይ የተመሠረተ መረጃን ማግኘት ዋናው ጠቀሜታ ተማሪዎች ከቋንቋው ትምህርት ምን እንሚጠብቁና አሁን ያላቸውን የችሎታ ደረጃ ለይቶ ለማወቅ ማስቻሉ ሲሆን በመጨረሻም ውጤቱን ገምግሞ ፕሮግራሙን አሻሽሎ ለመቅረፅ ያስችላል። ከተማሪው ሁኔታ አካባቢና ፍላጐት ጋር ስምሙ የሆኑ የማስተማሪያ ሥነዘዴዎችን ለመጠቀም፣ ተገቢ የትምህርት ዓላማን፣ ይዘትና ስልትን ለመምረጥም ያግዛል። / ዋይት 1988 : 91/

የመማሪያ መፃህፍት የተማሪዎችን የመማር ፍላጐትና ለትምህርቱ ያላቸውን አመለካከት ለማበረታታት በሚከተሉት ጭብጠ ነገሮች ሊመዘኑ እንደሚገባቸው እነዱቡን /1986:30/ ያመለክታሉ።

- የትምህርት መሣሪያዎች ሲዘጋጁ በሥራው ልምድ ባላቸው ሰዎች፣ የመምህራንና የተማሪዎች ቅንጅት ባለበት መንገድ መሆን ይገባዋል እንጂ ለገበያ ተብለው የቀረቡና ያለጥናት የተዘጋጁ ከሆኑ ከፍተኛ ድክመት ነው።
- በመፅሐፉ አማካይነት ለተማሪው እንዲቀርቡ የሚፈለጉ የትምህርት ልምዶች፣ የማስተማሪያ መርሆዎች፣ ይዘቶችና ቴክኒኮች ከሲለበሱ ጋር ጠንካራ ተጣምሮ ሊኖራቸው ይገባል። ይህ ካልሆነ ግን እንደገና እየተመዘኑ ሊታዩ ያስፈል ጋል።
- ተገቢ የመማሪያ መሣሪያዎች መምህሩ ለማስተማር ተማሪው ለመማር የሚያስችል ዕድል የሚሰጡ እንጂ ሁለቱንም የሚወስኑና ጫና የሚያደርጉ መሆን የለባቸውም።
- ለተለየ ዓላማ ካልሆነ በስተቀር የመማሪያ መፃህፍት ሁሉንም የቋንቋ ክኂላት አዋህደው እንዲይዙ ያስፈልጋል እንጂ ለአንዱ ክፍል ትኩረት ሰጥተው ሌላውን ሊዘነጉ አይገባም።
- የመማሪያ መሣሪያዎች በመምህሩም ሆነ በተማሪው ሊተገበሩ የሚችሉ የትምህርት ይዘቶችና ልምዶችን መያዝ ይጠበቅባቸዋል።

የመማሪያ መፅሀፍት በተማሪው ማንነት ላይ ተመሥርተው በጥንቃቄ ከተዘጋጁ የተማሪውን የመማር ፍላጐት አነቃቅተው ለቋንቋውና ለትምህርቱ የሚቀርፀውን አመለካከት አዎንታዊ አድርገው ለጥሩ ውጤት ያደርሳሉ።

ሙለር /1971 ፡ 296/ እንደሚሉት መምህሩ የሚያስተምርበት አሰልቺና ከክፍሉና ከተማሪዎች ሁኔታ አንፃር ሊለዋወጥ የሚይችል ግትር ስልት እንዲሁም ተማሪውን የማያነቃቁ፣ የማይስቡ፣ የመማር ዓላማና ፍላጐቱን መሠረት ያላደረጉ የማስተማሪያ መፅሀፍት ለአሉታዊ አመለካከት መነሾ ናቸው። ስለዚህ ይላሉ ጃኮቦቪትስን በመጥቀስ፣ የትምህርት አቅርቦት ጥራት የሚጠበቀው ትምህርቱን ከተማሪው ቅድመ ችሎታ፣ ዝንባሌና ፍላጐት ጋር አጣጥሞ ማቅረብ ሲቻል ነው። የመማሪያ መፃህፍትን ጉዳዩ ይመለከተናል በሚሉ ሰዎች ግምት ብቻ በማዘጋጀት ሳይሆን ተማሪው ይጠቅመኛል በሚለው ጭብጠ ነገር ላይ መሥርቶ በተገቢው የማስተማር ስልት ማቅረብ ሲቻል ነው አመለካከታቸውን ለውጠ ንቁ ተሳታፊ ማድረግ የሚቻለው ይላሉ።

ተማሪዎች ለቋንቋው ትምህርት ያላቸው አመለካከት ተለውጦ የበለጠ የክፍል ውስጥ እንቅስቃሴ እንዲያሳዩ ለማገዝ፣ መምህሩ የተማሪዎችን ሁኔታ በመገምገም ከቀረበው ማስተማሪያ መፅሐፍ በተጨማሪም ሌሎች አነቃቂ የትምህርት ልምዶችን ከውጭ በአጋዥነት ማቅረብ ከቻለ ተማሪዎች በመፅሐፉ ላይ የሚኖራቸው አሉታዊ አመለካከት ሊቀንስ ይችላል። አሉታዊ አመለካከት ካላቸው ግን ሊማሩ አይፈልጉም ቢማሩም ሊሠሩ የሚችሉትን ያህል ለመሥራት አይጣጣሩም። /እንደርውድ 1987 ፡ 12/

ቻስቴይን /1983 ፡ 139/ የቋንቋ ማስተማሪያ መጣሪያዎች የሰዋሰውና የቃላትን ክምር ተሸክመው በተማሪው ላይ የሚጭኑ ሳይሆኑ ለተግባቦታዊ ችሎታ የሚረዱ መረጃዎችና ክንውኖችን የሚያቀብሉ እንዲሆኑ ይመሬጣል። የሁለተኛ ቋንቋ መምህራንም በነዚህ የማስተማሪያ መፃህፍት የቀረቡትን የትምህርት ልምምዶች አስደሳችና አነቃቂ በሆነ ዘዴ እያቀናበሩ ማቅረብ ከቻሉ የተማሪውን የመማር ትኩረት ስበው የቋንቋ ክኂላትን ቀልጥፈው ማስጨበጥ ይችላሉ ይላሉ።

በመቀጠልም ለሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት የሚቀርቡ የመማሪያ መፃህፍት ሊያካትቱ የሚገባቸውን ነጥቦች የጆንሰን /1985/ መርሆዎች በመጥቀስ ሲያስፍሩ፤ መፃህፍቱ ለተመደቡበት የክፍል ደረጃ መጣኝነት ያላቸው፤ ከትምህርቱ ዓላማ ጋር በውል የተቀናጁ፤ ማህበራዊ ተራክቦን ለማጠናከር የሚረዱ፤ የቋንቋ ክኂላትን በአንድ ላይ አዋህደው የያዙ፤ ተማሪው ቀደም ብሎ ያካበተውን ዕውቀት ሊጠቀምበት የሚያስችሉ፤ የቋንቋ ችሎታን አለማምደው እንዲተገበር የሚያደርጉ፤ የተለያዩ የክፍል ውስጥ እንቅስቃሴዎችን የሚያሠሩ፤ የተማሪውን የመማር ፍላጐት የሚያነሳሱና ይሁነኝ ብሎ እንዲማር የሚያነቃቁ … ወዘተ ሊሆኑ ይገባቸዋል በማለት ያመለክታሉ። /ዝኒ ከማሁ 141/

ሀቸንስንና ዎተርስ /1987፡ 108/ ደግሞ የማስተማሪያ መፅሀፍትን ጠቀሜታና ሲዘጋጁም ሊደረግባቸው የሚገባውን ጥንቃቄ ዘርዘር አድርገው ሲያስቀምጡ፤ ጥሩ የትምህርት መሣሪያዎች የማያስተምሩ ግን ተማሪውን ለመማር የሚያነሳሱ፤ አስደሳች ይዘቶችን ያካተቱ፤ እያዝናኑ የተማሪውን አእምሮ የሚያሰሩ፤ ተማሪው በቋንቋው ባለው ችሎታ እንዲጠቀምበት ዕድል የሚሰጡ እንጂ የግድ በመመሪያ የማይጫኑ፤ ግልፅ ሆነው ተማሪውንና መምህሩን በቋንቋው የተለያዩ ክፍሎች ላይ የሚያሳትፉ፤ የቋንቋና የመማር ባህርያትና ሂደቶችን ያቀፉ፤ ለመምህሩም አዲስ የማስተማር ስልትን የሚጠቁሙ፤ ትክክለኛና ሞዴል የሚሆን የቋንቋውን አጠቃቀም አስረግጠው ሊያለማምዱ የሚችሉ … ወዘተ ሊሆኑ ይገባል ሲሉ ያስምሩበታል።

በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት ተማሪው በቋንቋው ትምህርት ላይ ለሚቀርፀው አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ አመለካከት ምሥረታ የመማሪያ መፃህፍት ከተጠቃሽ ተላውጠዎች ውስጥ አንዱ በመሆናቸው በዝግጅትና አቀራረባቸው ከፍተኛ ጥንቃቄ እንዲደረግባቸው ያስፈልጋል። በተማሪው ፍላጐትና የመማር ዓላማ ላይ ተመሥርተው የቀረቡ መፃህፍት ለአዎንታዊ አመለካከት ምሥረታ የሚያግዙትን ያህል ሳቢነትና ተገቢነት የጐደላቸውና የተማሪው ሁኔታ ከግምት ሳይገባ የተዘጋጁት ደግሞ በአንፃሩ በተማሪው ላይ አሉታዊ አመለካከት እንዲዳብር ምክንያት በመሆናቸው በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ በተለያዩ የቋንቋው ክፍሎች ላይ ንቁ ልምምድ የማድረግ ፍላጐቱን ያቀጭጫሉ። ተከታታይና ተደጋጋሚ ልምምድ በሌለበት የቋንቋ ትምህርት ሂደት ደግሞ

የቋንቋ ክኂል ዕድገት ሊመጣ ስለማይችል በመጨረሻ በተማሪው የፈተና ውጤት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያስከትላሉ።

ከፍ ብሎ ጋርድነር እንደጠቆሙት እንዲያውም በመጀመሪያ ተማሪው ለቋንቋው ቀና አመለካከት ቢኖረው እንኳ በማስተማሪያነት የቀረቡት መፃህፍትና የመምህሩ የማስተማር ስልት ዘመናዊነትና አነሳሽነት በሌለው መንገድ የቀረቡ ከሆነ የተማሪውን አመለካከትና ፍላጐት ከመጉዳታቸውም በላይ ውጤቱ እንዲያሽቆለቁል ምክንያት ይሆናሉ። በወጤቱ ዝቅተኛና ደካማ የሆነ ተማሪ ደግሞ ለትምህርቱ፣ ለመምህሩና ለቋንቋውም ጥላቻ ከማሳደሩም በላይ ለመሻሻል የሚያደርውም ጥረት የግብር ይውጣ ዓይነት ስለሚሆን የግድ ሊማር እንደቀረበ አድርጐ እንደሚቆጥረው እሙን ለመሆኑ ቀደም ሲል የተጠቀሱ ጽሑፎች ይመሰክራሉ።

## 2·3 የአመለካከትና የውጤት ዝምድና

ከፍ ብሎ እንደተመለከተው አመለካከት አንድ ሰው ከሚገጥመው ወይም በውስጡ ከሚያልፍበት ነገር ጋር በሚያደርገው ተራክቦ ስለጉዳዩ የሚኖረው ግምት፣ ቅርበትና ርቀት፣ ውዴታና ጥላቻ ነው፡

በቋንቋ ትምህርት ሂደትም ተማሪው የሚገጥመውና በውስጡ የሚያልፍበት ሁነት፣ የሁለተኛ ቋንቋው ትምህርት፣ የቋንቋው መምህር፣ የማስተማሪያ መሣሪያዎች፣ አጠቃላይ የትምህርቱ ሥርዓትና ሌሎች ማህበራዊ የሆኑ ጉዳዮች ናቸው። በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪው ከነዚህ ጉዳዮች ጋር በሚያደርገው መስተጋብርና የመማር እንቅስቃሴ የሚመነጭ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ አመለካከትን ያዳብራል። ያዳበረው አመለካከት ደግሞ ተማሪው በትምህርቱ ሂደት ከሚያደርገው የመማር ጥረትና ከሚደርስበት ውጤት ጋር ይገናኛል። /ታደለ 1990 ፡ 141/

የአመለካከትና የውጤትን ተዛምዶ አስመልክቶ ሙለር /1971፡ 290/ የሚከተለውን ሐሳብ ሰንዝረዋል።

> ተማሪዎች ለሚማሩት ቋንቋ፣ ትምህርቱ ለሚሰጥበት ሁኔታ፣ ለትምህርት ለቀረበው ቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰቦችና ለባህላቸው፣ ለቋንቋው መምህርና ለመማሪያ መፅሀፍት ያላቸው አመለካከት ከውጤታቸው ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አለው። በዚሁ ጉዳይ ላይ የተሠሩ ድርሳናትም የሚያመለክቱት ይህንኑ ነው። አሉታዊ አመለካከት ያላቸው ተማሪዎች ከአማካይ የተማሪዎች ውጤት /GPA/ ከዝቅተኛው ጋር ጥምረት ሲያሳይ አዎንታዊነት ያላቸው ደግሞ ከከፍተኛ ውጤት ጋር ተዛምዷል። ይላሉ።

በዚሁ መሠረት የተለያዩ ምሁራን በተለያዩ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችና ቋንቋዎች ላይ የአመለካከትንና የውጤትን ተዛምዶ አጥንተው "አዎንታዊ" አመለካከት ያላቸው በትምህርቱ ሂደት ንቁ ተሳታፊ፣ በፍላጐት ተነሳስተው ለመማር የሚጣጣሩ፣ በቋንቋ ክኂሎት ዕድገትም ፈጣን የሆኑ፣ በመጨረሻም ከፍተኛ ውጤት ማምጣት እንደቻሉ ሲያረጋግጡ በአንፃሩ ደግሞ አሉታዊ አመለካከት ያላቸው፣ አዝጋሚ፣ ተስፋ ቆርጠው ትምህርታቸውን የሚያቋርጡ፣ በቋንቋ ክኂል ዕድገትና መሻሻል የማያሳዩ፣ በውጤታቸውም ዝቅተኛ ከመሆናቸውም በላይ ትምህርትንና ትምህርት ቤትን እንደጭንቀት መብቀያ ማዕከል የሚመለከቱ እንደሆኑ በርካታ ምሁራን በአንድ ምታ ተቀራራቢ ስምምነት ያረጋግጣሉ። /ጋርድነር 1985፣ ኮርቴን 1979፣ 282፣ እና ዱቢን 1986 ፡ 14፣ አኖዳ፣ 1976 ፡ 152፣ ዴቪድና አንድሪው 1976 ፡ 92፣ ሹይና ፋሶልድ 1973 ፡ 36፣ ማክላጉሊን 1991፡ 126/

በምሁራኑ ጥናት መሠረት አዎንታዊ አመለካከት ከከፍተኛ ውጤት፣ አሉታዊ አመለካከት ከዝቅተኛ ውጤትና ከደካማ የትምህርት ተሳትፎ ጋር ተዛምዷል። ከነዚህ ሥራዎች ውስጥ ለአብነት ያህል፡

ዮሊ፣ ቱዳና ጁሪይ /1985 ፡ 473/ የተማሪዎችን አመለካከት ከራስ መተማመን /confidence/ ጋር አጣምረው ባጠኑት ጥናት ተማሪዎች ለሚማሩት ቋንቋ መልካም አመለካከት ካላቸው በትምህርቱ ንቁ ተሳታፊ ከመሆናቸውም በላይ በራሳቸው ላይ የተደላደለ መተማመን ሊያሳድሩ ይችላሉ። በራሳቸው የሚተማመኑ ተማሪዎች ደግሞ የቋንቋውንም ትምህርት በፍላጐትና ባላሰለሰ ጥረት ስለሚማሩ ውጤታቸው የተሻለ ሆኗል ከሚል ድምዳሜ ላይ ደርሰዋል።

አኖዳ /1976 ፡ 152/ ጃፓን አሜሪካዊያን በሆኑ የሳንሲ ጉሣዎች ላይ ባደረጉት ጥናት ተማሪዎች ያላቸው የስብዕና ባህርያትና አመለካከታቸው ከቋንቋ ትምህርት ፍላጐትና ውጤት ጋር ጠንካራ ግንኙነት እንዳለው ደርሰውበታል። ጭብጠ ሐሳቡን ሰፋ በማድረግ፣ ተማሪዎች በትምህርት ሂደት በመምህራን፣ በጓደኞቻቸው፣ በትምህርት ሐላፊዎች … ወዘተ ላይ ፍራቻና ጥላቻ ካሳደሩ ወይም ጭንቀትና በራስ አለመተማመን ስሜትን እንዲያዳብሩ የሚገፋፉና ሜና የሚደረግባቸው ከሆነ የተበላሸ የስብዕና መሠረተ ባህርያት ከማዳበራቸው በተጨማሪ አመለካከታቸው አሉታዊ ይሆናል። በተበላሸ ስብዕና፣ በራስ አለመተማመን ስሜት፣ በጭንቀትና ውጥረት ድባብና በአሉታዊ አመለካከት ውስጥ በሚሰጥ ትምህርት ከተማሪዎች የሚጠበቀው ደካማ ውጤት ነው ይላሉ። ጥናታቸው መሠረት ባደረጋቸው የሳንሲ ጉሣዎች ጥሩ ውጤት ያስመዘገቡት የተደላደለ ስብዕናና ለቋንቋው ትምህርት መልካም አመለካከት ያላቸው እንደሆኑ አረጋግጠዋል።

በካናዳ ውስጥ ተማሪዎች ለፈረንሳይኛ ቋንቋና ለፈረንሳይ ካናዳዊያን ማህበረሰብ ያላቸውን አመለካከት ከመነቃቃት /attitude/motivation/ ጋር በማያያዝ ጋርድነርና ላምበርት መነሻ የሚሆኑ ሰፊ ጥናቶችን አካሂደዋል። ሌሎች አጥኚዎችም በነዚሁ ነጥቦች ላይ በተለያዩ ቋንቋዎችና ተማሪዎች ላይ ጥናት አድርገው ተመሳሳይ ውጤት ያገኙ በርካታ እንደሆኑ ታደለ /1990 ፡ 126/ ይጠቅሷቸዋል። /ጋርድነር፣ ስሚዝ፣ ክሊሞንትና ግሊስካን 1976፣ ስሚዝ፣ ስቲኔትና ፌኒስታ 1972፣ ክሊሞንት፣ ጋርድነርና ስሚዝ 1977፣ 1980፣ ጋርድነረና ሌሎች 1985/። ታደለ /1990 ፡ 139/ በመቀጠል የነዚህ ሰዎች የጥናት ውጤት ተማሪዎች ለቋንቋው፣ ለትምህርቱና ለተናጋሪው ማህበረሰብ ያላቸው አመለካከትና መነቃቃት ለቋንቋው ትምህርት ሂደት መቀልጠፍ ወይም አዝጋሚ መሆን ቁልፍ ጉዳዮች እንደሆኑ አረጋግጠዋል ይላሉ።

በነዚህ ምሁራን ሐሳብ ላይ ተቃውሞ ያላቸው ማክናማራ፣ ተማሪዎች ለቋንቋውና ለቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ ያላቸው አመለካከት በትምህርት ሂደት ላይ ይህንን ያህል ፋይዳ ያለው ሚና አይጫወትም። ይልቁኑ ወሳኙን ድርሻ የሚወስደው ተማሪዎች ለቋንቋው ትምህርት ያላቸው "ፍላጐት" ነው በማለት የመከራከሪያ ነጥብ አንስተዋል። ማክናማራ ሐሳቡን ዘርዘር በማድረግ፣ አንድ ህፃን ወደማያውቀው ቦታ ቢወሰድ /ከቶሮንቶ ወደ

በርሊን/ ከሚገናኛቸው ልጆች ጋር መግባባት አይችልም። ይሁን እንጂ ብቸኛ ከመሆን ለማምለጥ እንዲችልና ባልንጀራም እንዲያፈራ ለቋንቋውና ለቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ ያለው አመለካከት ምንም ይሁን ምን ቋንቋውን /ጀርመንኛ/ በፍላጐት ተነሳስቶ በጥሩ ሁኔታ ይማረዋል/ይለምደዋል። ከዚህ ሌላ አይሪሾች ለእንግሊዞችና ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ያላቸው አመለካከት አሉታዊ ነው። ነገር ግን እንግሊዝኛ አይሪሽኛን እየተካው አይሪሾችም በፍላጐት እየተማሩት በመሆኑ አመለካከት በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያለው ተፅዕኖ ከግምት የሚገባ አይደለም በማለት ማስረጃ ያቀርባሉ። /1973 ፡ 38/

ይህንን ሐሳብ ጋርድነርና ተባባሪዎቹ አይቀበሉትም። ጋርድነር /1985፡ 4/፣ በርግጥ ፍላጐት በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት ላይ ተፅዕኖ ማድረጉ አሌ አይባልም። ነገር ግን ለቋንቋውና ለትምህርቱ ጥሩ አመለካከትና ግምት ከሌለ ፍላጐት ከባዶ አይመነጭም። እንግሊዝኛ አይሪሽኛን መተካቱም በአይሪሾች ፍላጐት ወይም በሁኔታዎች አስገዳጅነት ለመሆኑ መሠረት ያለው ጭብጥ አልቀረበም። ስለዚህ አመለካከት በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት ላይ ያለው ተፅዕኖ እንደ አንድ ወሳኝ ተለውጦ መታየት አለበት የሚል አቋማቸውን ያሰምሩበታል።

ስለዘህም አመለካከት ከተማሪዎች የትምህርት እንቅስቃሴና ውጤት ጋር ተዛምዶ ያለው ትምህርታዊና ማህበራዊ ጉዳይ ነው የሚለውን በብዙዎች ጥናት ውጤት የተረጋገጠውን ጭብጠ ነገር ልንቀበለው ያሻል።

## ምዕራፍ ሦስት

## የአጠናን ስልት

### 3·1 የተማሪዎች፣ የመምህራንና የትምህርት ቤቶች አመራረጥ

### 3·1·1 የትምህርት ቤቶች አመራረጥ

በሀዲያ ዞን አምስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ። እነርሱም፡

1· ዋቸሞ አጠቃላይ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
2· የካቲት 25/67 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
3· ሞርሲጦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
4· ጊምቢቹ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
5· ሲቄ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ናቸው።

ከነዚህ ውስጥ ሲቄ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከማዕከላዊ የዞኑ ክልል ተገንጥሎ ለብቻው የሚገኝ ሲሆን ከሌሎቹ ትምህርት ቤቶች በጣም የራቀ ነው። በተጨማሪም በነበረው የጊዜና የበጀት እጥረት ምክንያት ይህንን ትምህርት ቤት ማካተት አልተመቸም። ስለዚህ የሲቄ ትምህርት ቤት ሲቀር መረጃውን በቅርብ ማግኘት የሚቻልባቸው የተቀሩት አራቱ ተወስደዋል። እነዚህ ትምህርት ቤቶች በዞኑ ከሚገኙ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ 80% የሚይዙ በመሆናቸው ከአራቱ ለሥራው ብቃት ያለው መረጃ ይገኛል ተብሎ ይታመናል።

### 3·1·2 የተማሪዎች ናሙና አወሳሰድ

ጥናቱ የተመሠረተባቸው ትምህርት ቤቶች በአደረጃጀትም ሆነ በስፋት በተለያየ ደረጃ ላይ የሚገኙ ናቸው። ተቀብለው የሚያስተናግዱቸው የተማሪ ቁጥርም እንዲሁ የተለያየ ነው። የመጀመሪያው ሥራ ተጠኝ ተማሪዎችን መለየቱ በመሆኑ አሥራ ሁለተኛ ክፍል ከሚማሩ አጠቃላይ ተማሪዎች ውስጥ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሀዲይኛ የሆኑት ብቻ ከየትምህርት ቤቶች ሆን ተብሎ በሙሉ ተለቅመዋል። ከዚህ በመቀጠል በየትምህርት ቤቶቹ ከሚገኙ ሀዲይኛ ተናጋሪ ተማሪዎች ቁጥር አንፃር በብድግ ብድግ ናሙና አወሳሰድ ዘዴ /randum sampling/ ተመርጠዋል። በዚህ መሠረት በየትምህርት ቤቶቹ 12ኛ ክፍል

የሚማሩ ተማሪዎችን ብዛት በማገናዘብ ከዋቸሞ 40፤ ከየካቲት 30፤ ከሞርሲጦ 25፤ ከገምቢቹ 25 በድምሩ 120 /አንድ መቶ ሀያ/ ተማሪዎች በጥናቱ ታቅፈዋል። በየትምህርት ቤቶቹ የሚማሩ ሀዲይኛ ቋንቋ ተናጋሪ ተማሪዎች አጠቃላይ ብዛት 281 ሲሆን በሥራው የታቀፉት 120 ተማሪዎች የአጠቃላዩን ቁጥር 41·7% የሚይዙ በመሆናቸው አማካይ ውክልና ይኖራቸዋል ተብሎ ይገመታል። /ሂንክል 1988፡170/

### 3·1·3 የመምህራን ናሙና አወሳሰድ

ከላይ እንደተጠቀሰው እንደየትምህርት ቤቶቹ ስፋትና እንደተማሪዎቹ ብዛት ሁሉ በየትምህርት ቤቱ የሚገኙ የአሥራ ሁለተኛ ክፍል የአማርኛ መምህራን ቁጥርም እንደዚሁ ይለያያል። የመምህራኑ ቁጥር በጣም አነስተኛ በመሆኑ በአራቱም ትምህርት ቤቶች አሥራ ሁለተኛ ክፍል አማርኛ የሚያስተምሩ መምህራን በሙሉ በጥናቱ ተካትተዋል። በዚህ መሠረት ከዋቸሞ ሁለት፣ ከየካቲት ሁለት፣ ከሞርሲጦ አንድ፣ ከጊምቢቹ አንድ በድምሩ ስድስት መምህራን ተወስደዋል።

## 3·2 የመረጃ መሠብሰቢያ መሣሪያዎች

### 3·2·1 መጠይቆች

#### 3·2·1·1 የተማሪዎች መጠይቅ

ይህ ጥናት ያነሳውን ጥያቄ መልሶ የታቀደውን ዓላማ ይመታ ዘንድ ከሚጠቀምባቸው የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች አንዱ መጠይቅ ነው። ስለዚህም ለመምህራንና ለተማሪዎች በሊከርት አፃፃፍ ስልት የተዘጋጁ መጠይቆች ቀርበዋል። መጠይቆቹ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸውን አመለካከት ሊለኩ ስለመቻላቸው ከመበተናቸው በፊት በሁለት ባለሙያዎችና በጥናቱ አማካሪ ተገምግመዋል። የመጠይቆቹ አዘገጃጀት ቀደም ብሎ ለተማሪዎች ቀርቦ በነበረው ክፍት መጠይቅ ምላሽ ላይ የተመሠረተ ሲሆን አመለካከትን መለካት እንዲችሉ ያስተማማኝነት ደረጃቸውን እንዲጠብቁ ጥረት ተደርጓል። ይህንን የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያ አስተማማኝነት ለመለካት በዋናው ሥራ ውስጥ ባልገቡ ሀምሳ ሁለት ተማሪዎች ላይ በተደረገው ቅድመ ጥናት /pilot study/ 0·8135 የደረሰ የአስተማማኝነት /reliability/ ውጤት አስገኝቷል።

ለተማሪዎች የቀረበው መጠይቅ በአራት ክፍል ተከፍሎ አርባ ስምንት ጥያቄዎች የያዘ ነው። የመጠይቆቹ ትኩረት ተማሪው ለመምህሩና ለማስተማሪያው ሥነዘዴ፣ ለመማሪያ መፅሐፉ፣ ለቋንቋውና ለትምህርቱ ያለውን አመለካከት የሚጠይቁ ሲሆን ሌላው የተማሪው ወላጆች፣ ባልንጀሮችና ማህበረሰቡ በተማሪው አመለካከት ላይ የሚያሳድሩትን ተፅዕኖ ለማወቅ የሚያስችሉ እንዲሆኑ ተደርገው በየተለውጦው ተከፍለዋል። በቅንብራቸውም የጥያቄዎቹ አቀራረብ ተከታታይ ሆኖ ወይም አንዱ ክፍል በዝቶ ሌላው አንሶ በሚሰጠው ምላሽ ላይ ተፅዕኖ እንዳያደርስ ለያንዳንዱ ክፍል አሥራ ሁለት ጥያቄዎች የቀረቡ ሲሆን በውስጣቸው አዎንታዊና አሉታዊ መንፈስ ያላቸው ጥያቄዎች ሥራዩ ተብሎ ተዘበሬርቀው ተቀምጠዋል። ለተማሪዎች የቀረቡት ጥያቄዎች በሙሉ ዝግ ናቸው።

3·2·1·2 <u>የመምህራን መጠይቅ</u>

ለመምህራን የቀረበው መጠይቅ እንደተማሪዎቹ ሁሉ የሊከርት ስልትን የተከተለ ነው። መጠይቆቹ በሦስት ቡድኖች ተከፍለው ትኩረታቸው መምህራን ስለተማሪዎቻቸው፣ ስለመማሪያ መፅሐፉና ስለሙያቸው ያላቸውን አመለካከት የሚጠይቁ ናቸው። እያንዳንዱ የመጠይቅ ቡድን በውስጡ አሥራ ሁለት ጥያቄዎችን ሲይዝ በድምሩ ሰላሳ ስድስት ዝግ ጥያቄዎች ቀርበው ተሞልተዋል። ከነዚህ በተጨማሪ በዝግ ጥያቄዎች ላይ የተመሠረቱ ሦስት ክፍት መጠይቆች ቀርበው መምህራን ሰፋ ያለ አስተያየታቸውን ሰጥተውባቸዋል። የመጠይቆቹ ውጫዊ ተገቢነት /face favlidty/ እንደተማሪዎች መጠይቅ ሁሉ በሁለቱ ባለሙያዎችና በጥናቱ አማካሪ ከመሞላታቸው በፊት ተገምግመው አስፈላጊ በሆኑ ቦታዎችእርምት ተደርጎባቸዋል።

ለመምህራንና ለተማሪዎች ለቀረቡት ዝግ ጥያቄዎች ለእያንዳንዱ አምስት አማራጭ መልሶች የተሰጡ ሲሆን ሁለቱ አዎንታዊ፣ ሁለቱ አሉታዊ፣ አንዱ ገለልተኛ /neutral/ የሆኑ ናቸው። ለእያንዳንዱ ጥያቄ ለተሰጠው ምላሽ የሚመዘገበው ውጤት እንደሚከተለው ይሆናል።

የቀረበው የጥያቄ መንፈስ አዎንታዊ ከሆነ ውጤቱ፣

| | | |
|---|---|---|
| በጣም እስማማለሁ | - | 5 |
| እስማማለሁ | - | 4 |
| ለመወሰን እቸገራለሁ | - | 3 |
| አልስማማም | - | 2 |
| ፍፁም አልስማማም | - | 1 |

በአንፃሩ ጥያቄው አሉታዊ መንፈስ ካለው ውጤቱ የአዎንታዊው ዋጋ አሰጣጥ ግልባጭ ይሆናል።

| | | |
|---|---|---|
| በጣም እስማማለሁ | - | 1 |
| እስማማለሁ | - | 2 |
| ለመወሰን እቸገራለሁ | - | 3 |
| አልስማማም | - | 4 |
| ፍፁም አልስማማም | - | 5 |

የማጠቃለያ ውጤቱም አንድ ተማሪ ወይም መምህር ለሁሉም ዝግ ጥያቄዎች የሰጠው/ችው ምላሽ አማካይ ከሦስት በላይ ከሆነ አዎንታዊ፣ ከሦስት በታች እያነሰ ሲሄድ አሉታዊ እንደሚሆን ይሰላል። ከሁለቱ መሀል ላይ ሦስት ከሆነ ግን ተማሪው ያለው አመለካከት ገለልተኛ ይሆናል። በመጨረሻ የተማሪው አመለካከትና በሁለቱ ፈተናዎች ያገኘው/ችው ውጤት ተቆራኝቶ በፒየርሰን የተዛምዶ ቀመር ስልት /pearson's product moment correlation/ ተሰልቶ በሁለቱ መካከል ያለው ጥምረት ይቀርባል። የጥምረቱን ውጤት የበለጠ ለማጠናከር ይረዳ ዘንድ የተማሪውን የአንድ ጊዜ የፈተና ውጤት ብቻ ወስዶ ከማስላት ይልቅ በሁለት ፈተናዎች መመዘኑ የተሻለ ስለሚሆን የአንደኛ መንፈቀ ዓመትና የመሰናዶ /model/ ፈተና ውጤት ድምር አማካይ ተወስዷል።

3·2·2 <u>የክፍል ምልከታ</u>

በአራቱም ትምህርት ቤቶች ስለትምርት ቤቱ አደረጃጀት፣ ስለተማሪዎች የመማር እንቅስቃሴና አጠቃላይ ሁኔታ፣ ስለመምህሩ የማስተማር ስልትና ብቃት፣ ስለትምህርትና

የክፍል አያያዝ … ወዘተ መረጃ ለማግኘት ይቻል ዘንድ በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ሦስት ጊዜ በድምሩ አሥራ ሁለት ጊዜ የክፍል ምልከታ ተደርጓል። የምልከታው ሂደት ዱዋ ሪቻርድስ /1990 ፡ 44-45 / ዝርዝር ምልከታ /qualitative observation/ በሚሉት ስልት የተከናወነ ሲሆን በትንተናው ወቅት ግን በምልከታው ከተገኙ ቅኝቶች ውስጥ ከጥናቱ ጋር በጥብቅ የሚገናኙትን ብቻ ጠቅለል ባለ መልክ በመረጃ ደጋፊነት እንዲቀርቡ ተደርጓል። ከቅኝቶቹ ውጤት በተለይም በመምህራን የክፍልና የትምህርት አያያዝ እንዲሁም በተማሪዎች የክፍል ወስጥ እንቅስቃሴ ላይ ትኩረት ተደርጐባቸዋል።

የምልከታው ውጤት ከተማሪዎች ሁኔታና የአመለካከት ምሥረታ ጋር ተቀናጅቶ በመረጃ ደጋፊነት ይቀርባል። ከመምህራን የአመለካከት ምላሽ ጋርም እየተጣቀሰ ጭብጠ ነገሮችን ለማስረገጥ ይገባል።

# ምዕራፍ አራት

# የመረጃዎች ውጤትና ትንተና

## 4·1 ከተማሪዎች መጠይቅ የተገኘ የአመለካከት ውጤት ትንተና

የዚህ ጥናት ማዕከላዊ ዓላማ የተማሪዎች አመለካከት ከፈተና ውጤታቸው ጋር ያለውን ጥምረት ማረጋገጥ ነው። ከታለመው ውጤት ላይ ለመድረስ አጥኚው ከተጠቀመባቸው የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች አንዱ ተማሪዎችን የፅሑፍ መጠይቅ ማስሞላት ነበር።

በዚሁ መሠረት በምዕራፍ ሦስት እንደተጠቀሰው አርባ ስምንት ጥያቄዎችን ያዘለ መጠይቅ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሀዲይኛ የሆነ 120 ተማሪዎች እንዲሞሉት ተደርጓል። መጠይቁ ሳይበላሽና ሳይባክን ምላሹን ለማግኘት እንዲቻል እንዲሁም ስለአሞላሉና ግልፅ ላልሆኑ ሐሳቦች ማብራሪያ ለመስጠት እንዲያመች ከየትምህርት ቤቱ የተመረጡት ተማሪዎች በሙሉ አጥኚው በአካል በተገኘበት መጠይቁን ሞልተዋል።

ጥናቱ አመለካከትን ከውጤት ጋር አነፃፅሮ የሚመረምር በመሆኑ የተመረጡት ተማሪዎች በሚሞሉት መጠይቅ ላይ አጥኚው ብቻ የሚያውቀው መለያ /ኮድ/ ተደርጎ ተሞልቷል። የመለያው ምልክት የአንዱን ተማሪ አመለካከት ከሌላው ተማሪ የፈተና ውጤት ጋር እንዳይቀላቀል ለማድረግና መጠይቁን የሞሉ ተማሪዎችን የፈተና ውጤት ብቻ ከየትምህርት ቤቱ በትክክል ለማግኘት እንዲቻል የተደረገ ስልት ነው። በዚሁ መሠረት ከየትምህርት ቤቶቹ ጥናቱ የሚመለከታቸው ተማሪዎች ውጤት በአማርኛው መምህር ፊርማና በትምህርት ቤቱ ማህተም ተረጋግጦ ከማርክ ሊስት ተለቅሟል።

መጠይቁ ከተሞላ በኋላ እያንዳንዱ ተማሪ ያስመዘገበውን የአመለካከት ውጤት ታሊ በማድረግ በጥንቃቄ ተመዝግቧል። ውጤቱ በትምህርት ቤቶች፣ በተላውጦዎች፣ በፆታና በመኖሪያ ቦታ ተለይቶ በአማካይና በመቶኛ ተሰልቷል። ስሌቱ የበለጠ ግንዛቤና ማረጋገጫ እንዲያስገኝ አስፈላጊ በሆኑ የሠንጠረዥ መረጃዎች ተደግፎ ቀርቧል። የመጠይቁ አስተማማኝነትና የአመለካከትና ውጤት ዝምድና ማረጋገጫ ስታቲስቲካዊ

ስሌት ተደርጐበታል። የተገኘው የተማሪዎች አመለካከት ውጤት ከመምህራን መጠይቅ ውጤትና ከክፍል ምልከታ ማስታወሻ ጋር እየተገናዘበ ይተነተናል።

4·1·1 <u>በአራቱ ተላውጦዎች/variables/ የተገኘ የተማሪዎች አመለካከት</u>

በክፍል 3·2 እንደተመለከተው ለተማሪዎች የተበተነው መጠይቅ ሁለት ክፍሎች አሉት። ክፍል አንድ የተማሪውን ፆታ፤ ዕድሜ፤ መኖሪያ፤ ብሔረሰብና የአፍ መፍቻ ቋንቋን የሚጠይቅ ነው። በዚህ ክፍል መጠይቁን ከሞሉ ተማሪዎች ውስጥ 39 ሴቶች፤ 83 ወንዶች ናቸው። ዕድሜአቸውን በተመለከተ ከ16-19 ባለው ውስጥ ሲሆን በመኖሪያ ቦታ፤ 39 ከተማ 81 የገጠር ነዋሪ ሆነው ተገኝተዋል። በብሔረሰብና የአፍ መፍቻ ቋንቋ ደግሞ ሁሉም ሀዲዮች፤ሀዲይኛ ተናጋሪ ናቸው።

ክፍል ሁለት ደግሞ 48 የአመለካከት መለያ ዝግ ጥያቄዎችን ያቀፈና በአራት ቡድን የተመደበ ነው። እያንዳንዱ ቡድን አዎንታዊና አሉታዊ መንፈስ የያዙና ተሰባጥረው የተቀመጡ አሥራ ሁለት ጥያቄዎች ቀርበውበታል። የቡድን አከፋፈሉ በተላውጦ ሲሆን በሚከተሉት የጥያቄ ተራ ቁጥሮች ይለያል።

ከ1-12 ተራ ቁጥር ያሉት ተማሪው ለቋንቋውና ለትምህርቱ
ከ13-24 " " " " ለመማሪያው መፅሐፍ
ከ25-36 " " " " ለመምህሩ
ከ37-48 " " " ወላጆች ፤ ባልንጀሮችና ማህበረሰቡ
ስለሚያደርስበት ተፅዕኖ የተማሪውን አመለካከት የሚጠይቁ ናቸው።

በነዚህ ተላውጦዎች ተጠኝ ተማሪዎች ያስመዘገቡት ውጤት ከእያንዳንዱ ጥያቄ አኳያ በአማካይና በመቶኛ ተሰልቶ እንደሚከተለው ተተንትኗል። የውጤት አመዘጋገቡ ቀደም ብሎ በተገለፀው ስልት መሠረት ለአምስቱ አማራጭ መልሶች የዋጋ አሰጣጥና የጥያቄ መንፈስ መሠረት ነው። የአመለካከት አማካይ ውጤት በቀራቢ አሥር ቤት፤ የመቶኛ በቀራቢ አንድ ቤት ተጠጋግቷል። በዚህ ስሌት መሠረት ቀጥለን በእያንዳንዱ ጥያቄ ላይ የተሰጠውን የምላሽ ውጤት እንመለከታለን።

ሀ· ለቋንቋውና ለትምህርቱ

በዚህ ተላውጦ ሥር ተማሪው ለአማርኛ ቋንቋና ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያለውን አመለካከት ለማወቅ ስድስት አዎንታዊና ስድስት አሉታዊ ስሜትን የሚያንፀባርቁ በድምሩ አሥራ ሁለት ጥያቄዎች ቀርበዋል። በእያንዳንዱ ጥያቄ ላይ የተሰጠውን ምላሽ ከመተንተናችን በፊት የሚከተለውን የተጨቃለለ ውጤት በሠንጠረዥ እንመልከት።

ሠንጠረዥ 2

ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋና ለትምህርቱ ያላቸው አመለካከት

| የመጠይቆች ተራ ቁጥር | ለምላሾች የሚሰጥ የብዜት ዋጋና የተማሪ ብዛት | | | | | | | | | | የአመለካከት ድምር ውጤት | አማካይ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 5 | | 4 | | 3 | | 2 | | 1 | | | |
| | የተማሪ ብዛት | % | የተማሪ ብዛት | % | የተማሪ ብዛት | % | የተማሪ ብዛት | % | የተማሪ ብዛት | % | | |
| 1 | 18 | 15.0 | 28 | 23.3 | 3 | 2.5 | 31 | 25.8 | 40 | 33.3 | 313 | 2.61 |
| 2 | 91 | 75.8 | 11 | 9.2 | - | - | 9 | 7.5 | 9 | 7.5 | 526 | 4.38 |
| 3 | 29 | 24.2 | 13 | 10.8 | 5 | 4.2 | 30 | 25.0 | 43 | 35.8 | 315 | 2.63 |
| 4 | 46 | 38.3 | 28 | 23.3 | 3 | 2.5 | 18 | 15.0 | 25 | 20.8 | 412 | 3.43 |
| 5 | 46 | 38.3 | 47 | 39.2 | 2 | 1.7 | 16 | 13.3 | 9 | 7.5 | 465 | 3.88 |
| 6 | 28 | 23.3 | 35 | 29.2 | 4 | 3.3 | 32 | 26.7 | 21 | 17.5 | 377 | 3.14 |
| 7 | 79 | 65.8 | 21 | 17.5 | 2 | 1.7 | 10 | 8.3 | 8 | 6.7 | 513 | 4.28 |
| 8 | 46 | 38.3 | 29 | 24.2 | - | - | 22 | 18.3 | 23 | 19.2 | 443 | 3.44 |
| 9 | 44 | 36.7 | 34 | 28.3 | 15 | 12.5 | 9 | 7.5 | 18 | 15 | 437 | 3.64 |
| 10 | 27 | 22.5 | 45 | 37.5 | 11 | 9.2 | 23 | 19.2 | 14 | 11.7 | 408 | 3.40 |
| 11 | 27 | 22.5 | 41 | 34.2 | 5 | 3.2 | 27 | 22.5 | 20 | 16.7 | 388 | 3.23 |
| 12 | 24 | 20 | 35 | 29.2 | 4 | 3.3 | 27 | 22.5 | 30 | 25.0 | 356 | 2.97 |
| ጠ· ድምር | 505 | | 367 | | 54 | | 254 | | 260 | | 4923 | 3.42 |

*ውጤቱ 120ዎቹ ተማሪዎች በአሥራ ሁለቱ ጥያቄዎች ላይ ያስመዘገቡት ድምር ውጤትና አማካይ ነው።

በዚህ ተላውጦ ሥር የሚገኙትን እያንዳንዱ ጥያቄ ለመተንተን እንሞክር

1· "ከእንግሊዝኛ ይልቅ የአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ቢያመልጠኝ በጣም ይጎዳኛል።"

ለዚህ አዎንታዊ መንፈስ ላዘለ የመጀመሪያ ጥያቄ በ120ዎቹ ተማሪዎች የተሰጠው መልስ፣ 18(15%) በጣም እስማማለሁ፣ 28(23.3%) እስማማለሁ፣ 3(2.5%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 31(25.8%) አልስማማም፣ 40(33.3%) ደግሞ ፍፁም አልስማማም የሚል ነው። አሉታዊና አዎንታዊ መልሶች ሲጠቃለሉ፣ 38·3% ያህሉ ተማሪዎች የደገፉት ሲሆን 54.1% ደግሞ ተቃውመውታል። በዚህ ውጤት መሠረት ለዚህ ጥያቄ የተማሪዎች አመለካከት አሉታዊ መሆኑን የመጨረሻው አማካይ ውጤት 2·61 መሆኑ ይጠቁማል። የአሠራር ስልቱ ጥያቄው አዎንታዊ በመሆኑ፣

በጣም እስማማለሁ x 5 + እስማማለሁ x 4 + ለመወሰን እቸገራለሁ x 3 + አልስማማም x 2 + ፍፁም አልስማማም x 1 ÷ ለእጠቃላላይ መለሾች ቁጥር ይሆናል።

$$\text{ስለዚህ} - \frac{18x5+28x4+3x3+31x2+40x1}{120}$$

$$= \frac{90+112+9+62+40}{120}$$

$$= \frac{313}{120}$$

$$= 2.61$$

ይህ ውጤት ከአማካዩ /ከሦስት/ በታች በመሆኑ ተማሪዎች የአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ቢያመልጣቸው ከእንግሊዝኛ አንፃር ሲታይ እንደማይጐዳቸው አድርገው እንደሚቆጥሩትና አሉታዊ ግምት እንደሚሰጡት ያመለክታል።

2· "ግድ ሆኖብኝ እንጂ የአማርኛ ቋንቋን ባልማረው እመርጣለሁ" ለሚለው አሉታዊ መንፈስ ላዘለ የሁለተኛው ጥያቄ ተማሪዎች የሚከተለውን ምላሽ አስመዝግበዋል። ጥያቄው አሉታዊ በመሆኑ ለምላሹ የሚሰጠው ዋጋ የአዎንታዊው ግልባጭ ይሆናል። ይኸውም በጣም እስማማለሁ 1፣ እስማማለሁ 2፣ ለመወሰን እቸገራለሁ 3፣ አልስማማም 4፣ ፍፁም አልስማማም 5 ይሆናል። በዚህ መሠረት ለጥያቄው የተሰጠው ምላሽ፣ በጣም

እስማማለሁ 9(9.2%) ፤ እስማማለሁ 9(7.5%)፤ አልስማማም 11(9.2%) ፍፁም አልስማማም 91(75.8% የሚሉ ናቸው። የመጨረሻ ውጤቱ ሲሰላ

$$= \frac{91x5+11x4+0x3+9x2+9x1}{120}$$

$$= \frac{455+44+0+18+9}{120}$$

$$= \frac{526}{120}$$

= 4.38 ይሆናል።

ይህንን አሉታዊ ጥያቄ ከአጠቃላዩ የተማሪ ብዛት 85.5% የሚሆኑት በከፍተኛ ደረጃ ሲቃወሙት 15% ብቻ ደግፈውታል። ስለዚህም ተማሪዎች ቋንቋውን የግድ ሳይሆን በፍላጎት ሊማሩት እንደሚሹ ያሳያል።

ይህ ውጤት ከጥያቄ አንድ አኳያ ሲታይ የተቃረነ ይመስላል። በአንደኛው መጠይቅ የአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ቢያመልጥ የእንግሊዝኛን ያህል ሊጐዳ እንደማይችልና ለትምህርቱ ጥሩ ግምት እንደማይሰጠው ተመዝግቧል። ለውጤቱ መለያየት መንስዔው አማርኛ ከእንግሊዝኛ ጋር ሲወዳደር የሚሰጠው ቦታ በመሆኑ ሁለቱን በማወዳደር የተገኘ ነው። ከዚህ አንፃር ከዚህ በፊት ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸውን አመለካከት የፈተሹ /ብርሃኑ ገብረማርያም 1976፤ ፀሐዬ ተፈራ 1977፤ ወርቁ በሻዳ 1982/ ሥራዎች አብዛኛው መለኪያቸው አማርኛን ከእንግሊዝኛ ጋር የሚያወዳድር በመሆኑ ተማሪዎች ለቋንቋው አሉታዊ አመለካከት እንዳላቸውና የማስተማሪያ ቋንቋ እንዲሆን አለመፈለጋቸውን ሊያሳዩ የቻሉት በዚህ ሳቢያ ለመሆኑ የአንደኛው ጥያቄ ያረጋግጣል። ስለዚህም በዚህ ጥናት ለማረጋገጥ እንደሚሞከረው አማርኛ ከሌላ ቋንቋ ጋር ሳይነፃፀር ለብቻው መጠናት እንደሚገባው በውል ይጠቁማል።

3· “የአማርኛ ቋንቋ በሁለተኛ ደረጃ የሁሉም ትምህርቶች መስጫ ቋንቋ ቢሆን እመርጣለሁ” ለሚለው አዎንታዊ ጥያቄ ከላይ በዝርዝር በተሰጠው የአሠራር ስልት

መሠረት የሚከተለው ውጤት ተገኝቷል። 29 ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ፣ 13 እስማማለሁ፣ 5 ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 30 አልስማማም፣ 43 ፍፁም አልስማማም የሚል ምላሽ ሰጥተው 2·63 ውጤት አስመዝግበዋል። በውጤቱ መሠረት የተማሪዎች አመለካከት አሉታዊ ነው። ከላይ እንደተጠቀሰው ምንም እንኳን መጠይቁ በቀጥታ ስለአማርኛ ብቻ የጠየቀ ቢሆንም አሁን የሁለተኛ ደረጃ የትምህርት መስጫ ቋንቋ እንግሊዝኛ በመሆኑ ለተሰጠው ውጤት የእንግሊዝኛ ቋንቋ አብሮ መታሰብ ካስከተለው ተፅዕኖ የመነጨ ይመስላል። ምንም ይሁን ምን ግን ውጤቱ አሉታዊ ነው።

4· “በሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና የአማርኛ ፈተና ውጤት እንደ እንግሊዝኛና ሂሳብ ትምህርቶች አይቀሬ ተደማሪ /ኮምፐልሰሪ/ አለመሆኑ ጥሩ ነው”

ይህንን አሉታዊ ጥያቄ 35% የሚሆኑት ሲደግፉት 61.6% ደግሞ ተቃውመውታል። አማካይ ውጤታቸው 3·43 በመሆኑ ቋንቋው ኮምፐልሰሪ ትምህርት ቢሆን እንደሚፈልጉና እንዲያውም ጥሩ ውጤት ሊያስመዘግቡበት እንደሚችሉ የሚጠቁም አዎንታዊ አመለካከት አላቸው።

5· “የሳምንት የአማርኛ ክፍለ ጊዜ ብዛት በጣም ስለሚያንስ ቢጨመር ይሻላል” ለሚለው አዎንታዊ ጥያቄ 77.5% ተማሪዎች ሲስማሙበት 20.8% ደግሞ ተቃውመውታል። በዚህ ምላሽ መሠረት ተማሪዎች ለቋንቋውና ለትምህርቱ አዎታንዊ አመለካከት እንዳላቸውና በሳምንት ተጨማሪ ክፍለ ጊዜ ተሰጥቷቸው መማር እንደሚፈልጉ 3·88 በሆነ አዎንታዊ ውጤት አረጋግጠዋል።

6· “የአማርኛ ትምህርት ብዙም ስለማይጠና ሰፊ ጊዜ ስጥቼ ለማትረክ ፈተና የምዘጋጀው ለሌሎች ከባድ ለሆኑ ትምህርቶች ነው”

ይህ ጥያቄ አሉታዊ መንፈስ ያለው ሲሆን 44.2% ሲደግፉት 52.5% የሚሆኑት ተቃውመውታል። 3.3% ለመወሰን ሲቸገሩ በጥቅሉ 3·14 የሆነ ነጥብ ተገኝቷል። ውጤቱ አዎንታዊ ቢሆንም ዝቅተኛ ነው። ቁጥራቸው ትንሽ የማይባል ተማሪዎች አማርኛን እንደቀላል ትምህርት በመቁጠር ለሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጠንከር ያለ ዝግጅት እንደሚያደርጉ ይጠቁማል። ምናልባትም ቋንቋውን ከሌሎች ትምህርቶች የመማሪያ ቋንቋ

/እንግሊዝኛ/ ይልቅ በተሻለ ደረጃ እናውቀዋለን ከሚል ግምት የመነጨ ሊሆን ይችላል። ለዚህም ነው በተራ ቁጥር አራት ላይ የተሰጠው ምላሽ አማርኛ ኮምፕልስሪ ቢሆን ሊጐዱ እንደማይችሉ ገምተው ፍላጐታቸው መሆኑን የገለፁት።

7· "የአማርኛ ቋንቋ የሀዲያ ዞን የሥራ ቋንቋ ሆኖ ቢያገለግል እወዳለሁ"

በምዝገባው ውጤት መሠረት ይህንን ሐሳብ የደገፉ 83.3% ሲሆኑ 15% ደግሞ ተቃውመውታል። በክፍል 2·1 እንደተጠቆመው የሀዲያ ዞን መስተዳድር በአሁኑ ሰዓት የሥራ ቋንቋ አድርጐ የመረጠውና ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት መስጫ ቋንቋነት የሚጠቀመው የብሔረሰቡን ቋንቋ ሀዲይኛ ነው። ከዚህ አንፃር በዚህ መጠይቅ የተገኘው ውጤት ተማሪዎች ከራሳቸው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ይልቅ አማርኛ የዞኑ የሥራ ቋንቋ እንዲሆን መፈለጋቸውን 4·28 በሆነ አማካይ ውጤት አዎንታዊ አመለካከት እንዳላቸው ያመለክታል። ይህ ውጤት ተማሪዎች ለአፍ መፍቻ ቋንቋቸው አሉታዊ ግምት አላቸው ወደሚል ድምዳሜ ሊያደርስ ባይችልም አማርኛ በዞኑ ለሥራ ቋንቋነት ቢውል ውዴታቸው መሆኑን ግን አጠንክሮ ይጠቁማል።

8· "በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የፈተና ውጤቴ ዘወትር ዝቅተኛ ነው"

ለዚህ መጠይቅ የተሰጠው የምላሽ ውጤት 3·44 ነው። አብዛኛው ተማሪ 62.5% ሐሳቡን ሲቃወሙ 37.5% ደግፈውታል። ስለዚህ የፈተና ውጤታቸው ዝቅተኛ እንዳልሆነ ይጠቁማሉ።

9· "ወደፊት በኮሌጅና በዩኒቨርሲቲ የአማርኛ ቋንቋን ለማጥናት ከፍተኛ ፍላጐት አለኝ"

ይህንን በዛሬ ላይ ተመሥርቶ የነገ ተስፋን በሚጠይቅ አዎንታዊ ጥያቄ ላይ 44(36.7%) በጣም እስማማለሁ፣ 34(28.3%) እስማማለሁ፣ 15(12.5%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 9(7.5%) አልስማማም፣ 18(15%) ፍፁም አልስማማም የሚል መልስ ሰጥተውበታል። ይህ መጠይቅ ለመወሰን እቸገራለሁ የሚሉ መላሾች የበዙበት ቢሆንም 78(65%) ግን ደግፈውታል። ስለዚህ ተማሪዎች ወደፊት በኮሌጅና በዩኒቨርሲቲዎች የአማርኛ ቋንቋን ለማጥናት ተስፋና ፍላጐት እንዳላቸው 3·64 በሆነ አዎንታዊ አማካይ

ውጤት ገልፀዋል። ተማሪዎች ዛሬም ሆነ ወደፊት ለቋንቋው ጥላቻ እንደሌላቸው ያስመዘገቡት ነጥብ ያስረዳል።

10· "በአማርኛ ቋንቋ ያለችግር መናገርና መፃፍ እችላለሁ" ለሚለው አዎንታዊ ጥያቄ 60% ያህሉ ተማሪዎች ስምምነታቸውን ሲያሳዩ 34.9% ተቃውመዋል። 9.2% ደግሞ የችሎታቸውን ደረጃ ለመወሰን ተቸግረዋል። በዚህ መጠይቅ 3·44 አማካይ ውጤት አስቆጥረዋል።

ከተገኘው ውጤት አኳያ በአማርኛ የመናገርና የመፃፍ ችግር የሌለባቸው መሆኑ ይታያል። ይሁን እንጂ ውጤቱ ዝቅተኛ አዎንታዊ በመሆኑ የትክክለኝነቱ ደረጃ አንፃራዊ ነው። ምናልባትም በቋንቋው በመግባቢያነት ሊጠቀሙበት ቢችሉ እንጂ ምሉዕ ልሳነ ክልኤ /absolute bilingual/ ከሚያሰኝ የፍፁምነት ደረጃ ላይ እንዳልደረሱ የውጤቱ ዝቅተኛ አዎንታዊነት /3·44/ ይጠቁማል።

11· "የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በጣም ከባድና አስቸጋሪ ነው" ለሚለው አሉታዊ ጥያቄ 47(39.2%) የሚስማሙበት ሲሆኑ 68(56.7%) ደግሞ ተቃውመውታል። ቀሪዎቹ 5 (4.2%) ግን ለመወሰን መቸገራቸውን አስቀምጠዋል። በውጤቱ መሠረት ለአብዛኞቹ ተማሪዎች የአማርኛ ትምህርት የማያስቸግርና ገራገር እንደሆነ 3·23 በሆነ አማካይ ውጤት አረጋግጠዋል። ይህ ውጤት አሁንም ተማሪዎች ለቋንቋው ትምህርት ያላቸውን ቀና አመለካከት ከማመልከት ባሻገር የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ቀላል መሆኑን የሚያመለክት ጥንካሬ የለውም። ቢሆንም ግን ከጥያቄ ተራ ቁጥር አራትና ስድስት ጋር ሲገናዘብ ከሌሎች ትምህርቶች አንፃር የአማርኛ ትምህርት እምብዛም እንደማይጠጥርባቸው ያሳያል።

12· "የአማርኛን ትምህርት አጠናሁትም አላጠናሁትም የፈተና ውጤቱ በጣም ጥሩ ነው"

በዚህ ጥያቄ ላይ 59(49.2%) ተማሪዎች ተቃውሞ ሲያቀርቡ 57(47.5%) ተማሪዎች ደግፈውታል። 4(3.3%) ደግሞ ለመወሰን የተቸገሩ ናቸው። ያስመዘገቡት አማካይ ነጥብ 2·97 ነው። በዚህ ጥያቄ መሠረት ከላይ የተሰጡትን ምላሾች /ተራ ቁጥር 4፣ 6 እና 11/

ስናገናዝባቸው ትምህርቱ መጠናትና ክትትል የሚያስፈልገው እንጂ ትኩረት የሚነፈገውና የሚናቅ አለመሆኑን ይገልፃል። ካልተጠና በስተቀር ጥሩ ውጤት ሊገኝበት እንደማ ይችልም ያመለክታል።

ከዚህ ላይ ለተላውጠ አንድ /ለቋንቋውና ለትምህርቱ/ ተማሪዎች ያላቸው አመለካከት ሲጠቃለል አዎንታዊ ነው። በአሥራ ሁለቱ ጥያቄዎች ላይ መቶ ሀያዎቹ ተማሪዎች ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት 3·42 መሆኑን ለቋንቋው ትምህርት ቀና አመለካከት እንዳላቸው በመነሻው የተቀመጠው ሠንጠረዥ ያሳያል።

በምዕራፍ ሁለት በቀረበው ክለሳ ድርሳናት ውስጥ ተማሪው ለሚማረው ሁለተኛ ቋንቋና ለትምህርቱ ቀና አመለካከት ያለው ከሆነ በፍላጎት ተነቃቆቶ ለመማር የሚጣጣር፣ በራስ የመተማመን ስብዕናን የሚያዳብር፣ በቋንቋ ኪኒል እድገቱ ፈጣን፣ በውጤቱም የተሻለ ሊሆን እንደሚችል ተጠቅሷል። ነገር ግን ይህንን አዎንታዊ አመለካከት ሌሎች ተፅዕኖ አድራሽ ተላውጦዎች ሊጫኑት እንደሚችሉ መዘንጋት አይገባም።

ለ· <u>ለመማሪያ መፅሐፉ</u>

የተማሪው መማሪያ መፃህፍት ከመርሀ ትምህርቱ ዓላማ አኳያ የተቀረፁ፣ በመጨረሻ በተማሪው ላይ ሊመጣ የሚፈለገውን የባህርይ ለውጥ ለማስገኘት የሚያስችሉ የትምህርት ዓላማዎች፣ ይዘቶች፣ ልምዶችና ግምገማዎችን የያዙ የትምህርት መሣሪያዎች በመሆናቸው ከተማሪው ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት አላቸው። ተማሪዎች በመማሪያ መፃህፍቱ ላይ የሚኖራቸው ቀናና አጉል አመለካከት ደግሞ በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ክንውን ላይ ከፍተኛ ትዕዕኖ እንደሚያደረስ በክለሳ ድርሳናት ክፍል ተመላክቷል።

ይህ ጥናት የሚመለከታቸው ተማሪዎች በአሥራ ሁለተኛ ክፍል የመማሪያ መፅሐፍ ላይ ስላላቸው አመለካከት የሚጠይቁ ከጥያቄ ተራ ቁጥር 13-24 ባሉት ጥያቄዎች ላይ ያስመዘገቡት የአመለካከት ውጤቶች ቀጥሎ በተቀመጠው ሠንጠረዥ ላይ ተጠቃልለው ቀርበዋል።

ሠንጠረዥ 3

ተማሪዎች ለመማሪያው መፅሐፍ ያላቸው አመለካከት

| የመጠይቆች ተራ ቁጥር | ለምላሾች የሚሰጥ የብዜት ዋጋና የተማሪ ብዛት | | | | | | | | | | የአመለካከት ድምር ውጤት | አማካይ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 5 | | 4 | | 3 | | 2 | | 1 | | | |
| | የተማሪ ብዛት | % | የተማሪ ብዛት | % | የተማሪ ብዛት | % | የተማሪ ብዛት | % | የተማሪ ብዛት | % | | |
| 13 | 42 | 35 | 30 | 25 | 1 | 0.8 | 24 | 20 | 23 | 19.2 | 404 | 3.37 |
| 14 | 15 | 12.5 | 8 | 6.7 | 6 | 5 | 35 | 29.2 | 56 | 46.7 | 251 | 2.9 |
| 15 | 22 | 18.5 | 44 | 36.7 | 3 | 2.5 | 29 | 24.2 | 22 | 18.3 | 375 | 3.13 |
| 16 | 30 | 25 | 31 | 25.8 | 4 | 3.3 | 30 | 25 | 25 | 20.8 | 371 | 3.09 |
| 17 | 24 | 20 | 26 | 21.2 | 2 | 1.7 | 28 | 23.3 | 40 | 38.3 | 326 | 2.70 |
| 18 | 16 | 13.3 | 18 | 15 | 1 | 0.8 | 37 | 30.8 | 48 | 40 | 277 | 2.31 |
| 19 | 45 | 37.5 | 40 | 33.3 | 2 | 1.7 | 19 | 15.8 | 14 | 11.7 | 443 | 3.69 |
| 20 | 18 | 15 | 28 | 23.3 | 5 | 4.2 | 27 | 22.5 | 42 | 35 | 313 | 2.61 |
| 21 | 29 | 24.2 | 42 | 35 | 7 | 5.8 | 23 | 19.2 | 19 | 15.8 | 399 | 3.33 |
| 22 | 15 | 12.5 | 25 | 20.8 | 5 | 4.2 | 46 | 38.3 | 29 | 24.2 | 311 | 2.59 |
| 23 | 42 | 35 | 33 | 27.5 | 5 | 4.2 | 27 | 22.5 | 13 | 10.8 | 424 | 3.53 |
| 24 | 37 | 20.8 | 39 | 32.5 | 2 | 1.7 | 26 | 21.7 | 16 | 13.3 | 415 | 3.46 |
| ጠ· ድምር | 335 | | 364 | | 43 | | 351 | | 347 | | 4309 | 2.99 |

ከዚህ የሠንጠረዥ መረጃ በመነሳት ለጥያቄዎቹ የተሰጠውን ምላሽ እንዘረዝራለን።

13· "የአማርኛ መማሪያ መፅሐፌን ሁል ጊዜ እንደሌሎቹ ትምህርቶች አጠናዋለሁ" በዚህ አዎንታዊ ጥያቄ 72(60%) ተማሪዎች ሲስማሙበት 47 (39.2%) ተቃውመውታል። አንድ ተማሪ (0.8%) ለመወሰን ተቸግሯል። አጠቃላይ የአመለካከት ውጤቱ 3·37 ሆኗል። በዚህ ጥያቄ መሠረት ተማሪዎች አዘውትረው መፅሐፉን እንደሚያጠኑት አረጋግጠዋል። ምንም እንኳን ውጤቱ ዝቅተኛ ቢሆንም ከተራ ቁጥር አሥራ ሁለት ጋር የተጣጣመ መልስ የተሰጠበትና መጠናት የሚገባው መሆኑን ያመለክታል።

14· "አሁን ያለው የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍ በአዲስ ቢለወጥ የመማር ፍላጐቴ ይነቃቃ ነበር" ይህንን አሉታዊ ጥያቄ 91 ተማሪዎች ሲደግፉት 23 ተማሪዎች ተቃውመውታል። በጥቅሉ ለጥያቄው የተሰጠው ምላሽ አማካይ 2·09 መሆኑ በጣም ዝቅተኛ አሉታዊ አመለካከታቸውን ይጠቁማል። ስለዚህ መፅሐፉ የተማሪውን የመማር ፍላጐት የማያነቃቃና ሳቢነት የሌለው በመሆኑ ለተሻለ መነቃቃት አዲስ መፅሐፍ ተዘጋጅቶ ቢቀርብላቸው ፈልገዋል።

15· "የመማሪያው መፅሐፍ ሳቢነት የሌለው፣ አሰልቺና አስቸጋሪ ነው።" ለዚህም ጥያቄ 3·13 አማካይ ነጥብ ተመዝግቧል። ሐሳቡ ከተራ ቁጥር አሥራ አራት ጋር የተቀራረበ ከመሆኑም በላይ አዎንታዊነቱ በጣም ዝቅተኛ ነው።

16· "የመማሪያ መፅሐፉ ያለ አስተማሪ እንኳን ለመማር /ለማጥናት/ ብቃት ያለው ጥሩ ዝግጅት ነው።" በዚህ ጥያቄ የተመዘገበው አመካይ ውጤት 3·09 ሲሆን ወደ ገለልተኛ /neutral/ አመለካከት የሚጠጋ እጅግ በጣም ዝቅተኛ አዎንታዊ መሆኑ ይታያል። መፅሐፉ ተማሪዎች ብቻቸውን ሊሠሩበት ስለማስቻሉ የተሰጠው ምስክርነት በድረበቡ የተቀመጠ ነው።

17· "የመማሪያው መፅሐፍ በተማሪዎች ፍላጐትና የዕውቀት ደረጃ መሠረት የተዘጋጀ ስለሆነ ያረካኛል።" በዚህ ጥያቄ ላይ 68 ተማሪዎች ተቃውሞ ሲያሳዩ 50 ተማሪዎች ደግፈውታል። ሁለት ተማሪዎች ግን ለመወሰን ተቸግረዋል። አማካይ ነጥቡ ደግሞ 2·72 በመሆኑ በመፅሐፉ ላይ ያላቸውን አሉታዊ አመለካከት አጠንክሮ ያረጋግጣል። የተራ ቁጥር አሥራ ሦስት ጥያቄን ግምትም በወጉ ያጠናክራል።

18· "መፅሐፉ የልቦለድ ፅሑፎችን ቢይዝ ያስደስተኛል" ይህንን መጠይቅ 85 ተማሪዎች ሲደግፉት 34 ደግሞ ተቃውመውታል። አንድ ተማሪ ለመወሰን ተቸግሯል። ከውጤቱ እንደምንመለከተው 2·31 አማካይ ነጥብ በመፅሐፉ ውስጥ የልቦለድ ፅሑፎች በብዛት አለመገኘት በተማሪው የመማር ፍላጐትና ርካታ ላይ ተፅዕኖ እንዳለው እንመለከታለን። ሐሳብና ውጤቱ ከተራ ቁጥር አሥራ አራት ጋር በእጅጉ የተዛመደ ነው።

19· "መፅሐፉ በፊት ያልነበረኝን የመፃፍና የማንበብ ችሎታዬን አዳብሮልኛል" በሚለው አዎንታዊ መጠይቅ ላይ 85 (70.8%) ተማሪዎች በከፍተኛ ደረጃ ድጋፍ ሲሰጡ 33(29.5%) ተቃውመውታል። ሁለት ተማሪዎች ደግሞ ለመወሰን ተቸግረዋል።

ለጥያቄው የተመዘገበው አማካይ ነጥብ 3·69 ሲሆን አዎንታዊ ምላሽ አግኝቷል። ነገር ግን ከላይ ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጠው ምላሽ አንፃር፤ ተማሪዎች መፅሐፉ በአዲስ ቢተካ እንደሚረኩ፤ ሳቢነት የሌለውና አሰልቺ ስለመሆኑ፤ ያለአስተማሪ ለመማር እንኳ ብቃት እንደሌለው ከገለፁት በመነሳት ሲታይ የተሰጠው ውጤት የተቃረነ ነው። ቢሆንም ግን ባለበት ደረጃ የተማሪዎችን የማንበብና የመፃፍ ክኂል ሊያዳብር መቻሉን አንፃራዊ በሆነ መንገድ ልንቀበለው እንችላለን።

20· "ለአሥራ ሁለተኛ ክፍል ተብሎ የተዘጋጀው የመማሪያ መፅሐፍ ይዘት ከሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ይዘት ጋር የጠበቀ ግንኙነት የለውም።"

ለዚህም ጥያቄ 46 ተማሪዎች የመፅሐፉ ይዘት ከፈተናው ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዳለው ሲያረጋግጡ 69 ደግሞ ግንኙነት የለውም በማለት መልሰዋል። አምስት ተማሪዎች ለመወሰን ሲቸገሩ በጥቅሉ 2·61 አማካይ አሉታዊ ነጥብ ተስጥቶበታል።

21· "በመማሪያው መፅሐፍ ውስጥ የቀረቡት መልመጃዎች በተግባር ሊሠሩ የሚችሉና ቀላል ናቸው።" በዚህ ጥያቄ ላይ 3·33 አማካይ ነጥብ የተመዘገበ በመሆኑ መልመጃዎቹ ሊሠሩ የሚችሉና ቀላል ለመሆናቸው መጠነኛ ደጋፊ ሐሳብ ተስጥቶታል። ውጤቱ እንደሚጠቁመው የመልመጃዎቹ ቅለትና ተተግባሪነት ተጋንኖ የሚነገርለት ሳይሆን ክብደት ቅለለቱን አቻችሎ የተመለሰ መካከለኛ ምላሽ መሆኑን ከተከታዩ መጠይቅ ያጤኗል።

22· "በመፅሐፉ ውስጥ የቀረቡት አንዳንድ መልመጃዎች በአካባቢያችን ልናገኘው ወይም ልንሠራው የማንችለውን ጉዳይ እንድንሠራ የሚያዝዙ ናቸው"

በተራ ቁጥር ሀያ አንድ ላይ በተገኘው የምላሽ ውጤት በዝቅተኛም ደረጃ ቢሆን መልመጃዎቹ ቀላልና ሊተገበሩ የሚችሉ መሆናቸው ሲጠቆም በዚህ መጠይቅ ላይ ግን 75 (62.5%) ተማሪዎች አንዳንድ መልመጃዎች ሊሠሩ የማይችሉና በአካባቢው የማይገኙ

ሥራዎች እንዲሠሩ የሚያገዘዙ መሆናቸውን ተስማምተውበታል። አማካይ ውጤቱም 2·59 በመሆኑ አሉታዊ ነው።

23· "በመፅሐፉ ውስጥ የቀረቡት መልመጃዎችና ምንባቦች ክብደት አማርኛ የአፍ መፍቻውም ሆነ የሁለተኛ ቋንቋው ለሆነ ተማሪ ዕኩል ናቸው።"

በጥናቱ የተካተቱት ተማሪዎች አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው በመሆኑ የቀረቡት ምንባቦችና መልመጃዎች ክብደትና ቅለት ለሁሉም ተቀራራቢ ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ በአማርኛ አፈ - ፈት ለሆነ ተማሪ ትምህርቱ ይቀለዋል ማለትም አያስኬድም። በውጤቱ መሠረት መላሾች ከራሳቸው የችሎታ ደረጃ አንፃር ለሁሉም ዕኩል ክብደት አለው በሚል ግምት 3·53 አማካይ አዎንታዊ ነጥብ ሰጥተዋል። ቢሆንም ይህንን ምላሽ ከጥያቄ ተራ ቁጥር ሀያ አንድ ጋር በማዛመድ ሲታይ በእርግጥም ላይከብዳቸው ይችላል።

24· "በመፅሐፉ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦችና መልመጃዎች ለቋንቋ ትምህርት የማያግዙና እርስ በርሳቸውም የማይገናኙ ናቸው።"

በዚህ አሉታዊ ጥያቄ ላይ 42 ተማሪዎች ሲስማሙበት 76(63.3%) ደግሞ ተቃውመውታል። ስለዚህም መልመጃዎቹና ምንባቦቹ እርስ በርሳቸው ግንኙነት ያላቸውና ለቋንቋ ትምህርትም አጋዥነት እንዳላቸው 3·46 በሆነ አማካይ ነጥብ አዎንታዊ አመለካከታቸውን አሳይተዋል።

በዚህ ተላውጦ ላይ ጠቅላላ ተማሪዎች በእያንዳንዱ ጥያቄ ላይ ያስመዘገቡት ድምር 4309 ነው። ይህንን አጠቃላይ ድምር ለጠቅላላው ተማሪ ቁጥርና ለአሥራ ሁለቱ ጥያቄዎች ሲካፈል 2·99 አጠቃላይ የተላውጦ አማካይ ነጥብ ይሰጣል።

በዚህ ውጤት መሠረት ተማሪዎቹ ለመማሪያው መፅሐፍ ያላቸው አመለካከት አሉታዊ እንደሆነ ለመገንዘብ ይቻላል። በአሉታዊ አመለካከት በሚሰጥ የትምህርት ሂደት ደግሞ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ላይም ሆነ የቀረቡት መል መጃዎች የሚያገዙትን የቋንቋ ትምህርት ልምምዶች በፍላጐት እንዳይሳተፉበት እንቅፋት ይሆናል። በክለሳ ድርሳናት ክፍል እንደተመለከተው ሳቢነትና አነቃቂነት

እንዲሁም ተተግባሪነት የሌላቸው የትምህርት መግሪያዎች በተማሪው የመማር ፍላጐትና የክፍል ውስጥ ክንውን ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንደሚያደርሱ ተጠቁሟል። ስለዚህም የ12ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍ ቀደም ብሎ በጥናት ላይ ባልተመሠረተና የየአካባቢውን የቋንቋ ችግር በማይፈታ ሲለበስ ላይ ተመሥርቶ የወጣ በመሆኑ /አሥራ ሁለተኛ ክፍል አማርኛ ሲለበስ 1984 ዓ.ም/ በተማሪዎች ላይ አሉታዊ አመለካከት አሳድሯል። ለዚህም በጥያቄ ተራ ቁጥር 14፣ 16፣ 17፣ 17 እና 22 ላይ የተሰጠው ምላሽ ጥሩ ማረጋገጫ ይሆናል። እነዚህና መሰል ችግሮች ለወደፊት ዝግጅትም ጠቃሚ የመነሻ ነጥቦች ተደርገው ሊወሰዱ የሚገቡ የፍላጐት አሰሳ መረጃዎች ናቸው።

ሐ· <u>ለመምህሩና ለማስተማሪያው ስልት</u>

በዚህም ተለውጦ ላይ ተማሪዎች ያላቸውን አመለካከት ለመቃኘት አሥራ ሁለት ጥያቄዎች የቀረቡ ሲሆን በውስጣቸው ስለመምህሩ ዕውቀትና ችሎታ፣ ስለሚያስተምርበት ስልት፣ ከተማሪዎች ጋር ስለሚያደርገው መልካም ቅርርብ፣ ለሙያው ስላለው ፍቅርና የማስተማር ፍላጐት … ወዘተ አስመልክቶ ተማሪዎች የሚሰጡትን ግምት የሚለኩ ናቸው። በዚህ ተላውጦ ላይ ተማሪዎች የሚሰጡት አስተያየት ለመምህራን ከቀረበው መጠይቅ ጋር ተገናዝቦ ይቀርባል። በቅድሚያ ግን በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ተማሪዎች ያስመዘገቡትን የአመለካከት ውጤት በሚከተለው ሠንጠረዥ ላይ እንመልከት። ሠንጠረዡ ከተራ ቁጥር 25-36 ያሉትን ጥያቄዎች አጠቃልሎ የያዘ ነው።

ሠንጠረዥ 4

ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ መምህራቸው ያላቸው አመለካከት

| የመጠይቆች ተራ ቁጥር | ለምላሾች የሚሰጥ የብዜት ዋጋና የተማሪ ብዛት | | | | | | | | | | የአመለካከት ድምር ውጤት | አማካይ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 5 | | 4 | | 3 | | 2 | | 1 | | | |
| | የተማሪ ብዛት | % | የተማሪ ብዛት | % | የተማሪ ብዛት | % | የተማሪ ብዜት | % | የተማሪ ብዛት | % | | |
| 25 | 46 | 28.3 | 28 | 23.3 | - | - | 22 | 18.3 | 24 | 20.8 | 410 | 3.42 |
| 26 | 15 | 12.5 | 15 | 12.5 | 1 | 0.8 | 20 | 16.7 | 69 | 57.5 | 247 | 2.05 |
| 27 | 37 | 30.8 | 49 | 40.8 | 4 | 3.3 | 20 | 16.7 | 10 | 8.3 | 443 | 3.69 |
| 28 | 14 | 11.7 | 24 | 20 | 5 | 4.2 | 37 | 30.8 | 40 | 33.3 | 295 | 2.46 |
| 29 | 55 | 45.8 | 23 | 19.2 | 3 | 2.5 | 21 | 17.5 | 18 | 15 | 436 | 3.63 |
| 30 | 19 | 15.8 | 31 | 25.8 | 2 | 1.7 | 34 | 28.3 | 34 | 28.3 | 327 | 2.73 |
| 31 | 29 | 24.2 | 41 | 34.2 | 4 | 3.3 | 28 | 23.3 | 18 | 15 | 395 | 3.29 |
| 32 | 32 | 26.7 | 34 | 28.3 | 3 | 2.5 | 36 | 30 | 15 | 12.5 | 392 | 3.27 |
| 33 | 44 | 36.7 | 45 | 37.5 | 7 | 5.8 | 13 | 10.8 | 11 | 9.2 | 458 | 3.82 |
| 34 | 48 | 40.0 | 38 | 31.7 | 5 | 4.2 | 17 | 14.2 | 12 | 10 | 453 | 3.78 |
| 35 | 42 | 35 | 31 | 25.8 | 5 | 4.2 | 20 | 16.7 | 22 | 18.3 | 411 | 3.43 |
| 36 | 47 | 36.7 | 9 | 7.5 | 3 | 2.5 | 34 | 28.3 | 67 | 15.8 | 215 | 1.79 |
| ጠ· ድምር | 388 | | 368 | | 42 | | 302 | | 340 | | 4482 | 3.11 |

ጥያቄዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

25· "መምህራችን የሚሰጡንን የቤትና የክፍል ሥራ አዘውትረው ስለሚያርሙ ያልገባንን ጠይቀን ለመረዳት ወይም ከስህተታችን ለመማር ሰፊ ዕድል አለን።"

ለዚህ ጥያቄ 61·7% ተማሪዎች ስምምነት ሲያሳዩ 38·3% ደግሞ አል ተስማሙበትም። አማካይ ውጤቱ 3·42 በማሳየቱ መምህራን ተማሪዎች ከስህተታቸው እንዲማሩ ወይም ያልገባቸውን ጠይቀው እንዲረዱ ዕድል እንደሚሰጡ ተረጋግጦላቸዋል። የክፍልና የቤት ሥራም አዘውትረው በመስጠት እንደሚያርሙም ውጤቱ ይመሰክራል።

26· “በቂ ችሎታና ብቃት ያለው ሌላ መምህር ቢመደብ ትምህርቱን በሚገባ ለመከታል ፍላጐቴ ይነቃቃ ነበር።”

በዚህ አሉታዊ ጥያቄ ላይ 89 (74.2%) ተማሪዎች ሲስማሙ 30(25%) ደግሞ ተቃውመዋል። በውጤቱ መሠረት መምህራን በቂ ዕውቀትና ችሎታ እንደሚጐድላቸው ተማሪዎች ከመግለፃቸውም በተጫማሪ ሌላ የተሻለ መምህር እንደሚፈልጉም ያሳያል። አማካይ ውጤቱ 2·06 በመሆኑ በመምህራን ችሎታና ዕውቀት ላይ ጠንካራ አሉታዊ አመለካከት አላቸው። ይሁን እንጂ ይህ ውጤት በጥቅል መልክ በስድስቱ መምህራን ላይ ከተሰጠው አስተያየት ላይ የወጣ በመሆኑ እንጂ በየትምህት ቤቱ ለእያንዳንዱ መምህር በተናጠል የተሰጠው ውጤት አለመሆኑን ማጤን ይገባል። ይህም ቢሆን ግን ጥሩ ችሎታና ዕውቀት ያላቸው መምህራን የመኖራቸውን ያህል ደካሞችም እንደማይታጡ መገመት ይቻላል። የዚህ መጠይቅ ውጤትም የሚጠቁመው ይህንኑ ነጥብ ነው።

27· “መምህሩ ክፍል ሲገቡ ጥሩ ዝግጅት የሚያደርጉና ለሙያቸውም ፍቅር ያላቸው ናቸው።”

ለመጠይቁ የተሰጠው አማካይ ነጥብ 3·69 ሲሆን መምህራን ተዘጋጅተው ክፍል የሚገቡና ለሙያቸውም ፍቅር እንዳላቸው ተማሪዎቻቸው መስክረዋል።

28· “የአማርኛ መምህራችን የሙያ ማሻሻያ ኮርስ መከታተል ወይም የትምህርት ደረጃቸውን ማሻሻል አለባቸው።”

በዚህ ጥያቄ ላይ 77 ተማሪዎች ስምምነታቸውን ሲያመለክቱ 38 ተማሪዎች ነቅፈዋል። አምስት ተማሪዎች ግን ለመወሰን ተቸግረዋል። የተገኘው አማካይ ውጤት 2·96 በመሆኑ መምህራን የሙያ ማሻሻያ ኮርስ ወይም የትምህርት ደረጃቸውን ሊያሻሽሉ እንደሚገባቸው የተጠቆመበት ነው። በነዚህና ወደፊት በሚቀጥሉት ጥያቄዎች መሠረት መምህሩ ጥሩ ዝግጅት የሚያደርግ፣ ለሙያው ፍቅር ያለው፣ ሳቢነት ያለው የማስተማር ስልት የሚጠቀም፣ ተማሪዎችን ባልገባቸው የሚረዳ፣ ተጨማሪ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን የሚጠቀም… ወዘተ ቢሆንም ቅሉ በቋንቋው ትምህርት ላይ በቂ ችሎታና

ዕውቀት ስለሌለው የተሻለ መምህር ቢቀየር /ጥያቄ 26/ ወይም ትምህርቱን ቢያሻሽል ጥሩ መሆኑን በመጠይቆቹ የተገናዘበ መልስ ተሰጥቶበታል እንጂ ተቃርኖ አይታይበትም።

29· "መምህሩ ከመማሪያው መፅሐፍ ውጭ ከጋዜጣ፣ ከመፅሔትና ከመፃህፍት የተለያዩ ፅሑፎችን ክፍል ውስጥ በማምጣት በቋንቋው ላይ ያለንን ችሎታ እንድናዳብር ይረዱናል።" ለጥያቄው የተሰጠው አማካይ ነጥብ 3·69 ሲሆን መምህራን ተማሪዎችን ለመርዳት የማያደርጉትን ጥረት ያሳያል። በሐሳቡ 78 ተማሪዎች ተስማምተዋል። 39 ተማሪዎች ሲነቅፉት ሦስት ደግሞ ገለልተኞች ናቸው።

30· "የሚሰጠን የአማርኛ ፈተና ከተማርነው ጋር ስለማይገናኝ ውጤታችን ዝቅተኛ ይሆናል።"

የመጠይቁን ሐሳብ68(56.7% ተማሪዎች ትክክል እንደሆነ ሲገልፁ 50 (41.7%) ደግሞ አይሆንም ብለዋል። ሁለት ተማሪዎች ሐሳብ የለኝም ያሉ ናቸው። በዚህ ምላሽ መሠረት መምህራን የማያስተምሩትን እንደሚፈትኑ 2·73 በሆነ አሉታዊ ውጤት አመል ክተዋል። ይህ ውጤት በቀጥታ ስለመምህራን የፈተና አወጣጥ ድክምት የሚያሳይ ቢሆንም በስላች ደግሞ የተማሪውን ጠንክሮ አለማጥናትም ሊጠቁም ይችላል። ቢሆንም ተማሪዎች በፈተናው አወጣጥ ላይ ያላቸውን አሉታዊ አመለካከት ገልፀዋል።

31· "የአማርኛ መምህራችን የማስተማር ስልትና አቀራረብ ማራኪና ሳቢነት አለው።" ለዚህ ጥያቄ 3·29 በሆነ አማካይ ነጠብ አዎንታዊ አመለካከት ተመዘግቧል። በእርግምም ውጤቱ ደጋፊ ነው። ይሁን እንጂ በጠነከረ መልኩ የተሰጠ ባለመሆኑ የመምህራን የማስተማር ስልት እስከዚህ የሚደነቅ ያህል እንዳልሆነ ያሳያል።

32· "መምህራችን በአማርኛ ሲፅፉና ሲናገሩ የቋንቋ ግድፈት ስለሚያደርጉ ተማሪዎች የሚፈፅሟቸውን ስህተቶች ፈጥነው ለማረም አይችሉም።"

ይህ አሉታዊ ጥያቄ በ51 ተማሪዎች ተደግፎ በ66 ተማሪዎች ተነቅፏል። በመጨረሻም መምህሩ የቋንቋ ግድፈት እንደማያሳዩ 3·27 በሆነ ዝቅተኛ አማካይ ነጥብ መስክረዋል። ስለዚህም በመምህራን መጠይቅ ላይ እንደተመለከተው አብዛኛቹ መምህራን

የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው አማርኛ መሆኑ ለዚህ ምላሽ አዎንታዊ መሆን አጋዥነት አለው። ለተቃውሞውም እንዲሁ። ይሁን እንጂ የመምህራንን ርቱዕነት ጠንክሮ አይጠቁምም።

33· "መምህሩ አሁን የሚጠቀሙበትን የማስተማር ስልትና ዘዴ አሻሽለው ባይቀርቡም ለአማርኛ ትምህርት ያለኝ ፍለጐት ከፍተኛ ነው።" ለሚለው አዎንታዊ ጥያቄ 24 ተማሪዎች ተቃውሟቸውን ሲገልፁ 89 ተማሪዎች ደግሞ ተስማምተውበታል። 7 ተማሪዎች ለመወሰን ሲቸገሩ 3·82 በሆነ አማካይ ነጥብ በከፍተኛ ደረጃ ያላቸውን አዎንታዊ አመለካከት አሳይተዋል። ይህ ምላሽ በተራ ቁጥሩ 31 ላይ ከተሰጠው ምላሽ ጋር የሚቀራረብ ነው። ቢሆንም ግን ለቋንቋው ትምህርት ጥሩ ግምት መኖሩን ቢያሳይም ከመምህሩ አሁንም የአቀራረብ ዘዴ መሻሻል የሚጠበቅ መሆኑን እግረ መንገዱን ይጠቁማል።

34· "የአማርኛ መምህራችን በክፍል ውስጥ የሚቆጡና የሚሳደቡ ስለሆኑ ለመቅረብም ሆነ ጥያቄ ለመጠየቅ እንፈራቸዋለን።" ለሚለው አሉታዊ ጥያቄ 29(20%) ተማሪዎች በሐሳቡ ሲስማሙ 86(74.2%) ተቃውመውታል። በተገኘው ውጤት መሠረት መምህራን ከተማሪዎቻቸው ጋር ግብቡና መልካም ቅርርብ እንደሚያደረጉ 3·78 በሆነ ከፍተኛ አማካይ ነጥብ አዎንታዊነቱ ተመዝግቧል።

35· "መምህራችን በክፍል ውስጥ ሁሉንም ተማሪዎች በዕኩልነት የሚያዩና በውጤት አሰጣጥም የማያዳሉ ናቸው።"

ጥያቄው መምህራን ከተማሪዎቻቸው ጋር ያላቸውን መፈቃቀድ የሚጠይቅ ሲሆን 77 ተማሪዎች ሐሳቡን ደግፈውታል። 42 ተማሪዎች ሲቃወሙ 5 ደግሞ ገለልተኛ ሆነዋል። አማካይ ነጥቡ 3·43 ነው። ይህ ነጥብ መምህራን የማያዳሉና ለተማሪዎቻቸው ጥሩ ግምገማ የሚያካሂዱ መሆኑን ያሳያል።

36· "የአማርኛ ቋንቋ መምህራችን በቋንቋው ትምህርት ላይ የተሟላ ዕውትና ችሎታ አላቸው።" ለዚህ አዎንታዊ ጥያቄ 16 ተማሪዎች ስምምነታቸውን ሲገልፁ 91 ተማሪዎች ደግሞ ተቃውመዋል። በመጨረሻም 1·79 አማካይ ነጥብ የተመዘገበበት መጠይቅ ሲሆን

ተማሪዎች በመምህራቸው ዕውቀትና ችሎታ ላይ አሉታዊ ግምት አላቸው። ይህ ውጤት ከተራ ቁጥር 26 ጋር በቀጥታ የሚገናኝና የመምህራንን የችሎታ ዝቅተኛነት የሚጠቁም ነው።

በዚህ ተላውጦ ላይ የተመዘገበው አጠቃላይ የአመለካከት አማካይ ውጤት 3·11 ነው። ይህ ውጤት ተማሪዎች በመምህራን ላይ ያላቸው አመለካከት አዎንታዊ ነው ሊያሰኝ ቢችልም በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ያመለክታል። ከአራቱም ትምህርት ቤቶች በ120 ተማሪዎች በዚህ ክፍለ መጠይቅ ላይ የተመዘገበው የ12 ጥያቄዎች ድምር 4882 ሲሆን ውጤቱ ለመቶ ሀያ መላሾችና ለአሥራ ሁለቱ ጥያቄዎች ሲካፈል 3·11 ያስገኛል።

መ · <u>የወላጆች፣ ባልንጀሮችና የማህበረሰቡ ተፅዕኖ</u>

በዚህ ተላውጦ ላይ የተመዘገበው የአመለካከት አጠቃላይና አማካይ ውጤት በእያንዳንዱ ጥያቄ ላይ መቶ ሀያዎቹ ተማሪዎች ያስመዘገቡት ውጤት በሚከተለው ሠንጠረዥ ላይ ተጠቃልሎ ሠፍሯል።

ሠንጠረዥ 5

ወላጆች፣ ባልንጀሮችና ማህበረሰቡ በሚያደርሱት ተፅዕኖ ላይ የተማሪዎች አመለካከት

| የመጠይቆች ተራ ቁጥር | ለምላሾች የሚሰጥ የብዜት ዋጋና የተማሪ ብዛት | | | | | | | | | | የአመለካከት ድምር ውጤት | አማካይ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 5 | | 4 | | 3 | | 2 | | 1 | | | |
| | የተማሪ ብዛት | % | የተማሪ ብዛት | % | የተማሪ ብዛት | % | የተማሪ ብዛት | % | የተማሪ ብዛት | % | | |
| 37 | 20 | 16.7 | 48 | 40 | 9 | 7.5 | 24 | 20 | 19 | 15.8 | 386 | 3.22 |
| 38 | 37 | 30.8 | 28 | 23.3 | 2 | 1.7 | 27 | 22.5 | 26 | 21.7 | 383 | 3.19 |
| 39 | 33 | 27. | 32 | 26.7 | 8 | 6.7 | 19 | 15.8 | 28 | 23.3 | 383 | 3.19 |
| 40 | 21 | 17.5 | 25 | 20.8 | 5 | 4.2 | 34 | 28.3 | 35 | 29.2 | 323 | 2.69 |
| 41 | 29 | 24.2 | 50 | 41.7 | 5 | 4.2 | 23 | 19.2 | 13 | 10.8 | 419 | 3.49 |
| 42 | 17 | 14.2 | 34 | 28.3 | 4 | 3.3 | 42 | 35 | 23 | 19.2 | 340 | 2.83 |
| 43 | 84 | 70 | 25 | 20.8 | - | - | 3 | 2.3 | 8 | 6.7 | 534 | 4.45 |
| 44 | 38 | 31.7 | 35 | 29.2 | 5 | 4.2 | 23 | 19.2 | 19 | 15.8 | 410 | 3.42 |
| 45 | 40 | 33.3 | 22 | 18.3 | 1 | 0.8 | 23 | 19.2 | 34 | 28.3 | 371 | 3.09 |
| 46 | 30 | 25 | 24 | 20 | 1 | 0.8 | 28 | 23.3 | 37 | 30.8 | 342 | 2.85 |
| 47 | 83 | 69.2 | 22 | 18.3 | - | - | 3 | 2.3 | 12 | 10 | 521 | 4.34 |
| 48 | 59 | 49.2 | 31 | 25.6 | 7 | 5.8 | 11 | 9.2 | 12 | 10 | 474 | 3.95 |
| ጠ · ድምር | 491 | | 376 | | 47 | | 260 | | 266 | | 4886 | 3.39 |

በዚህ ክፍልም እንደቀደምቶቹ ተላውጦዎች 12 ጥያቄዎች ቀርበዋል። መጠይቆቹ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ላይ ስለሚኖራቸው አመለካከት፣ ጓደኞቻቸው፣ ቤተሰባቸውና የአካባቢ ነዋሪዎች ሊያደርሱ ስለሚችሉት ተፅዕኖ ተማሪዎችን የሚጠይቅ ነው። ውጤቱን ቀጥሎ ከተራ ቁጥር 37-48 በተቀመጡት ጥያቄዎች መሣሪያነት እንመለከታለን።

37· "ጓደኞቼ የአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜን በጉጉት ይጠብቃሉ።" ለሚለው የመጀመሪያ ጥያቄ 68(56.7%) ተማሪዎች ስምምነት አሳይተው 43(35.8%) ደግሞ አሉታዊ መልስ ሰጥተውበታል። 9(7.5%) ደግሞ ለመወሰን ተቸግረዋል። በዚህ ጥየቄ ውጤት መሠረት አብላጫው ተማሪ የትምህርቱን ክፈለ ጊዜ በናፍቆት የሚጠብቁ መሆናቸውን 3·22 በሆነ ውጤት ድጋፋቸውን ሰጥተዋል።

38· "በአማርኛ ስናገር በማደርገው ስህተት በአማርኛ አፋቸውን የፈቱ የክፍል ጓደኞቼ ያፌዙብኛል።" ጥያቄውን 35፡8% ያህሉ ተማሪዎች ሲስማሙበት 56·7% ደግሞ ተቃውመውታል። አማካይ ነጥቡም 3·19 ሲሆን ዝቅተኛ አዎንታዊነት ተመዝግቦበታል። ደረጃው የጠነከረ ባይሆንም የውጤቱ አነስተኛነት በመጠነኛ ደረጃም ቢሆን ተፅዕኖ መኖሩን ይጠቁማል።

39· "ወላጆቼ ለአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰብ ባህልና ለቋንቋቸው ጥሩ አመለካከት አላቸው።" መጠይቁ በ65 ተማሪዎች ድጋፍ ሲያገኝ በ47 ተማሪዎች ተቃውሞ ተደርጎበታል። አማካይ ነጥቡ 3·19 መሆኑ የመረረ ጥላቻን ባያሳይም አማካይ የሆነ ውዴታ እንዳላቸው ያመለክታል። ቢሆንም ግን በጣም ዝቅተኛ ነው።

40· "በአማርኛ ክፍለ ጊዜ አንዳንድ ተማሪዎች መምህሩ ከመግባቱ በፊት ክፍሉን ትተው የሚወጡ አሉ።" ይህንን ሐሳብ 69 ተማሪዎች ሲቀበሉት 46 ተማሪዎች ተቃውመውታል። በተመዘገበው ውጤት መሠረት የአንዳንድ ተማሪዎች ከክፍል መውጣት በሌሎች ትምህርቱን በሚፈልጉት ላይ ተፅዕኖ ሊያደርስ መቻሉን መገንዘብ ይቻላል። አጠቃላይ አማካይ ውጤቱ 2·69 መምጣቱ ደግሞ የክፍል ጓደኞች የሚያሳድሩትን አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳያል።

41· "የአካባቢዩ ነዋሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ መልካም ግምት አላቸው።" ይህ መጠይቅ እንደ ተራ ቁጥር 39 ሁሉ አዎንታዊ ምላሽ ተሰጥቶበታል። ወላጆችም ይሁኑ የአካባቢው ነዋሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸው አመለካከት ቀና መሆን በተማሪው የመማር ፍላጐትና ያመለካከት ምሥረታ ላይ አዎንታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል። ለዚህ ጥያቄ 3·49 አዎንታዊ አማካይ ውጤት ተሰጥቶታል።

42· "ባልንጀሮቼ እንደሌላው ትምህርት ያህል ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት እምብዛም ትኩረት አይሰጡም።" ለጥያቄው የተሰጠው ምላሽ ከተራ ቁጥር 40 ጋር በቀጥታ የተዛመደና አሉታዊ ተፅዕኖውን አጉልቶ የሚያሳይ ነው። የተማሪው የክፍል ጓደኞች ክፍል ትተው የመውጣትና ለትምህርቱ ትኩረት መንፈግ ለሌሎች በፍላጐት ለሚማሩት እንቅፋት ሊሆኑ መቻላቸው አሌ አይባልም። በጥያቄው ላይ 65 ተማሪዎች ሲስማሙበት 51 ተቃውመውታል። በመጨረሻ ተጠቃልሎ 2·83 አማካይ ነጥብ ተሰጥቶታል።

43· "ቤተሰቦቼ አማርኛን መማር ከቦታ ቦታ ተዘዋውሮ ከብዙ ሰዎች ጋር ለመገናኘት ያስችላል ብለው ያምናሉ።"

አማርኛ በአገሪቷ ውስጥ ከሚገኙ ቋንቋዎች ሁሉ በስፋት የተሠራጨና በጋራ መግባቢያነት ሊያገለግል የቻለ ቋንቋ መሆኑን የተማሪው ቤተሰብ የተረዳው መሆኑን በ109(90.8%) መደገፉ ይጠቁማል። 11(9.2%) የሚሆኑት ብቻ አፍራሽ ግምታቸውን ሰንዝረዋል፡ በዚህ ጥናት ከቀረቡ መጠይቆች ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ የስምምነት ውጤት የተሰጠው ይህ መጠይቅ 4·45 አማካይ ነጥብ ተመዝግቦበታል። ስለዚህም አማርኛን መማር ከቦታ ቦታ ለመዘዋወርና ከተለያዩ የአገሪቱ ህዝቦች ጋር ተግባቦት ለመፍጠር ድል ድይ መሆኑንና የተማሪዎች ቤተሰቦች ተረድተው የሚደግፉት መሆኑን ያመለክታል።።

44· "የአካባቢዩ ነዋሪዎች የአማርኛን ቋንቋ መማር ለወደፊት ህይወቴ ጠቀሜታ አለው ብለው አይገምቱም።" ጥያቄው አሉታዊ ሲሆን 73 (60.8%) ተማሪዎች ተቃውሞ ሲያሳዩ 42 (35%) ግን ተስማምተውበታል። ከቁጥሩ እንደሚታየው ተቃዋሚ ተማሪ ብዛት ያለው ቢሆንም 3·42 ይማካይ አዎንታዊ ውጤት አሳይቷል። ስለዚህም አማርኛን መማር ለወደፊት ህይወት ጠቀሜታ እንደሚሰጥ ተማሪዎች አዎንታዊ ግምታቸውን ገልፀዋል።

ውጤቱ ከተራ ቁጥር 43 ውጤትና ሐሳብ ጋር የተዛመደ መሆኑ አስተያየቱን የበለጠ ያረጋግጠዋል።

45· "በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ምትክ የአፍ መፍቻ ቋንቋዬን እንድማር ቢደረግ ወላጆቼና የአካባቢዬ ነዋሪዎች ይደግፉታል።"

በተገኘው ውጤት መሠረት ሐሳቡን 62(51.7%) ተማሪዎች ሲቃወሙት 57(47.5%) ደግፈውታል። አጠቃላይ አማካይ ውጤቱም 3·09 ሲሆን የአካባቢው ነዋሪዎች ከራሳቸው ቋንቋ ጋር እንኳን ቢወዳደር ለቋንቋው አዎንታዊ ግምት እንዳላቸው በመጠኑ ይታያል። ይሁን እንጂ የመጠይቅ 7 ምላሽ ውጤት ያካክሰዋል።

46· "አማርኛ ለአማሮች እንጂ ለእኔ ያለው ጥቅም ዝቅተኛ ነው።" መጠይቁን 65 ተማሪዎች በስምምነት 54 ደግሞ በተቃውሞ መልሰውታል። አማካይ ነጥቡ 2·85 በመሆኑ ቋንቋው ለአማሮች እንጂ መጠይቁን ለሞሉ ተማሪዎች ያለው ጠቀሜታ ዝቅተኛ ነው የሚል ድምዳሜ ላይ ያደርሳል። ይሁን እንጂ ከላይ ከተሰጡት ምላሾች አንፃር ስንመለከተው ተማሪው ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ለዕለት ጉዳይ ማስፈፀሚያ በራሱ ቋንቋ የመጠቀም ዕድል ስላለው አማርኛ የሚሰጠው ጠቀሜታ ዝቅተኛ ሊሆን የችላል። ይህ ደግሞ የሚጠበቅና ሊሆን የሚገባው ጉዳይ ነው።

47· "አማርኛ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት መስጫ ቋንቋ መሆኑ ቀርቶ በተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ መሰጠቱን የአካባቢዬ ነዋሪዎች አብዛኛው አይፈልጉትም።"

መጠይቁን ብዛታቸው 105(87.5%) የሆን ተማሪዎች በሐሳቡ ላይ ስምምነታቸውን ሲገልፁ 15(12.5%) ተቃውመውታል። የመጨረሻው ውጤት 4·34 በሆነ አማካይ ነጥብ የአማርኛ ቋንቋ በአካባቢው በሚገኙ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የትምህርት መስጫ ቋንቋ ከመሆን መታገዱን የአካባቢው ማህበረሰብ የማይደግፈው መሆኑን በከፍተኛ ውጤት አረጋግጠዋል።

ይህ ውጤት በተራ ቁጥር 39፣ 41፣ 43፣ 44፣ 45 ከተሰጠው ምላሽ ጋር በእጅጉ የተቆራኘና ያካባቢው ህዝብና የተማሪው ወላጆች ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸው ግምት ደጋፊ መሆኑን ያመለክታል።

48· "በአማርኛ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ለእኔ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ከበሬታ ስለሌላቸው እኔም ለአማርኛ ከበሬታ የለኝም።"

በዚህ ጥያቄ ላይ 23 ተማሪዎች ሲስማሙ 90 ተማሪዎች ተቃውሟቸውን አሳይተዋል። ስለዚህም የአማርኛ አፈ ፈቶችም ሆኑ ሀዲይኛ ተናጋሪዎች ለሁለቱም ቋንቋዎች ጥሩ ግምትና ክብር ተሰጣጥተዋል። በዚህም መቻቻል ሳቢያ ሀዲይኛ ተናጋሪ ተማሪዎች ለአማርኛ ያላቸውን ጥሩ ግምት 3·95 በሆነ አዎንታዊ ውጤት ገልፀዋል።

በዚህ ተላውጠ በተጠኚ ተማሪዎች ላይ ወላጆችና የአካባቢው ህዝብ አዎንታዊ አመለካከት እንዲያድርባቸው ሲያግዙ የተማሪው ባልንጀሮችና የክፍል ጓደኞች ግን አሉታዊ ተፅዕኗቸው ጐልቶ ይታያል። በጥቅሉ ተማሪዎች በ12 መጠይቆች ታጅቦ ለተበደነው ተላውጠ 3·39 አዎንታዊ አመለካከት እንዳላቸው አስመዝግበው አጠቃል ለውታል።

4·1·2 <u>የተማሪዎች አመለካከት በፆታ</u>

ቀደም ባለው ክፍል ከተማሪዎች የተገኘው የተጠቃለለ የአመለካከት አማካይ ነጥብ አዎንታዊ እንደሆነ ተመልክተናል፡ ከዚሁ ጥቅል ውጤት ውስጥ የተማሪዎች አመለካከት በፆታ፣ በመኖሪያ ቦታና በየትምህርት ቤቱ ልዩነት መኖር አለመኖሩን በመቃኘት የተገኘውን አጠቃላይ ውጤት ከተለያዩ አቅጣጫዎች በመመርመር ማስረገጥ ጠቃሚነት አለው።

በዚሁ መሠረት በጥናቱ የታቀፉት ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋና ለትምህርቱ ያላቸውን አመለካከት በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለውን ልዩነት ለመመልከት ተሞክሯል። ውጤቱን ከመተንተናችን በፊት ግን ለትንተናው መንደርደሪያ ይሆን ዘንድ የሚከተለውን ሠንጠረዥ እናስተውል።

### ሠንጠረዥ 6

### የተማሪዎች አመለካከት በፆታ ልዩነት

| ተራ ቁጥር | ትምህርት ቤት | ሴቶች | | | ወንዶች | | | የአመለካከት ድምር ውጤት | አማካይ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የተማሪ ብዛት | ድምር | አማካይ | የተማሪ ብዛት | ድምር | አማካይ | | |
| 1 | ዋቸሞ | 11 | 1523 | 2.88 | 29 | 4481 | 3.21 | 6004 | 3.13 |
| 2 | የካቲት | 10 | 1471 | 3.06 | 20 | 2992 | 3.12 | 4463 | 3.10 |
| 3 | ሞርሲጦ | 8 | 1272 | 3.31 | 17 | 2625 | 3.22 | 3897 | 3.25 |
| 4 | ጊምቢቹ | 8 | 1412 | 3.68 | 17 | 2824 | 3.46 | 4236 | 3.53 |
| ጠቅላላ ድምር | | 37 | 5678 | 3.20 | 83 | 12922 | 3.24 | 18600 | 3.23 |

የሠንጠረዥ መረጃው የሚያመለክተው በየትምህርት ቤቱ መጠይቁን የሞሉ የወንድና ሴት ተማሪዎች ብዛትና በአርባ ስምንቱ ጥያቄዎች ላይ ያስመዘገቡትን አጠቃላይ የአመለካከት ውጤት ነው። በጥናቱ 37 ሴቶችና 83 ወንዶች ታቅፈዋል። ባስገኙት ውጤት መሠረት የዋቸሞ አጠቃላይና የየካቲት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሴት ተማሪዎች ከወንዶች ያነሰ አማካይ የአመለካከት ነጥብ አሳይተዋል። በትምህርት ቤት ደረጃ ደግሞ የዋቸሞ ሴት ተማሪዎች ለቋንቋውና ለትምህርቱ የበለጠ አሉታዊ አመለካከት አላቸው። የጊምቢቹና የሞርሲጦ ሴት ተማሪዎች ደግሞ በተቃራኒው ከወንዶች የተሻለ አዎንታዊ አመለካከት እንዳላቸው ሠንጠረዡ ያሳያል። ሁለቱ ትምህርት ቤቶች /ዋቸሞና የካቲት/ አማርኛ በሰፊው በሚነገርበት በሆሳዕና ከተማ የሚገኙ ሲሆን ጊምቢቹና ሞርሲጦ ደግሞ የገጠር ከተማዎች ናቸው። በጥቅሉ በሰፊው ከተማና በአካባቢው የሚኖሩ ሴት ተማሪዎች በወረዳ ከተማና አካባቢው ከሚኖሩ ሴቶች ያነሰ አመለካከት አላቸው ማለት ነው። ይሁን እንጂ በከተማና አካባቢው የሚኖሩ ወንዶች ለምን የተሻለ አመለካከት አሳደሩ? ለሚለው ጥያቄ ግን አጥጋቢ ምላሽ ለመስጠት በርዕሱ ላይ ጥናት ማካሄድ ያስፈልጋል።

ከዚሁ ጋር በማያያዝ የወንዶች ተማሪዎች አመለካከት ደግሞ የአራቱም ትምህርት ቤት ተማሪዎች /ወንዶች/ አዎንታዊ አመለካከት አላቸው። በመካከላቸው ያለውን ልዩነት

ስንመረምር ግን የየካቲት ትምህርት ቤት በጣም ዝቅተኛ አዎንታዊነት ሲያሳዩ /3·12/ የጊምቢቹ ተማሪዎች ደግሞ የተሻለ /3·46/ አማካይ ነጥብ አስመዝግበዋል።

በቀረቡት አራት ተላውጦዎች ላይ በአጠቃላይ ከተመዘገበው ውጤት እኳያ ሲታይ በወንዶችና በሴት ተማሪዎች መካከል የጐላ የአመለካከት ልዩነት አይታይም። ሴት ተማሪዎች ያስመዘገቡት ድምር አማካይ ነጥብ 3·20 ሲሆን የወንዶች ደግሞ 3·24 ያሳያል። ስለዚህ የተማሪዎች አመለካከት በፆታ ልዩነት ላይ የተራራቀ ውጤት አልተገኘበትም ለማለት ያስችላል።

4·1·3 <u>የተማሪዎች አመለካከት በመኖሪያ ቦታ</u>

መጠይቁን የሞሉ ተማሪዎች የገጠርና የከተማ ነዋሪዎች ናቸው። የከተማ ነዋሪዎች ትምህርት ቤቶቹ በሚገኙበት ከተማ ውስጥ የሚኖሩ ሲሆኑ የገጠር ነዋሪዎች ደግሞ ከከተማው ክልል ውጭ የሚኖሩና ትምህርት ቤቶቹ ወደሚገኙበት ከተማ ተመላልሰው የሚማሩ ናቸው። በሁለቱ መካከል የተመዘገበው የአመለካከት ውጤት በሚከተለው ሠንጠረዥ ላይ ሠፍሯል።

ሠንጠረዥ 7

አመለካከት በመኖሪያ ቦታ

| ተራ ቁጥር | ትምህርት ቤት | ከተማ | | | ገጠር | | | የአመለካከት ድምር | አማካይ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የተማሪ ብዛት | ድምር | አማካይ | የተማሪ ብዛት | ድምር | አማካይ | | |
| 1 | ቀቸሞ | 17 | 2662 | 3.26 | 23 | 3342 | 3.03 | 6004 | 3.13 |
| 2 | የካቲት | 13 | 1999 | 3.20 | 17 | 2464 | 3.02 | 4463 | 3.10 |
| 3 | ሞርሲጦ | - | - | - | 25 | 3897 | 3.25 | 3897 | 3.25 |
| 4 | ጊምቢቹ | 9 | 1551 | 3.59 | 16 | 2685 | 3.50 | 4236 | 3.53 |
| ጠቅላላ ድምር | | 39 | 6212 | 3.32 | 81 | 12388 | 3.19 | 18600 | 3.23 |

መረጃው እንደሚጠቁመው በመኖሪያ ቦታ የአመለካከት ልዩነት ላይ ከሞርሲጦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የከተማ ነዋሪ የሆኑ ሀዲይኛ ተናጋሪ ተማሪዎች አል ተገኙም።* ሁሉም ተማሪዎች የገጠር ነዋሪ ናቸው። የከተማ ነዋሪዎችን በተመለከተ በየትምህርት ቤቶቹ ተቀራራቢ ውጤት ቢታይም የጊምቢቹ ትምህርት ቤት ከፍተኛ አማካይ ነጥብ ሲያስቆጥር የካቲት ዝቅተኛውን ይይዛል። በጥቅሉ ግን በሁሉም ትምህርት ቤቶች የከተማ ነዋሪዎች አዎንታዊ አመለካከት አላቸው። በገጠር ነዋሪዎች በኩልም በየትምህርት ቤቶቹ የተሻለ ልዩነት የማ ታየ ከመሆኑም በላይ እንደከተሜዎቹ ሁሉ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አዎንታዊ ግምት አላቸው።

ቀደም ሲል በሴቶችና በወንዶች መካከል ሚዛን የሚያነሳ የአመለካከት ልዩነት እንዳልታየ ሁሉ በገጠርና በከተማ ነዋሪዎችም መካከል የሰፋ ልዩነት አልተገኘም። ቢሆንም ግን የከተማ ነዋሪዎች 3·32 በሆነ ውጤት 3·19 ካመጡ የገጠር ነዋሪዎች የተሻለ አመለካከት እንዳላቸው መረጃው ያመለክታል። ለዚህ መጠነኛ ልዩነት መነሻ ሊሆን የሚችል አስተያየት ለመስጠት ያህል፤ የከተማ ነዋሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አዘውትረው የመጠቀም ዕድላቸው የሰፋ ሲሆን የገጠር ነዋሪዎች ግን በትምህርት ቤት ውስጥ ሲማሩ ወይም ከአካባቢያቸው ርቀው ካልሄዱ በስተቀር በቋንቋው ብዙም አይጠቀሙም። ከቤተሰብና ከአካባቢው ነዋሪ ጋር የዕለት በዕለት መገልገያ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ነው። ስለዚህ በቋንቋው ላይ የሚያደርጉት የልምምድ መጠን እያነሰ በሄደ ቁጥር ምንም እንኳን ለአማርኛ አሉታዊ ግምት ባይኖራቸውም ከከተሜዎቹ ያነሰ ውጤት ለማስመዝገብ ምክንያት ይሆናል የሚል አስተየያት ሊያሰጥ ይችላል።

በአጠቃላይ ግን የከተማ ነዋሪዎችም ሆኑ የገጠሩ በአራቱ ተላውጦዎች ላይ ባስመዘገቡት ውጤት ለአማርኛ ቋንቋና ለትምህርቱ ያላቸው አመለካከት ዝቅተኛም ቢሆን አዎንታዊ ነው።

4·1·4 <u>የተማሪዎች አመለካከት በየትምህርት ቤቱ</u>

በተሞላው መጠይቅ ውጤት ላይ ከአራቱም ትምህርት ቤቶች ከተገኘው ነጥብ የአመለካከት ልዩነት ይታያል። ዝርዝሩ በሚከተለው ሠንጠረዥ ላይ ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 8

የተማሪዎች አመለካከት በየትምህርት ቤቱ

| ተራ ቁ. | ትምህርት ቤት | የተማሪ ብዛት | ድምር | አማካይ |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ዋቸሞ | 40 | 6004 | 3.13 |
| 2. | የካቲት | 30 | 4463 | 3.10 |
| 3. | ሞርሲጦ | 25 | 3897 | 3.25 |
| 4. | ጊምቢቹ | 25 | 4236 | 3.53 |
| | ጠቅላላ ድምር | 120 | 18600 | 3.23 |

ከሠንጠረዡ እንደሚነበበው ከጠቅላላ መጠይቆች በተገኘው ውጤት መሠረት ለአማርኛ ቋንቋና ለትምህርቱ በሁሉም ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎች አዎንታዊ አመለካከት አላቸው። የተገኘውን የአመለካከት ልዩነት በደረጃ ለማመልከት ያህል፣ የጊምቢቹ ትምህርት ቤት ከሁሉም የተሻለ አማካይ ውጤት /3·53/ ሲያሳይ፣ ሞርሲጦ ሁለተኛ /3·25/፣ ዋቸሞ ሦስተኛ /3·13/ ደረጃ ላይ ይገኛሉ። አዎንታዊ ሆኖ ግን ከሁሉም ዝቅተኛ የሆነው /3·10/ የየካቲት ትምህርት ቤት ነው። ቀደም ብለን በፆታም ይሁን በመኖሪያ ቦታ ባየናቸው ውጤቶች የየካቲት 25/67 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል። ለዚህ ውጤት መንስዔው ምናልባትም ትምህርት ቤቱ የ12ኛ ክፍልን በቅርብ ጊዜ የከፈተ በመሆኑ /ሦስት ዓመት/ በቂ የአማርኛ መምህራን ማጣት ወይም የውስጥ አደረጃጀት በበቂ ሁኔታ አለመሟላት አለበለዚያም ከቋንቋው መምህር ተፅዕኖ /በክፍል ምልከታው ውስጥ ቀርቧል/ የመጣ ሊሆን ይችላል። ቢሆንም ግን ውጤቱ አሉታዊነትን አያሳይም።

4·1·5 <u>አጠቃላይ የተማሪዎች አመለካከት ውጤት</u>

ከዚህ በላይ በዝርዝር በቀረበው መሠረት ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋና ለትምህርቱ፣ ለመማሪያ መፅሐፉ፣ ለመምህሩ ያላቸውን አመለካከት እንዲሁም የተማሪው ቤተሰብና ባል ንጀሮች ሊያደርሱ የሚችሉትን የአመለካከት ተፅዕኖ በአራቱ ተለውጦዎች ከፍሎ ለመመልከት ተችሏል። የተደረሰበትን ውጤት በፆታ፣ በመኖሪያ ቦታና በየትምህርት ቤቱ ያለው ልዩነትም ተቃኝቷል። በመጨረሻ የዚህ ሁሉ ድምር ውጤት ተማሪዎች ለአማርኛ

ቋንቋኛለትምህርቱ ያላቸውን አመለካከት ለመረዳት በቅድሚያ የሚከተለውን ሠንጠረዥ የመረጃ ምንጭ አድርገን ለማብራራት እንሞክር።

ሠንጠረዥ 9

አጠቃላይ የተማሪዎች አመለካከት

| ትምህርት ቤት | የተማሪ ብዛት | ተላውጦዎች | | | | | | | | የአመለካከት ድምር ውጤት | አማካይ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1 | | 2 | | 3 | | 4 | | | |
| | | ድምር | አማካይ | ድምር | አማካይ | ድምር | አማካይ | ድምር | አማካይ | | |
| ዋቾሞ | 40 | 1614 | 3.36 | 1383 | 2.88 | 1362 | 2.83 | 1645 | 3.43 | 6004 | 3.13 |
| የካቲት | 30 | 1153 | 3.20 | 1049 | 2.91 | 1093 | 3.04 | 1168 | 3.24 | 4463 | 3.10 |
| ሞርሲጦ | 25 | 1015 | 3.32 | 956 | 3.20 | 929 | 3.19 | 997 | 3.38 | 3897 | 3.25 |
| ጊምቢቹ | 25 | 1141 | 3.8 | 921 | 3.07 | 1086 | 3.62 | 1076 | 3.59 | 4236 | 3.53 |
| ጠ·ድምር | 120 | 4923 | | 4309 | | 4482 | | 4886 | | 18600 | 3.23 |

ተላውጦዎች
1· ለቋንቋውና ለትምህርቱ
2· ለመፅሐፉ
3· ለመምህሩ
4· ወላጆች፣ ባልንጀሮችና ማህበረሰቡ

ከዚህ የተጠቃለለ ውጤት ላይ መድረስ የተቻለው እያንዳንዱ ተማሪ ለአርባ ስምንቱም ጥያቄዎች የሰጠው ድምር ውጤትና በእያንዳንዱ ጥያቄ ላይ መቶ ሀያዎቹ ተማሪዎች ያስመዘገቡትን የምላሽ ውጤት በዝርዝር በመመዝገብ በተደረገ ስሌት ነው። ይህ ሠንጠረዥ የሚያሳየውም በተላውጦች ውስጥ ለተካተቱት ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከየትምህርት ቤቱ የተመረጡት ተማሪዎች ያስመዘገቡትን የአመለካከት ውጤት ነው። /ለዝርዝር መረጃ አባሪ '1' ን ይመለከቷል/

ውጤቱ በሀዲያ ዞን በሚገኙ አራት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሀዲይኛ የሆነ የአሥራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች በዚህ ጥናት መሠረት ለአማርኛ ቋንቋና ለትምህርቱ አዎንታዊ አመለካከት አላቸው። የተመዘገበው የአጠቃላይ ድምር አማካይ ነጥብ 3·23 በመሆኑ ተማሪዎች ቀና አመለካከት እንዳላቸው ሊጠቁም ችሏል። ይህ ውጤት ታሪኩ ፋንታዬ /1988፣ 74/ 91% የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው አማርኛ

እንደሆኑት የአዲስ አበባ ተማሪዎች በከፍተኛ ደረጃ /ኳፊተ/ ባይሆንም አማርኛ በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎችም አዎንታዊ አመለካከት እንዳላቸው አሳይቷል።

ተማሪዎቹ ለቋንቋውና ለትምህርቱ ያላቸውን አመለካከት ለመለካት በጥቅም ላይ ከዋሉ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች አንዱ ይህ የፅሑፍ መጠይቅ ነው። ከላይ የቀረበው ውጤት የተገኘውም በዚሁ መሣሪያ አማካይነት ነው። ለተገኘው ውጤት እርግጠኝነት በሥራ ላይ የዋለው መሣሪያ በእርግጥም አመለካከትን ለመለካት የሚያስተማምን ለመሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል። ቀደም ብሎ በክፍል 3 እንደተጠቆመው መሣሪያው በባለሙያዎች ገፃዊ ተገቢነቱ /face validity/ ተገምግሟል። በተጨማሪም በቅድመ ጥናት /pilot study/ ተሞክሮ አስተማማኝ መሆኑ ተረጋግጦ በዚያው ላይ ጥቂት ማሻሻያና እርምት ተደርጐበት የዋናውን ጥናት ለማካሄድም መጠቀሚያ ሆኗል።

የመጠይቁን አስተማማኝነት እንደገና አሁን ከተደረሰበት ውጤት በመነሳት የኩዶር ሪቻርድስን የመጠይቅ አስተማማኝነት መፈተኛ ቀመር "21" ን በመጠቀም ሲሰላ የሚከተለውን ውጤት ያስገኛል።

ቀመር $$\frac{N}{N-1}\left[1-\frac{X(N-X)}{N(SX)^2}\right]$$ /ሜህረንስና ሌህማን 1991፣ 256/

የሐሳብ ወካይ ምልክቶች

N = የጥያቄዎች ብዛት /48 x 5/

$\overline{X}$ = አማካይ /155.1/

SX = መደበኛ ልይይት /18.478/

በዚህ መሠረት $$\frac{240}{239}\left[1-\frac{155.1\,(240-155.1)}{240\,(18.478)^2}\right]$$

$$=\frac{240}{239}\left[1-\frac{155.1\,(84.9)}{240\,(341.435)}\right]$$

$$=\frac{240}{239}\left[1-\frac{13167.99}{81944.411}\right]$$

$$= \frac{240}{239} \quad 1 - 0.160694$$

$$= 1.0042\ (0.8393059)$$

$$= 0.84282$$

$$= 0.84$$

ይህ ውጤት የቀረበው መጠይቅ 0·84 የሆነ ከፍተኛ የአስተማማኝነት ብቃት እንዳለው ያሳያል። የመማሪያው አስተማማኝ መሆን የተገኘውን የመጨረሻ የተማሪዎች አመለካከት ወጤትም የተረጋገጠ ያደርገዋል።

ከዚህ በተደራቢ በቀረቡት ተላውጦዎች መካከልና በመጨረሻ በተገኘው ውጤት መካከል ያለውን ጥምረትና ተደጋጋፊነት ወይም አንዱ ከአንዱ ጋር ያለውን የእርስ በርስ ተገላላጭነት ለማየት ሁሉንም በተዛምዶ ስልት ቀመር /correlation/ በማስላት ውጤቱን ቀጥሎ በተቀመጠው የተዛምዶ ሜትሪክስ /correlational matrix / ሠንጠረዥ ውስጥ እንመለከታለን።

ሠንጠረዥ 10

የተለውጦዎች የእርስ በርስ ተዛምዶ ሜትሪክስ

| ተለውጦዎች | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | - | | | | |
| 2 | .261* | - | | | |
| 3 | .332* | .212* | - | | |
| 4 | .377* | .145 | .152 | - | |
| 5 | .735* | .585* | .657* | .630* | - |

*ከግምት የሚገባ ተዛምዶ ያላቸውና በ ·05 ደረጃ የተረጋገጠላቸው ነጥቦች

*የተዛምዶ ውጤቶቹ በሦስት ዴሲማል ቁጥሮች የተቀመጡት እጥኚው በተጠቀመበት የጊልፎርድ /1965፣ 581/ የተዛምዶ ኮአፊሸንት ሠንጠረዥ መሠረት እንጂ ወደ ሁለት ዴሲማሎች ሊጠጋጋ ይችላል።

መግለጫ 1· ተለውጦዎች

1· ተማሪዎች ለቋንቋውና ለትምህርቱ ያላቸው አመለካከት

2· ተማሪዎች ለመማሪያ መፅሐፉ ያላቸው አመለካከት

3· ተማሪዎች ለመምህሩ ያላቸው አመለካከት

4· የወላጆች ፤ ባልንጀሮች ማህበረሰቡ ተፅዕኖ

5· አጠቃላይ የአመለካከት ውጤት

2· በየሳጥኑ ውስጥ የተቀመጡት የተለውጦዎች ቁርኝት ውጤት የተሰላው በሚከተለው የፒየርሰን የተዛምዶ ቀመር ስልት መሠረት ነው። /ጊልፎርድ 1965፡ 97፤ ክዎል 1988፡ 240/

$$r = \frac{N\Sigma xy - (\Sigma x)(\Sigma y)}{\sqrt{N\Sigma x^2 - (\Sigma x)^2}\sqrt{N\Sigma xy^2 - (\Sigma y)^2}}$$

ሁለት ተላውጦዎች ያላቸው ተዛምዶ በዚህ ቀመር መሠረት ከተሠራ በኋላ የተገኘው ውጤት በሚትሪክስ ሳጥን ውስጥ በየተላውጦዎቹ ትይዩ ተቀምጧል። የተገኘው ውጤት የሚያሳየው ተዛምዶ ጠቃሚ ወይም ከግምት የማይገባ መሆን አለመሆኑን በማናፃፀሪያነት ከተቀመጠው የ 'ቲ' ዋጋ መለያ /T-value/ ሠንጠረዥ ላይ በ·05 ደረጃ ላይ ለማረጋገጥ የተዛምዶ ውጤት በሚከተለው የ 'ቲ' ዋጋ /t-critical value/ ማረጋገጫ ስልት ተሰልቷል።

ቀመር /ጊልፎርድ 1965፡163/

$$t_o = \frac{r\sqrt{n-2}}{\sqrt{1-r^2}}$$

2·1 የሒሳብ ወካይ ምልክቶች

r = ተዛምዶ /correlation/

N = የተጠኝዎች ብዛት።/Total number of the sample/

$\Sigma x$ = በ "x" የተያዘው ተለውጦ ድምር ውጤት /summation of x /

$\Sigma y$ = በ "y" የተያዘው ተለውጦ ድምር ውጤት /summation of y /

$\Sigma xy$ = የ "x" እና "y" ድምር ብዜት /summation of product of x & y /

$t_o$ = ተሰልቶ የተገኘ የ "ቲ" ዋጋ /t observed value/

በነዚህ የማስሊያና የማረጋገጫ ቀመሮች መሠረት ተሰልቶ በተዛምዶ ሜትሪክስ ሳጥኑ ውስጥ የተቀመጠው ውጤት ለተማሪዎች የቀረቡት የመጠይቅ ተለውጦዎች እርስ በርሳቸው ያላቸውን ተደጋጋፊነትና አንዱ እንደኛውን ምን ያህል ሊገልፀው ወይም ተፅዕኖ ሊያሳርፍበት መቻል አለመቻሉን ያሳያል። ከዚሁ ጋርም ከቀረቡት ተለውጦዎች ውስጥ ለተደረሰበት የአመለካከት ውጤት በፍተኛ ደረጃ አስተዋፅዖ ያደረገውንና ተፅዕኖ ያሳረፈውን ተላውጭ ይጠቁማል። ውጤቱን በየተላውጦዎቹ ፊት ለፊት የተቀመጡ ቁጥሮችን የሳጥኑን አቆልቋይና ወርዳዊ መስመሮች በመከተል ማየት ይቻላል።

የቀረቡት አርባ ስምንት የተማሪ መጠይቆች 0·84 ውጤት በማሳየት መዛሪያነታቸው አስተማማኝ እንደሆነ ቀደም ብሎ ተጠቁሟል። በዚህም ስሌት ተላውጦ ሁለት እና፣ ተላውጦ ሦስት ከአራት ጋር ያላቸው ጥምረት ዝቅተኛ ከመሆኑ በስተቀር ሌሎቹ ተላውጦዎች ከግምት ሊገባ የሚችል የእርስ በርስ ተዛምዶ /significant correlation/ እንዳላቸው በየፈርጃቸው በሳጥኑ ውስጥ የተመዘገበው ውጤት ያሳያል። ውጤቱ በ 'ቲ' ዋጋ መፈለጊያው ማንፀሪያ ዝርዝር ላይ በ ·05 ደረጃ ከተቀመጠው ማናፀሪያ "ቲ" ዋጋ 1·979 የበለጠ በመሆኑ ጥሩ ጥምረት ያለው እንደሆነ ሜትሪክሱ ያረጋግጣል። ውጤቱን በ'ቲ'ጋ ዋጋ ማረጋገጫ ቀመር በማስላት ማረጋገጥ ይቻላል።

ይሁን እንጂ በዚህ ጥምረት ውስጥ ምንም እንኳን እርስ በርሳቸው ያላቸው ጥምረት ከሚፈለገው ማናፀሪያ የበለጠ ቢሆንም የደረጃ ልዩነት ግን ይታያል። ከነዚህ ውስጥ ተላውጦ አንድና አምስት በከፍተኛ ደረጃ ሲጣመሩ /·734/ አንድና ሁለት ግን ጥምረታቸው አነስተኛ /·261/ ሆኖ ይታያል። አንድ ከአራትና ከሦስት ጋር ያለው ዝምድና ደግሞ ከሁለት የተሻለ ሆኖ ተገኝቷል።

በሌላ በኩል ደግሞ ተላውጦ ሁለት ከአምስት ጋር በከፍተኛ ደረጃ /·585/ ተጣምሮ ሲያሳይ ከአራት ጋር ያለው /·145/ ዝቅተኛ ነው። ተላውጦ ሦስት ደግሞ ከአምስት ጋር፣ ተላውጦ አራትም ከአምስት ጋር ·657 እና ·630 በሆነ ተከታታይ ውጤት ያላቸው ከፍተኛ ተጣምሮ ይታያል።

ተላውጦ ሁለትና ሦስት በአመዛኙ ከሌሎች ተላውጦዎች ጋር ያላቸው ጥምረት ከ "ቲ" ዋጋ /T-value/ አንሶ ባይታይም ከአራት ጋር ግን አነስተኛ መሆኑን ውጤቱ ያሳያል። የተማሪዎችን አመለከካት በተንተንበት ክፍል በመማሪያ መፅሐፉ /ተላውጦ ሁለት/ ላይ ተማሪዎች አሉታዊ አመለካከታቸውን ሲያንፀባርቁ በመምህሩ /ተላውጦ ሦስት/ ግን አሉታዊ ባይባልም ከሌሎች ተላውጦዎች ይልቅ ያላቸውን ዝቅተኛ አዎንታዊ አመለካከት ያስቀመጡባቸው ናቸው። ይህ ስሌትም በተገኘው የእርስ በርስ ተዛምዶ ውጤት እነዚህ ሁለት ተላውጦዎች በመጠይቁ ውስጣዊ ቅንብር ደረጃ ከሌሎች ተላውጦዎች ጋር ያላቸውን የአንድምታ ሐሳብ በውል ቢያሳዩም በተማሪው የአመለካከት ምሥረታ ላይ ተፅዕኖ ያደረጉ መሆኑ እንዲታይ አድርጓል። የተማሪው ወላጆች ባልንጀሮችና አጠቃላይ ማህበረሰቡ ግን ተማሪው ለቋንቋውና ለትምህርቱ አዎንታዊ አመለካከት እንዲቀርፅ ከፍተኛ እገዛ ያደረጉ መሆኑን የተላውጦው ከፍተኛ የጥምረት ውጤት ያሳያል። በጥቅሉ ግን ሁሉም ተላውጦዎች ለአጠቃላዩ የአመለካከት ውጤት አጋዥ ናቸው።

ከዚህ በመነሳት ለተማሪዎች የቀረቡት መጠይቆች አስተማማኝነትና ተላውጦዎቹም እርስ በርስ የተደጋገፉ መሆናቸውን የተሠሩት የአስተማማኝነትና የተዛምዶ ስሌት ውጤቶች ያረጋግጣሉ። ስለዚህም መጥይቆቹ ጥሩ የመረጃ መሠብሰቢያ መሣሪያዎች ለመሆናቸው እምነት አሳድሯል።

## 4·2 ከመምህራን መጠይቅ የተገኘ ምላሽ

ቀደም ብሎ በክፍል 3·2 እንደተጠቆመው በሊከርት አፃፃፍ ስልት የተዘጋጀ በሦስት ክፍሎች የተቦደነና ሣሰት ክፍት ጥያቄዎችን የያዘ መጠይቅ ለስድስት መምህራን ተሠራጭቶ ምላሽ ተሰጥቶበታል።

መጠይቁ መምህራን ለተማሪዎቻቸው፣ ለመፅሐፉና ለሙያቸው ያላቸውን አመለካከት ለመመርመር የተዘጋጀ ነው። እያንዳንዳቸው አሥራ ሁለት ጥያቄዎች በያዙ በነዚሁ ሦስት ክፍሎች ከመምህራን የተገኘው ምላሽ በተጠቃለለ መልክ ይቀርባል። የመምህራን መጠይቅ ለጥናቱ ድጋፍ ሰጭ እንጂ ዋንኛ ማዕከላዊ ጥያቄ ባለመሆኑ

በየምድቦቹ የተሰጠውን ውጤትና ለክፍት ጥያቄዎች የተሰጠውን ምላሽ በዝርዝር ሳይሆን በአጭሩ ጠቅልለን እንመለከታለን። መጠይቆቹ አባሪ '3' ላይ ይገኛሉ።

የመምህራን መጠይቅ በክፍል አንድና ሁለት የተለየ ሲሆን ክፍል አንድ፣ ስለመምህራን ሁኔታ አጠቃላይ መረጃ የሚሰጥ ነው። በዚህ ክፍል የመምህራንን ፆታ፣ ዕድሜ፣ የሰለጠኑበትን የትምህርት ተቋም፣ ዋንኛና ተከታይ የትምህርት ዓይነት፣ የአገል ግሎት ዘመንና የአፍ መፍቻ ቋንቋ በተደራቢም ብሔረሰብ ተጠይቆበታል። ውጤቱ በፆታ አንድ ሴት፣ አምስት ወንዶች፣ ዕድሜ ከ24-38፣ የትምህርት ተቋም አራቱ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ሁለቱ ኮተቤ መምህራን ኮሌጅ፣ ዋንኛ ትምህርት አማርኛ የአፍ መፍቻ ቋንቋ አምስቱ አማርኛ አንድ ከምባትኛ፣ የአገልግሎት ዘመን ከ1-18 ዓመት ተመዝግቧል። ክፍል ሁለት፣ ሦስት ክፍል ያለው የአመለካከት ጥያቄ ሲሆን ቀጥሎ በየክፍሉ ይቀርባል።

## 4·2·1 <u>መምህራን ለተማሪዎቻቸው ያላቸው አመለካከት</u>

በዚህ ክፍል አሉታዊና አዎንታዊ ስሜት የሚያንፀባርቁ አሥራ ሁለት ጥያቄዎች የቀረቡ ሲሆን በውስጣቸው፣ የተማሪዎችን የመማር ፍላጐት፣ ስለፈተና ውጤታቸው፣ ስለክፍል ውስጥ እንቅስቃሴያቸው፣ በቋንቋውና በትምህርቱ ላይ ስላላቸውን አመለካከት፣ ስለቋንቋ ክኂሎታቸው፣ በአመለካከታቸው ላይ ተፅዕኖ ስለሚያደርጉባቸው ጉዳዮችና ስለመፍትሔያቸው፣ … ወዘተ አስመልክቶ መምህራን ለተማሪዎቻቸው ያላቸውን አመለካከት የሚጠይቁ ናቸው። የዚህ ክፍል ከጥያቄ 1-12 የምላሽ አጠቃላይ ውጤት በሚከተለው ሠንጠረዥ ላይ ተቀምጧል።

ሠንጠረዥ 11

የመምህራን አመለካከት በተማሪዎች ላይ

| ተራ ቁጥር | ለመልሶች የተሰጠ የብዜት ዋጋና የመምህራን ብዛት | | | | | የአመለካከት ድምር ውጤት | አማካይ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 5 የመ/ ብዛት | 4 የመ/ ብዛት | 3 የመ/ ብዛት | 2 የመ/ ብዛት | 1 የመ/ ብዛት | | |
| 1 | 2 | 4 | - | - | - | 26 | 4.33 |
| 2 | 1 | 5 | - | - | - | 25 | 4.17 |
| 3 | 2 | 3 | - | - | 1 | 23 | 3.83 |
| 4 | - | 2 | - | 2 | 2 | 14 | 2.33 |
| 5 | - | 2 | - | 4 | - | 12 | 2.00 |
| 6 | - | 4 | - | - | 2 | 18 | 3.00 |
| 7 | - | 1 | - | 4 | 1 | 13 | 2.17 |
| 8 | - | - | - | 5 | 1 | 11 | 1.83 |
| 9 | - | 2 | - | - | 4 | 12 | 2.00 |
| 10 | - | - | - | 4 | 2 | 10 | 1.67 |
| 11 | - | - | - | 3 | 3 | 9 | 1.50 |
| 12 | - | - | - | 5 | 1 | 11 | 1.83 |
| ጠ·ድምር | 5 | 23 | - | 23 | 21 | 184 | 2.56 |

ከሠንጠረዡ እንደሚታየው መምህራን ስለተማሪዎቻቸው የመማር ፍላጐትና ጥረት እንዲሁም ለቋንቋውና ለትምህርቱ ስላላቸው አሉታዊ አመለካከት በአሥራ ሁለቱ ጥያቄዎች ላይ ያስመዘገቡት አጠቃላይ አማካይ 2·56 ነጥብ ያሳያል። ከቀረቡት አሥራ ሁለት ጥያቄዎች ውስጥ በሦስቱ ላይ ብቻ /1, 2, 3/ አዎንታዊ ምላሽ ሲገኝ የተቀሩት ስምንት ጥያቄዎች አሉታዊ መልስ ተሰጥቶባቸዋል። አንዱ ገለልተኛ አመለካከት /3·00/ ይታይበታል። የውጤት አወሳሰዱ እንደተማሪዎች መጠይቅ ሁሉ የተገኘው አማካይ ነጥብ ከሦስት በላይ ከሆነ አዎንታዊ፣ ከሦስት በታች ከሆነ አሉታዊ፣ ሦስት ከሆነ ደግሞ ገለል ተኛ ይሆናል።

መምህራን ተማሪዎቻቸው በፈተና ውጤታቸው አብዛኞቹ ጥሩ ውጤት እንደሚያገኙና ትምህርቱንም የሚከታተሉ እንደሆኑ በሦስቱ አዎንታዊ ምላሽ በተሰጠባቸው ጥያቄዎች ላይ አረጋግጠዋል። በአንፃሩ ደግሞ ተማሪዎች እንደሌሎቹ ትምህርቶች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ትኩረት እንደማይሰጡ፤ በቋንቋው የመናገርና የመፃፍ ችግር እንዳለባቸው፤ የሚሰጧቸውን የቤትና የክፍል ሥራዎች ቁጥጥርና ግፊት ካልተደረገባቸው በስተቀር ለመሥራት ፍላጎት እንደሌላቸው፤ ቋንቋውን በመማር ፍላጎታቸው ላይ ተፅዕኖ የሚያደርሱባቸው የተለያዩ ምክንያቶች እንዳሉና በዚህም ሳቢያ ለትምህርቱ አሉታዊ አመለካከት እንዳዳበሩ አመልክተዋል። /ዝርዝር ጥያቄዎቹ አባሪ "3" ውስጥ ይገኛሉ/።

ይሁን እንጂ አዎንታዊ ምላሽ በተሰጣቸው ጥያቄዎች ላይ ተማሪዎች የእንግሊዝኛ ቋንቋን ከመማር ጋር የሚመጣጠን አማርኛን የመማር ፍላት አላቸው፤ በተማሪው ወላጆች፤ ባልንጀሮችና በአካባቢው ነዋሪዎች ተማሪው በቋንቋው ትምህርት ላይ ጥላቻ እንዲያሳድር የጎላ ጫና አይደረግበትም … ወዘተ የሚል ምላሽ ተገኝቷል። በሌላ በኩል ደግሞ ፍላጎት እንደሌላቸውና የአካባቢ ተፅዕኖ እንደሚያርፍባቸው ተጠቁሞ አሉታዊ አመለካከት እንዳሳደሩ ተገልጿል። ሐሳቡ የተቃረነ ነው። ፍላጎት ያለው ተማሪ ለመሥራት ፍቃደኛ ነው። አጉል አመለካከት የቀረፀ ተማሪ ደግሞ የትምህርት ክፍለ ጊዜውን ትቶ የመውጣት አዝማሚያ ያሳያል፤ በፈተና ውጤቱም ደካማ ይሆናል። ስለዚህ የተሰጡት አዎንታዊ ምላሾች በአሉታዊዎቹ ይፈርሳሉ። በጥቅሉ ግን ውጤቱ መምህራን በተማሪዎቻቸው ላይ ያላቸውን አሉታዊ ግምት አጉልቶ ያሳያል።

ለተማሪው አሉታዊ ግምት ያለው መምህር ተማሪዎችን አነቃቅቶ፤ በሚደከሙበት የትምህርት ዘርፍ ላይ እገዛ አድርጎ ከተፈለገው ውጤት ላይ ማድረስ አይችልም። ሥራውም በብልሃት የማስተማር ግዴታን መወጣት ሳይሆን የእንጀራ መብሊያ ያህል ተቆጥሮ የተሰላቸ እንደሚሆን ይጠበቃል። በተቃራኒው ግን ከተማሪዎች መጠይቅ ምላሽ ተማሪዎች ለመምህሮቻቸው አዎንታዊ አመለካከት አላቸው። ተማሪው ቋንቋውንና መምህሩን ሲወድ መምህሩ አፀፋውን እንኳን ለመመለስ አልቻለም ማለት ነው።

በነዚሁ ጥያቄዎች ላይ የተመሠረቱ /በተራ ቁጥር 11 እና 12/ ሁለት ክፍት ጥያቄዎች ቀርበው መምህራን ሰፋ ያለ አስተያየት ሰጥተውባቸዋል። ጥያቄዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

ሀ· "ለ11ኛ ጥያቄ በተማሪው የመማር ፍላጐት ላይ ተፅዕኖ ያደርሳሉ የሚሏቸውን ጉዳዮች በነጥብ ያስቀምጧቸው።" በሚለው ጥያቄ ሥር ስድስቱም መምህራን በርካታ ነጥቦችን አስቀምጠዋል። ከነዚህ ነጥቦች ውስጥ ሁሉም በጋራ የጠቀሷቸውና ጐላ ብለው የታዩት የሚከተሉት ናቸው።

- የአካበቢው ቋንቋ የሥራና የአንደኛ ደረጃ ትምህርት መስጫ ቋንቋ በመሆኑ ከትምህርት ቤት ውጭ በቋንቋው የመጠቀም ሁኔታ ዝቅ እያለ መምጣት፤
- በአካባቢው አማርኛ "የነፍጠኛ ቋንቋ" ነው የሚል ውግዘት ስለሚሰነዘርበት በቋንቋው በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ከመጠቀም መታቀብ፤
- በሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና አማርኛ ኮምፕልሰሪ አለመሆን፤
- በሃይማኖታዊ ምክንያቶች የግጥምና የልቦለድ ፅሑፎችን ማንበብ እንደዓለማዊነት ተደርጐ መቆጠር በቋንቋው የማንበብና የመፃፍ ክሂላት ላይ ተፅዕኖ ማድረስ፤
- በየክፍሉ የተማሪ ብዛት የተንሳ ተማሪዎችን ለመርዳትና በቋንቋው የተለያዩ ክሂላት ላይ ለማለማመድ መቸገር …ወዘተ/።

በነዚህና በሌሎች ምክንያቶች ሳቢያ ፍላጐታቸውን አነቃቅቶ ተሳታፊ ለማድረግ እንቅፋት የሆኑ ነጥቦች መሆናቸውን በጋራ ጠቅሰዋል። ስለዚህም እነዚህና ሌሎች ጉዳዮች ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋና ለትምህርቱ የተሻለ አመለካከት እንዳይኖራቸው ሥነልቡናዊ ጫና ይደርስባቸዋል በማለት ነጥቦቹን ጠቁመዋል።

ለ· "ለጥያቄ 12፤ የተማሪዎችን አመለካከት ወደ አዎንታዊነት ለመለወጥ ይረዳሉ የሚሏቸውን የመፍትሔ ሐሳቦች በነጥብ ያስፍሯቸው።" ለሚለው ጥያቄም ከተሰጡ በርካታ የመፍትሔ ሐሳቦች ውስጥ፤

- የአማርኛ ቋንቋን "የአማራ" ቋንቋ ብቻ አድርጐ ከመቁጠር ይልቅ የሀገሪቱ ብሔራዊ ቋንቋ እንዲሆን የመንግሥት ዕውቅና ቢያገኝ፤

- በሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና አማርኛ የጋራ መግባቢያ ቋንቋ በመሆኑ እንደበፊቱ ከምፐልሰሪ ትምህርት አድርጐ መቀበል ቢቻል፣
- በመማሪያው መፅሐፍ ላይ የቀረቡ መልመጃዎች ቢቻል አማርኛ የአፍ መፍቻና የሁለተኛ ቋንቋቸው የሆኑ ተማሪዎች ሊለማመዱባቸው እንዲችሉ ከተማሪው ማንነት ጋር ተገናዝበው ቢወጡ፣
- የትምህርት አቀራረቡ ከንድፈ ሐሳብ ይልቅ ተማሪው በተግባር ሊያከናውናቸው በሚችሉ ይዘቶች ላይ ቢያተኩርና የተማሪውን ስሜት በሚስብ ስልት ቢቀርብ፣
- ቋንቋው በየአካባቢው የሚሰጠውን የአገልግሎት ሁኔታ በማጥናት ትምህርቱ ከአካባቢው ጋር ተጣጥሞ እንዲቀርብ የሚችልበት የትምህርት ይዘት ተጠንቶና ተመርጦ በመፅሐፉ ቢቀርብ፣
- የመማሪያ መፅሐፉ አማርኛ አፍ መፍቻቸውና ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆነ ተማሪዎችን ለይቶ ማስተማር በሚቻልበት ሁኔታ ቢዘጋጅ።

የሚሉ ይገኙባቸዋል።

በሁለቱ ክፍት ጥያቄዎች ላይ ለአሉታዊ አመለካከት መንስዔ የሆኑ ነጥቦችና የመፍትሔ ሐሳቦች ቀርበዋል። ከመንስዔው ውስጥ የአካባቢው ቋንቋ የሥራና የትምህርት መስጫ ቋንቋ መሆን የአማርኛን ትምህርት በመማር ላይ የሚያደርሰው ተፅዕኖ ጠንካራ ሆኖ ቋንቋው እንዲጠላ የማድረግ ኃይሉ ከግምት የሚገባ ሊሆን አይችልም። ይልቁኑ መምህራን ተማሪዎቻቸው በትምህርቱ ክንውንና ልምምድ ላይ የነቃ ተሳትፎ እንዲያሳዩ የተለያዩና ከተማሪዎች ሁኔታ ጋር ሊጣጣሙ የሚችሉ የማስተማር ዘዴዎችና ከአካባቢው ሁኔታ ጋር የሚቀናጁ የትምህርት ይዘቶችን በመምረጥ ለማስተማር ጥረት ቢያደርጉ እስ የተባለውን አሉታዊ ስሜት ለውጦ ተማሪዎችን በፍላጐት ወደ ትምህርት ክንውኑ ማስገባት አይሳናቸውም። አማርኛ የጋራ መግባቢያ እንጂ 'የነፍጠኛ' ቋንቋ አለመሆኑንም ቋንቋው ከሚሰጠው ጠቀሜታ አንፃር በተለያዩ አጋጣሚዎች በመጠቀም ተማሪውን አስገንዝቦ አመለካከቱን መለወጥ ባይቀልም ይቻላል። ከዚሁ ጋር ግን ተማሪውም ሆነ ማህበረሰቡ ለአማርኛ ቋንቋ ጥላቻ የሌለው መሆኑን ቀደም ካሉት መልሶች በማገናዘብ አስተያየቱ ደርዝ ያለው መሆን አለመሆኑን መመዘን ይቻላል።

የአማርኛ ትምህርት በሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና አይቀሬ ተደማሪ አለመሆን በእርግጥ ለቋንቋው ሊሰጠ የሚገባውን ትኩረት ሊቀንስ ይችላል። ነገር ግን በአማርኛ ፈተና ጥሩ ውጤት ማምጣት በሌሎቹ ትምህርቶች ሊመጣ የሚችለውን ውጤት አብሮ የሚያሳድግ መሆኑን ተማሪው ሳይገነዘብ አይቀርም። ለቋንቋው አሉታዊ ግምት እንዲኖር የሚያደርገው ምክንያት ይህ ከሆነ ከእንግሊዝኛና ሒሳብ ትምህርቶች ውጭ ያሉትም የዚህ ዓይነቱ ዝቅተኛ ግምት የማይሰጣቸው ምክንያት ባለመኖሩ የተሰጠው አስተያየት በአማርኛ ላይ ብቻ ሊጐላ ይችላል ለማለት አያስደፍርም።

በክፍል ውስጥ የተማሪ ቁጥር መብዛትም እንዲሁ አሳማኝ ችግር አይሆንም ባይባልም በሌሎች የትምህርት ዓይነቶችም ላይ ተመሳሳይ ተፅዕኖ አለው። ስለዚህ የቋንቋ መምህራን የአገሪቱ የኢኮኖሚ አቅም ፈቅዶ በርካታ መምህራንን አሰልጥኖና ከአሁኑ የተሻለ የመማሪያ ክፍሎችን ገንብቶ በክፍል ውስጥ ቁጥራቸው አነስተኛ የሆነ ተማሪዎችን ማስተማር የሚያስችል ደረጃ ላይ እስኪደርስ ድረስ ተማሪዎችን በቡድን በመክፈል ሊያሰሩና ራሳቸውም ለሥራቸው ትኩረትና ሰፊ ጊዜ በመውሰድ በተናጠል ባይሆን እንኳን በጋራ በመረዳት ችግሩን ጨርሶ ባያጠፋውም መቀነስ ይቻላል።

በመፍትሔ ሐሳብነት ከተጠቆሙት ውስጥ ደግሞ፣ አማርኛ ዛሬም ቢሆን የአገሪቱ የጋራ መግባቢያ መሆኑ ግልፅ ነው። /ትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ረቂቅ 1985፡61/ ይበል ጥ ደግሞ ብሔራዊ ቋንቋነቱ ቢረጋገጥ ወዲህም በሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና አይቀሬ ተደማሪ /compulsary/ ቢሆን አጋዥነት አለው። በሌላ በኩል የመማሪያ መጻሕፍት ከአካባቢው ማህበረሰብ፣ ከተማሪው የመማር ፍላጐትና ዓላማ ጋር ተገናዝቦ መውጣት በእርግጥም ተገቢ ትኩረት የሚሰጠው ነው። ነገር ግን በመማሪያው መፅሐፍ በአማርኛ አፈ ፈቶችና ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆኑ ተማሪዎች ተለያይተው እንዲማሩ ማድረግ በተማሪዎች መካከል የመለያየት ስሜትን ከመቀስቀሱ በተደራቢ በተማሪዎች መካከል ሊደረግ የሚፈለገውን የእርስ በርስ መረዳዳት የሚቀንስ በመሆኑ የሚደገፍ አይሆንም። ለዚህ ሁሉ መፍትሔ የሚሆነው ግን የመጻህፍት ዝግጅት በተማሪው ማንነትና የቋንቋ ችግር እንዲሁም የመማር ፍላጐት ላይ ተመሥርተው ለሁሉም በጋራ ሊያገለግሉ በሚችሉበት መንገድ ቢዘጋጁና መምህራንም ለተማሪዎቻቸው ተስማሚ በሚሆን

በተቀላጠፈና በዘመናዊ የማስተማሪያ ስልት ለማስተማር ጥረት ቢያደርጉ የተማሪዎች አመለካከት አዎንታዊ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል።

4·2·2 <u>በመማሪያ መፅሐፉ ላይ የመምህራን አመለካከት</u>

በዚህ ክፍል አሥራ ሁለት ዝግ ጥያቄዎች ቀርበውበታል። ከተራ ቁጥር 13-24 ለቀረቡ ለነዚህ ጥያቄዎች ከመምህራን የተሰጠውን አጠቃላይ ምላሽ በሚከተለው ሠንጠረዥ ላይ እንመልከት።

ሠንጠረዥ 12

በመማሪያ መፅሐፉ ላይ የመምህራን አመለካከት

| የጥያቄ ተራ ቁጥር | ለመልሶች የብዜት ዋጋና የመምህራን ብዛት | | | | | የአመለካከት ድምር ውጤት | አማካይ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | | |
| | የመምህራን ብዛት | የመምህራን ብዛት | የመምህራን ብዛት | የመምህራን ብዛት | የመምህራን ብዛት | | |
| 13 | | | | 3 | 3 | 9 | 1.5 |
| 14 | | | 1 | | 5 | 8 | 1.33 |
| 15 | 1 | 5 | | | | 25 | 4.17 |
| 16 | | | | 1 | 5 | 7 | 1.17 |
| 17 | | | | 3 | 3 | 9 | 1.5 |
| 18 | | | 1 | | 5 | 8 | 1.33 |
| 19 | | | | 5 | 1 | 11 | 1.83 |
| 20 | | 5 | | | 1 | 21 | 3.50 |
| 21 | | 3 | | 3 | | 18 | 3.00 |
| 22 | | | | 5 | 1 | 11 | 1.83 |
| 23 | | | | 4 | 2 | 10 | 1.69 |
| 24 | | | | 5 | 1 | 11 | 1.83 |
| ጠ·ድምር | 1 | 13 | 2 | 29 | 27 | 148 | 2.06 |

ይህ የመጠይቅ ክፍል፣ መምህራን በአሥራ ሁለተኛ ክፍል የእንግሊዝኛ መማሪያ መፅሐፍ ላይ ያላቸውን አመለካከት ለማወቅ የቀረበ ነው። ጥያቄዎቹ፣ መፅሐፉ በተማሪዎች ማንነት፣ የአካባቢ ሁኔታና የመማር ፍልጐት ላይ ተመሥርቶ መዘጋጀት አለመዘጋጀቱን፣ በመፅሐፉ የቀረቡ ምንባቦችና መልመጃዎች ተማሪዎች በተግባር ሊከውኗቸው መቻል አለመቻላቸውን፣ በመፅሐፉ የቀረቡ የትምህርት ይዘቶች ቋንቋውን ለማስተማር ማገዝ አለማገዛቸውን፣ የክፍሉ የትምህርት ይዘትና ክንውን በተማሪዎች ቀደምት የክፍል ደረጃዎችና ችሎታ ላይ ተመሥርተው እያደጉ መምጣትና መጣኝና ተገቢነት ያላቸው መሆን አለመሆናቸውን፣ መፅሐፉ በጥቅሉ የተማሪዎችን የመማር ፍላጐት መቀስቀስ መቻል አለመቻሉን … ወዘተ የሚጠይቁ ናቸው። /ዝርዝር ጥያቄዎቹ አባሪ 3 ውስጥ ይገኛሉ/።

ከዚህ ውስጥ መምህራን በመፅሐፉ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦችና መልመጃዎች የእርስ በርስ ግንኙነት እንዳላቸውና የቋንቋ ትምህርትን ለማስተማር ያግዛሉ በማለት አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ /ጥያቄ ተራ ቁጥር 15፣20/ በሌሎቹ ዘጠኝ ጥያቄዎች ላይ አሉታዊ አመለካከታቸውን አስቀምጠዋል። ይህ ክፍል ከቀሩት ሁለቱ ተላውጦዎች ሁሉ ዝቅተኛ አሉታዊ ነጥብ 2·06 የተመዘገበበት በመሆኑ መምህራን በመማሪያው መፅሐፍ ላይ በከፍተኛ ደረጃ ጥላቻቸውን ገልፀዋል ለማለት ይቻላል።

መምህራን በቀረቡት መጠይቆች አማካይነት መፅሐፉ፣

- ከሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ጋር ግንኙነት እንደሌለው፣
- የቀረቡትን መልመጃዎች ተማሪው በተግባር ሊሠራቸው እንደማይችል፣
- በተማሪዎች አካባቢና የቋንቋ ትምህርት ዓለማ ላይ ሳይመሠረት በደፈና የተዘጋጀ ስለመሆኑ፣
- የመርሀ ትምህርትና የመፃሕፍት ዝግጅት ልምድ አለን በሚሉ የቢሮ ሰዎች ብቻ ሳይሆን መምህራን መሳተፍ እንደሚገባቸው፣
- ሲለበስና የመምህሩ መምሪያ በወቅቱ ወይም ጭራሽ የማይደርሱ መሆናቸውን፣

- ይዘቶቹ ተማሪዎች አልፈዋቸው ከመጡት የክፍል ደረጃዎችና ካካበቱት ዕውቀት ላይ ተመሥርተው ያልመጡና ተከታታይነት የሌላቸው መሆናቸውን፤
- መፅሐፉ የተማሪዎችን የመማር ፍላጐት የሚቀሰቅስና የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርጉ የሚያበረታታ አለመሆኑ …ወዘተ

በማለት የተቃውሞ ይስተያየቶች ተሰጥተዋል።

በእርግጥ የመማሪያ መፃህፍትም ሆነ የመርሀ ትምህርት አዘገጃጀት በቅድሚያ የፍላጐት አሰሳ ሳይደረግና የቋንቋው ትምህርት በሚሰጥበት አካባቢ የተማሪዎች የቋንቋ ትምህርት ዓላማና ፍላጐት እንዲሁም የየአካባቢ የቋንቋ ችግር የሚፈታበት ሁኔታ ተጠንቶ ሁኔታዎች ሳይመቻቹ ከተዘጋጁ የማስተማሪያ መሣሪያነታቸው ፋይዳ የለሽ እንደሆነ በክለሳ ድርሳናት ክፍል በሰፊው ተብራርቷል። መፅሐፉ በጥናቱ መነሻ ላይ እንደተባለውም በጥናት ባልተዘጋጀና የየአካባቢ የቋንቋ ችግርን በማይፈታ ሲለበስ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ የተመዘገበው ውጤት የሚጠበቅ ነው። ይህ ውጤት በመምህራን መጠይቅ ብቻ የተረጋገጠ ሳይሆን የተማሪዎች ምላሽም በተደራቢ ይህንኑ አሉታዊ ውጤት ማሳየቱ /የተለውጦ ሁለት ውጤት/ ችግሩን የበለጠ ያጐላዋል። ስለዚህም መምህራንም ሆኑ የመፅሀፍት አዘጋጆች በጉዳዩ ላይ በጥልቅ ሊያስቡበት የሚገባ ወሳኝ ነጥብ ነው።

ይሁን እንጂ የችግሩ ምንጭ የአዘገጃጀት ጉድለት ነው ብሎ ማለፍ አያስኬድም። ከየትኛውም ጉዳዩ ከሚመለከተው ክፍል ይልቅ ተማሪዎችንና አካባቢያቸውን፤ ቋንቋው ለአካባቢው የሚሰጠውን ጠቀሜታ፤ የተማሪዎችን ቀደምትና የአሁን ችሎታ …ወዘተ በቅርብ ሆነው የሚያውቁት መምህራን በመሆናቸው ተጨማሪና አመቺ የትምህርት ይዘቶችን በመፈለግና ስምሙ የማስተማሪያ ዘዴዎችን እንደሁኔታው በመቀያየር ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ክንውኑ እየሳቡ የማስገባት ሐላፊነት ይጠበቅቸዋል።

4·2·3 <u>መምህራን ለሙያቸው ያላቸው አመለካከት</u>

ይህንን አመለካከት ለመለካት የቀረቡት የመምህራን ጥያቄዎች ከተራ ቁጥር 25 እስከ 36 ሲሆኑ በእያንዳንዱ ጥያቄ ላይ የተመዘገበውን የጠቅላላ ድምር አማካይ ነጥብ ቀጥሎ የተቀመጠው ሠንጠረዥ ያስረዳል።

ሠንጠረዥ 13

መምህራን በሙያቸው ላይ ያላቸው አመለካከት

| የጥያቄ ተራ ቁጥር | ለመልሶች የተሰጠ የብዜት ዋጋና የመምህራን ብዛት | | | | | የአመለከከት ድምር ውጤት | አማካይ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | | |
| | የመምህራን ብዛት | የመምህራን ብዛት | የመምህራን ብዛት | የመምህራን ብዛት | የመምህራን ብዛት | | |
| 25 | 1 | 4 | - | 1 | - | 23 | 3.83 |
| 26 | 1 | - | - | 5 | - | 15 | 2.50 |
| 27 | - | - | - | 4 | 2 | 10 | 1.67 |
| 28 | - | - | - | 3 | 3 | 9 | 1.50 |
| 29 | - | 2 | - | 4 | - | 16 | 2.67 |
| 30 | - | 2 | - | 2 | 2 | 14 | 2.33 |
| 31 | 1 | - | 1 | 4 | - | 16 | 2.69 |
| 32 | - | - | - | 5 | 1 | 11 | 1.83 |
| 33 | - | 5 | - | - | 1 | 21 | 3.50 |
| 34 | 1 | 1 | - | - | 4 | 13 | 2.17 |
| 35 | 2 | - | - | - | 4 | 14 | 2.33 |
| 36 | - | 2 | - | - | 4 | 12 | 2.00 |
| ጠ·ድምር | 6 | 16 | 1 | 28 | 21 | 174 | 2.42 |

በዚህ ክፍል በቀረቡ መጠይቆች፣ መምህራን ከየትምህርት ተቋሙ ተመርቀው በአማርኛ ቋንቋ መምህርነት ከተሰማሩ ወዲህ የሙያ ማሻሻያና የትምህርት ደረጃቸውን ለማሳደግ ዕድል እንደገጠማቸው /ተራ ቁጥር 25/ እና በክፍል ውስጥ መምህራን ብዙ ገለፃና ማብራሪያ ከመስጠት ይልቅ ተማሪዎች እርስ በርሳቸው እየተረዳዱ እንዲማማሩ ማድረጋቸውን /ተራ ቁጥር 33/ ለሚጠይቁ ሁለት ጥያቄዎች ብቻ የድጋፍ ምላሽ ሲሰጡ በተቀሩት አሥር መጠይቆች ላይ ያስመዘገቡት ነጥብ በሙሉ አሉታዊ ነው። ከአሉታዊ መልሶች ውስጥ በተለይ ለተማሪዎች በተደጋጋሚ የቤትና ክፍል ሥራዎች ሰጥቶ በወቅቱ

አርሞ ለመመለስ አለመቻል /ተራ ቁጥር 27 እና 28/ እንዲሁም የሥራ ባልደረቦች በማወቅም ይሁን ባለማወቅ አማርኛን ማስተማር ቀላል ሥራ እንደመሥራት አድርገው የሚገምቱና የሚተቹ መኖራቸውን /ተራ ቁጥር 32/ በሚመለከት በቀረቡ አሉታዊ ጥያቄዎች ላይ ሁሉም በከፍተኛ ደረጃ ተስማምተውበት በተከታታይ 1·67፤ 1·5፤ 1·83 የሆነ አማካይ ውጤት አሳይተዋል።

እዚህ ላይ በተራ ቁጥር 4 ላይ ለተጠየቀው ጥያቄ "ተማሪዎች ግፊትና ቁጥጥር ካል ተደረገባቸው በስተቀር የሚሰጣቸውን የቤትና የክፍል ሥራዎች የመሥራት ፍላጐት የላቸውም" በማለት በተማሪዎች የሥራ ፍላጐት ላይ ያላቸውን አሉታዊ አመለካከት ገል ፀው ሳለ በነዚህ ጥያቄዎች ደግሞ መምህራን የቤትና የክፍል ሥራዎችን ሰጥተው በወቅቱ አርሞ ለመመለስ የማይቻላቸው መሆኑን ጠቁመዋል። ሁለቱንም ምላሾች ስናነፃፅራቸው ግን፣ የተማሪዎች የመሥራት ፍላጐት የሚታየው በቅድሚያ ሥራው ሲሰጣቸው ነው። ተማሪዎች ለትምህርቱ አሉታዊ አመለካከት አላቸው የሚባለውም የመምህራቸውን ትዕዛዝ ጠብቀው እንዲሠሩ የታዘዙትን ለመሥራት ፍቃደኛ ሳይሆኑ ሲቀሩ ነው። ከዚህ አኳያ የሥራው ፍላጐት የጠፋው ከተማሪዎች ሳይሆን ከመምህሩ ነው የሚል ግምት እንዲሰጥ የቀረበው የምላሽ ውጤት ይጋብዛል። ከዚህ በተጨማሪ ሌሎች አሉታዊ አመለካከት የተንፀባረቀባቸው ነጥቦች ደግሞ፡

- የአማርኛ መምህር በመሆናቸው ውስጣዊ ቅሬታ ያደረባቸው መሆኑ፤
- የአካባቢው ማህበረሰብ ለመምህራንና ለመምህርነት ሙያ ከበሬታ አለመስጠቱ፤
- በአማርኛ አፋቸውን የፈቱና ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆኑ ተማሪዎችን በአንድ ክፍል ቀላቅሎ ማስተማር አዳጋች መሆኑን፤
- አጋጣሚ ሁኔታና ዕድል ቢያገኙ የመምህርነት ሙያቸውን ቢቀይሩ የሚመርጡ መሆኑን፤
- ከወጡበት የትምህርት ተቋማት የተማሯቸው የትምህርት ይዘቶች የቋንቋ መምህር ሊያደርጋቸው እንደማይችል … ወዘተ፤

ሲሆኑ በሁሉም ነጥቦች ላይ በመስማማት 2·42 በሆነ ነጥብ በመምህርነት ሙያቸው ላይ ያላቸውን አሉታዊ አመለካከት አንፀባርቀዋል።

የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው፣ ለሚያስተምሩት ቋንቋ፣ ለተማሪዎቹ፣ ለመፅሐፉ ይልቁንም ለሙያቸው እሉታዊ ግምት የሚሰጡ መምህራን ተማሪዎችን ከሚፈለገው ግብ ላይ ያደርሳሉ ተብሎ አይጠበቅም። እንዲያውም ተማሪዎች ለትምህርቱም ሆነ ለቋንቋው አዎንታዊ አመለካከት ቢኖራቸው እንኳን መምህራን በሚያሳድሩባቸው የሞራልና የሥነልቡና ድቀት ወደ አሉታዊ አመለካከት ሊለወጡ ይችላሉ። በዚህ ጥናትም የተገኘው መረጃ ይንንኑ ሐሳብ በእጅጉ የሚያመለክት ነው። እንዲያውም የተገላቢጦሽ ተማሪዎች ለመምህራቸውና ለቋንቋው ትምህርት ያላቸው አመለካከት አዎንታዊ /3·11/ መሆኑ ሲታይ በራሳቸው ጥረትና ትግል ወደቋንቋው ትምህርት የመጡ ናቸው በማሰኘት ሊያስወድሳቸው ይችላል። እንዲያውም የመማሪያ መፃህፍት አዘገጃጀት በጥናት ላይ ተመሥርቶ በተማሪው ማንነትና አካባቢ ላይ የተነሳ ቢሆንና መምህራንም ለተማሪዎቻቸው፣ ለመፅሐፉና በእጅጉም ለሙያቸው ቀና አመለካከት ቢኖራቸው የተማሪዎች አመለካከት አሁን ከተገኘው ውጤት ተሽሎ በከፍተኛ ደረጃ አዎንታዊ ሊሆን ይችል ነበር ብሎ መተንበይም ይቻላል። የመማር ማስተማሩን ሂደት አቀላጥፎ የተማሪውን ተሳትፎና ውጤት ለማሳደግ ይቻል ዘንድ ከተማሪው ቀድሞ የመምህራን አመለካከት ሊለወጥ ይገባል። የሙያ ማሻሻያና የትምህርት ማሳደጊያ ኮርሶችን ከመውሰድ የተገኘው ውጤት ይህ ከሆነ /ተራ ቁጥር 25/ ትምህርቱ በመምህራን ላይ የባህርይ ለውጥ አላመጣም ማለት ይቻላል። በሌላ በኩል ደግሞ መምህራን በሰለጠኑባቸው የትምህርት ተቋማት የሚሰጧቸው የትምህርት ይዘቶች በቀጥታ የቋንቋ መምህራንን ለመቅረፅ ካልቻሉ /ተራ ቁጥር 36 እና መጠ፡ ሐ/ መምህርነትና መምህር ባልተገናኙበት ሁኔታ ትምህርቱ ይከናወናል ማለት በመሆኑ በጥናቱ የታቀፉት መምህራን ካለሙያቸው የተሠማሩ ስለሆነ ውጤቱም አመለካከቱም ተገቢ ነው ብሎ መቀበልም ያስኬዳል። የምላሹን ባህርይ እንመልከት፣

ከነዚሁ ጋር ተያይዞ የቀረበው ክፍት መጠይቅ 'ሐ' "ከወጡበት የትምህርት ተቋም የተማሯቸው ኮርሶች ይዘት በቀጥታ ብቃት ያለው የቋንቋ መምህር ለመቅረፅ በሚያስተማምን ደረጃ የአማርኛ መምህር አስልጥኖ ለማውጣት የሚያስችል ነው?" ለሚለው የ36ኛ ተራ ቁጥር ጥያቄ መልስ ምክንያት የሚሆኑ ተጠቃሽ ነጥቦችን ለአብነት

ያህል ያስቀምጧቸው"። የሚል ሲሆን ለዚህ ጥያቄ ሁለት ከኮተቤ መምህራን ኮሌጅ የተመረቁ መምህራን ብቻ "አዎን" በማለት መልሰው ምክንያቱን ሲያስቀምጡ፣

- ብቃት ባላቸው አንጋፋ መምህራን ስለተማርኩ፣
- ትምህርቱን ከተግባር ጋር እያዋሀድኩ ስለተማርኩ፣
- ቀጥታ ቋንቋውን የሚመለከቱ ኮርሶች በስፋት ይሰጡ ስለነበር

የሚል የአዎንታዊ ምላሽ ምክንያቶችን ሰጥተዋል።

ቀሪዎቹ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የተመረቁት ደግሞ፣

- በመጀመሪያም መምህር እንደምሆን አውቂ አልተማርኩም፣
- የተማርኳቸው በርካታ ኮርሶች አሁን ከምሠራው የማስተማር ሙያ ጋር ፈፅሞ አይገናኙም፣
- አብዛኛዎቹ ኮርሶች በርዕስ ካልሆነ በስተቀር አማርኛን ስለማስተማር የሚያዘጋጁ አይደሉም፣
- አብዛኞቹ ኮርሶች በቋንቋ ዕውቀት ላይ ብቻ የሚያተኩሩ እንጂ የቋንቋ ክኂላትን ለተማሪዎች እንዴት ማስተማር እንደሚገባ ከሥነዘዴው ጋር አገናዝበው የሚያስለጥኑ አይደሉም፣
- አባዛኞቹ ኮርሶች ከማስተማር ይልቅ የሥነፅሑፍ ዕውቀት ላይ የሚያተኩሩ በመሆናቸው ሙያውን በውል አላውቅም፣

የሚሉ አስተያየቶችን ሠንዝረዋል።

ይህ ምላሽ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል በአማርኛ ሰልጥነው ከወጡ መምህራን የተገኘ ውጤት ነው። ከላይ እንደተጠቆመው በእርግጥም በሰለጠኑበት የትምህርት ተቋም የተማሯቸው የትምህርት ዓይነቶች አማርኛን በማስተማር ሙያ በወጉ ሊቀርፃቸው ካልቻለ መላሾቹ ባልሰለጠኑበት ሙያ እንዲሰሩ ተደርገዋል ማለት ነው። ይህ ከሆነ ደግሞ የተመዘገበው የአመለካከት ውጤትም ምክንያታዊ ይሆናል።

ነገር ግን ይህ ክፍለ ትምህርት በመምህርነትና ከመምህርነት ሙያ ውጭ የሚሰለጥኑ ተማሪዎችን በመለየት ማስተማር ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ከትምህርት ክፍሉ የሚወጡ መምህራን የዚህ ዓይነት የጐላ ችግር ሊገጥማቸው እደማይችል ተስፋ ይደረጋል። ይሁን እንጂ በሁለገብ የትምህርት ይዘቶች ቀደም ሲል ሰልጥነው አሁን በአማርኛ ቋንቋ መምህርነት በመሥራት ላይ የሚገኙ መምህራን ቋንቋና አማርኛን በማስተማር ዘዴ ሊሰለጥኑ የሚችሉበት መንገድ ወይም የሙያ ማሻሻያ ኮርሶች፣ ሴሚናሮችና ወርክሾፖች ሊዘጋጁላቸው ይገባል። ይህ ካልሆነ ግን በያሉበት ቦታ ከትምህርቱ ሂደትም ሆነ ከተማሪዎቻቸው ፍላጐት ጋር የማይጣጣሙ እንዲሁም ተፈላጊውን ውጤት ሊያስገኙ የማይችሉ መሆኑ መታሰብ ይኖርበታል።

በጥቅሉ እኙዚህንና የመሳሰሉትን ነጥቦች ይዘው በቀረቡ 36 ጥያቄዎች ላይ የተገኘው ነጥብ፣ መምህራን ለተማሪዎቻቸው፣ ለመማሪያ መፅሐፉና ለሙያቸው ያላቸው አመለካከት አሉታዊ መሆኑን የተመዘገበው አማካይ ነጥብ /2·34/ ያስረዳል።

ከዚህ ውጤት ላይ የደረሰውን አጠቃላይ የመምህራን አመለካከት በየተላውጦዎቹ የተመዘገቡትን ዝርዝር ውጤቶች የሚከተለው ሠንጠረዥ ይገልፀዋል።

ሠንጠረዥ 14

የመምህራን አጠቃላይ አመለካከት

| ተለውጦዎች | የመልሶች የብዜት ዋጋና የመምህራን ብዛት | | | | | የአመለካከት ድምር | አማካይ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | | |
| 1 | 5 | 23 | - | 23 | 21 | 184 | 2.56 |
| 2 | 1 | 13 | 2 | 29 | 27 | 148 | 2.06 |
| 3 | 6 | 16 | 1 | 28 | 21 | 174 | 2.42 |
| ጠ· ድምር | 12 | 52 | 3 | 80 | 69 | 506 | 2.34 |

መግለጫ:- ተላውጦዎችው

1· መምህራን በተማሪዎቻቸው ላይ ያላቸው አመለካከት።

2· መምህራን ለመማሪያው መፅሐፍ ያላቸው አመለካከት።

3· መምህራን ለሙያቸው ያላቸው አመለካከት።

በመጨረሻም በመምህራን የተሞሉት በሦስቱ ተላውጦዎች ውስጥ ተካትተው የቀረቡት 36 ዝግ ጥያቄዎች የታሰበውን ጉዳይ መለካት ስለመቻላቸው ከምሁራን ግምገማ በተደራቢ ስታቲስቲካዊ ስለሌት ተደርጓባቸዋል። ስሌቱ የተማሪዎች መጠይ ቅ በተሠራበት የኩደር የአስተማማኝነት ቀመር '21' መሠረት ሲሆን 0·73 ነጥብ አስገኝቷል። ስለዚህም የመምህራን መጠይቆች እንደተማሪዎች መጠይቆች ሁሉ አስተማማኝ መለኪያ መሆናቸው በቀመሩ ተረጋግጧል። ጊልፎርድ /1965፥ / የስሌቱን አስተማማኝነት በሚከተሉት መግለጫዎች በመታገዝ በቀመሩ ውስጥ አስገብቶ ማስላት ይቻላል።

መግለጫ

ቀመር $\frac{n}{n-1}\left(1 - \frac{\bar{x}(n-\bar{x})}{n(sx)^2}\right)$

$n = 36$
$m(\bar{x}) = 14.06$
$(sx)^2 = 29.254$
$sx = 5.4087$

## 4·3 የክፍል ምልከታ ማስታወሻ ዘገባ

በአራቱም ትምህርት ቤቶች በእያንዳንዳቸው ሦስት ጊዜ በድምሩ አሥራ ሁለት ጊዜ በተደረገው የክፍል ምልከታ /class observation/፤ የመምህሩን የክፍልና የትምህርት አያያዝ /subject and class management/፤ የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ እንቅስቃሴ፤ አጠቃላይ የመማር ማስተማሩን ሂደትና የትምህርት ቤቶቹን ሁኔታ ዴይ/1990፥ 44-45/ ዝርዝር ምልከታ /qualitative observation/ ብለው ባስቀመጡት ስልት ለመቃኘት ተሞክሯል።

በምልከታው ወቅት በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት የተለያዩ ሁኔታዎች የተቃኙና ያጋጠሙ ቢሆንም አስፈላጊና ጉልህ ነጥቦች ካልሆኑ በስተቀር የየዕለቱ ሁነት በተናጠል አይዘረዘሩም። በማስታወሻ ዘገባው በሁሉም ትምህርት ቤቶች ከታዩ ዝርዝር ሁኔታዎች ውስጥ ከጥናቱ ጋር ሊገናኙ የሚችሉትና ለሁሉም የጋራ ጉዳዮች የሆኑት ብቻ ጠቅለል

ብለው ይቀመጣሉ። የዝርዝር ምልከታው ማጠቃለያ ነጥቦች አባሪ 5 ላይ ቀርበዋል። ነገር ግን የግድ መታለፍ የሌለባቸውና ትኩረትን የሚስቡ ከሆኑ ለአብነት ያህል በተናጠል እንዲጠቀሱ ይደረጋል።

ምልከታው ከተደረገባቸው ትምህርት ቤቶች ውስጥ አንዱ /የካቲት/ በሆሳዕና ከተማ መሀል የሚገኝ በመሆኑ ከውጭ የሚሰማ የመኪናና ከሙዚቃ ቤቶች የሚወጣ ድምፅ በክፍል ውስጥ የመማር ሂደት ላይ ተፅዕኖ የሚሳያድር ከመሆኑ በስተቀር የሌሎቹ ትምህርት ቤቶች ይዞታና አቀማመጥ በተመቻቸ ቦታ ላይ ይገኛል።

በሁሉም ትምህርት ቤቶች /ከዋቸሞ ጥቂት ክፍሎች በተስቀር/ በአንድ ክፍል ውስጥ በርካታ ተማሪዎች ይገኛሉ። በአንዳንድ ምድብ ክፍሎች /sections/ አንድ ዴስክ ለሦስትና ለአራት ተጋርተው የተቀመጡ፣ ጠረጴዛ ጠብቧቸው በጭናቸው ላይ ደብተራቸውን አስደግፈው የሚፅፉ ተማሪዎች ታይተዋል። እነዚህ ክፍሎች ከመጨናነቃቸው የተነሳ በተማሪዎች መካከል ተዘዋውሮ ለማለፍ ችግር ይፈጥራል። ከዚህም የተነሳ ይመስላል መምህራን እየተዘዋወሩ የተማሪዎችን ሥራ ለመቃኘት ሲሞክሩ ያልታዩት። ከዚህ ምልከታ በመነሳት ለመምህራን በቀረበው መጠይቅ ላይ "ለተማሪዎች ተደጋጋሚ የቤትና የክፍል ሥራ ሰጥቼ በወቅቱ እርሞ ለመመለስ ያቸግረኛል" የሚል ምላሽ መሰጠቱ ለችግሩ ምንጭ ሊሆኑ ከሚችሉ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ይኸው በክፍል ውስጥ የተማሪዎች ቁጥር መብዛት መሆኑን መገመት ያስችላል።

የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ክንውን፣ የመምህራንን የክፍልና የትምህርት አያያዝ እንዲሁም የተማሪውን መስተጋብር አስመልክቶ በተደረገው ምልከታ የሚከተሉት አንኳር ማስታወሻዎች ተይዘዋል።

በሁሉም ትምህርት ቤቶች የሚገኙ መምህራን ክፍል እንደገቡ የቀዘቀዘ ሰላምታ ካቀረቡ በኋላ የሁሉም አማካይ የመጀመሪያ ጥያቄ "የት ላይ ነበር ያለነው? ባለፈው ጊዜ የቤት ሥራ ተሰጥቷል?" የሚሉ ጥያቄዎች መሆናቸው በተደጋጋሚ የተደመጡ ናቸው። እዚህ ላይ መምህሩ ከተማሪዎች ይልቅ በቀዳሚው ክፍለ ጊዜ ምን እንደተሠራ፣ የቱን

የትምህርት ክፍል እንዲለማመዱበት እንዳደረገና በዕለቱም ከየት ተነስቶ የት ላይ መቋጨት እንዳለበት አውቆና ተዘጋጅቶ መቅረብ ይጠበቅበታል። መምህሩ እነዚህንና የመሳሰሉ የዕለት ክንውኖችን የሚዘነጋ ከሆነ ተማሪዎችን ለመቆጣጠር ካለመቻሉም በላይ የሥራ ፍላጐት የሌላቸው ተማሪዎች እንዲገፉበት መንገድ ይከፍታል። በተለይም የቤት ሥራ ጥያቄ ሲነሳ ከፊል ተማሪዎች እንደተሰጣቸው ሲናገሩ ከፊሎቹ ደግሞ አልተሰጠንም የሚል ምላሽ ሲሰጡ የተደመጠውም ከዚሁ ከመምህራን ሁኔታ የመነጨ መሆኑ ይታሰባል። በእርግጥ በአንዳንድ ትምህርት ቤቶች አንድ መምህር በብዙ ክፍሎች ሊያስተምር ስለሚችል የሁሉንም ክፍሎች የትምህርት ክንውን ለማስታወስ ሊቸገር ይችላል። ይሁን እንጂ የራሱ ማስታወሻ ሊኖረው ይገባል።

አብዛኞቹ መምህራን በክፍል ውስጥ ከተማሪው ፊት ለፊት ከመሃል ቦታ ላይ ቆመው የመዕሀፉን መልመጃዎች፣ የራሳቸው ዝግጅት ወይም ጥያቄና መልስ /እንደዝግጅቱ ሊለያይ ይችላል/ ከማቅረብ ሌላ መላውን ክፍል በመቃኘት የሁሉንም ትኩረት ለመሳብ የሚያደርጉት ጥበባዊ ክዋኔ በአመዛኙ ሲታይ የቀለጠፈ አይደለም። ትኩረት ይስባል ሊባል ቢችል እንኳን የመምህራን ዓይን ፈጥኖ ከሚያርፍባቸው ከፊት ወንበር ከተቀመጡ ተማሪዎች የሚዘል አይደለም።

መምህራን በአመዛኙ የሚጠቀሙበት የማስተማር ስልት መምህር ተኮር ነው። በእለቱ ከተመደበው የትምህርት ክፍለ ጊዜ ውስጥ አብላጫውን እጅ የመምህሩ ገለፃና ማብራሪያ ይሸፍነዋል። በሁሉም ትምህርት ቤቶች የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ዝቅተኛና ቢኖርም በተወሰኑ ጥቂት ተማሪዎች ዙሪያ የሚሽከረከር ነው። የተማሪዎች ተሳትፎ ሊታይ የሚችለው በጥያቄና መልስ ጊዜ ሲሆን በዚህ ክንውን ወቅትም እጃቸውን የሚያወጡ ጥቂት ተማሪዎች ቢኖሩም እነርሱው በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ይሆናሉ እንጂ ሌሎቹ ዕድሉም አይሰጣቸው። ለዚህ ክንውን በርካታው ተማሪ እጁን አውጥቶ ከመመለስና ተሳታፊ ከመሆን ይልቅ አንገቱን የሚቀብረው ያመዝናል። አንዳንዶች ደግሞ ደብተርም ሆነ መዕሐፍ በእጃቸው ሳይኖር እጃቸውን አጣምረው የሚቀመጡ መኖራቸውም ታይቷል። አንዳንዶች ጥያቄ እንዲመልሱ ቢጠየቁም "አልገባኝም፣ አልሠራሁም፣

ደብተሬን አልያዝኩም …" የሚል መልስ በምንተግዱ ሲመልሱ ተደምጠዋል። መምህራንም "ለምን?" የሚል ጥያቄ አጠንክረው አይጠይቁም። ወደሌላው ከማለፍ ሌላ እርምጃ ሲወስዱም ሆነ ሲገስፁ አልተስተዋሉም። መምህሩ እያስተማረ ሳለ በክፍል ውስጥ በተለይ ከወደኋላ የሚቀመጡ ተማሪዎች እርስ በርሳቸው ሲንሾካሾኩና ሲሳሳቁ አጥኚው ታዝቧል። በዚህ በኩል የመምህራን የክፍል አያያዝ ድክመት ታይቶበታል። በተቃራኒው ደግሞ በየካቲት 25/67 ትምህርት ቤት የታየው የተለየ ሁኔታ ነው። በእርግጥ መምህሩ ዐይነ ስውር በመሆናቸው ችግር ሊኖርባቸው ይችላል። ምልከታው በተደረገበት በአንድ ዕለት በክፍል ውስጥ መኖር ከሚገባቸው 58 ተማሪዎች ውስጥ አሥራ ስድስት ብቻ የተገኙበት ሲሆን ከነዚህም ከፊሎቹ መምህሩ ከገቡ በኋላ የመጡ ናቸው። በሌሎች ክፍሎች ደግሞ መምህሩ እያሉ የወጡም ታይተዋል። መምህሩ የተማሪዎችን ቁጥር ማነስ ከክፍል አለቃው ጠይቀው ከተረዱ በኋላ "በል ስም ጥራልኝ፣ ደብተራቸውንም ሰብስብል ኝ፣ ዛሬ የሌለ ተማሪ ማትሪክን አይፈተናትም፣ ኢንኮፕሊት አደርገዋለሁ …" የሚሉ የንዴትና የዛቻ ቃላትን ወርውረው ክፍሉን ጥለው ሲወጡ ተማሪዎች በሳቅ ሲያውካኩ መታየቱ ችግሩን ያጐላዋል። ይልቁኑ በዚህ ዓይነቱ የቁጣና የማስፈራራት ስልት ተጠቅሞ ለማስተማር ከመጣር ይልቅ ተማሪውን እንደባህርይው በመያዝ ለትምህርቱ እንዲሳብ ለማድረግ ቢሞከር አማራጭ በሆነ ነበር። በዚህ ረገድ ሲታይ የመምህራን የክፍል አያያዝ ጥበብ የረገበ ይመስላል። አጥፊና ግዴለሽ ተማሪ ለሌሎቹ ንቁ ተማሪዎች እንቅፋት መሆኑ ታውቆ ተገቢ እርምጃ አለመውሰድ ይባስ ብሎም ተሸንፎ ክፍል ጥሎ መውጣትና ድንበር በማይገፋ የማስፈራሪያ ስልት መጠቀም ሊደገፍ የማይችል ስህተት ነው። ቀደም ብሎ እንደተመለከተው በዚህ ትምህርት ቤት ሊመዘገብ የቻለው ዝቅተኛ አመለካከት ከዚህ የመነጨ ነው ብሎ መገመት ይቻላል። የመምህሩ ዐይነ ስውር መሆን ለዚህ ሁኔታ በመጠኑም ቢሆን አስተዋፅዖ እንዳለው ሊታሰብ ይገባል።

በአብዛኞቹ ትምህርት ቤቶች ቀደም ባሉት ዓመታት የወጡ የሁለተኛ ደረጃ መል ቀቂያ የአማርኛ ፈተናዎች በክፍል ውስጥ በመምህሩ አቅራቢነት ሲሰሩ እንደነበር አጥኚው ተመልክቷል። በእርግጥ ተማሪዎች የፈተናው አወጣጥ ስልትና ይዘቱ ምን እንደሚመስል እንዲያውቁ መደረጉ ባልከፋ። ነገር ግን ቀደም ብሎ የተጀመረና ለተከታታይ ሳምንታት የዘለቀ በመሆኑ የፈተናው ወረቀት የማስተማሪያ መሣሪያ ሊሆን

መቻሉ የሚደገፍ አይደለም። የዚህ ዓይነቱ ልምድ ደግሞ ተማሪው የመጨረሻ ዓላማ የሚያደርገው የብሔራዊ ፈተናን በማለፍና በፈተናው አወጣጥ ስልት ላይ ብቻ ስለሚሆን ለክፍሉ ትምህርትም ሆነ ለመማሪያው መፅሐፍ የሚያደርገውን ትኩረት ይቀንሳል። መምህራን ብሔራዊ ፈተናዎችን በመሥራትና በማሠራት ለመደበኛው ትምህርት የተመደበውን ክፍለ ጊዜ ከመሻማት ይልቅ ተማሪዎቻቸው መጪውን ፈተና በጥሩ ሁኔታ ሠርተው ጥሩ ውጤት እንዲያመጡ ለዚያ የሚያበቁ የትምህርት ይዘቶችን በማቅረብ ሊያዘጋጇቸው በተገባ ነበር።

ምልከታው በተደረገባቸው ዕለታት የመማሪያውን መፅሐፍ ጥቂት መምህራን ሲጠቀሙበት ከመስተዋሉ በቀር አብዛኞቹ ከራሳቸው የግል ማስታወሻና ከሌሎች መፃህፍት ላይ የተገኙ የትምህርት ይዘቶችን ሲያስተምሩ ታይቷል። ተጨማሪ የትምህርት ይዘቶችን ማስተማር የሚደገፍ ቢሆንም የተመደበውን የመማሪያ መፅሐፍ በተደጋጋሚ አለመጠቀም ደግሞ ተማሪዎች ለመፅሐፉ ትኩረት እንዳይሰጡ ስለማበረታታ ሊታሰብበት ይገባል።

በቋንቋው ትምህርት ላይ መምህራን ስላላቸው ብቃትና ችሎታ በተመለከተ ጥቂት መምህራን አንዳንድ ጥያቄዎችን ለመመለስ ግር ሲሰኙ ከመታየቱ በስተቀር ለተመደቡበት የክፍል ደረጃ ሊመጥን የሚችል ችሎታና ዕውቀት አላቸው የሚል እምነት አለ።

መምህራን በክፍል ውስጥ ተገቢ ቁጥጥርና ክትትል አለማድረግ፣ የቤትና የክፍል ሥራዎችን ከመስጠት መታቀብ፣ የክፍል ውስጥ ተሳትፎን ለተወሰኑ ተማሪዎች ብቻ መስጠት የተሰላቸ አቀራረብና ተገቢነት የሌለው ቁጡነት እንዲሁም ተማሪዎች ለተወሰነ ፈተና ብቻ አተኩረው የክፍሉን ትምህርት እንዲዘነጉ ማድረግ ተማሪዎች በትምህርቱ፣ በመፅሐፉ፣ በመምህሩና በማስተማር ዘዴው ላይ አሉታዊ አመለካከት እንዲቀርፁ መንገድ የሚከፍቱ ድክመቶች ናቸው። የነዚህ ድክመቶች መታየት ደግሞ መምህራን በቀረበላቸው መጠይቅ ላይ እንዳንፀባረቁት ለተማሪዎቻቸው፣ ለመፅሐፉና ለሙያቸው ካላቸው አሉታዊ አመለካከት ጋር የሚገናኝ ነው። ከዚሁ ጋር በተወሰኑ ትምህርት ቤቶች ከተማሪዎች

የተገኘው ውጤት በአንዳንድ ተላውጦዎች ላይ የተመዘገበው እሉታዊ አመለካከት ይህንኑ ተንተርሶ የመጣ ለመሆኑ እርስበርሱ የተጣቀሰ ምክንያት ነው ማለት ያስችላል።

## 4·4 የአመለካከትና የፈተና ውጤት ዝምድና

የጥናቱ ማዕከላዊ ጉዳይና ዓላማ የሆነውን የተማሪዎች አመለካከትና የፈተና ውጤት ዝምድናን አገናዝቦ ከተጨባጭ ውጤት ላይ ለመድረስ ቀደም ብለው የተጠቁሱት ስል ቶች፣ መሣሪያዎችና ነቢባዊ ዳራዎች በጥቅም ላይ ውለዋል። የነዚህ ድምር ውጤት የዚህን ክፍል አጠቃላይ ጭብጥ ይገልፃል።

በጥናቱ ክለሳ ድርሳናት ክፍል የተማሪዎች አዎንታዊ አመለካከት ከጥሩ ውጤት፣ አሉታዊ አመለካከት ከዝቅተኛ ውጤት ጋር ጥምረት እንዳሳየ የምሁራን ጥናቶች እንዳረጋገጡ ተጠቁሟል። በሌላ በኩል ደግሞ አጠቃላይ ትወራው ይህ ቢሆንም አንዳንድ ጊዜ በተለያዩ ተፅዕኖዎች ምክንያት ይህ ጥምረት ሁል ጊዜ ሊታይ እንደማይችል እነዚሁ ምሁራን መጠቆማቸውም /ጋርድነር 1985፡41/ ተወስቷል።

በዚህ ጥናትም እነዚህ ሁለት ኢትበሀሎች ተንፀባርቀዋል። ጥናቱ የተመሠረተባቸው ተማሪዎች ለቋንቋው ትምህርት ዝቅተኛም ቢሆን አዎንታዊ አመለካከት አላቸው። በእርግጥ በመለኪያንት ከቀረቡት ተላውጦዎች ውስጥ በሦስቱ ላይ ደረጃው ይለያይ እንጂ ቀና አመለካከት እንዳለ የተጠናቀረው መረጃ ያስረዳል /ሠንጠረዥ 9/። ነገር ግን የእያንዳንዱን ትምህርት ቤትና የእያንዳንዱን ተማሪ የአመለካከት ውጤት በተናጠል ስንመለከት በተወሰኑ ተላውጦዎች ላይ እሉታዊ አመለካከታቸው ጐልቶ ታይቷል። ይኸው የተማሪዎች አመለካከት /በስሌት ውስጥ ሳይገባ/ ከፈተና ውጤታቸው ጋር ሲነፃፀር አብዛኛው ተማሪ አመለካከቱ ከውጤቱ ጋር ስምሙ ሲሆን የተወሰኑ ተማሪዎች አመለካከት በዝርዝር ሲታይ ደግሞ እሉታዊ አመለካከት ከጥሩ ውጤት፣ አዎንታዊ አመለካከት ከዝቅተኛ ውጤት ጋር ተያይዞ ይገኛል። ጥምረቱ ጋርድነር /1985/ ያስቀመጡትን የአጋጣሚ ሁኔታዎች ሐሳብ የሚደግፍ ነው። ይሁን እንጂ ዝምድናቸውን በዓይን በመቃኘት ብቻ በፍፁምነት ማረጋገጥ ስለማይቻል ከፍ ሲል በተጠቀምንበት የተዛምዶ ስሌት ቀመር /correlation/ ውስጥ በማስገባት የፈተናውን

ውጤት ከአጠቃላይ የተማሪዎች አመለካከት ጋር በማቆራኘት በስሌት በተገኘው ውጤት መሠረት ይፈረጇል።

በዚህ ትንታኔ ውስጥ የፈተናው ውጤት ተማሪዎች በአንደኛው መንፈቀ ዓመትና በመሰናዶ /model/ ፈተናዎች በክፍል መምህራን የተሰጡ አማካይ ነጥቦች የገቡ ሲሆን የአመለካከቱ ደግሞ 120ዎቹ ተማሪዎች ለአርባ ስምንቱ ጥያቄዎች በተናጠል ያስመዘገቡት የአመለካከት አማካይ ነጥቦች ተወስደዋል።

የስሌቱ ዐብይ ጉዳይ የሆኑትን የተማሪዎች አጠቃላይ የአመለካከት አማካይና የሁለት ፈተናዎች አማካይ ውጤቶች ተቀናጅተው ሲሰሉ 0·15 የተዛምዶ ውጤት አስገኝተዋል። የዚህ ተዛምዶ ውጤት ከግምት የሚገባ ወይም ፋይዳ የሌለው ጥምረት መሆኑን ለመለየት በ"ቲ" ዋጋ /t-value/ መፈለጊያ ቀመር ሲሰላ ውጤቱ 1·648 ይሆናል።

ውጤቱ በሚከተለው የ"ቲ" ቀመር ተፈትኖ የተገኘ ነው።

$$t_o = \frac{r\sqrt{n-2}}{\sqrt{1-r^2}}$$ /ጊልፎርድ 1965፡163/

$$t_o = \frac{0.15\sqrt{120-2}}{\sqrt{1-(0.15)^2}}$$

$$t_o = \frac{0.15 \times \sqrt{118}}{1-0.0225}$$

$$t_o = \frac{1.6294171}{0.988686}$$

$$t_o = 1.6480633$$

$$t_o \quad 1.648$$

ለዚህ ውጤት ማረጋገጫ በ"ቲ" ዋጋ ማረጋገጫ / T-critical value / ከተሰጠው ሠንጠረዥ ላይ በአልፋው ·05 ደረጃ ላይ ከተቀመጠው መናፀሪያ 1·976 ያነሰ በመሆኑ

ጥናቱ የተመሠረተባቸው ተማሪዎች ባስመዘገቡት አመለካከትና ባገኙት የፈተና ውጤት መካከል ፋይዳ ያለው ጠንካራ ዝምድና የለውም ለማለት ይቻላል።

ይሁን እንጂ ውጤቱ በሚፈለገው ደረጃ ላይ ሳይደርስ ቀርቶ በዝቅተኛ ደረጃ ላይም ቢሆን በሁለቱ መካከል መጠነኛ ግንኙነት እንዳለ አሀዞቹ ያመለክታሉ። ሆኖም በ"ቲ" የፋይዳ ሙከራ /t-test level of significance/ መመዘኛ ግን ጥምረቱ ዋጋ የሌለው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። ይሁን እንጂ ውጤቱን በዚሁ ከመደምደም ይልቅ ምናልባት ለዚህ ዝቅተኛ ውጤት መምጣት መንስዔ የሆኑ ጉዳዮች እንዳሉ በየአቅጣጫው መርምሮ ተጣምሮውን በሌላ ዘዴ ማየት ያስፈልጋል።

ጥናቱ የተማሪዎችን አመለካከት በክፍል መምህራን ከተሰጠ የፈተና ውጤት ጋር የሚያነፃፅር በመሆኑ ምናልባትም ለተጣምሮው ዝቅተኛ መሆን ምክንያቱ ይኸው የፈተና ውጤት አሰጣጥ ስልት ወይም ራሱ የፈተናው አወጣጥ ብቃት ደረጃ ሊሆን ይችላል። ጥናቱ የፈተናዎችን ብቃትና ተገቢነት የመመዘን ዓላማ ይዞ ባይነሳም የውጤት አሰጣጡን ሁኔታ ለመመርመር ያመች ዘንድ ወደ አስታራቂ "ቲ" ስኮር /normilizing (standardizing) t-score/ በመለወጥ ለማየት ተሞክሯል።

የተማሪዎች የፈተና ውጤት ከተለያዩ ትምህርት ቤቶች፣ በተለያዩ መምህራን በወጡ ፈተናዎች የተገኘ በመሆኑ የሁሉንም ውጤት በተመሳሳይ ስኬል ለማየት አስታራቂው ደረጃ የተሻለ መላ ሆኖ በመገኘቱ የሁለቱን ፈተናዎች /አንደኛ ተርምና መሰናዶ/ አማካይ በመውሰድ በሚከለተው የአስታራቂ "ቲ" ቀመር ስልት መሠረት የሁሉም ትምህርት ቤቶች ውጤት ተሠርተዋል። ለውጤቱ አባሪ '1'ን ይመለከቷል።

ቀመር $T = \frac{10}{\sigma}(x-m) + 50$ (ከፖል 1988፡233)

መግለጫ፡ T - የተማሪ እገሌ ስኮር (student 'T' score)

50 - የ"ቲ" ስኬል አማካይ(T-scale mean)

10- የ"ቲ" ስኬል መደበኛ ልይይት(T-scale standard deviation)

$\sigma$ የቡድን መደበኛ ልይይት(group standard deviation)

$X$ ጥሬ ስኮር (raw score)

$\bar{X}$ የቡድኑ አማካይ(group mean)

በዚህ ቀመር የእያንዳንዱ ተማሪ አማካይ የፈተና ውጤት በማስገባት የእስታራቂውን ቲ ስኮር ውጤት በማግኘት የየትምህርት ቤቶቹን የውጤት አሰጣጥ ስልት ልዩነት ማረጋገጥ ይቻላል። ለተጨማሪ የስሌት መረጃ ሠንጠረዥ '15'ን ይጠቀሟል።

ሠንጠረዥ 15

በ'T' ስኮር ተቀምሮ የተገኘ የትምህርት ቤቶች የውጤት አማካይና መደበኛ ልይይት

| | ትምህርት ቤት | የተማሪዎች ብዛት | $\bar{X}$ | X n-1 |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ዋቸሞ | 40 | 56.94 | 9.22 |
| 2 | የካቲት | 30 | 55.57 | 4.63 |
| 3 | ሞርሲጦ | 25 | 57.04 | 10.37 |
| 4 | ጊምቢቹ | 25 | 63.6 | 8.11 |

በዚህ አሠራር መሠረት በዋቸሞ /9·22/ በሞርሲጦ /10·37/ በጊምቢቹ /8·11/ ትምህርት ቤቶች የውጤት አሰጣጥ ሰፋ ያለ ልይይት /deviation/ ተጠብቆ የተሰጠ ሲሆን የየካቲት /4·63/ ግን ከመደበኛው መለኪያ በላይ እጅግ ተጣብቦ ተገኝቷል። የፈተና ማስተካከያው ሲሰላ ደግሞ በከፍተኛ ደረጃ ከጣራ በላይ አልፎ ይታያል። /ዝርዝሩ አባሪ 1 ላይ ሠፍሯል/ ልዩነቱን በምሳሌ ለማስቀመጥ ያህል፤ በሁሉም ትምህርት ቤቶች 63 አማካይ ነጥብ ያመጣ ተማሪ፤ በዋቸሞ 58፤ በሞርሲጦ 53፤ በጊምቢቹ 61 የእስታራቂ "ቲ" ስኮር ውጤት ሊመዘገብለት ሲችል በየካቲት ግን 63 ያገኘ ተማሪ 123·9 ይመዘገብለታል።

ይህ ውጤት አንድም ለተማሪዎች የተሰጠው ነጥብ የሁሉንም ውጤት በተቀራራቢ ደረጃ ለማጠጋጋት ሲባል ለየት ባለ ስልት የተመዘገበ ወይም የፈተናው ባህርይ ተማሪዎች በተወሰነ ነጥብ ዙሪያ እንዲሰባሰቡ ያደረገ ለመሆኑ በእስታራቂው "ቲ" ስኮር ስልት የተሠራው ውጤት በዝርዝሩ ላይ ያስነብባል። /አባሪ 1 ከተራ ቁጥር 41-70/ የዚሁ

ትምህርት ቤት በእያንዳንዱ ተማሪ መካከል ያለው የውጤት ልይይት 4·63 /standard deviation/ ይህንኑ የተጣበበ አሰጣጥ ያመለክታል። /ሠንጠረዥ 15/

የሁሉም ትምህርት ቤቶች የፈተና ውጤት በዚህ ዘዴ ከተስተካከለ በኋላ በአንድ ላይ የአመለካከትና ውጤት ተዛምዶ ሲሰላ -0·059 የሆነ ከግምት የማይገባ አፍራሽ የተዛምዶ ውጤት አስገኝቷል። ከዚህ ውጤት በመነሳት በአስታራቂው "ቲ" ስኮር ውጤት የተለየ ባህርይ የሚታይበት የየካቲት ትምህርት ቤት ተለይቶ የሦስቱ ትምህርት ቤቶች ብቻ ሲሰላ ·272 ውጤት አሳይቷል። ይህ የተዛምዶ ውጤት በ"ቲ" ዋጋ ማግኛ ቀመር ሲሰላ 2·755 ያለው ሲሆን የ"ቲ" ዋጋ ማረጋገጫ በ·05 ደረጃ ከተቀመጠው ማናፀሪያ 1·987 የበለጠ ሆኖ ተገኝቷል። እንዲያውም ይህ ውጤት በ·01 ደረጃ ከተቀመጠውም ማናፀሪያ 2·632 የበለጠ በመሆኑ የጥምረቱን ፋይዳ 99% እርግጠኛ ያደረገዋል። በዚህ የፈተናዎች ማስተካከያ ስልት መሠረት በሦስቱ ትምህርት ቤቶች የ90 ተማሪዎች አመለካከትና የፈተና ውጤት ከግምት የሚገባ ተጣምሮ ተገኝቶበታል። ስለዚህም መሠረት አድርገን የተነሳነውን የአመለካከትና ውጤት ተዛምዶን አጋግጠልናል። ውጤቱ ቀደም ሲል ባስቀመጥነው የተዛምዶ ቀመር ውስጥ ገብቶ የተሰላበትን ተዋረድ ቀጥሎ እንመለከተዋለን።

$$r = \frac{N\sum xy - (\sum x)(\sum y)}{\sqrt{N\sum x^2-(\sum x)^2}\ \sqrt{N\sum y^2-(\sum y)^2}}$$ /ከፆል 1988፡240/

$$r = \frac{90(106009.1305) - (294.48)\ (4863.11)}{\sqrt{90(975.6758)^2 - (294.48)^2}\ \sqrt{90\ (273242.3063) - (4863.11)^2}}$$

$$r = \frac{1440821.745 - 1432088.633}{\sqrt{87810.822 - 86718.47}\ \sqrt{24591808 - 23649839}}$$

$$= \frac{8733.1122}{\sqrt{1092.352}\ \sqrt{941969}}$$

$$= \frac{8733.1122}{(33.050749)\qquad(970.55087)}$$

$$= \frac{8733.1122}{32077.433}$$

$= 0.2722510607$

$= 0.272$

በሌላ በኩል ደግሞ የየካቲት ትምህርት ቤት በራሱ የፈተና ውጤት እሰጣጥ ስሌት መሠረት ለብቻው ከላይ በተጠቀምንበት ቀመር ሲሰላ 0·376 የተዛምዶ ውጤት አሳይቷል። ይህ የተዛምዶ ውጤት በ"ቲ" ውጤት ማግኛ ዘዴ ሲቀመር 2·147 ነው። የ"ቲ" ዋጋ ማረጋገጫ በ29 (n-1) የነፃነት መንሸራሸሪያ ዲግሪ /degree of freedom/ ሠንጠረዥ ላይ በአልፋው ·05 ደረጃ የተቀመጠው ደግሞ 2·045 በመሆኑ የተገኘው ውጤት ከማናፀሪያው ዋጋ የበለጠ ስለሆነ በዚህ ትምህርት ቤትም ከግምት የሚገባ ተዛምዶ መኖሩ ተረጋግጧል።

የተማሪዎችን የአመለካከት ውጤት በየትምህርት ቤቱ ባየንበት ክፍል የየካቲት ትምህርት ቤት ከሁሉም ያነሰ ነጥብ እንዳለው ተመልክተናል። የፈተና ውጤት ድምር አማካይ ነጥቡ ደግሞ 55·57 ሲሆን ከሌሎች ትምህርት ቤቶች ከተገኘው አማካይ ያነሰ ነው። ስለዚህ የዚህ ትምህርት ቤት አነስተኛ የአመለካከት ነጥብ ከዝቅተኛ ውጤት ጋር የተዛመደ ሲሆን የተቀሩት ሦስት ትምህርት ቤቶች ግን የተሻለ አዎንታዊ አመለካከት ከተሻለ ውጤት ጋር መቆራኘቱን ውጤታቸው ያረጋግጣል።

ይሁን እንጂ ለመማሪያ ተብለው የሚዘጋጁ መፃህፍት በተማሪው ማንነትና ፍላጐት፣ በአካባቢ ሁኔታና የመማር ዓላማ ላይ በተመሠረተ የጥናት መረጃ ላይ ተነስተው ቢዘጋጁ የተማሪዎች አመለካከት በከፍተኛ ደረጃ አዎንታዊ ሆኖ ለጥሩ ውጤት በበቃ ነበር። ከዚሁ ጋር መምህራን ለተማሪዎቻቸውም ሆነ ለሙያቸው እንዲሁም ለማስተማሪያ መፅሐፉ ያላቸው አጉል አመለካከት ተለውጦ አነቃቂ በሆነ የማስተማር ዘዴ ተማሪውን እያገዙ ለማስተማር ጥረት ቢያደርጉ ከአሁኑ የተሻለ የፈተና ውጤት ማግኘት በተቻለ ነበር።

ከዚህ በመነሳት በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት ተማሪዎች በቋንቋውና በትምህርቱ ላይ የሚቀርፁት አመለካከት ከመማር ማስተማር ክንውኑ ጋር በጥብቅ የሚገናኝና ተፅዕኖውም ሆነ አስተዋፅዖው በፈተና ውጤት ላይ ሊንፀባረቅ መቻሉን ማረጋገጥ ተችሏል። የተማሪዎች አሉታዊ አመለካከት በመምህሩ የማስተማር ጥበብና ብቃት፣ በመማሪያው መፅሐፍ አዘገጃጀት ጥራትና ተገቢነት፣ በቤተሰብና በማህበረሰቡ አጋዥነት፣ ጥሩ መለኪያ ሊሆኑ በሚችሉ የተፈተኑ ፈተናዎች … ወዘተ ወደ አዎንታዊነት ሊለወጥ የሚችል መሆኑን አመልክተን ይህንን ክፍል በዚሁ እንቋጫለን።

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያ፣ የጥናቱ ግኝትና አስተያየት

በዚህ ክፍል የጥናቱ ማጠቃለያ፣ የጥናቱ ግኝትና ከነዚህ የመነጩ አስተያየቶች በቅደም ተከተል ይቀርባሉ።

### 5·1 ማጠቃለያ /Conclusion/

ጥናቱ የተካሄደው በመግቢያው እንደተጠቆመው "ተማሪዎች ለውጤታቸው ዝቅተኛ መሆን ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ነው" የሚለውን መላምት ተመርኩዞ፣ በተማሪዎች አመለካከትና በፈተና ውጤታቸው መካከል ያለውን ተዛምዶ መመርመር የሚለውን አጠቃላይ ዓላማ የመነሻ መሠረት አድርጐ ነው። ጥናቱ መሠረት ያደረጋቸው ተጠኝዎች በሀዲያ ዞን በሚገኙ አራት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ የአፍ መፍቻቸው ሀዲይኛ የሆነ 120 የአሥራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው። ተጠኝ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋና ለትምህርቱ፣ ለመምህሩና፣ ለመማሪያ መፅሐፉ ያላቸውን አመለካከት ለመለካት እንዲሁም የተማሪዎቹ ወላጆች፣ ባልንጀሮችና ማህበረሰቡ ተማሪዎች በቋንቋው ትምህርት ላይ በሚኖራቸው አመለካከት ላይ የሚያደርሱትን ተፅዕኖ ለመመርመር የሚያስችሉ የፅሑፍ መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል።

ጥናቱ ከአጠቃላይ ዓላማው ለመድረስ ይችል ዘንድ በመጠይቆቹ አማካይነት የሚመለሱ የሚከተሉት ዝርዝር ጥያቄዎችም ነበሩት።

- ተማሪዎች ለመማሪያ መፅሐፉ ያላቸው አመለካከት ምንድነው?
- ተማሪዎች ለመምህራቸውና ለሚያስተምርበት ስልት ምን አተያይ አላቸው?
- የተማሪው ባልንጀሮችና ማህበረሰቡ በተማሪው የአመለካከት ምሥረታ ላይ የሚያደርሱት ጫና ምን ያህል ነው?
- ተማሪዎች ለቋንቋውና ለትምህርቱ ያዳበሩት አመለካከት ምንድነው?
- የተማሪዎች አመለካከት በፈተና ውጤታቸው ላይ ምን ያህል ይንፀባረቃል?

እነዚህን ዝርዝር ዓላማዎችና ከፍ ሲል የተጠቀሱትን መላምትና የመነሻ ጥያቄ ለመመርመር በቅድሚያ የተደረገው ትንተና የተማሪዎችን አመለካከት መለየት ነበር።

አምስት ምርጫዎችን ይዘው በሊከርት አፃፃፍ ስልት በቀረቡት መጠይቆች እያንዳንዱ ተማሪ በአርባ ስምንቱ ጥያቄ ያስመዘገበው ውጤት እንዲሁም አንድ መቶ ሀያዎቹ ተማሪዎች ለእያንዳንዱ ጥያቄ ያስመዘገቡት የአመለካከት አማካይ ውጤት ከሦስት በላይ ከሆነ አዎንታዊ፣ ከሦስት በታች አሉታዊ፣ ሦስት ከሆነ ደግሞ ገለልተኛ /neutral/ ሲሆን ተማሪዎች በየተላውጦው /variables/ ያስገኙት የአመለካከት ውጤት ተለይቷል።

በቅድሚያ የቀረቡት መጠይቆች አመለካከትን ለመለካት ያላቸው የአስተማማኝነት ደረጃ ተረጋግጦ /0·84/ እንዲሁም ተለውጦዎቹ እርስ በርሳቸው ያላቸው ውስጠ ተዛምዶ /inter item correlation/ ከግምት የሚገባ መሆኑ ታይቶ በየዝርዝር ዓላማዎቹ ውጤቱ ተተንትኗል። በዚህ መሠረት መጠይቁን የሞሉት ተማሪዎች ከቀረበላቸው አራት ተላውጦዎች ውስጥ ለመማሪያ መፅሐፉ 2·99 አማካይ ነጥብ በማስመዝገብ ያላቸው አሉታዊ አመለካከት ታይቷል። ከዚህ ሌላ ለመምህሩ 3·11፣ ለቋንቋውና ለተናጋሪው ማህበረሰብ 3·42 አማካይ ነጥብ በማስቆጠር አዎንታዊ አመለካከት እንዳላቸው ተረጋግጧል። የተማሪው ቤተ ዘመዶች፣ ባልንጀሮችና ማህበረሰቡ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋና ለትምህርቱ አዎንታዊ አመለካከት እንዲያሳድሩ አጋዥ ለመሆናቸው የተገኘው 3·39 አማካይ ነጥብ ያሳያል። ከነዚህ ተላውጦዎች ድምር ውጤት የተገኘው የተማሪዎች አጠቃላይ የአመለካከት ውጤት አዎንታዊ ሆኖ ተገኝቷል። ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋና ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸውን የተጠቃለለ አዎንታዊ አመለካከት ሠንጠረዥ "9" ያመለክታል። ይህ ውጤት ከፍ ሲል የቀረቡ ጥያቄዎች እንዲመለሱ አድርጓል።

የተማሪዎችን አመለካከት በፆታ ለመመርመር በተደረገው ትንተና ሴቶች 3·20 አማካይ ውጤት ሲያስመዘግቡ ወንዶች ደግሞ 3·24 አስቆጥረዋል። በዚህ ውጤት በወንዶችና በሴቶች መካከል ከግምት የሚገባ የአመለካከት ልዩነት አልታየም። በከተማ ነዋሪዎችና በገጠር ነዋሪ ተማሪዎች መካከል ግን የከተማ ነዋሪዎች 3·32 በማስገኘት 3·19 አማካይ ነጥብ ካስቆጠሩት የገጠር ነዋሪዎች የተሻለ አመለካከት እንዳላቸው ውጤቱ አሳይቷል። በትምህርት ቤቶች መካከልም እንዲሁ የየካቲት 25/267 ትምህርት ቤት ተማሪዎች ዝቅተኛ አመለካከት ሲያሳዩ /3·13/ የጊምቢቹ ደግሞ የተሻለ አዎንታዊ /3·50/ አመለካከት እንዳላቸው በውጤቱ ተረጋግጧል።

ከዚህ ቀጥሎ ስለተማሪዎች አመለካከት ምሥረታ ድጋፊ ሀሳብ ለማግኘት ለመምህራን በቀረው መጠይቅ መሠረት መምህራን ለተማሪዎቻቸው 2·56፤ ለማስተማሪያ መፅሐፉ 2·06 ለሙያቸው 2·42 በማስመዝገብ ያላቸው አመለካከት በከፍተኛ ደረጃ አሉታዊ መሆኑን የተደረገው ቆጠራና ስሌት አመልክቷል። ውጤቱን ሠንጠረዥ 10፤ 11፤ እና 12 በውል ያሳያሉ። በተማሪዎችና በመምህራን አመለካከት መካከል በተደረገው ንፅፅር የሁለቱ ውጤት የተቃረነ ሆኖ ተገኝቷል። በተለይም መምህራን ስለተማሪዎቻቸው ያላቸው አመለካከት ተማሪዎቻቸው ወደ ትምህርቱ እንዳይሳቡና የነቃ የክፍል ውስጥ ተስትፎ አድርገው ጥሩ ውጤት ማስገኘት እንዳይችሉ ተፅዕኖ የሚያደርስ መሆኑ ከግንዛቤ ገብቷል። የተደረገውም የክፍል ምልከታ ይህንኑ ሁኔታ የሚያጠናክር ሆኗል።

የጥናቱ ማዕከላዊ ርዕሰ ነገር የሆነውን የተማሪዎች አመለካከትና ውጤት ዝምድና ለመመርመር ከሁሉም ተማሪዎች በተገኙ የአመለካከትና የፈተና ውጤቶች መካከል ስታቲስቲካዊ ንፅፅር ተደርጓል። የፈተናው ውጤት ከአራቱም ትምህርት ቤቶች በአንደኛ መንፈቀ ዓመትና በመሠናዶው ፈተና በክፍል መምህራን የተሰጠው አማካይ ውጤት ነው። የሁለቱ አማካይ ውጤቶች /የአመለካከትና የፈተና/ በስታቲስቲካዊ የተዛምዶ ቀመር ውስጥ ገብቶ ሲሰላ 1·648 ውጤት አስገኘ። ይህንን ውጤት በ"ቲ" ማናፀሪያ ዋጋ /T-critical value/ ከተቀመጠው ነጠብ 1·976 ጋር ሲነፃፀር የተገኘው ውጤት ያነሰ በመሆኑ በአመለካከትና በፈተና ውጤት መካካል ከግምት የሚገባ ዝምድና እንደሌለ ቢያሳይም፤ በሌላ መልኩ። ለንፅፅር የቀረበው የፈተና ውጤት በተለያዩ መምህራን በተለያዩ ፈተናዎች የተመዘኑ ተማሪዎች ውጤት እንደመሆኑ መጠን የሁሉንም ውጤት በተመሳሳይ ስኬል ለማየት እንዲቻል የሁለቱን ፈተናዎች ውጤት አማካይ ወደ እስታራቂ "ቲ" ስኮር /normalized T-score/ ተለውጦ እንዲሰላ ተደረገ። በዚህም መሠረት የማስተካከያው ስሌት ከየካቲት ትምህርት ቤት የተገኘው ውጤት ከሌሎቹ የተለየ የፈተና ውጤት አሰጣጥ ስልት የተደረገበት መሆኑ በገልፅ አሳይቷል /ሠንጠረዥ '15'ን ይመለከቷል/። የተቀሩት ሦስት ትምህርት ቤቶች /ቀቸሞ፣ ሞርሲጦና ጊምቢቹ/ የ90 ተማሪዎች በቲ-ስኮር የተሰላው የፈተና ውጤትና አመለካከት እንደገና በተዛምዶው ቀመር ውስጥ ሲገባ በአመለካከትና በፈተናው ውጤት መካከል ፋይዳ ያለው ዝምድና መታየቱን ለማረጋገጥ ተችሏል። የተገኘው የተዛምዶ ውጤት 2·755 ሲሆን ከ"ቲ" ዋጋ ማናፀሪያ ከተቀመጠው ነጥብ

1·987 የበለጠ በመሆኑ /P<0.05/ ዝምድናው የጠነከረ መሆኑን ስሌቱ በ95% ያረጋግጣል። የየካቲት ትምህርት ቤት 30 ተማሪዎች የአመለካከት ውጤትም እንዲሁ ከራሱ የፈተና ውጤት ጋር ሲነፃፀር በራሱ ያለው ጥምረት 2·147፣ የ"ቲ" ዋጋ ደግሞ 2·045 በመሆኑ ፋይዳ ያለው ተዛምዶ አስገኝቷል።

ከተማሪዎች የተገኘው አጠቃላይ የአመለካከት አማካይ ነጥብ /3·23/ እንዲሁም የሁሉም ተማሪዎች የፈተናዎች ድምር አማካይ ውጤት /57·6/ አሀዞች ሲታዩ ከፍተኛ አዎንታዊ አመለካከትና ከፍተኛ የፈተና ውጤት የሚባሉ አይደሉም። ስለዚህ የጥናቱ ማጠቃለያ ዝቅተኛ አዎንታዊ የአመለካከት ነጥብ ከዝቅተኛ የማለፊያ ፈተና ውጤት ጋር ቁርኝት አሳይቷል ለማለት ያስችላል። ይህ ውጤት መምህራን በሁሉም ተላውጦዎች ላይ ካስመዘገቡት አሉታዊ አመለካከትና በክፍል ምልከታው ከታየው የቀዘቀዘ የክፍልና የትምህርት አያያዝ /class and subject management/ እንዲሁም ከአንስተኛ የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ አኳያ ሲመዘን,የሚጠበቅ ውጤት ተገኝቷል ማለትም አስችሏል።

በዚህ መሠረት በተማሪዎች አመለካከትና በፈተና ውጤታቸው መካከል ከግምት የሚገባ ዝምድና መኖሩን ይህ ጥናት አረጋግጧል። የተገኘው ውጤት "የተጠኙ ተማሪዎች የፈተና ውጤት ዝቅተኛ መሆን መንስዔው አመለካከታቸው ነው" የሚለውን የመነሻ መላምት አረጋግጦ በክለሳ ድርሳናት ከተጠቀሱ ምሁራን ሥራዎች ጋር ስምሙ ሆኗል ከሚል መደምደሚያ ያደርሳል። የቀረቡት መረጃዎች፣ የተገኙ ውጤቶችና የተቀመሩት ስታቲስቲካዊ ስሌቶችም ይህንኑ ያመለክታሉ።

## 5·2 የጥናቱ ግኝቶች /Findings/

በማጠቃለያው ክፍል የተጠቀሱትን ጥያቄዎችና የጥናት ዓላማዎች መነሻና ግብ በማድረግ፣ በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ምሁራን በሰጡት የአስተያየት ጭብጦች ላይ በመመሥረት በተካሄደው ጥናትና በተሰሩት ስታቲስቲካዊ ስሌቶች የሚከተሉት ውጤቶች ላይ ተደርሷል።

1· ተማሪዎች ለቋንቋውና ለትምህርቱ፤ ለመማሪያ መፅሐፉ፤ ለመምህሩ እንዲሁም ለተማሪዎች አመለካከት ምሥረታ ወላጅችና ማህበረሰቡ ያላቸውን ድርሻ በሚለኩ የተማሪዎች መጠይቅ ውጤት የሚከተሉት ግኝቶች ላይ ተደርሷል። ከቀረቡት አራት ተላውጦዎች ውስጥ ተማሪዎች ለአሥራ ሁለተኛ ክፍል መማሪያ መፅሐፍ አሉታዊ አመለካከት እንዳላቸው ውጤቱ አሳይቷል። ለመምህሩ ደግሞ ዝቅተኛ አዎንታዊ አመለካከት አስመዝግበዋል። የተማሪው ወላጅች፤ ባልንጀሮችና ማህበረሰቡ ተማሪዎች ለቋንቋው ትምህርት አዎንታዊ አመለካከት እንዲቀረፁ አጋዥ መሆናቸውን ውጤቱ አረጋግጧል።

2· የተማሪዎችን አመለካከት በፆታና በመኖሪያ ቦታ እንዲሁም በትምህርት ቤት በመክፈል በተደረገው ጥናት፣ የከተማ ነዋሪ ተማሪዎች ከገጠር ነዋሪዎች የተሻለ አመለካከት አላቸው። በሴቶችና በወንዶች መካከል የጐላ የአመለካከት ልዩነት አል ታየም። ከትምህርት ቤቶች የየካቲት 25/67 ተማሪዎች ከሁሉም ያነሰ የአመለካከት ውጤት ሲያስመዘግቡ የጊምቢቹ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ግን ከፍተኛ አዎንታዊ ውጤት አስገኝተዋል።

3· በነዚህ ተላውጦዎች መሠረት በጥናቱ የታቀፉ ተማሪዎች አጠቃላይ የአመለካከት ድምር አማካይ ውጤት ለአማርኛ ቋንቋና ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አዎንታዊ አመለካከት አሳይተዋል።

4· በአመለካከትና በፈተና ውጤታቸው መካከል ስላለው ተዛምዶ በተደረገው ስታቲስቲካዊ ቅመራ በመምህራን የፈተና ውጤት አሰጣጥ ስልት ልዩነት መኖሩ ቢታይም በተማሪዎች አመለካከትና በፈተና ውጤታቸው መካከል ፋይዳ ያለው ተዛምዶ መኖሩን ስሌቱ አሳይቷል።

5· የሁሉም ተማሪዎች የፈተና ውጤት የጠቅላላ ድምር አማካይ 57·6 ሲሆን ለቋንቋውና ለትምህርቱ የተመዘገበው የአመለካከት ድምር አማካይ ደግሞ 3·23 ነው። የፈተናው ውጤት ለማለፍ የሚያስችል እንጂ ከፍተኛ የሚባል አይደለም። የአመለካከቱም ዝቅተኛ አዎንታዊ እንጂ ከፍተኛ አይደለም። ስለዚህ ዝቅተኛ አዎንታዊ አመለካከት ከዝቅተኛ የማለፊያ ፈተና ውጤት ጋር ዝምድና እንዳለው አህዞቹ ያሳያሉ። ይህ ውጤት "በጥናቱ የታቀፉት ተማሪዎች ለውጤታቸው ዝቅተኛ

መሆን በቋንቋው ትምህረት ላይ ያላቸው አመለካከት ነው።” የሚለውን መላምት መልሷል ለማለት ይቻላል።

6· ለመምህራን በቀረቡት መጠይቆች መሠረት መምህራን ለተማሪዎቻቸው፣ ለመማሪያ መፅሐፉና ለመምህርነት ሙያቸው ያላቸው አመለካከት አሉታዊ መሆኑን የሰጡት ምላሽ ውጤት አሳይቷል።

7· በአራቱም ትምህርት ቤቶች በተደረገው የክፍል ምልከታ መምህራን የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ እንቅስቃሴ ለማበረታታት የሚያደርጉት ጥረት፣ የክፍል ውስጥ ሥርዓትን ለማስጠበቅ የሚጠቀሙበት ስልት፣ በጥቅሉ የክፍል አያያዝ ስልታቸው በአማካይ ሲታይ ድክመት ያለበት መሆኑ ተዘግቧል። የሚጠቀሙበት የማስተማር ሥነዘዴ መምህር-ተኮር ሲሆን የተማሪዎችም የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በተወሰኑ ጥቂት ተማሪዎች ዙሪያ የሚሽከረከር መሆኑ ታይቷል። ከዚህም በመነሳት ለተማሪዎች አመለካከትና የፈተና ውጤት ዝቅተኛ መሆን የመምህራን የአመለካከት ውጤትና የትምህርትና የክፍል አያያዝ ብቃት አነስተኛ መሆን ነው ከሚል መደምደሚያ ላይ ያደርሳል።

ከነዚህ ውጤቶች በመነሳት የዚህ ጥናት የመነሻ ጥያቄዎችና ዐብይ ዓላማዎች ተገቢውን መልስ አግኝተዋል።

## 5·3 አስተያየት/Recommendation/

ለጥናቱ ከተሰበሰቡት መረጃዎችና ከተገኙት ውጤቶች ላይ በመነሳት አጥኚው የሚከተሉትን የአስተያየት ነጥቦች ይሰነዝራል።

1· በጥናቱ ውጤት መሠረት ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋና ለትምህርቱ ያላቸው አመለካከት አዎንታዊ ቢሆንም /3·23/ ዝቅተኛ ነው። የፈተና ውጤታቸው ድምር አማካይም እንደዚሁ ለማለፊያ የሚያበቃ ውጤት /57·8/ ቢሆንም ከፍተኛ አይደለም። ስለዚህ ተማሪዎች ለቋንቋው ትምህርት ያላቸው አመለካከትና የሚያስመዘግቡት ውጤት አሁን ከተገኘው ውጤት የተሻለ ይሆን ዘንድ የትምህርት ባለሙያዎች፣ የሥርዓተ ትምህርት አዘጋጆች፣ የክልል ትምህርት ቢሮዎችና መምህራን እንዲሁም

ጉዳዩ የሚመለከታቸው ክፍሎች ሁሉ የተማሪዎች አመለካከት ከመማር ማስተማር ክንውኑና ከውጤታቸው ጋር ግንኙነት ያለው መሆኑን ከግምት በማስገባት ለፍላጎታቸው ተስማሚ፣ ለስሜታቸው ቅርብ፣ ለአመለካከታቸው ደጋፊ ሊሆኑ የሚችሉ የትምህርት መማሪያዎችን፣ የትምህርት ይዘቶችንና የማስተማር ስልቶችን … ወዘተ ከተማሪዎች ሁኔታ አኳያ ሊያቀርቡላቸው ቢጥሩ የተሻለ ውጤት ሊመዘገብ ይችላል።

2· ከተማሪዎች መጠይቅ በተገኘው ምላሽ መሠረት ተማሪዎቹ ለመማሪያው መፅሐፍ ያላቸው አመለካከት አሉታዊ /2·99/ ሆኗል። የመማሪያ መፃህፍት ተማሪዎች በቋንቋው የተለያዩ ክሂላትና የአጠቃቀም ዐውዶች ላይ የነቃ ልምምዶች እንዲያደርጉ የሚረዱና ከተማሪዎች ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ሰነዶች በመሆናቸው በዝግጅቱ ወቅት ከራሱ ከተማሪው የተነሳ የፍላጎት አሰሳ መረጃ ሊወሰዱ ያሻል። የመማሪያ መፃሕፍት አቀራረብ ጉድለት በተማሪዎች የመማር ፍላጐትና ለትምህርቱ በሚቀርፁት አመለካከት ላይ የሚያሳድሩት አፍራሽ ተፅዕኖ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ነው። በእርግጥ የእያንዳንዱን ተማሪ ፍላጐትና ዓላማ ሊያሟላ የሚችል መማሪያ መፅሐፍ ለማዘጋጀት አዳጋች ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ አቅም በፈቀደ መጠን ተቀራራቢ የሥነልቡና፣ የባህል፣ የቋንቋና የመማር ዓላማ ላላቸው የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችና አካባቢዎች ቢያንስ በአማካይ ስምሙ ሆነው ሊያገለግሉ እንዲችሉ በጥናት መረጃዎች ላይ የተመሠረቱ መፃህፍትን ለማቅረብ መሞከር የተሻለ እርምጃ ይሆናል። ነገር ግን "ሲለበሱ በጥናት ላይ ያልተመሠረተና የየአካባቢን የቋንቋ ችግር የማይፈታ ‥ " በሚል የመንደርደሪያ ሐሳብ አሸሞ ተራፊውን ተግባር መምህሩ እንዲሞላው ሀላፊነትን ሰጥቶ በየአካባቢው ከመበተን ይልቅ የተማሪውን ማንነት፣ አካባቢና ለትምህርቱ የቀረበበትን ሁኔታ በአማካይ ሊያሳዩ የሚችሉ መረጃዎችን ከየአካባቢው /ቢያንስ ከየክልሉ/ መሰብሰብ ቢቻል በተማሪዎች ዘንድ ተወዳጅነትን የማያጡ የትምህርት መማሪያዎችን ለማቅረብ አማራጭ መንገድ ይሆናል።

3· የትምህርት መማሪያዎችን የማዘጋጀት ሀላፊነት የመርሀ ትምህርትና የመማሪያ መፃህፍት አዘጋጆች እንዲሁም የሌሎች የትምህርት ባለሙያዎች ብቻ ሳይሆን ይል ቁንም የተማሪዎችን ፍላጐት፣ የቋንቋ ችሎታ፣ አካባቢና የመማር ዓላማ … ወዘተ በቅርብ ሆነው የሚያውቁ መምህራንም ጭምር ነው። ስለዚህም በዝግጅቱ ወቅት

መምህራን በእጅጉ /ቢቻል ተማሪዎችም/ እንዲሳተፉበት ቢደረግ የተማሪዎችም ሆነ የመምህራን አመለካከት ከአሁኑ የተሻለ አዎንታዊ ሆኖ ለበለጠ ውጤት ማብቃት አይሳነውም የሚል እምነት አለ።

4· በዚህ ጥናት የቀረበውን መጠይቅ ከሞሉ መምህራን የተገኘው ውጤት፤ ለመማሪያ መፅሐፉ፤ ለተማሪዎችና ይልቁንም ለሙያቸው ያላቸው አመለካከት አሉታዊ መሆኑን አስይቷል። ከፊሎች ደግሞ በሠለጠኑባቸው የትምህርት ተቋማት ያገኙት ሥልጠና ለመምህርነት ሙያ የማያበቃቸውና መምህር በመሆናቸውም ቅሬታ ያለባቸው መሆኑ ታውቋል ነገር ግን፡-

- የቋንቋ መምህራን ለተማሪዎች የቋንቋ ክሂላት ዕድገትና ለሚያደርጉት የዕለት በዕለት ልምምድ ቁልፍ ድርሻ ያላቸውና ለቋንቋውም ሞዴሎች ናቸው። በመሆናቸውም ተማሪዎች ለቋንቋው ትምህርት ያላቸውን አመለካከትና የክፍል ውስጥ የነቃ ተሳትፎ አሻሽሎ ከሚፈለገው ግብ ላይ ለማድረስ በቅድሚያ መምህራን ለሥራቸው ፍቅር፤ ለተማሪዎቻቸው ውዴታ ለማስተማር ብቁ ሊሆኑ ይገባል። ይህ በሌለበት ሁኔታ የሚሰጥ ትምህርት ፍሬ አልባ ስለሚሆን በጥናቱ የታቀፉት የአማርኛ መምህራን አመለካከታቸው ተቀይሮ ተማሪዎችን ወደ ቋንቋው ትምህርት ለመሳብ ጥረት ሊያደረጉ ይገባል።
- በሌላ በኩል ደግሞ እንደ መምህራኑ አስተያየት /መጠይቅ 36 እና ሐ/ በእርግጥም ብቃት ያለው የቋንቋ መምህር ሊያደርጋቸው በማይችል የስልጠና ፕሮግራም ውስጥ አልፈው የመጡ ከሆነ የማስተማር ፍላጐቱና ጥረቱ ብቻውን ከጥሩ ውጤት አያደርስም። ስለዚህ የሚመለከተው ክፍልና የቋንቋ መምህራንን የሚያሰለጥኑ ተቋማት ጉዳዩን ከግንዛቤ በማስገባት እነዚህና መሰል መምህራን የሙያ ማሻሻያ ኮርሶችን፤ ሴሚናርና ወርክሾፖችን፤ የተሀድሶ ስልጠናዎችን … ወዘተ የሚያገኙበትን መንገድ ቢያመቻቹ ችግሩን መቅረፍ ይቻላል።

5· ይህ ጥናት በተመሠረተበት አካባቢና ክልል በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ላይ ቁጥራቸው እጅግ የሚባሉ ጥናቶች አልተካሄዱም። የአካባቢውን ተማሪዎች የሁለተኛ ቋንቋ የመማር ፍላጐትና ዓላማ በውል ተረድቶ የተመቻቸ የቋንቋ ትምህርት ፕሮግራም ለመዘርጋት በነዚህና በመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ ሌሎች ጥናቶች ቢካሄዱና በተሠሩትም ለመጠቀም ቢቻል የአካባቢውን የትምህርት ጥራት መጠበቅና ማሳደግ

ይቻላል። በአካባቢውም ብቃት ያለው የተማረ የሰው ኃይል ለማፍራት እስተዋፅዖ ስላለው ጥናቱ በተለያየ ዘርፍ እንዲቀጥል ሊበረታታ ይገባል።

6· በዚህ ጥናት በተለያዩ ትምህርት ቤቶች በሚያስተምሩ መምህራን መካከል የፈተና ውጤት አሰጣጥ ስልት ልዩነት መኖሩ ታይቷል። ስለዚህም የክፍል መምህራን ስለሚጠቀሙበት የውጤት አሰጣጥ ስልትና በእጅጉም ስለሚያወጧቸው ፈተናዎች ብቃትና ተገቢነት አስመልክቶ ወደፊት ጥናት ሊደረግበት የሚገባ ጭብጠ ጉዳይ መሆኑን እንጠቁማለን። ከዚሁ ጋር ይህ ጥናት በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት በተማሪው የመማር እንቅስቃሴ ላይ ተፅዕኖ ከሚያደርሱ በርካታ ተላውጦዎች ውስጥ አንዱን ማለትም አመለካከትን ብቻ የቃኘ ነው። ነገር ግን ሌሎች ተላውጦዎችን ለምሳሌ የተማሪውን ዝንባሌ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዳራ፣ ሰብእና፣ ዕድሜ፣ ፆታ ··ወዘተ አስመልክቶ ጥናት ቢደረግ በአካባቢው አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ስለመማር ማስተማር ሂደትና ውጤት የተጠቃለለ መረጃና አዲስ የጥናት ውጤት ማግኘት ይቻላልየሚል ግምት አለ።

## ዋቢ መጻሕፍት /Reference Books/


Anderson, Anders Norrl (1967) "Multilingualism and Attitude: An Explorative Descriptive Study among Secondary School Students in Ethiopia and Tanzania" Uppsala University.

Braukemper, Ulrich(1973). "The Correlation of Oral Tradition and Historical Records in Southern Ethiopia: A Case Study of the Haddiya-Sidamo past" Journal of Ethiopian Studies. Vol.XI, No.w.

Bureau of Planning and Economic Development (1996) "Socio-Economic Profile". Southern Nations, Nationalities and Peoples Regional Government. Awassa (unpublished).

Chastain, Kenneth (1985) Developing Second Language Skills: Theory and Practice. San Diego: Harcourt Brace Jovanovich, Inc.

Cunningsworth, Alan (1984). Evaluating and Selecting EFL Teaching Materials: With a Glossary of Basic EFL Terms. Oxford: Heinemann.

Curtin, John B. (1979) "Attitude to Language Learning: The Adult Student" ELT Journal Vol.33, No. 4 .

Day, R.Richard (1990). "Teacher Observation in Second Language Teacher Education" Richards and Nunan (eds.) Second Language Teacher Education. Cambridge: CUP.

Dubin, Fraida and Elite Olshtain (1986) Course Design: Developing Programs and Materials for Language Learning. Cambridge: CUP.

Ellis, Rod (1985). Understanding Second Language Acquistion. Oxford: OUP.

Ethiopian Herald (1970) "Life and History of Hadiya People: Anthropological Studies" Vol. VIII No. 256, November 8, 1970.

Federal Republic of Ethiopia, Office of Population and Housing Census Commission Central Statistical Authority. (1995) The 1994 Population and Housing Census of Ethiopia: Results for Tigray Region. Vol.1, 1995. Addis Ababa.

__________(1995a) Results for Addis Ababa Region,. Vol. 1"Addis Ababa.

__________(1995b) Results for Amhara Region. Vol.1, part 1. Addis Ababa.

__________(1995c) Results for Gambela Region. Vol. 1 Addis Ababa.

__________(1995d)Results for Oromiya Region Vol.I, part I Addis Ababa.

__________(1995e) Results for Dire Dawa Provisional Administrative Region. Vol.I, Addis Ababa.

__________(1995f) Results for Harrari Region. Vol.I, Addis Ababa.

__________(1996a) Results for Southern Nations, Nationalities and People Region. No.q, part I. Addis Ababa.__________(1996b) Results for Afar Region Vol. I Addis Ababa.

__________(1996c) Results for Benishangual-Gumuz Region Vol. I, Addis Ababa.

Gardner, R.C. (1985) Social Psychology and Second Language Learning. The Role of Attitude and Motivation. London: Edward Arnoled, Ltd.

Gardner, R.C. and L. Kliksmom(1982) "Exchange on 'Gardner on Affect' Discussion of values as It Relates to the Attitude/Motivation Battery. A Response from Gardner" Journal of Applied Linguistics: Language Learning. Vol. 23, No. 1

Green, D. Jerry (1979). "Developing Language Attitudes, Habits and Skills." ELT Journal. Vol. 33, No. 3

Guilford, J.P. (1965) Fundamental Statistic in Psychology and Education. New York: McGraw-Hill Book Company.

Haile Bubamo (1971) "Some Notes on Fandaano Religion in Haddiya (Southern Shoa)" First Annual Conference of Historical Society of Ethiopia: State, Religion and Society in Ethiopian History. (April 30-May 2,1971)

________(1973). "Some Notes on Traditional Haddiya Women" Journal of Ethiopian Studies Vol. 11, No. 2.

Haile-Iyesus Engda Eshet (1984) "Haddiya Phonology" Ministry of Culture, Academy of Ethiopian Languages, Department of Linguistics. Addis Ababa (unpublished).

Harmer, Jermy (1990). The Practice of English Language Teaching. New York: Longman Group Ltd.

Hinkle, D.E.(et al.)(1988) Applied Statistics for Behaviourial Science. Dallas: Houghton Miffin Company.

Hutchenson, Tom and Alan Waters (1987) English for Specific Purpose: A Learning Centered Approach. Cambridge: CUP.

Knapp, E. Clifford(1972)"Attitude and Values in Environmental Education" Journal of Environmental Education. Vol.3, No.4

Koul, Lokesh (1988) Methodology of Educational Research (2nd rev. ed) Delhi: Hindustan Offset Prentetrs.

Lambert, E. Wallace(1974) "Culture and Language as Factors in Learning and Education" Paper presented at the 5th Annual Learning, Symposium. Washington. Vol.5.

______and G.R. Tucker (1972) Bilingual Education of Children: The St. Lambert Experiment. Massachusetts: Newbury House Publishers.

Lewis, Michael and Jo'mmie Hill (1985) Practical Techniques for Language Teaching. London: Commercial Colour Press.

Littlewood, William (1984) Foreign and Second Language Learning: Language Acquisition Research and It's Implication for the Classroom. Cambridge: CUP.

Ludwing, Jeanette (1983) "Attitude and Expectation: A Profile of Female and Male Students of College French, German and Spanish". The Modern Language Journals. Vol. 67, No. 3

Macnamara, John (1972) " Attitude and Learning Second Language" Language Attitudes: Current Trends and Prospects. Rogers, Shuy and Ralph Fasold (eds.) Washington D.C.: George Town University.

McArthur, Tom (1983) A Foundation Course for Language Teachers. Cambridge: CUP.

McLaughlin, Barry (1991) Theories of Second Language Learning. London: Edward Arnold.

Medhane Habte Ghiorhis (1986) The Attitude of Eleventh Grade Students Towards the Learning of English as Foreign Language. In Fire Selected Government Secondary Schools in Addis Ababa. A Thesis Presented to the School of Graduate Studies. Addis Ababa University.

Mehrens, A. William and Irvin, J. Lehmann (1991). Measurement and Evaluation in Education and Psychology. Sandiego: Harcourt Brace College Publishers.

Mueller, H. Theodor (1971) "Attitudes in Basic French Courses at the University of Kentucky" The Modern Language Journals Vol. 55, No.5.

Nunan, David(1990) "The Teacher as a Researcher' Brumfit and Mitchel (eds.) Research in Language Classroom. London: MacMillan Publishers.

Oller W.Jon (1992). "Gardner on Affect: A Reply to Gardner" Journal of Applied Linguistics, Language Learning. Vol. 23, No. 1.

Onoda, Lawrence (1976). "Personality Characteristics and Attitudes Toward Achievement Among Mainland High Achieving and Under Achieving Japanse-American Sansie" Journal of Educational Psychology. Vol. 68, No. 2.

OppenHeim, A.N. (1984) Questionnaire Design and Attitude Measurement. London: Gower Publishing Company, Ltd.

Pikunas, Justin (1976) Human Development: An Emergent Science. New York: McGraw-Hill Book Company.

Rienert, Harry (1970) "Student Attitudes Towards Foreign Language" The Modern Language Journals. Vol. 54, No. 2.

Richards, Jack C. (1987) The Context of Language Teaching. Cambridge: CUP..

__________ (1990) The Language Teaching Matric. Cambrdige: CUP.

Rivers, M. Wilga (1981) Teaching English Language Skills. chicago: The University of Chicago Press.

__________ (1983) Communicating Naturally in a Second Language: Theory and Practice in Language Teaching. Cambridge: CUP.

Robinson, C.Paulin (1991) ESP Today: A Practioner's Guide. London: Printice Hall International, Ltd.

Sheldon, E.(1987) ELT Textbooks and Materials: Problems in Evaluation and Development. London: Modern English Publishers.

Smith, Alfred, N. (1971) "The Importance of Attitude in Foreign Language Learning" The Modern Language Journals Vol. 55, No. 2.

Spolsky, Bernard (1969) "Attitudinal Aspects of Second Language Learning " Journal of Applied Linguistics: Language Learning. Vol. 19, No. 3.

__________ (1989) Conditions for Second Language Learning. Oxford: CUP.

Stinson, D. Lloyd (1990) "Two Cushitic Languages: Haddiya". In Languages in Ethiopian: Bender et al. eds.) Oxford: OUP.

Taddele Adamu (1990) "Individual Difference in Second Language Learning in Formal Context." Thesis submitted for the Degree of Ph.D Department of Linguistic Science: University of Reading.

Taron, Elaine and George Yule (1989) focus on the Language Learner. Oxford: OUP/

Tassew Gebre (1983) "The Family System of Haddiya Ethnic Group". The Department of Applied Sociology, College of Social Science, Addis Ababa University, in Partial Fulfilment of the Requirments for Degree of Bachler Arts. Addis Ababa University.

Tsehaye Teffera (1977) "A Sociolinguistic Survey of Language Use and Attitude Towards Languages in Ethiopia: Implication for Language Policy in Education." (Ph.D Thesis in Linguistics). George town University,

Underwood, Mary (1987). Effective Class Management. New York: Longman Inc.

White, V. Ronald (1988) The ELT Curriculum : Design, Innovation and Management. Oxford: Basil Blackmell , Ltd.

Wright, Tony (1987) Roles of Teachers and Learners. Oxford: OUP.

Yule, George (et al.) (1985) "Investigating Aspects of the Language Learner's Confidence: An Application of the Theory of Signal Dictation" Journal of Applied Linguistics: Language Learning Vol. 35, No. 4.

---

* CUP: Cambridge University Press.
* OUP: Oxford University Press.

ሀዲያ ዞን ትምህርት መምሪያ /1988 ዓ·ም/ "በሀዲያ ዞን ትምህርት መምሪያ ለሁለተኛው የትምህርት አመራርና አስተዳደር ጉባኤ የቀረበ ሪፖርት" /ሆሳዕና/።

ላፒሶ ጌ·ደሌቦ /1982/ የኢትዮጵያ ረጅም የህዝብና የመንግሥት ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት።

ቆጠራ ዮሐንስ /1975 ዓ·ም/ "የሀዲይኛ ተረትና ምሳሌዎች፣" በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነፅሑፍ ክፍል ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ፅሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ።

የአፀደ ሕፃፃት መደበኛ ትምህርት፣ የሥርዓተ ትምህርት ዋና ክፍል፣ የአማርኛው ትምህርት ቡድን /1984 ዓ·ም/ የአማርኛ ቋንቋ ሲለበስ፣ 12ኛ ክፍል። ት·መ·መ·መ·ድ· አዲስ አበባ።

ብርሃኑ ገብረማርያም /1976 ዓ·ም/ "ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸው አመለካከት/Attitude/ በስድስት የአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች"፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነፅሑፍ ክፍል ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ፅሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ።

ታሪኩ ፋንታዬ /1988 ዓ·ም/ "የአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በአማርኛና በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸው አመለካከት /Attitude/፤" በቋንቋዎች ተቋም አማርኛን በማስተመር ትምህርት ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ቴሲስ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ።

ወርቂ በሻዳ /1982 ዓ·ም/ "የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የማስተማሪያ ቋንቋ ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ ቢለወጥ በተማሪዎችና በመምህራን ዘንድ ያለውን አመለካከት ለማወቅ በአምስት የአዲስ አበባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተደረገ ጥናት።" የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነፅሑፍ ክፍል የአርትስ ባችለር ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉ ነጥቦች ከፊሉን ለማማላት የቀረበ ፅሑፍ። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ።

አየለ መሎሬ /1986 ዓ·ም/ "የሀዲያ ህብረተሰብ የልቅሶ ሥነሥርዓት"፣ የአርትስ ባችለር ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉ ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናታዊ ፅሑፍ። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ።

የሀዲያ ዞን ፕላንና ኢኮኖሚ ልማት መምሪያ /1987 ዓ·ም/ "የሀዲያ ዞን መስተዳድር የስታቲስቲክስ መፅሔት" /ያልታተመ/። ሆሳዕና።

የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽህፈት ቤት /1985 ዓ·ም/ አጠቃላይ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ረቂቅ" /ያልታተመ/ አዲስ አበባ።

ጣሰው ገብሬ /1988 ዓ·ም/ "ለሀዲያ ልማት ማህበር ሁለተኛ ዓመት ጠቅላላ ጉባኤ የቀረበ የሥራ ክንውን።" ሆሳዕና /ያልታተመ/።

አባሪ 1

ተማሪዎች በየተላውጠው ያስመዘገቡት አመለካከት፥ የክፍል ፈተናና የእስታሬቂ ቲ - ስኮር ውጤት

| የተማሪ መለያ ቁጥር | ተላውጦዎች | | | | ድምር | አማካይ | የፈተና ውጤት | | | ቲ-ስኮር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 | 4 | | | | | | |
| | | | | | | | 1ኛ | መሰናዶ | አማካይ | |
| 1 | 36 | 35 | 26 | 37 | 134 | 2.79 | 54 | 47 | 50.5 | 47.25 |
| 2 | 51 | 33 | 25 | 40 | 149 | 3.1 | 49 | 56 | 52.5 | 49.42 |
| 3 | 41 | 27 | 30 | 31 | 129 | 3.69 | 42 | 31 | 36.5 | 32.07 |
| 4 | 49 | 44 | 32 | 41 | 166 | 3.46 | 43 | 58 | 50.5 | 47.25 |
| 5 | 42 | 50 | 38 | 36 | 166 | 3.46 | 55 | 49 | 52 | 48.88 |
| 6 | 45 | 45 | 45 | 49 | 184 | 3.83 | 76 | 61 | 68.5 | 66.78 |
| 7 | 37 | 35 | 28 | 33 | 133 | 2.77 | 55 | 46 | 50.5 | 47.25 |
| 8 | 39 | 24 | 35 | 44 | 142 | 2.96 | 72 | 60 | 66 | 64.07 |
| 9 | 40 | 29 | 35 | 45 | 149 | 3.10 | 62 | 35 | 48.5 | 45.08 |
| 10 | 51 | 44 | 44 | 41 | 180 | 3.75 | 58 | 50 | 54 | 51.05 |
| 11 | 41 | 32 | 37 | 27 | 137 | 2.85 | 50 | 36 | 43 | 39.12 |
| 12 | 44 | 26 | 38 | 37 | 145 | 3.02 | 54 | 70 | 62 | 56.47 |
| 13 | 36 | 35 | 29 | 48 | 148 | 3.08 | 45 | 52 | 48.5 | 45.08 |
| 14 | 47 | 39 | 46 | 48 | 180 | 3.75 | 61 | 53 | 57 | 54.31 |
| 15 | 31 | 37 | 35 | 44 | 147 | 3.06 | 55 | 37 | 46 | 43.37 |
| 16 | 51 | 38 | 31 | 49 | 169 | 3.52 | 44 | 51 | 47.5 | 43.99 |
| 17 | 38 | 36 | 27 | 27 | 128 | 2.67 | 53 | 58 | 55.5 | 52.68 |
| 18 | 43 | 30 | 29 | 41 | 143 | 2.98 | 79 | 49 | 64 | 61.89 |
| 20 | 31 | 31 | 31 | 36 | 129 | 2.69 | 72 | 61 | 66.5 | 64.61 |
| 21 | 39 | 39 | 42 | 46 | 166 | 3.46 | 59 | 60 | 59.5 | 57.02 |
| 22 | 47 | 38 | 23 | 46 | 154 | 3.21 | 67 | 52 | 59.5 | 57.02 |
| 23 | 46 | 44 | 42 | 44 | 176 | 3.67 | 80 | 61 | 70.5 | 68.95 |
| 24 | 26 | 38 | 31 | 52 | 147 | 3.06 | 69 | 69 | 69 | 67.32 |
| 25 | 36 | 38 | 31 | 40 | 145 | 3.02 | 66 | 69 | 67.5 | 65.69 |
| 26 | 38 | 28 | 36 | 35 | 137 | 2.85 | 51 | 48 | 49. 5 | 46.17 |
| 27 | 39 | 26 | 40 | 37 | 142 | 2.96 | 50 | 56 | 53 | 46.97 |
| 28 | 35 | 28 | 32 | 40 | 135 | 2.81 | 64 | 52 | 58 | 55.39 |
| 29 | 44 | 30 | 37 | 42 | 153 | 3.19 | 62 | 33 | 47.5 | 43.99 |
| 30 | 41 | 42 | 38 | 48 | 169 | 3.52 | 74 | 56 | 65 | 62.98 |
| 31 | 47 | 20 | 20 | 44 | 131 | 2.73 | 68 | 60 | 64 | 61.89 |
| 32 | 29 | 35 | 25 | 44 | 133 | 2.77 | 41 | 58 | 49 | 46.17 |
| 33 | 39 | 26 | 41 | 46 | 152 | 3.17 | 76 | 60 | 68 | 66.24 |
| 34 | 47 | 45 | 48 | 55 | 195 | 4.06 | 79 | 70 | 74.5 | 73.29 |
| 35 | 32 | 32 | 27 | 47 | 138 | 2.88 | 61 | 37 | 49 | 45.63 |
| 36 | 40 | 35 | 39 | 37 | 130 | 2.71 | 30 | 52 | 42 | 38.58 |
| 37 | 46 | 41 | 34 | 34 | 155 | 3.23 | 60 | 56 | 58 | 55.39 |
| 38 | 43 | 27 | 26 | 34 | 153 | 3.15 | 63 | 52 | 57.5 | 54.85 |
| 39 | 32 | 30 | 35 | 37 | 134 | 2.79 | 45 | 50 | 47.5 | 43.99 |
| 40 | 40 | 42 | 40 | 39 | 161 | 3.31 | 51 | 55 | 53 | 49.90 |
| 41 | 25 | 35 | 39 | 24 | 123 | 2.56 | 52 | 58 | 55 | 106.66 |
| 42 | 14 | 42 | 26 | 35 | 117 | 2.44 | 48 | 56 | 52 | 100.18 |
| 43 | 39 | 50 | 26 | 39 | 154 | 3.21 | 70 | 50 | 60 | 117.45 |
| 44 | 40 | 35 | 34 | 40 | 149 | 3.10 | 67 | 54 | 60.5 | 118.53 |
| 45 | 43 | 43 | 40 | 36 | 162 | 3.38 | 54 | 52 | 53 | 102.34 |
| 46 | 45 | 35 | 39 | 44 | 163 | 3.40 | 68 | 56 | 62 | 121.76 |
| 47 | 46 | 46 | 39 | 42 | 173 | 3.60 | 59 | 52 | 55.5 | 107.74 |
| 48 | 46 | 29 | 35 | 47 | 157 | 3.27 | 70 | 44 | 57 | 110.98 |

አባሪ 1 (የቀጠለ)

| የተማሪ መለያ ቁጥር | ተላውጦዎች | | | | ድምር | አማካይ | የፈተና ውጤት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 | 4 | | | 1ኛ | መሰናዶ | አማካይ | ቲ-ስኮር |
| 49 | 44 | 34 | 42 | 28 | 148 | 3.08 | 61 | 58 | 59.5 | 116.37 |
| 50 | 29 | 28 | 51 | 20 | 128 | 2.67 | 55 | 54 | 54.5 | 105.58 |
| 51 | 45 | 28 | 34 | 41 | 148 | 3.08 | 54 | 64 | 59 | 115.29 |
| 52 | 30 | 30 | 24 | 35 | 119 | 2.48 | 68 | 50 | 59 | 115.29 |
| 53 | 37 | 36 | 36 | 36 | 145 | 3,02 | 69 | 50 | 59.5 | 116.37 |
| 54 | 35 | 32 | 47 | 47 | 161 | 3.35 | 61 | 66 | 63.5 | 124.99 |
| 55 | 48 | 34 | 58 | 50 | 190 | 3.96 | 69 | 48 | 58.5 | 114.21 |
| 56 | 41 | 37 | 42 | 37 | 157 | 3.27 | 62 | 52 | 57 | 110.98 |
| 57 | 44 | 39 | 43 | 41 | 167 | 3.48 | 56 | 51 | 53.5 | 103.42 |
| 58 | 50 | 33 | 32 | 43 | 158 | 3.29 | 52 | 53 | 52.5 | 101.26 |
| 59 | 27 | 26 | 32 | 44 | 129 | 2.69 | 50 | 58 | 54 | 104.49 |
| 60 | 37 | 33 | 34 | 42 | 146 | 3.04 | 53 | 49 | 51 | 98.03 |
| 61 | 41 | 38 | 41 | 44 | 164 | 3.42 | 59 | 42 | 50.5 | 96.95 |
| 62 | 34 | 32 | 28 | 32 | 126 | 2.63 | 49 | 54 | 51.5 | 99.11 |
| 63 | 47 | 32 | 37 | 41 | 157 | 3.27 | 58 | 60 | 59 | 115.29 |
| 64 | 44 | 32 | 35 | 55 | 166 | 3.46 | 66 | 47 | 56.5 | 109.89 |
| 65 | 25 | 32 | 37 | 24 | 118 | 2.46 | 46 | 47 | 46.5 | 88.32 |
| 66 | 42 | 43 | 40 | 52 | 177 | 3.69 | 65 | 50 | 57.5 | 112.05 |
| 67 | 36 | 28 | 28 | 31 | 123 | 2.56 | 43 | 56 | 47.5 | 90.47 |
| 68 | 37 | 35 | 34 | 44 | 150 | 3.13 | 55 | 49 | 52 | 100.18 |
| 69 | 42 | 36 | 23 | 41 | 142 | 2.96 | 45 | 49 | 47 | 89.39 |
| 70 | 40 | 36 | 37 | 33 | 146 | 3.04 | 68 | 58 | 63 | 123.92 |
| 71 | 34 | 42 | 36 | 40 | 152 | 3.17 | 88 | 44 | 66 | 56.88 |
| 72 | 40 | 40 | 42 | 35 | 157 | 3.27 | 70 | 47 | 58.5 | 49.64 |
| 73 | 32 | 28 | 38 | 36 | 134 | 2.79 | 71 | 48 | 59.5 | 50.61 |
| 74 | 43 | 44 | 30 | 37 | 154 | 3.21 | 50 | 47 | 48.5 | 39.99 |
| 75 | 45 | 31 | 30 | 44 | 150 | 3.13 | 67 | 43 | 55 | 46.27 |
| 76 | 41 | 48 | 40 | 47 | 176 | 3.67 | 64 | 41 | 47.5 | 39.03 |
| 77 | 44 | 43 | 37 | 43 | 167 | 3.48 | 42 | 42 | 42 | 55.73 |
| 78 | 40 | 45 | 54 | 43 | 182 | 3.79 | 62 | 47 | 55 | 46.27 |
| 79 | 28 | 33 | 22 | 44 | 127 | 2.65 | 42 | 60 | 51 | 42.41 |
| 80 | 45 | 38 | 31 | 38 | 152 | 3.17 | 63 | 47 | 55 | 46.27 |
| 81 | 47 | 44 | 41 | 47 | 179 | 3.73 | 77 | 44 | 60.5 | 51.57 |
| 82 | 35 | 49 | 32 | 32 | 148 | 3.08 | 54 | 41 | 47.5 | 39.03 |
| 83 | 45 | 37 | 45 | 45 | 172 | 3.58 | 71 | 36 | 53.5 | 44.82 |
| 84 | 43 | 36 | 32 | 32 | 143 | 3.02 | 78 | 47 | 62.5 | 53.50 |
| 85 | 36 | 32 | 37 | 37 | 142 | 2.46 | 55 | 45 | 50 | 41.44 |
| 86 | 44 | 38 | 39 | 40 | 161 | 3.35 | 58 | 33 | 45.5 | 37.10 |
| 87 | 32 | 37 | 35 | 24 | 128 | 2.67 | 63 | 63 | 63 | 53.98 |
| 88 | 44 | 34 | 43 | 41 | 162 | 3.31 | 62 | 64 | 63 | 53.98 |
| 89 | 39 | 39 | 40 | 42 | 160 | 3.33 | 63 | 32 | 47.5 | 39.03 |
| 90 | 39 | 34 | 35 | 40 | 148 | 3.08 | 92 | 61 | 76.5 | 67.01 |
| 91 | 46 | 39 | 43 | 37 | 165 | 3.44 | 71 | 41 | 56 | 47.23 |
| 92 | 47 | 39 | 20 | 39 | 145 | 3.02 | 78 | 52 | 65 | 55.91 |
| 93 | 41 | 35 | 41 | 49 | 166 | 3.46 | 52 | 30 | 41 | 32.76 |
| 94 | 44 | 32 | 46 | 43 | 165 | 3.44 | 85 | 50 | 67.5 | 58.33 |
| 95 | 41 | 39 | 40 | 42 | 162 | 3.38 | 93 | 55 | 74 | 64.59 |

አባሪ 1 / የቀጠለ/

| | ተሳውጠዎች | | | | ድምር | አማካይ | የፈተና ውጤት 1ኛ | መሰናዶ | አማካይ | | ቲ-ስኮር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 96 | 49 | 35 | 52 | 43 | 179 | 3.73 | 63 | 61 | 62 | - | 59.71 |
| 97 | 48 | 37 | 48 | 46 | 179 | 3.73 | 54 | 65 | 59 | 5 | 56.62 |
| 98 | 47 | 31 | 47 | 43 | 168 | 3.5 | 69 | 66 | 67 | 5 | 66.49 |
| 99 | 50 | 35 | 39 | 42 | 166 | 3.46 | 65 | 60 | 62 | 5 | 60.33 |
| 100 | 46 | 44 | 38 | 47 | 175 | 3.65 | 65 | 48 | 56 | 5 | 52.92 |
| 101 | 46 | 46 | 43 | 39 | 174 | 3.63 | 39 | 40 | 34 | 5 | 31.95 |
| 102 | 45 | 43 | 50 | 45 | 183 | 3.81 | 51 | 32 | 56 | 5 | 52.92 |
| 103 | 49 | 40 | 56 | 43 | 188 | 3.92 | 78 | 67 | 72 | 5 | 72.66 |
| 104 | 46 | 44 | 33 | 35 | 158 | 3.29 | 70 | 58 | 64 | - | 68.18 |
| 105 | 44 | 31 | 33 | 45 | 153 | 3.19 | 63 | 58 | 60 | 5 | 57.86 |
| 106 | 46 | 36 | 56 | 51 | 189 | 3.94 | 55 | 56 | 55 | 5 | 51.69 |
| 107 | 51 | 49 | 52 | 44 | 196 | 4.08 | 68 | 59 | 63 | 5 | 61.56 |
| 108 | 37 | 29 | 41 | 43 | 150 | 3.13 | 68 | 67 | 67 | 5 | 66.49 |
| 109 | 47 | 30 | 32 | 45 | 154 | 3.21 | 63 | 61 | 62 | - | 59.71 |
| 110 | 42 | 31 | 54 | 42 | 169 | 3.52 | 74 | 66 | 70 | - | 69.58 |
| 111 | 40 | 42 | 40 | 37 | 159 | 3.31 | 69 | 67 | 68 | - | 67.11 |
| 112 | 45 | 33 | 37 | 44 | 159 | 3.31 | 68 | 65 | 66 | 5 | 65.26 |
| 113 | 51 | 41 | 43 | 42 | 177 | 3.69 | 76 | 71 | 73 | 5 | 73.89 |
| 114 | 50 | 43 | 39 | 47 | 179 | 3.73 | 67 | 64 | 65 | 5 | 64.03 |
| 115 | 36 | 30 | 40 | 42 | 148 | 3.08 | 70 | 59 | 64 | 5 | 62.79 |
| 116 | 39 | 31 | 35 | 40 | 145 | 3.02 | 48 | 49 | 48 | 5 | 43.06 |
| 117 | 52 | 45 | 46 | 48 | 191 | 3.98 | 67 | 68 | 67 | 5 | 66.49 |
| 118 | 52 | 43 | 48 | 41 | 184 | 3.83 | 61 | 72 | 66 | 5 | 65.26 |
| 119 | 38 | 23 | 49 | 36 | 146 | 3.04 | 72 | 75 | 73 | 5 | 73.89 |
| 120 | 45 | 29 | 47 | 46 | 167 | 3.48 | 77 | 76 | 76 | 5 | 77.59 |
| አጠ. ድምር | 4923 | 4309 | 4482 | 4886 | 18600 | 3.27 | 7371 | 6402 | 6911.5 | | 8100.6 |

* ከየትምህርት ቤቶች የተወሰዱ ተማሪዎች መለያ

1 - 40 ዋችሞ

41-70 የካቲት

71-95 ሞርሲጦ

96-120 ጊምቢቹ

አባሪ 2

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት
የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

በሀዲያ ዞን በሚገኙ አራት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሚማሩ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሀድይኛ በሆነ የ 12ኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሞላ በጠይቅ።

የመጠይቁ ዓላማ:-ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ለትምህርቱ፣ ለመማሪያ መፅሐፉ፣ ለመምህሩና ለማስተማሪያ ዘዴው ያላቸውን አመለካከት ለማጥናት ብቻ የሚፈልግ ነው።

ለጠይቁ ለ ኤም . ኤ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ፅሁፍ የሚያገለግል ሲሆን ውጤቱም ለተማሪዎች ፣ ለመምህራን ፣ ለትምህርት መሳሪያ አዘጋጆች ... ወዘተ. ጥቅም ይሰጣል ተብሎ ይታመናል።

ማሳሰቢያ:-1.መጠይቁ ሲሞላ ሥም መፃፍ አያስፈልግም።
2.ለመጠይቁ የሚሰጠው መልስ በሚስጥር የሚያዝ ለው።

3.የጥናቱ ውጤት ከተፈለገው ዓላማ ላይ ያደርስ ዘንድ ከተማሪዎች እውነተኛ መልስ ይጠብቃል። ስለዚህም የጥያቄቆቹን መንፈስ ለመመርመር ያለምንም ፍራቻና ጥርጣሬ ትክክል ነው ብላችሁ የምታምኑበትን መልስ በነፃ ፍላጎት እንድትሞሉ ትጠየቃላችሁ።

4.ጥያቄዎቹና የሚሰጥባቸው መልሶች ከላይ በዓላማው ከተጠቀሰው ጉዳይ በስተቀር ለሌላ ለምንም ጉዳይ አልደማይውሉና ችግር ሊፈጥሩ እንደማይችሉ በቅድሚያ እንዲታወቅ ያስፈልጋል።

5.የመጠይቁን አሞላል ስልት በተመለከተ:-በእያንዳንዱ ጥያቄ ፊት ለፊት አምስት አማራጭ መልሶች በሠንጠረዥ መልክ ተሰጥተዋል። ለጥያቄው መልስ ነው ብላችሁ የምታምኑበትን ትክክለኛ መልስ የ "X" ምልክት በሳጥኑ ውስጥ በማስቀመጥ ማረጋገጥ ይገባል። አማራጭ መልሶቹ ለአንድ ጥያቄ ከቀረቡት ውስጥ ሁለቱ "የመስማማትን" ሁለቱ ደግሞ "አለመስማማትን" ሀሳብ የያዙ ሲሆኑ አንዱ ደግሞ የመስማትንም ሆነ ያለመስማማትን "ሀሳብ ለመስጠት መቸገርን " የያዘ ነው።

የመስማማትንም ሆነ ያለመስማማትን ሀሳብ የያዙት አማራጮች በጥያቄው መንፈስ ላይ "በጣም መስማማትን" ወይም "በመጠኑ መስማማትን" የሚጠቁሙና በደረጃ የሚያስቀምጡ ሲሆን በተቃራኒው ያሉትም እንደዜሁ በጥያቄው ላይ "በመጠኑ አለመስማማትን" እና "ፍፁም አለመስማማትን" የሚያማርጡ በመሆናቸው በጥያቄው ላይ ያለውን የመስማማት ወይም አለመስማማት ደረጃን በመወሰን መልስ እንዲሰጥበት ያስፈልጋል::

በዚህ መሰረት የቀረቡ ጥያቄዎች እንዲመለሱለት የመጠይቁ አቅራቢ በትህትና ሲያሳስብ ለሚደረግለት ቅን ትብብር ሁሉ በቅድሚያ ያመሰግናል:: በመጨረሻም የሚደረስበትም ውጤት የናንተ የትብብር ፍሬ ውጤትም ጭምር መሆኑን በደስታ ይገልፃል::

የጥናቱ አቅራቢ

ታህሳስ፣1989 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

1.ከዚህ በታች በተሰጡት ባዶ ቦታዎች ላይ ተገቢውን መልስ በመሙላት አረጋግጡ::

1.ፆታ ______________ ዕድሜ ______________
2.የአፍ መፍቻ ቋንቋ ______________________
3.ብሔረሰብ ______________________________
4.መኖሪያ ቦታ /በአንድ ላይ የ "X" ምልክት አድርጉ /
ከተማ ____________ ገጠር ____________

II.ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ለእያንዳንዱ ከተሰጡት አምስት አማራጮች ውስጥ መልስ ሊሆን የሚችለው ቦታ ላይ " X" በማድረግ መልሳችሁን ስጡ::

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | ለመወሰን ያስቸግረኛል | አልስማማም | ፈፅሞ አልስማማም |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ከእንግሊዝ ይልቅ የአማርኛ ትምህርት ክፍለ ግዜ ቢያመልጠኝ በጣም ይጎዳኛል:: | | | | | |
| 2 | ግድ ሆኖብኝ እንጂ የአማርኛ ቋንቋን ባልማረው እመርጣለሁ:: | | | | | |
| 3 | በሁለተኛ ደረጃ የሁሉም ትምህርቶች መስጫ ቋንቋ ቢሆን እመርጣለሁ:: | | | | | |
| 4 | በሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና የአማርኛ ውጤት እንደ እንግሊዝኛና ሂሳብ ትምህርቶች የማይቀር ተደማሪ /ኮምፐልሰሪ/ አለመሆኑን ጥሩ ነው:: | | | | | |
| 5 | በሳምንት የአማርኛ ክፍለ ጊዜ ብዛት በጣም ስለሚያንስ ቢጨመር ይጫላል:: | | | | | |
| 6 | የአማርኛ ትምህርት ብዙም ስለማይጠና ሰፊ ጊዜ ሰጥቼ ለፈተና የምዘጋጀው ለሌሎች ከባድ ለሆኑ ትምህርቶች ነው:: | | | | | |
| 7 | አማርኛ ቋንቋ በሀዲያ ዞን የሥራ ቋንቋ ሆኖ ቢያገለግል እወዳለሁ:: | | | | | |
| 8 | በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የፈተና ውጤቴ ዘወትር ዝቅተኛ ነው:: | | | | | |
| 9 | ወደፊት በኮሌጅና በዩኒቨርሲቲ የአማርኛ ቋንቋ ለማጥናት ከፍተኛ ፍላጎት አለኝ:: | | | | | |
| 10 | በአማርኛ ቋንቋ ያለችግር በትክክል መናገርና መፃፍ እችላለሁ:: | | | | | |
| 11 | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በጣም ከባድና አስቸጋሪ ነው:: | | | | | |
| 12 | የአማርኛን ትምህርት አጠናሁትም አላጠናሁትም የፈተና ውጤቴ ጥሩ ነው:: | | | | | |
| 13 | የአማርኛ መማሪያ መፅሐፌን ሁልጊዜ እንደሌሎች ትምህርቶች አጠናዋለሁ:: | | | | | |
| 14 | አሁን ያለው የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍ በአዲስ ቢለወጥ የመማር ፍላጎቴ ይነቃቃ ነበር:: | | | | | |
| 15 | የመማሪያው መፅሐፍ በተማሪዎች ፍላጎትና የዕውቀት ደረጃ መሠረት የተዘጋጀ ስለሆነ ያረካኛል:: | | | | | |

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | ለመወሰን ያስቸግረኛል | አልስማማም | ፈጽሞ አልስማማም |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 16 | የመማሪያው መፅሐፉ ሳቢነት የሌለው፥አሰልቺና አስቸጋሪ ነው:: | | | | | |
| 17 | መፅሐፉ ያላስተማሪ እንኳን ለማጥናት ብቃት ያለው ጥሩ ዝግጅት ነው:: | | | | | |
| 18 | መፅሐፉ የልቦለድ ፅሁፎችን በብዛት ቢይዝ ያስደስተኛል:: | | | | | |
| 19 | መፅሐፉ በፊት ያልነበረኝን የመፃፍና የማንበብ ችሎታዬን አዳብሮልኛል:: | | | | | |
| 20 | ለ 12ኛ ክፍል ተብሎ የተዘጋጀው መማሪያ መፅሐፍ ይዘት ከሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ጋር የጠበቀ ግንኙነት የለውም:: | | | | | |
| 21 | በመማሪያው መፅሐፉ ውስጥ የቀረቡት መልመጃዎች በአካባቢያችን ልናገኘው ወይም ልንሰራው የማንችለውን ጉዳይ እንድንሰራ የሚያዙ ናቸው:: | | | | | |
| 22 | በመማሪያው መፅሐፍ ውስጥ የቀረቡት መልመጃዎች በተግባር ሊሰሩ የሚችሉና ቀላል ናቸው:: | | | | | |
| 23 | በመፅሐፉ ውስጥ የቀረቡት መልመጃዎችና ምንባቦች ክብደት አማርኛ የሁለተኛ ቋንቋውም ሆነ የአፍ መፍቻው ለሆነ ተማሪ ዕኩል ናቸው:: | | | | | |
| 24 | የቀረቡት መልመጃዎችና ምንባቦች ለቋንቋ ትምህርት የሚያግዙና እርስ በርሳቸው የማይገናኙ ናቸው:: | | | | | |
| 25 | መምህራችን የሚሰጡትን የቤት ሥራ አዘውትረው ስለሚያርሙ ያልገባንን ጠይቀን ለመረዳት ወይም ክስህተታችን ለመማር ሰፊ ዕድል አለን:: | | | | | |
| 26 | በቂ ችሎታና የማስተማር ብቃት ያለው ሌላ መምህር ቢመደብ ትምህርቱን በሚገባ ለመከታተል ፍላጎቴ ይነሳሳል:: | | | | | |
| 27 | መምህሩ ክፍል ሲገቡ በቂ ዝግጅት የሚያደርጉና ለሙያቸው ፍቅር ያላቸው ናቸው:: | | | | | |
| 28 | የአማርኛ መምህራችን የሙያ ማሻሻያ ኮርስ መከታተል ወይም የትምህርት ደረጃቸውን ማሻሻል አለባቸው:: | | | | | |

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | በጣም እስማማለው | እስማማለው | ለመወሰን ያስቸግረኛል | አልስማማም | ፈፅሞ አልስማማም |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 29 | መምህሩ ከመማሪያው መፅሐፍ ውጭ ከጋዜጣ፥ከመፅሔቶችና ከመፅሐፍት የተለያዩ ፅሁፎችን ክፍል ውስጥ በማምጣት በቋንቋው ላይ ያለንን ችሎታ እንድናዳብር ይረዱናል:: | | | | | |
| 30 | የሚሰጠን የአማርኛ ፈተና ከተማርነው ጋር ስለማይገናኝ ውጤታችን ዝቅተኛ ይሆናል:: | | | | | |
| 31 | የአማርኛ መምህራችን የማስተማር ስልትና አቀራረብ ማራኪና ሳቢነት አለው:: | | | | | |
| 32 | መምህራችን በአማርኛ ሲፅፉ ሲናገሩ የቋንቋ ግድፈት ስለሚያደርጉ ተማሪው የሚፈፅማቸውን ስህተቶች ፈጥኖ ለማረም አይችሉም:: | | | | | |
| 33 | መምህሩ አሁን የሚጠቀሙበትን የማስተማር ስልትና ዘዴ አሻሽለው ባይቀርቡም ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያለኝ ፍላጎት ከፍተኛ ለው:: | | | | | |
| 34 | የአማርኛ መምህራችን በክፍል ውስጥ የሚቆጡና የሚሳደቡ ስለሆኑ ለመቅረብም ሆነ ጥያቄ ለመጠየቅ እንፈራቸዋለን:: | | | | | |
| 35 | መምህራችን በክፍል ውስጥ ሁሉንም ተማሪዎች በዕኩልነት የሚያዩና በውጤት አሰጣጥም የማያዳሉ ናቸው:: | | | | | |
| 36 | የአማርኛ ቋንቋ መምህራችን በቋንቋው ትምህርት ላይ የተሟላ ዕውቀትና ችሎታ አላቸው:: | | | | | |
| 37 | ጓደኞቼ የአማርኛ ትምህርት ክፍለጊዜን በጉጉት ይጠብቃሉ:: | | | | | |
| 38 | በአማርኛ ስናገር በማደርገው ስህተት በአማርኛ አፋቸውን የፈቱ የክፍል ጓደኞቼ ያፌዙብኛል:: | | | | | |
| 39 | ወላጆቼ ለአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ባህልና ለቋንቋቸው ጥሩ አመለካከት አላቸው:: | | | | | |
| 40 | በአማርኛ ትምህርት ክፍለጊዜ አንዳንድ ተማሪዎች መምህሩ ከመግባታቸው በፊት ክፍሉን ትተው የሚወጡ አሉ:: | | | | | |
| 41 | የአካባቢዬ ህዝቦች ለአማርኛ ቋንቋ መልካም ግምት አላቸው:: | | | | | |
| 42 | ባልንጀሮቼ እንደሌላው ትምህርት ያህል ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት እምብዛም ትኩረት አይሰጡም:: | | | | | |
| 43 | ቤተሰቦቼ አማርኛ መማር ከቦታ ቦታ ተዘዋውሮ ከብዙ ሰዎች ጋር ለመገናኘት የሚያስችል ቋንቋ ነው ብለው ያምናሉ:: | | | | | |
| 44 | የአካባቢዬ ነዋሪዎች የአማርኛ ትምህርትን መማር ለወደፊት ህይወቴ ጠቀሜታ አለው ብለው አይገምቱም:: | | | | | |
| 45 | በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ምትክ የአፍ መፍቻ ቋንቋዬን እንድማር ቢደረግ ወላጆቼና የአካባቢዬ ነዋሪዎች ይደግፉታል:: | | | | | |
| 46 | አማርኛ ለአማሮች እንጂ ለእኔ ያለው ጥቅም ዝቅተኛ ነው:: | | | | | |
| 47 | አማርኛ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት መስጫ ቋንቋ መሆኑ ቀርቶ በተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ መሰጠቱን የአካባቢዬ ለዋሪዎች አብዛኞቹ አይፈልጉትም:: | | | | | |
| 48 | በአማርኛ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ለእኔ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ከበሬታ ስለሌላቸው እኔም ለአማርኛ ከበሬታ አልሰጥም:: | | | | | |

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት
የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

በሀዲያ ዞን በሚገኙ ከፍተኛ ሁለተኛ ትምህርት ቤቶች በሚያስተምሩ የ 12ኛ ክፍል መምህራን የሚሞላ መጠይቅ።

I.የመጠይቁ ዓላማ፥

ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ፥ለትምህርቱ፥ ለመማሪያ መፅሐፍቱና ለመምህራን ያላቸው አመለካከት ብቻ የሚፈለግ ነው።

II.ማሳሰቢያ፥

1.መጠይቁ ሲሞላ ሥም መፃፍ አያስፈልግም።
2.በመጠይቁ ለቀረቡ ጥያቄዎች በሙሉ መልስ እንዲሰጥባቸው ይፈለጋል።
3.የጥናቱ ውጤት ከተፈለገው ዓላማ ላይ ይደርስ ዘንድ ከመምህራን ትክክለኛ መልስ ይጠበቃል። ስለዚህም የጥያቄዎቹን መልፈስ በጥንቃቄ በመመርመር ያለምንም ፍራቻና ጥርጣሬ የሚያምኑበትን ትክክለኛ መልስ በነፃ ፍላጎት እንዲያስቀምጡ በትህትና ይጠየቃሉ።
4.ለአንድ ጥያቄ /ለምርጫዎቹ / አንድ መልስ ብቻ ሊሰጥበት ይገባል።

III.የመጠይቁ አሞላል ስልት፥

ለእያንዳንዱ ጥያቄ አምስት አማራች መልሶች ተሰጥተዋል። ለጥያቄው መልስ ይሆናል ብለው በሚያምኑት አማራጭ መልስ ሥር የ "X" ምልክት በማድረግ ማረጋገጥ ይገባል። ለአንድ ጥያቄ ከቀረቡት አማራጭ መልሶች ውስጥ ሁለቱ በጥያቄው መልፈስ ላይ "የመስማማትን" ሁለቱ ደግሞ በሃሳቡ "አለመስማማትን" ሀሳብ የያዙ ሲሆኑ አንድ ግን በጥያቄው ላይ የመስማማትን ሆነ ያለመስማማት ሃሳብ "ለመወሰን መቸገርን" ያዘለ ነው። የመስማማትና ያለመስማማትን ሀሳብ የያዙት አማራጮች ለሁለቱም መልሶች ደረጃ የሚሰጡ ናቸው። አማራጮቹ በጥያቄው ሀሳብ ላይ "በጣም መስማማትን" ወይም "በመጠኑ መስማማትን" ደረጃ የሚለዩ ሲሆኑ በተቃራኒው የቀረቡት ደግሞ እንደዚህ "ፈፅሞ አለመስማማትን" እና "በመጠኑ አለመስማማትን" ያሳያሉ። ስለዚህ በጥያቄው ላይ የሚኖርዎትን የመስማማት ወይም ያለመስማማት ደረጃና ልክ በመወሰን ሚዛናዊ መልስ እንዲሰጡት የመጠይቁ አቅራቢ ለትብብርዎ በቅድሚያ ምስጋናውን ያቀርባል።

ታህሳስ 1989፥ አዲስ አበባ

## ጥያቄዎች

1.በሚከተሉት ጥያቄዎች ፊት ለፊት በሚገኘው ባዶ ቦታ ላይ ተስማሚውን መልስ በመሙላት ያረጋግጡ::

1.ፆታ________

2.ዕድሜ________

3.የትምህርት ደረጃ

ሜጀር________

ማይነር________

4.የአገልግሎት ዘመን________

5. የሰለጠኑበት ተቋም________

6. በአማርኛ መምህርነት የቆዩበት ጊዜ ________

7. የአፍ መፍቻ ቋንቋ________

8. ብሔረሰብ________

11.ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አምስት አማራጭ መልሶች መካከል ትክክል ነው በሚሉት አቅጣጫ የ "X" ምልክት በማድረግ መልስ ይስጡ::

| ተ.ቁ. | ጥያቄዎች | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | ለመወሰን እቸገራለሁ | አልስማማም | ፈጽሞ አልስማማም |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ተማሪዎች የእንግሊዘኛ ቋንቋን ከመማር ጋር የሚመጣጠን አማርኛን የመማር ፍላጎት አላቸው:: | | | | | |
| 2 | ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ፈተና ውጤታቸው በአማካይ ሲታይ ከፍተኛ ነው:: | | | | | |
| 3 | የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ቁጥጥር ባይደረግባቸው ኖሮ በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ትተው የመውጣት ወይም ሌላ ሥራ የመሥራት አዝማሚያ ያሳያሉ:: | | | | | |
| 4 | ተማሪዎች የሚሰጣቸውን የክፍልና የቤት ሥራዎች ያለብዙ ቁጥጥርና ግፊት ለመሥራት ሙሉ ፍላጎት የላቸውም:: | | | | | |
| 5 | ተማሪዎች ወደፊት በኮሌጅ ደረጃ በአማርኛ ትምህርት ለመሰልጠን ሙሉ ፍላጎት እንዳላቸው እምናለሁ:: | | | | | |
| 6 | በአካባቢ ነዋሪዎች፣ በተማሪው የክፍል ጓደኞችና ባልንጀሮች ተማሪው በቋንቋው ትምህርት ላይ ጥላቻ እንዲያሳድሩ ይገፋፋሉ:: | | | | | |

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | ለመወሰን እቸገራለሁ | አልስማማም | ፈጽሞ አልስማማም |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 7 | በሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና በተማሪዎች በሚያደርጉት ዝግጅት ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት እንደሌሎቹ የትምህርት ዓይነቶች ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣሉ:: | | | | | |
| 8 | በአማርኛ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆነ ተማሪዎች በንግግርም ሆነ በንባብ ጊዜ በሚያደርጉት ስህተት ከመርዳት ይልቅ ያፌዙባቸዋል:: | | | | | |
| 9 | ተማሪዎቼ በአማርኛ ቋንቋ የመናገርና የመፃፍ ችግር የለባቸውም:: | | | | | |
| 10 | ከክፍል ትምህርቱ በተጨማሪ ተማሪዎች በቋንቋው ክፍል ላይ ለሚያደርጉት ልምምድ ሌሎች ድጋፍ ሰጭ ነገሮችና የትምህርት ቤቱ የውስጥ ድርጅት አመቺ ናቸው:: | | | | | |
| 11 | ተማሪዎች የአማርኛን ቋንቋን በመማር ፍላጎታቸው ላይ ተፅዕኖ የሚያደርሱባቸው የተለያዩ ጉዳዮች አሉባቸው:: | | | | | |
| 12 | ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋና በትምህርት ላይ አሉታዊ /NEGATIVE/ አመለካከት አሳድረዋል:: | | | | | |

ሀ.ለ11ኛ ጥያቄ በተማሪዎች አመለካከት ላይ ተፅዕኖ ያደርሳሉ የሚያስኛውን ጉዳዮች በነጥብ ያስቀምጧቸው::

________________________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

ለ.ለተራ ቁጥር 12 ጥያቄ የተማሪዎችን አመለካከት ወደ አዎንታዊ /POSITIVE/ ለመለወጥ ይረዳሉ የሚሏቸውን የመፍትሄ ሃሳቦች ይጠቁሙ::

________________________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

| | ጥያቄዎች | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | ለመወሰን ያስቸግረኛል | አልስማማም | ፍጹም አልስማማም |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 13 | እሁን በሥራ ላይ ያለው የ 12ኛ የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍ ይዘትና የማትሪክ ፈተና አቀራረብ ግንኙነት አላቸው | | | | | |
| 14 | የመማሪያው መፅሐፉ በተማሪዎች ሁኔታ ላይ ተመስርቶ ቢሻሻልና በአዲስ መልክ ቢዘጋጅ የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ሊያነቃቃ ይችል ይሆናል:: | | | | | |
| 15 | በመማሪያው መፅሐፍ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦችና ተማሪው እንዲያከናውናቸው የተሰጡት መልመጃዎች በጥብቅ ይገናኛሉ:: | | | | | |
| 16 | የመማሪያው መፅሐፍ ለተማሪዎች አካባቢ፥የቋንቋ ችሎታና የትምህርት ደረጃ ትኩረት ሰጥቶ የተዘጋጀ አይደለም:: | | | | | |
| 17 | በመማሪያው መፅሐፍ ውስጥ የቀረቡት መልመጃዎች አቀራረብና ይዘት ተማሪዎች ሙሉ ለሙሉ በተግባር የሚሰሯቸው ናቸው:: | | | | | |
| 18 | በመርሀ ትምህርትና በመማሪያ መፅሐፍ ዝግጅት ወቅት የቋንቋ መምህራን ባይሳተፉም ልምድ ያላቸው ሰዎች ብቻ ሊቀርፁት ይችላሉ:: | | | | | |
| 19 | የ 12ኛ ክፍል የአማርኛ ሲለበስና የመምህሩ መምሪያ በወቅቱና በበቂ መጠን ይዳረሳሉ:: | | | | | |
| 20 | በመፅሐፉ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦችና መልመጃዎች በቀጥታ የቋንቋ ትምህርትን ለማስተማር የሚያስችሉ አይደሉም:: | | | | | |
| 21 | መፅሐፉ ያካተታቸው ምንባቦችና መልመጃዎች የቋንቋ ትምህርት ዓላማዎችን ሊያስጠብቁ የሚችል ብቃት አላቸው:: | | | | | |
| 22 | መፅሐፉ ተማሪው አልፏቸው ከመጣው የክፍል ደረጃዎች ባካበተው እውቀት ላይ ተመስርቶ እያደገ የመጣና ተከታታይነት ያለው አይደለም:: | | | | | |
| 23 | የመፅሐፉ ይዘቶችና የትምህርት ልምዶች ለመምህሩ የተለያዩ የማስተማሪያ ሥልቶችን እንዲጠቀም የሚጠቁሙ ናቸው:: | | | | | |
| 24 | መፅሐፉ የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት የሚቀሰቅስና የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርጉ የሚያነሳሳ አይደለም:: | | | | | |
| 25 | ተመርቄ በመምህርነት ሙያ ከተሰማራሁ ወዲህ የሙያ ማሻሻያ ወይም የትምህርት ደረጃዬን ለማሻሻል እድል ገጥሞኛል:: | | | | | |
| 26 | ከሚያጋጥሙኝ የተለያዩ ሁኔታዎች አኳያ የአማርኛ መምህር በመሆኔ ውስጣዊ ቅሬታ አለብኝ:: | | | | | |

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | ለመወሰን ያስቸግረኛል | አልስማማም | ጭራሽ አልስማማም |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 27 | ተማሪዎች በተደጋጋሚ የቤት ሥራዎችን በመስጠት ሁሉንም በተከታታይ በማረም በወቅቱ ለመመለስ ያመቸኛል:: | | | | | |
| 28 | ከተማሪው ቁጥር መብዛትና ለትምህርቱ ከተሰጠው የጊዜ ሥርጭት ማነስ የተለሳ የተማሪዎችን የቤት ሥራዎች በየጊዜው ለማረምና ተከታታይ ቁጥጥር ለማድረግ ችግር አለብኝ:: | | | | | |
| 29 | በአጋጣሚ ይሁን በምርጫ በአማርኛ ቋንቋ ስልጥኜ የአማርኛ መምህር በመሆኔ ውስጣዊ ደስታ አለኝ:: | | | | | |
| 30 | ለአማርኛ የተሰጠው ክፍለ ጊዜ ሥርጭት ለተማሪዎች የቋንቋ ክኅሎትን በተሟላ ደረጃ አስተምሮ ለማስጨበጥ በቂ አይደለም:: | | | | | |
| 31 | የአካባቢዬ ማህበረሰብ ለመምህራልና ለመምህርነት ሙያ ከፍተኛ የአክብሮት ግምት ይሰጣል:: | | | | | |
| 32 | በማወቅም ይሁን ባለማወቅ የሥራ ባልደረቦቼ አማርኛን ማስተማር ቀላል ሥራ እንደመስራት አድርገው የሚገምቱና የሚተቹ ያጋጥማሉ:: | | | | | |
| 33 | በክፍል ውስጥ የመማር ሂደት እኔ ብዙ ገለፃና ማብራሪያ ከመስጠት ተቆጥቤ ተማሪዎች እርስ በርሳቸው እየተረዳዱ ራሳቸው እንዲማማሩ አደርጋለሁ:: | | | | | |
| 34 | በአማርኛ ቋንቋ አፍ የፈቱና ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆነ ተማሪዎችል በአንድ ክፍል ቀላቅሎ ማስተማር አስቸጋሪ ነው:: | | | | | |
| 35 | አጋጣሚ ወይም አመቺ ሁኔታና ዕድል ባገኝ የመምህርነት ሙያዬን ብቀይር እመርጣለሁ:: | | | | | |
| 36 | የወጣሁበት የትምህርት ተቋም የተማርኳቸው ኮርሶች ብቃት ያለው የቋንቋ መምህር አስልጥኖ ለማውጣት የሚያስችሉ ናቸው:: | | | | | |

ሐ . ለ 36ኛው ጥያቄ መልስዎ ምክልያት የሚሆኑ ተጨታጭ ለጥቦችን ለአብነት ያህል በለጥብ ይቸቀሷቸው::

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

በየትምህርጥ ቤቱ የተደረጉ ዝርዝር የክፍል ምልከታ ውጤቶችን የማጠቃለያ ዐብይ ነጥቦች

ቀን ______________________

ትምህርት ቤት__________________________

| ተ.ቁ | ዐብይ ነጥቦች | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ሀ. የመምህሩ/ሯ የክፍልና የትምህርት አያያዝ | | | |
| 1. | በክፍል ውስጥ ተማሪዎች ለማነቃቃት የሚደረጉት ጥረት | | | |
| 2 | በትምህርት ክፍለ ጊዜው ሁሉም ተማሪዎች እንዲሳተፉ የማድረግ ችሎታና የሚሰጡት ማበረታቻ | | | |
| 3 | የክፍል ውስጥ ሥርዓት እንዲጠበቅ የማድረግና ተየማሪዎች ሁኔታ የመከታተል ስልትና ችሎታ | | | |
| 4 | የሚጠቀሙበት የማስተማር ስልት ሳቢነትና ዘመናዊነት | | | |
| 5 | በቋንቋው ትምህርት ላይ ያላቸው ዕውቀትና ብቃት | | | |
| 6 | የተማሪ-ተማሪጸ÷የተማሪ-መምህር መስተጋብር የመፍጠር ስልት | | | |
| 7 | የተመደበውን የክፍል ጊዜ በአግባቡ የመጠቀም ሁኔታ | | | |
| 8 | በዕለቱ የተመረጡት የትምህርት ይዘቶች ለቋንቋ ትምህርት ያላቸው ጠቀሜታ | | | |
| 9 | ለማስተማር ያላቸው ግላጎት÷ ሰብዕና÷ብቃትና የሙያ ባለቤትንት ደረጃ | | | |
| 10 | በዕለቱ የተመደበውን ክፍለ ጊዜ በአግባቡ የመጠቀም ችሎታ | | | |
| | ለ. የተማሪዎች ሁኔታ | | | |
| 1 | በክፍል ውስጥ ተማሪዎች የሚያደርጉት ንቁ ተሳትፎ | | | |
| 2 | የተማሪዎች የክፍል ሥርዓት አጠባበቅና ለትምህርቱ ያላቸው ዝግጅት | | | |
| 3 | በዕለቱ ሰሚሰጠው ትምህርት የተማሪዎች ሙሉ ትኩረት የመስጠት ሁኔታ | | | |
| 4 | በትምህርቱ ሂደት መምህሩ የሚሰጡትን መመሪያና ትዕዛዝ ተቀብሎ የመተግበር ፈቃደኝነት | | | |
| 5 | ለመማር ማስተማሩ ሂደት የክፍሉ ሁኔታ አመቺነት | | | |

# ማረጋገጫ

እኔ ከታች ስሜ የተገለፀው ተማሪ፣ ይህ ጥናታዊ ፅሑፍ የኔ ሥራ መሆኑንና በጥናቱ ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን የተዛማጅ ጽሑፎችንና መረጃዎችን ምንጮች የጠቀስኩ መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

ስም ወንድወሰን በየነ

ፊርማ 15/9/89

ቦታ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም፣ አዲስ አባባ ዩኒቨርሲቲ

ቀን ግንቦት 15 ቀን 1989 ዓ.ም